# የኦሮሞ እና የአማራ

## እውነተኛው የዘር ምንጭ

በፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ



የሽፋን ስዕል፡- የጥንት ኦሮሞና አማራ ጠቢባን የፃፉባቸው ጥንታዊ ፊደሎች፡፡





**ማውጫ** **ገጽ**


**ስለደራሲው አጭር መረጃ** 5

**መቅድም** 7

## ክፍል አንድ

## ኦሮሞ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከተው አስተዋጽኦ..............................15

ስነ-ልሳናዊ አስተዋጽኦ..............................17

ፍልስፍናዊ አስተዋጽኦ..............................20

መንፈሳዊ አስተዋጽኦ..............................23

ለውትድርና ጥበብ አስተዋጽኦ........................26

ለትምህርት እና ለቅኔ/የግዕዝ ስነ-ቃል

ለግጥም የተደረገ አስተዋጽኦ........................29

ለዳንኪራ እና ለ ሙዚቃ የተደረገ አስተዋጽኦ-----.30

የሙዚቃ መሳሪያዎችን በተመለከተ..................30

ልዩ ልዩ አስተዋጽኦዎች..............................31

## ክፍል ሁለት

**የኦሮሞና የአማራ ሕዝብ እውነተኛው የዘር ምንጭ..............................37**

**ኦሮሞና አማራ በዘር አወራረድ...........................................51**

## ክፍል ሦስት

በኢትዮጵያ ሥርወ-መንግሥታት ውስጥ የአማራው ተሳትፎ መጠን...................................................142

የዘመነ መሳፍንት ክስተት...................................................198

የንግሥተ-ሳባ ማንነትና ስለ መኖር አለመኖርዋ......203

ማጠቃለያ እና መደምደሚያ-------------------------.-256

**ዋቢ መጻሕፍት**..........................................266





# ስለደራሲው አጭር መረጃ



ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ፣ /ፒ.ኤች.ዲ./ ገጣሚ፣ ጸሐፌ-ተውኔት እና ከ60 በላይ መጽሐፎችንና መጣጥፎችን በአማርኛ፣ በጀርመንኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች አሳትሞ ለንባብ ያበቃ ምሁር ነው። The Hidden and Untold History of *The Jewish People*

ውስጥ ተቀምጦ ሳለ ቤተ ክርስቲያኑ በአረብ ሙስሊሞች ሲቃጠል መጽሐፉ አለቱ ውስጥ ተረፈ። ያንን መጽሐፍ ነው መሪራስ አማን በላይ አግኝቶ ወደ ኢትዮጵያ ያመጣው። የብራና ጥቅሎቹ የተፃፉት በግዕዝ ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ያመጣልንና የእውነተኛው ታሪካችን ብርሃን እንደገና እንዲበራ ያደረገልን መሪራስ አማን በላይም ባለውለታችን ነው። በመሆኑም ምስጋና ይገባዋል።።

መሪራስ አማን በላይ በመጽሐፈ ሱባኤ ውስጥ ተካትተው ካገኛቸው መጻሕፍት ውስጥ በትልቁ ነብይ በሄኖክ የተጻፈውና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "የሠራዊት ጌታ ጦርነቶች መጽሐፍ" በሚል የተጠቀሰው ስለ ዓለም አፈጣጠር የሚተርከው "መጽሐፈ ጃን ሸዋ" ይገኝበታል። ሙሴ ከአማቱ ከጄትሮ (ዮቶር-አብ) ጋር በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በነበረበት ወቅት በኛ እጅ የነበረውን ይህን መጽሐፍ አግኝቶ ነው "ኦሪት ዘ ፍጥረት" የተሰኘ መጽሐፉን ከኛው መፅሐፍ ላይ ቀንጭቦ የጻፈው።

አማን በላይ እንደሚለው የተገኙት እና ለኛ የደረሱት የብራና ጥቅሎች የመጀመሪያ ጽሑፎች ሳይሆኑ የብራና ላይ የእጅ ቅጂዎች ናቸው። በዚያን ዘመን ማተሚያ ቤት አልነበረም። ስለዚህ የቁም ጸሐፊዎች ለራሳቸው ወይም ለደንበኞቻቸው መጽሐፎችን አሳምረው በእጅ ይገለብጡ ነበር። እነዚያ የብራና ጽሑፎች ከ350 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያን ይገዛ የነበረው ንጉሥ ማን እንደነበር ስሙን ይጠቅሳሉ። እሱም አዲያም ሰገድ ኢያሱ ነበር። መፅሐፎቹ ከዚያ በኋላ ስለማንም የኢትዮጵያ ንጉሥ ወይም ድርጊት የመዘገቡት ነገር የለም። ይህም በመሆኑ ምንም እንኳን የሚተርኳቸው ታሪኮች ጥንታውያን፥ ማለትም ከ 4000 ዐመታት በላይ ቢሆኑም፥ ጥቅሎቹ ቢያንስ 3500 ዓመት እድሜ እንዳላቸው እንገምታለን።

እንግዲህ በነዚህ ምክንያቶች ነበር የዝነኛውን ታሪካችንን ጎዳና የሳትነው። በመሆኑም ኦሮሞዎች ከእስያ፣ አማሮች ደግሞ ከአረቢያ እንደመጡ አሰብን። ለዚያ ነበር አማሮችን እንደ ሴማዊ፣ ኦሮሞዎችን ደግሞ እንደ ኩሻዊ የቆጠርነው። ሀቁ ግን ሁለቱም ኩሻውያን እንደነበሩ እና ከአንድ አባት ደሴት ወይም ደሹት ከተባለ መፍለቃቸው፤ ከአንድ አካባቢ ከጐጃም፤ ከአንዲት አገር ከኢትዮጵያ መገኘታቸው ነው። ምንጫቸው በተለይም ፈላስፋ እና ካህን እንዲሁም





የኢትዮጵያ መስራች የነበረው የኢትዮጵ ዝርያ ከሆነው በዚሁ በደሼት ወይም ደሴት ሥም እስከ ዛሬ ከሚጠራው ከጣና ሃይቅ አካባቢ ከኖረው ከደሹት ነው።

በእነዚህ መጽሐፎች አዲስ ከተካተቱት ጠቃሚ መረጃዎች ውስጥ ቀዳማዊ ኢትዮጵ ኢትዮጵያ ለምትባለዋ አገር መሥራች የሆነው ንጉሠ-ነገሥት ለኦሮሞ፣ ለአማራ እና ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን ሁሉ ቀደምት አባት መሆኑ መገለጹ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለእኛ ለዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን መገኛ የሆኑትን የኢትዮጵን ልጆች እና የልጅ ልጆች ስም ዝርዝር የያዘው የዘር ሐረግ ሰነድም ይገኝበታል። የጥንት የኦሮሞና አማራ ምሁራን፣ ፈላስፎች፣ ነቢያት እና ካህናት ታሪካቸውንና እውቀታቸውን ለመፃፍ የተጠቀሙበትን የሉባን ፊደልም ፈጥረው እንደ አስተላለፉልንም ይዘግባል።

እነዚህን መጽሐፎች ካገኘሁ በሁዋላ ነበር በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የነበረኝ የግንዛቤ አቅጣጫ ሙሉ ለሙሉ የተቀየረው። ይህም ከ25 ዓመት በፊት ስለ ኦሮሞ ሥረ-መሠረት እና ስለ አማራና ትግሬ ታሪክ በአውሮፓውያን *"የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ጠበብት"* ተብዬዎች በደረደሩልን የጠነዙ ገለፃዎች ላይ ተመስርቼ አዘጋጅቻቸው የነበሩትን ጽሑፎች እንድከልስ አድርጎኛል።

ታሪካችን በጊዜ ከፍተት ውስጥ ሲያልፍ በተቃራኒ ሃሳቦች የመቀየጥ እና የመድበስበስ አደጋ አጋጥሞታል። አሁን ግን ሀቁ ፍጥጥ ብሎ ወጥቷል። እውነት ተቀብራ አትቀርማ። እነዚህ አዳዲስ መረጃዎች በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ኢትዮጵያን ስለገዙ ኦሮሞ ንጉሦችና ንግሥቶች እንዲሁም ሁለቱም ኦሮሞና አማራ ለኢትዮጵያ ስልጣኔ ስላበረከቱት አስተዋጽኦ ቀደም ሲል የፃፍኳቸውን ጽሁፎች የሚያጠናክሩ ሆነዋል። በርግጥ ጽሁፎቹ በነዚህ ርዕሶች ላይ ተደሞም ምሉዕ ነበሩ። አዲሶቹ ግኝቶች የጽሁፎቼን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሚና ነው የተጫወቱት። እንዲሁ እነዚያን ጽሁፎቼንና በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ ያስቀመጥኩትን *"ለኢትዮጵያ ስልጣኔ የኦሮሞ አስተዋጽኦ"* የሚለውን ጨምሮ *በኢትዮጵያን ሪቪው* እና በኤሌክትሮኒክ ሚዲያው ላይ ወጥተው የነበሩ ጥቂት መጣጥፎችን ከመጠነኛ ማሻሻያ ጋር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አካትቻለሁ።

Nama gadi jedhe nyaatu tchiisani kajeelu.

አጎንብሶ የሚበላን ተኝተው ይቀላውጡታል (ይከጅሉታል)።

Haaren yo sierra kkaayan daarrarra gangalatti.

አህያ (የአህያ ሥጋ) ከአልጋ ሲሉት ከአመድ።

Na argaa na argaa kan jettu na dhossaa, na dhossaa jetti.

ዕዩኝ ዕዩኝ ያለች፣ ደብቁኝ፣ ደብቁኝ አለች።

Haaren gaafan du-e morgi hinbiqilin jettee.

አህያ፣ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል፣ አለ።

Quufan male hinutaalan, utalani male hintchabani.

ካልጠገቡ አይዘሉ፣ ካልዘለሉ አይሰበሩ።

Raadi hare wajiin oltu, deu dhuufu barti.

ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ተገባለች።

Harren khittu ilkan wa-irra hinfithu.

አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም።

Bishan dhagaa dubbissa.

ውሀን የሚያናግረው ድንጋይ ነው።

Mana ormaa bareedaorra, godo offi wayya.

ከሰው አዳራሽ የራስ ጎጆ ይሻላል።

Nammi gabaaban utu ulfina hinqbattin dua.

አጭር ሰው እንተ ሳይባል ይሞታል (ያረጃል)።





ከላይ ከተዘረዘሩት ምሳሌያዊ አነጋገሮች እና ብልኅ አባባሎች የኦሮሞዎችን አእምሮአዊ ኃይል እና ለአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገር ያበረከቱትን አስተዋጽኦ እንድንረዳ ያግዛሉ። አንዳንድ የኦሮምኛ ቃላት ለምሳሌ "ከጀሉ" እና "ሂንቢቂሉን" የሚሉትን ቃላት አንደቅደም ተከተላቸው "ከጀለ" እና "በቀለ" ከሚሉት የአማርኛ ቃላት ጋር አንድ ዘር መሆናቸውን እንገነዘባለን። ባለፉት ዘመናት ኦሮሞና አማራ ካልተቀላቀሉ በስተቀር ይህን መሳይ የቃላትና የምሳሌያዊ አነጋገሮች መመሳሰል በምን ታምር መጣ? በኦሮሞ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እና ቃላት ላይ ይበልጥ የሚደረግ ጥልቅ ጥናት ኦሮሞንና አማራን አንድ ላይ ስላስተሳሰሯቸው የጋራ ምክንያቶች ይበልጥ መታወቅ የተሻለ መረጃ ያስገኝ ይሆናል።

## መንፈሳዊ አስተዋጽኦ

ኦሮሞው በአማራው ሃይማኖታዊ ባሕል ላይም ጉላ ያለ ተጽእኖ አሳድሯል። ኦሮሞ ዋቃ ‹‹ዋቀ›› እያለ በሚጠራው እና ሰማይንና ምድርን በፈጠረ አንድ እግዚአብሔር ያምን ነበር። አሁንም ያምናል። ዋቃ ‹‹ዋቀ›› መንፈስ ሲሆን አያና ‹‹አየነ›› እና ‹‹አውሊያ›› በሚባሉ ትናንሽ መናፍስት የተከበበ ነው። ከነዚህ መናፍስት ውስጥ ‹‹ቦረንትቻ›› (የቦረና ኦሮሞ መንፈስ) እና ‹‹አቴቴ›› ይገኙበታል። የአማራ ክርስቲያኖች ከነዚህ መናፍስት የተወሰኑትን ወደራሳቸው እምነት ቀላቅለዋል። ‹‹ውቃቢ›› በመባል በሰፊው የሚታወቁት አቴቴ እና አውሊያ የሚጠቀሱ ናቸው። በሰው ዘር ዙሪያ 44 አውሊያዎች ወይም መናፍስት አሉ ብለው ኦሮሞዎች ያምናሉ። በሚያስግርም ሁኔታ ይህ ቁጥር የ44ቱን ቅዱሳን ሰሞች ከያዙት ከ44ቱ ታቦታት (የ10ቱ ትእዛዛት አምሳያ ታቦቶች) ጋር የሚገጣጠም ነው።

የቦረንቲቻ አምልኮ ክርስቲያን በሆኑም ባልሆኑም ኦሮሞዎች እንዲሁም በአማሮች እና በሌሎችም ኢትዮጵያውያን በግንቦት ወር የትድስት ማርያም ልደት /ልደታ/ ተብሎ በሚታመንበት ዕለት ያከበራል። ይህን በዓል ለማክበር ሰዎች ‹‹አድባር›› በሚሉት እንደ

ቅዱስ በሚታሰብ ዛፍ ስር ይሰበሰቡና ምግብ/ንፍሮ/ ይቀቅላሉ፤ የያዙትን ስጦታም ከቅድስት ማርያም ጋር ለሚያምታቱት ለቦረንትቻው ይሰጣሉ።

አማሮች የወረሷት በጣም ታዋቂዋ የኦሮሞ ተመላኪ ‹‹አቴቴ›› ናት። ‹‹አቴቴ›› እንደ ጠባቂ መልአክ ያለች ሴት መንፈስ ስትሆን ‹‹አቴቴ ጊንቢ›› የግንብ መንፈስ፣ "አቴቴ ሓራ"፣ የሐይቅ መንፈስ እና "አቴቴ ዱላ" የጦርነት መንፈስ በሚሉ ሶስት መልኮች ትከሰታለች። የአቴቴ አከባበር ስለሚረዝም አልጽፈውም።

‹‹ውቃቢ›› ወይም ‹‹አውሊያ›› የሚለው አምደ-ቃል ከረጂም ዘመን በፊት በቀጥታ ወደ አማርኛ መዝገበ ቃላት ገብቷል። ‹‹ውቃቢ ጠባቂ መልአክ ነው›› ተብሎ ስለሚገመት ሁለቱም /ኦሮሞዎችም አማሮችም/ ከውቃቢዎቹ አንዱ እንዲያድርባቸው ይመኛሉ። ለዚህ ነው አንድ ሰው ችግር ሲገጥመው አማሮች ‹‹ውቃቢ ራቀው›› የሚሉት። ‹‹ውቃቢዬ ወደደው፣ ውቃቢዬ አይወደውም›› የሚሉ አባባሎችም አሏቸው። አንዳንዶቹ ውቃቢዎች በመጨረሻው ስማቸው ላይ የኦሮሞ ስሞች አሏቸው፤ ለምሳሌ ‹‹ወስን ጋሻ›› እና ‹‹ጠቋር አባቡሌ›› የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው። ወንዶችና ሴቶች ውቃቢ ሲነሳባቸው ሩሓቸውን ይስታሉ፤ የውቃቢውን መንፈስ ይላበሱና በጤናማ ጊዜያቸው በማይችሉት ቋንቋና የድምጽ ቅላፄ ይናገራሉ። ውቃቢው ብዙውን ጊዜ እንስሳትንና የተለየ ቀለም ያላቸውን ዶሮዎች ጨምሮ ልዩ ልዩ ምስ ‹‹ጭዳ›› እንዲቀርብላቸው ይጠይቃሉ። ቢሆንም ከክርስቲያኖች አንፃር ውቃቢ የሰፈረበት ሰው ‹‹አጋንንት›› ወይም ‹‹ሰይጣን›› እንደያዘው ተደርጐ ነው የሚታሰበው።

በኦሮሞዎች፣ አማሮች እና በሌሎች ክርስቲያኖች በሆኑትና ባልሆኑት ኢትዮጵያውያን በጋራ የሚከበር ከዘመን መለወጫ የተለየ በዓል መስቀል ነው። ሲዳማዎች፣ ኦሮሞዎች፣ ጉራጌዎች፣ ቲጋሩዎች እና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን መስከረም 16 እና 17 ቀን ደመራ በማቀጣጠል፣ በመጨፈር እና በመደሰት ያከብሩታል። ይህ በዓል በተከበረ በሳምንቱ ታዲያ ክርስቲያኖች እና ክርስቲያን ያልሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ‹‹ኢሬቻ›› የተባለ የኦሮሞ በዓል ከአዲስ አበባ ብዙም ሳይርቅ ቢሾፍቱ (ደብረዘይት) ወይም ሌላ ስፍራ ያከብራሉ።





ኢሬቻ ሙሉ በሙሉ በየዐመቱ እግዚአብሄርን የማመስገኛ የኦሮሞ ሃይማኖታዊ ዐመትበዐል ነው። ከረምቱ ወጥቶ ዐዲሱ ዐመት መስከረም ሲጠባ እግዚአብሄር ከዘመን ዘመን በሰላምና በብልጽግና ስለአደረሳቸው ህዝቡ ያወድሱታል። በሸዋ በዐሉ በሚከበርበት ዕለት ከአካባቢውና ከሌሎችም ቦታዎች የተለያዩ ኢትዮጵያዊያን ወደ በዓሉ ማክበሪያ ቦታ /ደብረዘይት ሆራ ሓይቅ/ ይተምማሉ። በሆራ ሓይቅ መግቢያ ላይ በሬ ይታረዳል። አንዲት በህዝቡ የምትከበር እና የምትፈራ ሴት በውሃው ዳር ቆማ ካመሰገነች እና ከፀለየች በኋላ የበዓሉን ታዳሚዎች በመመረቅ የበአሉን ሥነ ሥርዓት ታከናውናለች። ለምሳሌ መካን ሴቶች በረከቷን ለማግኘት እፊቷ ያጐነብሳሉ። እሷም ቄጤማ ወደ ሓይቁ ውስጥ ነክራ ትፀልይና ለሚቀጥለው ዓመት ሌላ እሬቻ ለማከናወን እንደሚመጡ፤ ሲመጡ ታዲያ ልጅ ወልደውና ታቅፈው እንደሚሆን እየተነበየች በቄጤማው የጠቀሰችውን ውሃ አጐንብሰው ምርቃቷን በሚለምኑት መካን ሴቶች ላይ ትረጭባቸዋለች። አባገዳውም እንዲሁ ዋቃ የተባለውን እግዚአብሄርን አመስግኖ የተለመደውን ስርዐት ካከናወነ በሁዋላ የእሬቻው በዓል ከመፈፀሙ በፊት የበዓሉ ታዳሚዎች በዛፍ ጥላ ስር ይሰበሰባሉ። ይህን የሚያደርጉትም በዋቃ ለመባረክ እንደሆነ ያምናሉ። በዛፉም ስር ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ያስቀምጣሉ፣ ሉቲ/አዲስ ጨርቅ/ ዛፉን አልብሰው ያስጌጡታል።

የአቴቴ አምልኮን፣ የውቃቢን እና የኢሬቻን በዓላት የሚያከብሩትን አማሮች ከግምት ውስጥ ስናስገባና ባጠቃላይ ክርስቲያኖች በተለይ ደግሞ አማሮች መሆናቸውን ስናይ በኦሮሞ ሃይማኖት በአያሌው መሳባቸውን እንገነዘባለን።

ያንድ ሰው ዋናው እሱነት መንፈሱ ወይም ኅሲናው በመሆኑ ጥልቁ የአማራ ውስጣዊ ማንነት በኦሮሞ ሥነ-ልቦና የተሞላ ነው። በገሃዱ እውነታ እንዲህ ዓይነቱ የመንፈስ ውህደት ደግሞ ከስር መሠረቱ ኦሮሞና አማራ ካላቸው የሥጋ ዝምድና የበለጠ ይጠነክራል። ምክንያቱም መንፈስ ሥጋን ያዛልና። ሁለቱንም፤ መንፈስንም ሥጋንም ከግምት ውስጡ ስናስገባ ደግሞ ኦሮሞና አማራ ካንድ እናትና አባት ስለፈለቁ እና ላለፉት 3500 ዓመታት በኢትዮጵያ አገራቸው ውስጥ አብረው አንድ ላይ ስለኖሩ በመንፈስ፣ በደም እና

የማውጣት ልማድ ነበራቸው። ከጊዜ በሁዋላ የአማራ አልፎም የትግሬዎች ሹማምንት እና ጦረኞች ፈረሶቻቸውንና ራሳቸውን በዚህ በኦሮሞ ልማድ መጥራት ጀመሩ። ብዙውን ጊዜ የፈረሶቹ ስሞች የፈረሱ ጌታ እንዲታወቅበት የሚፈልገውን ጠባይ የሚያንፀባርቁ ነበሩ። በዚህም በፈረሶቹ ስሞች ሰዎቹም ተለይተው ይታወቁባቸው ነበር። ለምሳሌ የዳግማዊ ምኒልክ አያት የነበሩት የሸዋው ሣህለ-ሥላሴ በፈረሳቸው ስም "አባዲና" ተብለው ይጠሩ ነበር። በኦሮምኛ "አባዲና" ማለት ድንገት የሚወር አስፈሪ ጠላት አባት ማለት ነው። የባለቤቶቹም መጠሪያዎች የሆኑት ጥቂት የፈረስ ስሞችን ልጥቀስ፡-

አባ ታጠቅ....... አፄ ቴዎድሮስ

አባ ዳማ.......... አፈንጉስ ነሲቡ ዛማኔል

አባ ግርሻ..........ራስ ዳርጌ

አባ ድልድል.......ራስ ዘውዴ

አባ ዳምጠው......ንጉሥ ኃይለመለኮት

አባ ትጉ............ራስ ጉበና

አባ ጤና .........ልጅ ኢያሱ

አባ ጠጣው.........ራስ ወሌ

አባ ክራን............ደጃዝማች ዘውዱ

አባ መቻል (አባ መላ)....ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ

አባ ነጋ...............ራስ አሉላ (የትግሬው)

አባ ነፍሶ.............ደጃዝማች ባልቻ

አባ ቃኘው...........ልዑል ራስ መኮንን እና





አባ ጠቅል...........አፄ ኃይለሥላሴ ይጠቀሳሉ።

አለቃ አፅመ ጊዮርጊስ *የጋላ ታሪክ* እና *የሸዋ ስርወ መንግሥት* በተሰኙ መጽሐፋቸው ውስጥ እንደጠቀሱት አማሮች ጋሻቸውን የማስጌጥ ብልሃት ከኦሮሞዎች ተምረዋል። እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፍፃሜ እና እስካሁኑ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ለአማሮች እና ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ይሰጡ ከነበሩ በርካታ የጦር የማዕረግ ስሞች ውስጥ ከኦሮምኛ የተወሰዱ አሉ። ለምሳሌ መንጫ፣ ቢተዋ፣ ከለቻ እና ማልዳያ ይጠቀሳሉ። (3)

## ለትምህርት እና ለቅኔ /የግዕዝ ሥነ-ቃል ግጥም/ የተደረገ አስተዋጽኦ

ኦሮሞዎች የሆኑ የቤተ ክህነት ምሁራን ለኢትዮጵያ ባሕላዊ ትምህርት እና ለቅኔ ጠቃሚ ድርሻ አበርክተዋል። ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እየሰጡ ያገለገሉ በርካታ ዝነኛ የኦሮሞ ደብተራዎች፣ ሊቃውንትና ቀሳውስት ነበሩ። እነዚህ የኦሮሞ ምሁራን ምርጥ ችሎታ ያላቸው የግዕዝ ሥነ ግጥም /ቅኔ/ እና የሥነ መለኮት ሊቃውንት ነበሩ። የግል ቅኔ በማስተማር ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም በግዕዝ የቅኔ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ቅኔዎችን በመቀኘትም አገልግለዋል። የሚከተሉትን ብቻ ለአብነት እጠቅሳለሁ፡-

የሰላሌው ስሬ መድሃኒዓለም ቤተክርስቲያን ስሙ-ጥር አለቃ ጥበቡ ገኔ፤ የታዋቂው ገጣሚና ሰዓሊ የገብረ ክርስቶስ ወላጅ አባት፣ የሐረሩ ቤተክርስቲያን ስሙ-ጥር አለቃ ደስታ ነገዎ፤ የጉጃም ጫቢ ማርያም ስሙ-ጥር መሪጌታ ወልዴ እና የአቡነ ማርቆስ ዋና ፀሐፊ የነበሩት የሸዋው ስሙ-ጥር መሪጌታ ከበደ ጥቂቶቹ ናቸው።

የግዕዝ ቀሳውስት፣ ገጣሚያንና ሊቃውንት የነበሩ የጉጃም ኦሮሞዎች በርካታ ናቸው። የኦሮሞ ምንጩ ጉጃም ስለሆነ ይህ ይህን ያህል አያስገርምም። አንዳንድ ያላወቁ የኦሮሞ ልጆች የግእዝ ሊቃዉንትና ደብተሮች አማሮች ብቻ ይመስሏቸዋል። ከላይ እንደተጠቀሰው በርካታ ኦሮሞዎችም የግዕዝ ሊቃውንትና ደብተሮች እንደነበሩ ልብ ይሏል። እንደ እውነቱ ከሆነ አዲስ አበባ የሚገኘው

ገርላሞት..................ሞትን የምትገረስስ፣ ሞትን ድል የምታደርግ

ቢልለቢላ....................ቢልቢላ፣ ስለተናገርኩ ተናገረች፣ ትንሽ ደወል፣ ቃጭል እንደማለት

አልነጋሽ.................ንጉሥ

አርማሕ...............ምልክትህ

ግርማ አስፈሪ.........ግርማው የሚያስፈራ፣ ግርማ ሞገስ ያለው

አል ባሕር ነጋሽ......የባሕር ጠረፍ ንጉስ

ድግ....................መቅነት

ጉም.....................ዳመና

አስጉምጉም............በዳመና ሽፍነው

በካሣ....................በበደል፣ በድካም ዋጋ፣ በማካካሻ

ልትም.................የተጋጨ

ተላተም...............ተጋጭ

አይዙር................ፊቱን አይመልስ፣ አይሽሽ

ውድም አስፈሪ........በጦር ሜዳ ጠላቱን የሚያስፈራ፣ ወገኑን የሚያነቃቃ

ነጋሽ ዛሬ.............ዛሬ የሚገዛ ንጉሥ

መራ ተክለ-ሃይማኖት...የሃይማኖት መሥራች አለቃ

መሪመራሪ ድላድ.......ያንድ ድል መሪ

ላሲበላ..................ማር የሚበላ (17)፡፡





በዚህ መሰረት በርካታ ነገሥታት የአማርኛ ስሞች ያላቸው በመሆኑ አማርኛ እና አማራ እንደ ቋንቋ እና እንደ ሕዝብ ከ3500 ዓመት በፊት ጀምሮ ኖረዋል ማለት ነው፡፡

ኦሮሞውን በተመለከተ ባመዛኙ ኦሮሞው መደባይ፥ ጂማ እና መንዲ ከተባሉ ነገድ መምጣቱንና የመደባይ ሁለት ወንድሞችም ጂማና መንዲ መሆናቸውን ዘረ-ሃረጋቸው ያረጋግጣል፡፡ ከነዚህ ሶስት ወንድማማቾች መሀል መደባይ የታላላቆቹን አባቶቻቸውን የእነ ኢትዮጵን እና የነ ደሴትን ቅስናና የጥበብ መፃህፍት በመውረሳቸው ጠቢባን እና ካህናት ለመሆን በቅተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ በቤንሻንጉል-ጉምዝ ክልል አሶሳ ወይም መተከል አካባቢ እና በአማራ ክልል ጎጃም ዞን ወንበራ ወይም ወንበርማ በተባለ ቦታ በዚህ ‹‹መደባይ›› በሚለው ስም የሚጠራ እና ኦሮምኛ የሚናገር ነገድ አለ፡፡ በብልሕነቱና የባሕል መድሃኒት ቀማሚነቱ ይታወቃል፡፡ የኢትዮጵና የደሴት (ደሸት) ዘር በመሆኑ ነው፡፡

አንደ እውነቱ ከሆነ በሁለቱም በኦሮሞም በአማራም ይነገር በነበረውና ‹‹ሱባ›› በተባለው ቋንቋ ‹‹መደባይ›› ማለት ‹‹ፈላስፋ፣ መራቂ፣ (የሚመርቅ) እና ቄስ›› ማለት ነው፡፡ ሦስቱ ሰዎች "ማጂ" የተባለና ለአማራ እና ለጃማ ጎሣዎች አባት የሆነ ወንድም ነበራቸው፡፡ ማጂ ማለት "ብልሕ" ማለት ነው፡፡ ማጂዎች ለህፃኑ ኢየሱስ ስጦታ ለማበርከት ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ወደ ቤተልሄም ከተጓዙ 12ቱ ብልሖች መካከል ናቸው፡፡ ‹‹ማጂክ›› የሚለው ቃል የመጣው ከብልሕነታቸው የተነሳ ከነሱ ስም ይመስለኛል፡፡

በእርግጥ መደባይ፣ ጂማ፣ ማጂ እና መንዲ ወንድማማቾች ናቸው፡፡ አባታቸው ደሸት ወይም ደሴት የነቢይት ልጅና ራሱም ነቢይ፣ ፈላስፋና ንጉሥ የነበረ ሲሆን ጎጃም በጣና ሓይቅ አካባቢ ይኖር ነበር፡፡ ጣና ሓይቅንም ያስተዳድር ነበር፡፡ ደሴት የሚለው ስያሜ የተወለደው ከሱ/ከመሪው/ መጠሪያ ነው፡፡ ከ3500 ዓመት በፊት ነው የኖረው፡፡ አምን ልጆቹ እያንዳንዳቸው ኦሮሞንና አማራን ጨምሮ የበርካታ ነገዶች አባቶች ሆነዋል፡፡ ይህን ነጥብ ወደፊት አብራራዋለሁ፡፡ መደባይ የተባለ አገር በአክሱም ከተማ እና በመረብ ወንዝ መካከል ዛሬ ድረስ አለ፡፡ መደባይ ታቦር እና መደባይ ወለል

ተብሎ በሁለት ተከፍሏል። ይህ ‹‹መደባይ›› የተባለ ነገድ ከ3000 ዓመት በፊት መኖሩ በአለቃ አጽመ-ጊዮርጊስም ተረጋግጧል።

*‹‹የመጀመሪያው ጨዋ (ጨዋ ማለት ወታደር ማለት ነው) በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን የነበረው መደባይ ነው። እነሱም በትግሬ፣ በስሜን፣ በፀለምት እና በወገራ ሰፍረው የነበሩ ወታደሮች ናቸው። ከሱ (ከቀዳማዊ ምኒልክ) በሁዋላ የተነሱ ነገሥታትም እንዲሁ አድርገዋል። በሁዋላ፣ በ1130 ወይም በ1150 ዓ.ም በንጉሥ ላሊበላ ዘመን "አማራ" የተባሉ ወታደሮች በዋድላ፣ በበጌምድር፣ በሳይንት እና በወለጋ "ጨዋ"/መደበኛ የመንግሥት ጦር/ ሆኑ። በባላገሩ ላይ ተሰሪነት ገቡበት››*(18) ይላሉ አለቃ አፅመ-ጊዮርጊስ።

ከላይ በቀረበው ጥቅስ አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ ሦስት እውነታዎችን ነግረውናል፡-

ሀ. መደባይ የተባለ ነገድ ከሦስት ሺ ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖር ነበር።

ለ. ይህ መደባይ የተባለው ነገድ ኦሮሞ ሲሆን የመጀመሪያው "ጨዋ" ማለትም መደበኛ የጦር ሠራዊት ነበር።

ሐ. ሁለተኞቹ ጨዋዎች /መደበኛ ወታደሮች/ አማሮች ነበሩ፤ ይህም ከ2000 ዓመት በሁዋላ በንጉሥ ላሊበላ ዘመን ነው።

ላሊበላ በ11ኛው ክፍለ-ዘመን ሥልጣን ላይ ሲወጣ ባመዛኙ በአማሮች መደገፉ እውነት ቢሆንም ከዚያ በፊት አማራው ጨዋ /መደበኛ ወታደር/ አልነበረም ማለት አይደለም። የቀዳማዊ ምኒልክ የልጅ ልጅ ታላቁ አክሱማይ ከ2850 ዓመት በፊት ገና በ6 ወይም በ7 ዓመት እድሜው በግብጽ ላይ ‹‹ፈርኦን›› ተብሎ ሲነግስ አማሮች ነበሩ ዙፋኑን የጠበቁለት። ይህን ቆየት ብዬ አብራራለሁ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሆነ በኋላ ‹‹ሪብላ›› የተባለች ሴት ልጁን ለሜሶጵታሚያ ንጉሥ ለናቡከደነጾር ሚስት ትሆነው ዘንድ በበርካታ የአማራ ወታደሮች አሳጅቦ (እና የመንግስት አማካሪዎችንና ጠቢባንን ጨምሮ) ወደ ሜሶጵታሚያ ላከለት። በዚህ መሰረት ነበር ዝቅ ብለው የሚያገኙዋት ‹‹አማራ›› የተሰኘችው ከተማ በአሁኗ በኢራቅ የተመሰረተችው።





ሚያዚያ 5 ቀን 505 ዓ.ም የተወለደው ቅዱስ ያሬድ (የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዜማ ደራሲ ማህሌታዊ ያሬድ) በቅድመ-አያቱ ኦሮሞ ከሆነች መደባይ ይወለዳል። እንደ እውነቱ ከሆነ በአባቱ በኩል የንጉሣዊ ቤተሰብ አባል የሆነ አንድ ዘመዱም መደባይ/ኦሮሞ ነው። አክሱም አጠገብ መደባይ የተባለ ቦታ ተገኝቷል። ያሬድ አክሱምን ከለቀቀ በኂላ እናቱ ወደምትኖርበት ወደዚህ መደባይ ወደ ተባለው ቦታ ነው የሄደው።(19)

በዚያን ወቅት ከንጉሠ-ነገሥት አክሱማይት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት ኢትዮጵያውያን ዘመዶቻቸው የሆኑትን ልዕልቶችን ‹‹ሕንደኬ›› የሚል የማዕረግ ስም እየሰጡ በግብፅ፣ በሊቢያ እና በኑብያ ንግሥቶች እያደረጉ የማንገሥ ልማድ ነበራቸው። እነዚህ ተሹዋሚ ንግሥቶች ከነገሡ በሁዋላም ያንጋሾቻቸው ንጉሣውያን ቤተሰብ አባላት ነበሩ። ከ2500 ዓመታት በፊት መርዌን እንድትገዛ በአጼ ፈንታሌ ነግሣ የነበረችው ሦስተኛዋ ሴት ፋሲላ እኖኒ የምትባል መደባይ ነበረች። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ኦሮሞ ነበረች ማለት ነው።(20)

ታሪከ-ነገሥት እንደሚለው ቀዳማዊ አጼ ዮሃንስ (ከ1660-1674 የገዙት) ከንግሥት ሰብለ-ወንጌል (የመደባይ ነገድ ከሆነችው) አጼ ኢያሱን ወለዱ።(21)

በትግራይ ክልል ውስጥ መደባይ ዛና የተባለ አካባቢ አለ። ትግራይ ካሉዋት 36 ወረዳዎች አንዱ ነው። ትግራይ ከጎጃም በስተሰሜን እንደመሆንዋ የተወለኑ መደባዮች (ኦሮሞዎች) ከዋናው መኖሪያቸው ከጎጃም ትንሽ ከፍ ብለው አሁን ትግራይ በሚባለው ቦታ ሰፍረዋል ማለት ነው። ቆይተውም ከዚያ አልፈው ወደ ደቡብም ሄደው ዛሬ ወለጋ፣ ሊሙ እና እናሪያ በሚባሉት ቦታዎችም ኖረዋል። በትግራይ ውስጥ ከሌሎች ነገዶች ጋር ራሱን የቀላቀለው መደባይ (ኦሮሞ) ልክ የራያ ኦሮሞ ኦሮምኛን ትቶ ትግርኛ እንደሚናገረው ባሁኑ ወቅት ትግርኛ ተናጋሪ ሆኗል።

አማራውን በተመለከተም ከቀዳማዊ ምኒልክ መወለድ በፊት ጀምሮ ለመኖሩ ሌላው ማስረጃ ቀዳማዊ ምኒልክ ከንግሥት ሳባ እና ከንጉሥ ሰለሞን ከሦስት ሺ ዓመት በፊት ሲወለድ አማሮች "ምኒልክ"

የጎሣ መስፈርት ሆነና አማርኛ ወይም ኦሮምኛ የሚናገር ማንኛውም ሰው ከቋንቋው አንፃር አማራ ወይም ኦሮሞ ይባል ጀመር። ከሥነ-ሕይወት ወይም ከስነ-ዘር አንፃር ግን ከአንድ ምንጭ የመጡ በመሆናቸው አማራም ኦሮሞም ሥረ-መሠረታቸው አንድ ነው። ማንም ልጅ በመወለድ ወይም በጉዲፈቻ በማደግ አማራ ወይም ኦሮሞ መሆን ይችላል። ቋንቋ የጎሣ መለያ መሥፈርት ነውና። ሁለቱም፣ የአማራም የኦሮሞም ጎሳዎች በዚህ መልክ ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው ይኸው እስከዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ይኖራሉ። የአመጣጣቸው እና አኗኗራቸው ሁኔታ ተጨባጭ እና ጠንካራ እውነታ ነው።

ግለሰቦች በተፈጥሮአዊ መንገድ ቋንቋን ሲለምዱ ለሚለምዱት ቋንቋ ባሕል፣ ልምድ፣ ሃይማኖት እና ሥነ-ልቦና እና ያኗኗር ይትባሕሎች ይገዛሉ። ይማረካሉም። (ይጋለጣሉ።) በዚህ ምክንያት ከቋንቋው ባለቤቶች ጋር ራሳቸውን ያመሳስላሉ፣ ያዋህዳሉ። ሆኖም ከኗሪው ጋር እየተጋቡ ካልተቀላቀሉ በስተቀር በደም ራሳቸውን ነው የሚሆኑት። ከተጋቡና ከተዋለዱ ግን ልጆቻቸው እና 2ኛ፣ 3ኛ 4ኛ ትውልድ ዝርያዎቻቸው የተቀላቀለ ጎሣ አባላት ይሆናሉ።

የትግራይ ራያ ኦሮሞዎች ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው። በደም ኦሮሞዎች ሲሆኑ በጎሣ ግን ያፍ መፍቻ ቋንቋቸው ትግርኛ በመሆኑ የትግራዋይ ጎሣ አባላት ሆነዋል። ጥቂቶች ግን ልሳነ-ክልኤ ሆነው ትግርኛም ኦሮምኛም ይናገራሉ። ጎሣ የሚወሰነው አፍ በፈቱበት ቋንቋ በመሆኑ እነዚህ ልሳነ ክልኤ የሆኑ ግለሰቦች በጎሣ ረገድ የትግሬም የኦሮሞም የሁለቱ ጎሣዎች አባላት ናቸው። ሆኖም በአካባቢው የበላይነትን የያዘው ቋንቋ ባሕሉን፣ ወጉን፣ ሃይማኖቱን፣ ሥነ-ልቦናውን እና የአኗኗር ይትባሕሉን ስለሚጭንባቸው ጎሣቸው የዚሁ ቋንቋ ጎሣ መሆኑ አይቀርም።

ጠቅለል ለማድረግ፣ ዘር፣ ጎሣ እና ነገድ ስነ-ሕወታዊ፣ ስነ-ልሳናዊ እና ባሕላዊ ዳራ ያላቸው አምደ-ቃላት ናቸው። ጎሣቸውን እና ነገዳቸውን መወሰን ያለባቸውም ግለ-ሰቦች ራሳቸው ናቸው። ለምሳሌ አንድ ሰው ኦሮምኛ አቀላጥፎ እየተናገረ ያፍ መፍቻው ግን አማርኛ ቢሆን ጎሣውም አማራ ነው የሚሆነው። ሆኖም የኦሮሞ ጎሣ አባል መሆን ቢፈልግ የሚከለክለው ነገር የለም። የሚፈልገውን መሆን





ይችላል። ይህ የማይነካበት ሰብአዊ መብቱ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የማንኛውም ጎሣ እና ነገድ አባል ተደርገው መቆጠር የማይፈልጉ ግለሰቦች ይኖራሉ። ኢትዮጵያዊ ወይም ሰብአዊ ተደርገው መታየት ብቻ ይሆናል የሚፈልጉት። መብታቸው ነው። የድሬዳዋ ልጆች ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። ልሳነ-ብዙ፣ ባሕለ-ብዙ፣ አፍቃሬ-ሰብዕ ናቸው። አንድ የድሬዳዋ ሰው ኦሮምኛ፣ አማርኛ፣ ሶማልኛ አልፎም አረብኛ አቀላጥፎ ሲናገር መስማት የተለመደ ነገር ነው። ባመዛኙ ጎሣቸው የሚወሰንበት አንድ ያፍ መፍቻ ቋንቋ ይኖራቸዋል። ወላጆቻቸው ምንም ዓይነት ቋንቋ ይናገሩ፣ የማንኛውም ጎሣ አባላት ይሁኑ፣ የድሬ ልጆች ልሳነ-ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ ቋንቋ-ተኮሮች አይደሉም። ለድሬዎች ቋንቋ መግባቢያ እንጂ መለያያ አይደለም። በቋንቋ፣ በባሕል እና በስነ-ልቦና ተቀላቅለው እና ተዋህደው የድሬ ልጆች አንድ ሆነዋል። የሐረር ልጆችም እንዲሁ ናቸው። የሚያስተሳስራቸው ኢትዮጵያዊነት ነው። ድሬ እና ሐረር ጎሣ ቀልጦ የሚዋሃድባቸው ለመላዋ ኢትዮጵያ አርአያ የሆኑ የአንድነት እና የፍቅር ማለሮዎች ናቸው።

"ብሔር" የሚለውስ እንዴት ይታያል? የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ አራማጆች "ብሔር" የሚለውን ቃል አላግባብ ተጠቅመውበታል። ኋላቀርነትን ያንጸባርቃል በሚል ከጎሣ ጋር እምታተውታል። ስህተት ነበር። ብሔር ጎሣን አይተካም። ቦታን ነው የሚያመለክተው። ብዙውን ጊዜ ትልቅ ወይም ትንሽ አካባቢን ይጠቁማል። ለምሳሌ ቡልጋ፣ ሸንኮራ፣ ምንጃር ተጉለት፣ ዳሞት፣ ዘጌ፣ ጩልያ፣ ሰላሌ፣ ተምቤን፣ እና ጨርጨር የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል። ለዚህ ነው በኔ ዕድሜ ከነበረው ከዚያ ተራማጅ ትውልድ በተቃራኒው የነበሩት በሳል ሰዎች የትውልድ ቦታቸውን ሲጠቅሱ "ዘብሔረ ቡልጋ፣ ዘብሔረ ዘጌ፣ ዘብሔረ ተምቤን ወዘተ" ይሉ የነበረው። በዚህ ረገድ "ዘብሔረ ኦሮሞ፣ ዘብሔረ አማራ" ማለት ትክክል አይደለም። ግልጽ ለመሆን "የኦሮሞ ጎሣ፣ የአማራ ጎሣ" ነው ማለት ያለብን።

ብሄሮችና ብሄረሰቦች እንዴት ይታያሉ? ብሄርና ብሄረሰብ የሚሉት ፅንሰ ሃሳቦች ወደ ኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡት ተማሪዎቹ ማርክሲዝም-ሌኒኒዝም-እስታሊኒዝም-ትሮትስኪዝም በሚያጠኑበት ወቅት ነበር። ከእነዚህ ከአራቱ ኢዝሞች ባለቤቶች

ዋናው ኮምዩኒስቱ የሩስያው ጆሴፍ እስታሊን የዛሬ መቶ ዓመት ገደማ በሶቭየት ሕብረት ምስረታ ወቅት ያቀነቀነው ሃሳብ ነበር።

በዚያን ወቅት ስታሊን ‹‹የብሄሮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል›› የሚለውን ጨመረበት እና ፕሮፖጋንዳውን ሠራ። ሆኖም አንዳንድ ብሔሮች ከሕብረቱ መውጣት(ከሶቭየት ሕብረት መገንጠል) ሲፈልጉ ግን በወታደር ኃይል አመቃቸው። ስታሊን ስለ ብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ያቀረበውን ሃተታ የመሰረተው፣ የፖሊሸዋ ሲቪል ዴሞክራት ሮዛ ሉክዘምበርግ (1909) በከተበችው እና ቭላዲሚር ኢሊች ሌኒን በፃፈው ጽሁፎች ላይ ነበር።

ስታሊን ጽሁፉን መጀመርያ በ1913 ሲያሳትም ብሔረሰቦች የሚለውን ፅንሰሃሳብ ‹‹አንድ ጂኦግራፊያዊ አካባቢ እና አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚጋሩ፣ ተመሳሳይ ስነ-ልቦናዊ አመለካከት እና አንድ አይነት ባሕል ያላቸው ሕዝቦች›› ብሎ ነበር የፈታው። እነዚህ አራቱ ነጥቦች የስታሊን አበይት መስፈርቶች ነበሩ። ይሁንና የስታሊን ፍቺ ሁሉአቀፍ አልነበረም። በአንዳንድ የሶቭየት ሕብረት ክልሎች እና በምስራቅ አውሮፓ ብቻ ነበር የተሰራበት። ለምሳሌ በፈረንሣይ እና በእንግሊዝ ሲተገበር አይችልም ነበር። (አልተሠራበትም።) በኢትዮጵያም ባጠቃላይ የሚሠራ አይደለም። ሁሉም የስታሊን መስፈርቶች የኢትዮጵያን እውነታ አያሟሉም። የአማራ እና የኦሮሞ ጎሳዎችን እንውሰድ፤ አማሮች እና ኦሮሞዎች በየትኛውም አካባቢ ቢኖሩ እያንዳንዳቸው መጠነኛ የድምፅ ቅላጼ እና የቃላት ልዩነት ይኖራቸዋል እንጂ በየቋንቋዎቻቸው ይግባባሉ። ምክንያቱም ሁሉም አማሮች የአንድ የአማራ ጎሣ፣ ሁሉም ኦሮሞዎች የአንድ የኦሮሞ ጎሣ አባላት ስለሆኑ ነው። ሆኖም ሁሉም አማሮችና ሁሉም ኦሮሞዎች ለየራሳቸው ባንድ ክልላዊ አካባቢ አይኖሩም። በስነ-ልቦናዊ አመለካከት እና በባሕልም እንዲሁም አንድ ወጥ አይደሉም። በሸዋ አማራ እና በጎጃም ወይም በጎንደር አማራዎች መካከል ልዩነት አለ። በኦሮሞም እንዲሁ ነው። በወለጋ፣ በባሌ፣ በአርሲ፣ በሸዋ እና በሐረር ኦሮሞዎች መካከል አንድነታቸው በቋንቋ ነው እንጂ በባሕል ልዩነት አለ። ስለዚህ የስታሊን የብሔር ብሔረሰብ መስፈርት ከቋንቋ በስተቀር ሌላው አይሠራም። ቋንቋ ደግሞ በዚህ ጽሁፍ እንደተገለፀው (እንደተሠራበት) መስፈርትነቱ ለጎሣ ነው። ስለዚህ ለኢትዮጵያ አውድ ተስማሚው





አገላለጽ ‹‹የብሔረሰብ ጥያቄ›› የሚለው ሳይሆን ‹‹የጎሣ ጥያቄ›› የሚለው ነው።

“ሀገር” የሚለው እሳቤም የተለያዩ ጎሣዎች የሚኖሩበትን ሰፊ ክልል የሚያመለክት ቃል ነው። ለምሳሌ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወለጋ፣ ሸዋ፣ ባሌ፣ አርሲ፣ ሐረር፣ ኢሉባቦር፣ ሲዳሞ፣ ከፋ፣... እንደማለት ነው። በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን "ጠቅላይ ግዛት" ይባል ነበር። በደርግ ጊዜ ‹‹ክፍለ-ሐገር›› ብለውታል። አሁን ደግሞ ምናልባት "ክልል" የሚለው ቃል ይቀርበዋል።

ከላይ በቀረቡት አንቀጾች “ጎሣ፣ ነገድ፣ ብሔር እና ሀገር” የሚሉትን ጽንሰ-ሀሳቦች አብራራን። እነዚህን አምደ-ቃላት ግልጽ ለናደርግ ብንጓዝ በውዥንብር ሐይቅ ውስጥ መዋኘት ነበር የሚሆንብን። "የብሄር ጥያቄ" የሚለውን ሐረግ በተመለከተም አባባሉ ስህተት ነው። ብሔር የሚለው ቃል ሀገር ከሚለው ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ አካባቢን ያመለክታል። እንደ ኢትዮጵያ ዓይነትዋን ሰፊና ትልቅ አገር መግለጽ አይችልም። "ብሔር" ነጠላ ቁጥር ሲሆን ብዙ ቁጥሩ በግዕዝ “ብሔራት” ባማርኛ ደግሞ “ብሔሮች” ነው። ስለሁሉም ብሔሮች ጥያቄ መናገር ሲፈለግ "የብሔራት ጥያቄ" ማለት ይኖርብናል። ሁሉንም የኢትዮጵያን ክፍላተ-ሐገራት ለመጥቀስ "አሕጉራተ - ኢትዮጵያ" እንላለን። መላዋ ኢትዮጵያ ደግሞ “ሀገር” ከምትባል “ዜጋ” ብትባል ተገቢ ነበር። ዜጋ ማለት ኢትዮጵያዊ ዜግነት ነው። ሆኖም በሰፊው ስለተለመደ “ሀገር” የሚለውን መጠቀም እንቀጥላለን። "ብሔራዊ ቋንቋ" የሚለውም እንዲሁ ነው። “ብሔራተ-ቋንቋ” ቢባል ይሻላል። “ልሳነ-ብሔራት” ደግሞ ይበልጥ የተሻለ ነው።

ይህን የጎሳ እና የዘር ጉዳይ ራቅ አርገን ብንመለከት፥ “ጎሣ” የግዕዝ ቃል ሲሆን ግሱ "ጎሠ" እንደሆነ አስተውለናል። የሥርወ-ቃሉ ጥልቅ ፍቺ “ተናገረ” ማለት ነው። በዚህ ጽሁፍ ሰዎችን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲመድብ ተደርጎ ተገልግሎበታል። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ከ"ዘር"፣ ከ"ደም" ወይም ከሥነ-ሕይወታዊ አመጣጥ ጋር ምንም ዝምድና የለውም። ለምሳሌ የኦሮሞና አማራ የዘር ምንጫቸው ነቢይ ከነበረው ንጉሥ ከደሸት/ደሴት/ እንደሚነሳ አጢነናል። የሁለቱም፣ ማለትም የኦሮሞም የአማራም ወላጅ አባት እና አያት ደሸት ነው ብለናል። የደሸት ቅድመ-አባትም የሳሴም/የኢሩሳሴም/

ንጉሥና የእግዚአብሔር ዓቢይ ካህን የነበረው የመልከጼዴቅ ልጅ የሆነው ኢትኤል ወይም ኢትዮጵ እንደሆነ ተመልክተናል። የሳሌም ንጉሥ ይባል የነበረው ታላቁ ካሕን መልከጼዴቅ የባቢሎን ንጉሥ እና የባቢሎን ግንብ አሠሪ የነበረው የናምሩድ ተወላጅ ነው። ናምሩድ የኖኅ ዝርያ ሲሆን ኖኅም የማቱሳላ፣የሄኖክ፤ ሄኖክም የአዳም እና የሄዋን ልጅ ለባትኛ ልጅ ነው። ብናምንም በናምንም፥ ብነቀበለውም ባንቀበለውም፥ ትክክለኛው ሥነ-ሕይወታዊ ወይም ዘራዊ አመጣጣችን ይህ ነው። ይህን የሚለው ማን ቢወልድ ማን ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው የዘር ሃረጋችን ነው።

ቋንቋን በተመለከተ ደግሞ የባቢሎን ግንብ እስከሚፈርስ ድረስ ሁሉም ልሳነ-ሰብዕ ይባል የነበረውን የሱባን ቋንቋ ነበር የሚናገሩት። እግዚአብሔር የአማጽያኑን ቋንቋ ከቀያየረባቸው እና የባቢሎን ግንብ ከፈረሰ በኋላ ግን የሱባ ቋንቋ የካሕናቱ ብቻ መገልገያ ሆኖ ከመልከጼዴቅ ወደ ኢትዮጵ፣ ከኢትዮጵ ወደ ደሸት (ደሴት) ከደሸት በክህነት ስሙ እስያኤል ወደ ሚባለው ወደ እሴ ወይም አዜ እየተላለፈ እሱን በቂም በቀል በስተ አርጅናው ገድላ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠችው ንግሥት ሳባ ከንጉሥ ሰለሞን የወለደችው ቀዳማዊ ምኒልክ በአዋጅ እስካጠፋው ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ለ1000 ዓመት ሲነገር ኖሯል። የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት የመጨረሻዋ ገዢ ንግሥት ሳባ ነች። እኛ ኢትዮጵያውያን የሱባን ቋንቋ እና ለዚህ መጽሐፍ የሽፋን አርማ ዕንዲሆን የተደረገውን የሱባን ፊደል ያገኘነው በዚህ ሁኔታ ነው። የባቢሎን ግንብ ታሪክን ተረት ነው ብለን ብንተወው እንኳ የሱባን ቋንቋ ሕልውና ልንክደው አንችልም። ምክንያቱም ፊደሉ፥ መጣጥፎቹ እና መዝገበ ቃላቱ በእጃችን ይገኛሉና። ስለዚሕ ሥነ-ልሳናዊ በሆነው "ጎሣ" በሚለው ቃል እና ሥነ-ሕይወታዊ በሆነው "ዘር" በሚለው ቃል መካከል ልዩነት እንዳለ መገንዘብ ይኖርብናል። ምንም እንኳ የሰው ዘር በሙሉ ምንጩ አንድ ቢሆንም በሂደት እየተራባ በተለያዩ አካባቢዎች በመኖሩ የተነሳ የተለያዩ ቋንቋዎችን መናገር ሲጀምር የተለያዩ ጎሣዎች ባለቤቶች ሆኗል። በሱ ስርም አያሌ ነገዶችን አፍርቶአል።.

የዝርያ ብዙሃንነትን በተመለከተ "ኅብረ-ብሔራት" ማለት ተስማሚነት አለው። ኢትዮጵያ የበርካታ ዝርያዎች ሀገር መሆኗን ከማመልከቱም በላይ ዝርያዎቹ ኅብረት ፈጥረው በሰላም አብረው መኖራቸውንም ያመለክታል።





ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1000 ዓ.ዓ ገደማ የወንድማማቾቹ የጀማ እና የማራ (አማራ) ልጆች ከነባር የጋፋት ሕዝቦች ጋር መዋጋት ስለቻቸውና ወደ ምስራቅ አቀኑ። በዛም የጀማ ልጆች ዛሬ ሸዋ በሚባልው ውስጥ አንድ ወንዝ አገኙና ለአባታቸው መታሰቢያ እንዲሆን ጀማ ብለው ጠሩት (አሁን ዠማ ይባላል)። ማራ (አማራ) ዎች የሰፈሩባቸውን ቦታዎች ሸበል በረንታ፣ ዑሬራ፣ ግራርጌ፣ አዲስጌ፣ መራ (አሁን መራ-ቤቴ)፣ አማራ ሳይንት፣ ሊኮ (አሁን ወሎ)፣ ካቢ እና ገነቴ (እሁን የጁ) እያሉ ጠሩአቸው። (40)

ጀማዎች የግራኝን ወረራ አጥብቀው በመቃወማቸው በአህመድ ግራኝ ክፉኛ ነው የተጎዱት። ግራኝ ለደጋፊዎቹ አረቦች (ኢትዮጵያን የማጥፋት ዓላማ ይዘው ሳስታጠቁትና ከጎኑም ተሰልፈው ለተዋጉለት አረቦች) በባርነት ሸጣቸው። ሆኖም የተ ጫኑባቸውን መርከቦች እስፔናውያን ማረኩዋቸውና ዛሬ በስማቸው በጀማ ጃማካ ወይም ጃማይካ በተባለው አገር በባርነት ኖሩ። (41) አገሪትዋም በስማቸው ትጠራ ጀመር። ጀማዎች፥ ማለትም የአሁኖቹ ጃማይካዎች ኢትዮጵያን ከልክ በላይ የሚያፈቅሩትና ራሳቸውንም እንደ ኢትዮጵያውያን የሚቆጥሩት ያለምክንያት አይደለም። ምንም እንኩዋን የታላለቆቹ የኢትዮጵ እና የደሸት ዘር መሆናቸውን አእምሮአቸው ቢረሳውም የደማቸው ነፍስ ስለእስታወሰው ኢትዮጵያውያን ነን ብለው ግዕዝን እስከመማር እና የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርትያን እባላት እስከ መሆን በቅተዋል። በተጨማሪም አረንጉዋዴ፤ ቢጫ እና ቀይ የሆነችውን ማንነታችንን ያልተረዳን ሰዎች የምንንቃትን ሰንድቅአላማችንንም የራሳቸው አርማ አድርገው በኩራት ያውለበልባሉ። ከእነማይና ዘረ-ደሸቶች በተጨማሪ፥ የአባታቸውን ስም አሁን ድረስ ጠብቀው ያቆዩ ጥቂት የአማራና የመደባይ የሥጋ ዘመዶች በጎጃም ውስጥ አሉ። የቀሩት ግማሾቹ በስተ ሰሜን ዛሬ ጎንደር እና ትግራይ ወደ ሚባሉት ክልሎች፣ ግማሾቹ በስተ ደቡብ ወደ ወሰጋ እና እናሪያ (አሁን ሊሙ) ወደሚባሉት ቦታዎች ሄደዋል። ቀስ በቀስ ቁጥራቸው ሲበረክት ደግሞ ወደ ባሲ (አሁን ባሌ)፣ ሶማሊያ፣ ኬንያ (በቦረና በኩል)፣ ሩዋንዳ (የሩዋንዳ ቱቱሲዎች እሮሞ መሆናቸውን ያምናሉ፤ ኢትዮጵያዊ መልክም ይታይባቸዋል፤ ሁቱዎች ሲያጠቁዋቸው ሲፎክሩ ወደ ሃገራችሁ ኢትዮጵያ ተመለሱ እያሉ ነበር።) እልፎም እስከ ኒጀር እና ማደጋስካር ድረስ ዘልቀዋል።

ማደጋስካር ውስጥ በኦሮምኛ ቋንቋ የሚናገሩ ያገሪቱ ዜጎች እንደነበሩ እዚያ ይኖር የነበረ አንድ ጓደኛዬ ከ45 ዓመት በፊት አጫውቶኛል። የማሊ ህዝብም የኦሮሞ ተወላጅ ነው። በኦሮምኛ ‹‹ማሊ› ማለት ‹‹ምንድነው?›› ማለት ነው። ማሊ የሚኖር ሌላ ኢትዮጵያዊ ጓደኛዬም ከማሊያውያን ጋር በኦሮምኛ ቋንቋ ይግባባ ነበር።

አፍሪቃን ሲያካልሱ ቆይተው በተለያዩ ጊዜያት ወደ አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሱ ኦሮሞዎች ብዙ ናቸው።

ኢትዮጵያውያን የታሪክ አዋቂዎችን ለምሳሌ አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስን፣ አለቃ ታዬንና አልፎም አቶ ተክለጻድቅ መኩሪያን ኦሮሞዎች በሞዛምቢክ፣ ማደጋለካርና ኬንያ በኩል ከእስያ መጡ ለማለት ያነሳሳቸው ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል።

በዛሬዎቹ ጎጃም፣ ወሎ ጋ እና አናርያ የቀሩ በርካታ መደባዮች የጥንት አባቶቻቸውን የመልከጼዴቅን የንጉሦች ንጉሥ እና የሳሌም (የኢየሩሳሌም) ከፍተኛው ካህንን፣ የኢትዮጵንና የዝርያውን የደሸትን (የኦሮሞና የአማራ አባት)ን መንፈሳዊና አእምሮአዊ ባሕል ቀዳማዊ ምኒልክ የሃይማኖት ጭፍጨፋ እስከ አካሄደባቸው ጊዜ ድረስ ሳይለቁ ጠብቀው በመያዝ ቀላውስት፣ ፈላስፎች እና ሊቃውንት እየሆኑ ነበር።

ቀዳማዊ ምኒልክ መደባዮችን በከፊል የጨፈጨፋቸው ኢትዮጵያን ወደ አይሁድ ምድርነት ለመቀየር የነበረውን መሰሪ እቅድ በመቃወማቸው ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ እነሱንና መጽሐፎቻቸውን አጠፋ። ከአንድ ሺ ዓመት በሁዋላ እየሱስ ሲወለድ ወደ ኢየሩሳሌም እየመራ የሚወስዳቸው ኮከብ ምስል ያለበትን አርማቸውንና የጥበበ-ብልሃት ምልክታቸውን ለውጦ በዙፋኑ ላይ የይሁዳ አንበሳን ምስል አደረገ። አንዳንድ መደባዮች ጭፍጨፋውን በመፍራት በጥንቱ የሱባ ቋንቋ የተጻፉ መጽሓፎቻቸውን ደበቁ ወይም ለቀዳማዊ ምኒልክ አስረከቡ፣ እና እሱም የወረሳቸውንና በጁ የገቡትን መጽሓፎች በሙሉ አቃጠላቸው። በዚህ ያዘነ አንድ መደባይ መጽሐፉን ለንጉሡ ሳላስረክብም ብሎ ለሳሙ አብልቷታል። ጥቂት ቆየት ብሎ ላሚን ሊያርዳት የተወሰነ ጽሁፍ በስጋዋ ላይ ማግኘቱ ተዘግቧል። እሱና ልጆቹ አንዳንዶቹን ፊደሎች አገጣጥመው ለመተርጎምና ስለታሪካቸው ፍንጭ ለማግኘት በመሞከራቸው መደባይን "ኦሮሞ" ብሎ መጥራት





ተጀመረ። በሱባ ቋንቋ ‹‹ኦሮሞ›› ማለት ‹‹እውቀት ገላጭ፣ ተርጓሚ፣ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን የሚያነብ ብልኅ ሰው›› ማለት ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ‹‹መደባይ›› የሚለው መጠሪያ እየቀረና ‹‹ኦሮሞ›› የሚለው እየጎላና እንደ ለደድ እሳት እየተዛመተ መጣ።

የቀዳማዊ ምኒልክን መንግሥት እንዲያገለግሉና የአጋዚን ባህል እንዲሳበሱ የተገደዱ መደባዮች (አርባ ሺ የጋዛ ሰዎች፣ ሃያ ስምንት ሺዎቹ ጀቡሳይቶች/ኢያቡሳውያን/፣ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከእስራኤል መጥተው የነበሩ) የታላላቅ አባቶቻቸውን የኢትዮጵንና የደሸትን የሱባ ቋንቋ አርግፍ አድርገው ትተው የግዕዝ ተናጋሪዎች ሆኑ። እነዚህ አጋዚያን አቡሳውያን ይባላሉ። ራሳቸውን ያዳቀሉ ነገዶች ናቸው። ሐበሻ ወይም አበሻ የሚለው ቃል ‹‹ድብልቅ›› ወይም ‹‹ክልስ›› እለዛም ‹‹አበሳ›› የሚል ክብር ነኪ ፍቺ አለው። የተከበረውን ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን ከእስራኤል ክልሶች ጋር ማምታታት ካላስፈለገ በስተቀር የአማራ ብዙኃን አበሾች አይደሉም። ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵ ልጆች ናቸው። የኢትዮጵ ልጆች ስለሁኑም ኢትዮጵያውያን ናቸው። ኢትዮጵያውያን ተብለው ነው መጠራት ያለባቸው። ቀዳማዊ ምኒልክ አግኣዚዎችን ሥልጣን ላይ አውጥቶ መንግሥታቸውን፣ ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፣ የሰለሞን ሥርወ-መንግሥት የተባለውን በኢትዮጵያ መሰረተ።

በዘመነ-መሳፍንት ማብቂያ ላይ የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጎንደርን ማዕከል አድርጎ ራሱን ‹‹የጋላ እና የአቢሲኒያ ንጉሥ›› እያለ ይጠራ ከነበረው መንግሥት እውቅና ውጪ የራሳቸውን ግዛት መሰረቱ። ልጆቻቸው ንጉሥ ኃይለመለኮት እና ዳግማዊ ምኒልክም እንደዚያው በማድረግ ቀጠሉ። እነዚህ ሶስቱም ራሳቸውን ከአግኣዚ (አበሻ፤ አቢሲኒያ) ጋር አገናኝተው የሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት ይጠቅሱ ጀመር።

አፄ ምኒልክ ከሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት እና ከአግኣዚ ጋር አለኝ ለሚሉት ትስስር እውቅና ሲሰጡ ‹‹ንጉሠ-ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ስዩመ እግዚአብሔር ድል አድራጊው የይሁዳ አንበሳ›› ብለው ራሳቸውን ጠሩ። ምንም እንኳ እነዚህ ሶስቱ ነገሥታት ከአግአዚ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ብቻ ቢጠቅሱም የኦሮሞ ሥረ-መሠረታቸው የሚካድ አይደለም። የይኩኖ አምላክ (ተስፋ ኢየሱስ) የልጅ

የሆነችውን ናኦድ ሞገሳ እሌኒ 3ኛ ብሎ የጠራትን የቱሉ በዴላን ልጅ አግብቷል፡፡

ልጁ አጼ ልብነ ድንግል አባቱ ሲያርፍ ትንሽ ልጅ በነበረበት ወቅት ኦሮሞዋ እያቴ ንግስት ጃን ክብራ እሌኒ 2ኛ እና የቱሉ በዴላ ልጅ የሆነችው ወላጅ እናቱ እሌኒ ናኦድ ሞገሳ 3ኛ ከቱሉ በዴላ ጋር ሆነው ኢትዮጵያን ገዝተዋል፡፡ ብልህዋና ተከባሪዋ የኦሮሞ ንግሥት እሌኒ ጃን ክብራ 2ኛ ከፖርቱጋል ጋር ለተመሰረተው ፖለቲካዊና ወታደራዊ ግንኙነት አጋዥ ኃይል ነበረች፡፡ የእሌኒ ናኦድ ሞገሳ ወንድም፣ ዶሪ ቱሉ በዴሳ ንጉሠ ባህረ-ነጋሽ ተብሎ ነግሦ የቀይ ባሕር እና የኤርትራ ገዢ ሆኗል፡፡ ሲሞት ልጁ ባሕረ-ነጋሽ ይሥሃቅ ዶሪ ቱሉ በዴላ በእግሩ ተተክቶ ነግሷል፡፡ በዚህም የኦሮሞ ንግሥቶች ልጆች በተዋረድ የኦሮሞ ዝርያ ነገሥታት ሆነዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ታዋቂው የታሪክ ፀሐፊ ተክለ-ጻዲቅ *መኩሪያ (የኢትዮጵያ ታሪክ) ‹‹ንግሥት ናኦድ ሞገሳ እሌኒ ሐድያ ናት››* ብለው የጻፉትን እዚህ ላይ ማንሳት ይኖርብኛል፡፡(43) ‹‹ቱሉ በዴላ›› የሚለው ያባትዋ ስም ኦሮሞ መሆንዋን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪ ሐረር ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ ‹‹በዴላ›› እየተባለ የሚጠራ ቦታ አለ፡፡ የቱሉ አባት አቶ በዴላ ባላባት ሆኖ እሱን ለማታወስ ከጊዜ በሁዋላ በሉ ስም ቦታው በዴላ ተብሎ ይሆናል፡፡ ወይም እሱ ከመወለዱ በፊት በዴላ ተብሎ በዴላን ለመዘከር የተሰየመ ነው፡፡ ሐድያ ውስጥ ግን እኔ እስከማውቀው ድረስ ‹‹በዴላ›› የሚባል ቦታ የለም፡፡

ኦሮሞው በኢትዮጵያ በቀል ሕዝብ ሆኖ፤ በእግአዚ የሰለሞናዊው ስርወ-መንግሥት ንጉሳውያን ቤተሰብ አባላት ያን ያህል ሲከበርና በጋብቻም ተቀላቅሎአቸው ሳለ ለምን ተገለለ? ለምንስ "አረመኔ" እና "ያልተገረዘ" እየተባለ ተጠራ? ለምን እንደ ለደተኛና ወራሪስ ተቆጠረ? ሁለት ምክንያቶች አሉ፡- መደባይ፣ የኦሮሞ ግንዱ ከሦስት ሺ ዓመት በፊት "ኦሮሞ" የሚል አዲስ ስያሜ ተሰጠውና መደባይ የሚለው ጨርሶ ተረሳ፡፡ ጥቂት መደባዮች ብቻ የቆየውን መጠሪያቸውን/መደባይ የሚለውን/ እንደያዙ መኖር እና መበልጸጋቸውን ቀጠሉ፡፡ አሁንም ድረስ በዚሁ ስም መደባይ ዛና እና መደባይ እየተባሉ በትግራይ ውስጥ እና በወንበርማ አካባቢ በጎንደር





አሉ፡፡ አዲሱን መጠሪያ (ኦሮሞ የሚለውን) የያዙት ግን መደበኛውን መኖሪያቸውን እየተዉ በኢትዮጵያ ውስጥና በውጭ አገሮች አዳዲስ መኖሪያ ፍለጋ ተበተኑ፡፡ ያገራቸውን ድንበር አቋርጠው ሄደው ብዙ ዓመታት ያስቆጠሩ ኦሮሞዎች በኢትዮጵያውያን ዘመዶቻቸው ፈጽሞ ተረሱ፡፡ ከብዙ ዓመታት መለየት በሁዋላ ተመልሰው ሲመጡ እንደ ወራሪ ተቆጠሩ፡፡ ከኢትዮጵያ ሳይወጡ የኖሩት ኦሮሞዎች በሙስሊሙ አህመድ ግራኝ እና እንደገና በተመሰረተው ሰለሞናዊ ስርወ-መንግሥት ስር በነገሡ (እንደ እውነታው ግን ራሳቸውም ኦሮሞዎች በነበሩ) ክርስቲያናዊ ነገሥታት መካከል ጦርነት ሲካሄድ አጋጣሚውን ተጠቅመው አዳዲስ ስም መሬቶችን ተቆጣጠሩ፡፡ በዚህም አህመድ ግራኝን ባለመውጋታቸውና ገለልተኛ በመሆናቸው እንደ ጥቅመኛና ከሃዲ ተቆጠሩ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ለኦሮሞ ንጉሣዉያን ቤተሰብ ቅርበት የነበራቸው የኦሮሞ ጎሣ መሪዎች ዝና የወደቀበት ዋናው ምክንያት አንዳንዶቹ ለአህመድ ግራኝ በመወገናቸው ነው፡፡ መጀመሪያ ላይ ከኦሮሞ የጎሣ መሪዎች አንዱ የሸዋው አባ ጉቺ ኤልማያ በቱርክ፣ በአረብ፣ በሶማሊ፣ እና በአህመድ ግራኝ የአዳል ጦር ሰራዊቶች ላይ መሬት ጠብ የማይሉ መርዛማ ቀስቶችን እያዘነቡባቸው ከባድ ጉዳት አድርሰውባቸው ነበር፡፡ ይህ የሆነውም በባዱቂ (በሁዋላ ቢሾፍቱ በቅርቡ ደግሞ ደብረ-ዘይት በተባለው) ጦርነት ነው፡፡ ኢላማቸውን በማይስቱት ከአባ ጉቺ ኤልማያ ሰራዊት በሚተኮሱት ቀስቶች የሉ ሠራዊት ክፉኛ መጎዳቱን የተገነዘበው ግራኝ ለአባ ጉቺ ስጦታ ልኮ፣ ሌላ የበለጠ ስጦታ እንደሚሰጣቸው፣ ግዛታቸውን እንደማይነካባቸው እና እርሳቸውንም ሆነ ህዝባቸውን እስልምናን ተቀበሉ ብሎ እንደማያስገድዳቸው ቃል ገብቶ ከክርስቲያኑ ንጉሥ ከአጼ ልብነ-ድንግል ጎን ቆመው እሱን ከመውጋት ተቆጥበው ገለልተኛ እንዲሆኑ አግባባቸው፡፡ አባ ጉቺ ክርስቲያንም እስላምም ስላልነበሩ በክርስቲያኑና በሱ በእስላሙ መካከል በሚደረገው የሃይማኖት ጦርነት ጣልቃ ከመግባት እንዲታቀቡ መከራቸው፡፡ አባ ጉቺ ኤልማያም ክርስቲያኖችን እነደማይረዱ ማሉለት፡፡(44) አባ ጉቺ ኤልማያን መንግሥትንና አገሪቱን ከድተዋል ብለው የኢትዮጵያው ንጉሠ-ነገሥት ወነጀሏቸውና ለግድያ ሲያሳድዷቸው አባ ጉቺ የሰሌ (ሰላሌ) ኦሮሞ መሪዎችን፤ አባ መርዞ፣ አባቡላ፣ ንጉሥ አባ ቆርቾ እና አባ ጉታ የተባሉትን የኦሮሞ

ባላባቶች አስተባብረው ሽንብራ ኩሬ (አዳማ ወይም የዛሬዋ ናዝሬት) በተባለው ቦታ ድንገት ሳይታሰብ የንጉሠ-ነገሥቱን ጦር ገጥመው አጠቁ፡፡ የሽንብራ ኩሬ ጦርነት ከተካሄደ አንድ ቀን በኋላ ንጉሠ-ነገሥቱ ሰራዊታቸውን አሰባስበው ግራኝን እንደገና ስመግጠም ሲያስቡ የኦሮሞ ጎሣ መሪዎች በነዚያ መርዘኛ ቀስቶቻቸው በርካታ ክርስቲያን ወታደሮቻቸውን ገደሉባቸው፡፡ በዚህ ሳቢያ በጎሣ መሪዎቹና በንጉሠ-ነገሥቱ ጦር መካከል ከባድ ጦርነት ተደርጎ ከሁለቱም ወገን ብዙ ደም ፈሰሰ፡፡ በመጨረሻ የጎሣ መሪዎቹ ሁሉም ተገደሉና እነሱም ተከታዮቻቸውም ከሃዲዎች፣ ያልተገረዙ፣ አረመኔዎች ተባሉ፡፡ ከመላ ሐገሪቱ ውስጥ በጣት የሚቆጠሩ የጎሣ መሪዎች ንጉሠ-ነገሥቱን ስለከዱ ሁሉም ኦሮሞዎች መገለል እና መዋረድ ደረሰባቸው፡፡

በዚህም ኦሮሞዎች፣ የኢትዮጵ ልጆች፣ የደሸት እና የመደባይ ልጆች፣ የነገሥታት ዘሮች፣ ብልሆች፣ ነቢያት፣ ሊቃውንትና አገራቸውን አፍቃሪዎች በመሆናቸው እጅግ እንዳልተከበሩና እንዳልተፈቀሩ ሁሉ እየተናቁ በርካታ ዓመታት አሳለፉ፡፡ (45)

ሳልሳዊ ኢትዮጲስ ፣ የምድያም ከፍተኛ ካህን የሆነው የየትሮአብ የልጅ ልጅ ከ3400 ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ *ሱባ* የተባለ ከተማ መስርቶ ነበር፡፡ የመልከጼዴቅ ልጅ የኢትዮጵ ዝርያዎች በዚያ ከተማ ይኖሩ ነበር፡፡ የኬንያና የታንዛኒያ አባ ሱባዎች ምናልባት ከሱባ ከተማ የፈለሱ ይሆናሉ፡፡ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ከሦስቱ የኢትዮጵ ሴት ልጆች አንዷ *ሱባ* ትባል ነበር፡፡ አባ ባሕርይ እንደነገሩን ሜጫ ደእሌን ይወልዳል፡፡ ደእሌ ሱባን እና ሌሎችን ይወልዳል ፡፡ ኢትዮጵያ መጠሪያዋን ያገኘችበት ንጉሠ-ነገሥት ኢትዮጵ ከኦሮሞዎች ጋር ምንም ዝምድና ባይኖረው ኖሮ ኢትዮጵ ከ4000 ዓመት በፊት ለልጁ መጠሪያ ያደረገውን ‹‹ሱባ›› የሚለውን ስም እንዴት ኦሮሞም ለልጁ መጠሪያ ሊያደርገው ቻለ? ተዛምዶው ግልጽ ነው፤ ፍንትው ያለ! ይህ የሚያረጋግጠው የኦሮሞ ጥንተ-አባት ኢትዮጵ መሆኑን ነው፡፡ ኢትዮጵ ለኦሮሞ ብቻ ሳይሆን ለሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ሁሉ መገኛ አባት ነው፡፡ ሱባ ብርቅዬ የሆነ ቆንጆ የኦሮሞ ቃል ነው፡፡ የሰው እና የከተማ ስም ይሆናል፡፡ የቋንቋችንና የፊደላችን መጠሪያም ነው፡፡ ከአፍሪቃ ጥንታዊው መናፈሻ ሱባ ይባላል፡፡ በአምቦ መስመር መናገሻ ከተማን አለፍ ብሎ ከአዲስ አበባ 17 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ኦሮሞውና አማራው እስከ ዛሬ በሚኖሩባቸው ቦታዎች ‹‹ሱባ›› የሚል





ስያሜ መኖሩ ኢትዮጵ ከኦሮሞ እና ከአማራ ጋር እንዲሁም አማራ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ጋር ያለውን ዝምድና ያመለክታል፡፡

‹‹ሱባ›› ባለፉት ጊዜያት የተለየ ግምት የሚሰጠው ልዩ ቃል ነበር፡፡ የኦሮሞ ሊቃውንት እና ነቢያት የሚጽፉበት ፊደል ‹‹የሱባ ፊደል›› ይባል ነበር፡፡ የሱባ ቋንቋም አዳምና ሄዋን ይነጋገሩበት የነበረው የመጀመሪያው ሰብአዊ ቋንቋ እንደነበረ ይገመታል፡፡ ሱባ የሚለው ቃል የተገኘው ‹‹ሰብ›› ከሚለው ቃል ነው፡፡ ትርጉሙም በሱብኛ ‹‹ሰብአዊ›› ማለት ነው፡፡ የሱባ ፊደልም የሱባ ቋንቋ በጽሁፍ የሚገለጽበት ብልሃት ነበር፡፡

አዲስ አበባ የሚኖር የመረጃ ምንጩ፡- ‹‹ሱባ›› የሚባሉ አንድ አዛውንት ከብዙ አመታት በፊት አዲስ አበባ ይኖሩ እንደነበር ነግሮኛል፡፡ ያ ወዳጄ እንደነገረኝ አዛውንቱ ከኦሮምኛ ጋር ተመሳሳይ ቋንቋ ይናገሩ ነበር፡፡ የተወለዱት በትግራይ እና በኤርትራ ድንበር ኢሮብ አጠገብ ለየት ያሉ ሰዎች በሚኖሩበት “ሱባ” በተባለው ቦታ ነበር፡፡ የነዚህ ሰዎች ቋንቋ ከኦሮምኛ ጋር በደንብ የሚቀራረብ ከሆነ ኦሮምኛ የመጣው ከሱባ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ጉዳይ በወጉ ሊጠና ይገባል፡፡ አንድ የኢሮብ ማኅበረሰብ አለ፡፡ ምናልባት ይህ ማኅበረሰብ ሱባንና ኗሪዎቹን በተመለከተ ብርሃን ይፈነጥቅ ይሆናል፡፡

ግእዝ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ቋንቋ ከመሆኑ ከሦስት ሺ ዓመታት በፊት የመደባይ (ኦሮሞ) ማጂ ቀሳውስት እና ሊቃውንት ከጥንት አባቶቻቸው ከመልከጼዴቅ፣ ከኢትዮጵ እና ከደሸት በወረሱት መሰረት በሱባ ቋንቋ እና ፊደል ነበር የሚናገሩትና የሚጽፉት፡፡ ከፍ ብዬ እንደገለጥኩት፣ በኋላ ግን ቀዳማዊ ምኒሊክ በሱባ ቋንቋ የሚናገር እና የሱባ መጽሐፍ የሚገኝበት ማንኛውም መደባይ/ኦሮሞ/ ይገደል ሲል አወጀ፡፡ በዚህ ምክንያት የመደባይ/ኦሮሞ/ ሊቃውንት በሱባ ቋንቋ መጻፍ አቆሙ፡፡ እንደ እድል ሆኖ በሱባ ቋንቋና ፊደል የተጻፉ ጥቂት መጽሐፎች ተርፈውልናል፡፡ ቀጥሎ በሱባ ቋንቋ በብራና ላይ ከተጻፈ መጽሐፍ የተወሰዱ ጥቂት ገጾችን እና የሱባን ፊደል ለየብቻ እንመለከታለን፡-














Ya yi yă yā ye yu yue yuā yowa yo
Nga
Na ni nă nā ne nu nue nuā nowa no
Fa fi fă fā fe fu fue fuā fowa fo
Va vi vă vā ve vu vue vuā vowa Vo
Ba bi bă bā be bu bue buā bowa bo










2
Pa Pi Pă Pā Pe Pu Pue Puā Powa Po
Ma mi mă mā me mu mue muā mowa mo
Ra ri ră rā re ru rue ruā rowa ro
La li lă lā le lu lue luā lawa lo
Tda
Da di dă dā de du due duā dowa do
Ta
Ta ti tă tā te tu tue tuā towa to
Sa si să sā se su sue suā Sawa So

*ላይ)* እና ሁለተኛው አሜሪካዊ፣ ጊ. ደብልዩ. ቦዌርሶክ፣(*የአዱሊስ ዞ.ፋን*፣ *ገጽ* 69 ላይ) የግዕዝ ፊደል ከሳባዉያን ሆሄያት ጋር ስላለው ዝምድና ያሉት ነገር አለ፡፡ ስርግው ሃብለሥላሴ እስከ 20ኛው ክፍለ-ዘመን አጋማሽ ድረስ ግዕዝ ከሳቢያን ተገኘ ብለው ምሁራን ያምኑ ነበር፤ ሆኖም ግዕዝ ከሳባውያን ራሱን አግሏል ሲሉ ይህንን ግምት ውድቅ ያደርጉታል ብለዋል፡፡ ጊ. ደብልዩ. ቦዌርሶክ ደግሞ በተቃራኒው "የግዕዝ ፊደል ከሳባ ፊደል መቀዳቱ እውነት ነው፤ ሆኖም አሁን (በ4ኛው ክፍለ-ዘመን) ፊደላቱ የተለዩ ሆነዋል፤ አፃፃፉም ሳባ እንደ ሚጻፍበት ሳይሆን ከግራ ወደ ቀኝ ተቀይሯል" ሲሉ ጽፈዋል፡፡ አሜሪካዊው የታሪክ ሊቅ ወደ ሰነዘሩት ሃሳብ አደላለሁ፤ ምክንያቱም ሳቢያን ምንጫቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረችው እና ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1400 ዓመተ-ዓለም በአጼ እስያኤል የተመሰረተችው ሳባ ከተማ በመሆኗ እና አጼ እስያኤል የአረቢያ ቅኝ ገዢ የነበረና የሳባን ፊደል እና ዘመናዊ ሥልጣኔን ከኢትዮጵያ ወደ አረቢያ የወሰደ በመሆኑ ነው፡፡ የተገላቢጦሹ ግን አይደለም፡፡ ምክንያቱም በአረቢያ ውስጥ በዚህ ስም የሚጠራ ምንም ዓይነት ከተማ ከመመስረቱ በፊት ሳባ ከተማ ኢትዮጵያ ውስጥ ነበረች፡፡ በተጨማሪም በዚያን ጊዜ ቀይ ባሕር አጠገብ የነበረችውን አረቢያን ቀርቶ በአጼ እስያኤል ሥም የተሠየመውን እሕጉር እስያንም ኢትዮጵያ ትገዛ ነበር፡፡ ይህም ከአጼ እሰያኤል ቀጥሎ ወደ ሥልጣን የመጣችው እና አረቢያንና አስያን ከሉ ወርሳ ካስተዳደረችው ከንግሥት ሳባ በፊት ነው፡፡ አንዳንዶቹ የግዕዝ ፊደላት ከሳባ ሆሄያት ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ አንድ ሰው አንዳንድ የሳባ-ኢትዮጵያ ፊደላትን ቢገለብጥ ግዕዝ እስከ 4ኛው ክፍለ-ዘመን ሲቆጠር ለ1400 ዓመታት ከነሉ ርቆ ስለነበር ነው፡፡ አባክዎ አንዳንዶቹ ሆሄያት ከግዕዝ ፊደሳት ጋር መመሳስላቸውን በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ያለውን የሳባን ፊደል ተመልከተው ያረጋግጡ፡፡







በሳባዊ ፊደላት የተጻፈበጽ ጥንታዊ ሐውልት

የአያት ቅድመ-አያቶቻቸውን ክብር ታላቅነትና ዝና መረዳት የተሳናቸው አንዳንድ ኢትዮጵያውያን "ግዕዝ" እየተባለ የሚጠራው የኢትዮጵያ ፊደል "ከአርመን ፊደል የተቀዳ ነው" ይላሉ፡፡ ይህ ፍጹም ስህተት ነው፡፡ እውነታው የዚህ ተገላቢጦሽ ነው፡፡ ከክርስቶስ ልደት እስከ 5ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ድረስ አርመኖች የራሳቸው ፊደል



በሳባዊ ፊደላት የተጻፈበጽ ጥንታዊ ሐውልት

የኣያት ቅድመ-ኣያቶቻቸውን ክብር ታላቅነትና ዝና መረዳት የተሳናቸው አንዳንድ ኢትዮጵያውያን "ግዕዝ" እየተባለ የሚጠራው የኢትዮጵያ ፊደል "ከአርመን ፊደል የተቀዳ ነው" ይላሉ። ይህ ፍጹም ስህተት ነው። እውነታው የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። ከክርስቶስ ልደት እስከ 5ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ድረስ አርመኖች የራሳቸው ፊደል

አልነበራቸውም። አሽዲያዎን የተባለች ሜሪካዊ ተመራማሪ እንደምትነግረን፣ ቅዱስ መስሮብ ማሽቶትስ የተባለ አርመናዊ መነኩሴ "ለአርሜኒያ አዲስ ፊደል በመቅረጽ ሥራ ላይ ተጠምዶ ነበር።...ቅዱስ መስሮብ ኢየሩሳሌምን ስመሳለም በተጓዘበት ወቅት ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን እንዳገኘ እና ከእምነት መጽሐፎቻቸው አንዱን ይዞ እንደተመለሰ ብዙዎች ይናገራሉ። በግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ አየተመራ የተወሰኑ ሆሄያትን ከግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ ወስዶ የጀመረውን የፊደል ቀረፃ ሥራ እንዳሟላ መገመት የማያስኬድ አይሆንም።" (አሽዲያዎን "ስለ አርመን እና ኢትዮጵያ ጽሑፎች" ሰኔ 24፣2011)። አሽዲያዎን ሙሉ በሙሉ ትክክል ነች። የግዕዝ ፊደላት ከ2500 ዓመት በፊት ከኢትዮጵ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያውያን እጅ ነበሩ። ስለዚህ ለኢትዮጵያ እብሮ በቀል ናቸው። አርመኖች የራሳቸውን ፊደል ሲቀርጹ ከኢትዮጵያ ፊደል ኮርጀዋል። አርመኖች ፊደሎቻቸውን ያሟሉት ከኢትዮጵያ ወስደው ነው። ስነሱ ድምፀ-ልሳናት እንዲስማሙ ፊደላቱን ስለሰዋወጧቸው ከኛ ፊደላት ጋር ቁርጥ አንድ ዓይነት አይደሉም። እኛ ከአርመን የኮረጅን ቢሆን እንኳ እሮምኛነ ጨምሮ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች መጻፊያነት ከላቲን ፊደል ይልቅ የኛ ፊደል ይበልጥ የተሻለና የተመቸ ነው። በዚህ ተጨባጭ ምክንያት ብቻ እንኳ የላቲኑን ትተን በራሳችን ፊደል ልንጽፍ ይገባል።

በመጨረሻ በኢትዮጵያ የንግሥት ሕንደኬ ንብረት ሃላፊ የነበረውን ሰው ሃዋርያው ፊሊጶስ በሰረገላው ላይ ተቀምጦ ከብሉይ ኪዳን ላይ ስለእየሱስ የተነገረውን የኢሳይያስን ትንቢት ሲያነብ እንዳገኘውና ስለ እየሱስ ክርስቶስ መስክሮለት ስላመነ በውሃ እንዳጠመቀው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፏል። ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ኢትዮጵዊ መኮንን የአይሁድ እምነት እንደሚከተልና ያነብ የነበረውም ካገሩ ይዞት የሄደውን በራሱ ልሳን በግዕዝ ቋንቋ እና ፊደል የተጻፈ መጽሐፍ እንደነበር ግልጽ ነው። ያ የሆነው እየሱስ ክርስቶስ እንዳረገ ከዛሬ 2000 ዓመት በፊት ሲሆን አርመናዊያን ለቋንቋቸው ፊደል የቀረጹት ግን ከ400 ዓመት ወዲህ ነው። ከዚያ በፊት ፊደል አልነበራቸውም። ኢትዮጵያውያን ግን ከ2000 ዓመት በፊት መጽሐፍ ያነቡ እንደነበር ነቢዩ ፊሊጶስ ባስመዘገበው መሰረት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተረጋግጧል። ታዲ ማን ከማን ኮረጀ ቢባል ነው ሊያስኬድ የሚችለው?





አርሜንያ ከኢትየዮጵያ ጋር ስትነፃፀር ትንሽ አገር ናት። ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ናት። ከአራት ሚሊዮን ዓመት በላይ እድሜ ያለው የሰው አጽም የተገኘው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ገነትን ያጠጡ ከነበሩት አራት ወንዞች ሁለቱ ማለትም ግዮን እና ዋቢ ሸበሌ በኢትዮጵያ ውስጥ መገኘታቸው ቢያንስ ከፊል ገነት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደነበረች ያረጋግጣል። አክሱም ከተማ በንጉሠ-ነገሥት እከስ-ማይ የተመሰረተችው ከክርስቶች ልደት 900 ዓመት በፊት ሲሆን የአርመን ዋና ከተማ የሪቫን በንጉሥ አርጊሽቲ የተመሰረተችው ግን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ782 ዓመተ-ዓለም ነው። ይህ ማለት አክሱም በዕድሜ ከየሪቫን በ112 ዓመት ትበልጣለች ማለት ነው። በጃችን የሚገኙ የጽሑፍ ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት የሪቫን ከመቆርቆርዋ ከ100 ዓመት በፊት በፍትሃዊነቱ "የዓለም አባት" ይባል የነበረው ንጉሠ-ነገሥት አክሱማይ በአፍሪቃ፣ በአረቢያ እና በእስያ እሕጉራት በሥሩ ይተዳደሩ ለነበሩ ለ100 ነገሥታት ሕግ አውጥቶ በጽሁፍ ልኮላቸዋል። ሕጉም በጣኦታት ማምለካቸውን ትተው ባንድ ፈጣሪ አምላክ በእግዚአብሔር እንዲያምኑ የሚያሳስብ ነበር። ከዚህ 1400 ዓመት ቀደም ብሎ ኢትዮጵያን ያለ ዘውድ ማስተዳደሩ የተመዘገበለት "ዝዮን" የተባለው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ "ሁሉም ሰው ማንበብና መጻፍ መማር አለበት፣" ሲል አዋጅ አስነግሮ ነበር። በኋላም በግዛቱ ውስጥ የሚሰራጭ የዜና መጽሔት/ ጦማር/ ነበረው። ያ ጦማርም በዓለም ላይ የመጀመሪያው ጋዜጣ ነው።

ይህ የሆነው ከዛሬ 5350 ዓመት በፊት ነው። ይህም የአርመን ዋና ከተማ የሪቫን ከመመስረትዋ ከ2468 ዓመት በፊት ማለት ነው። ስለዚህ እንዴት ኢትዮጵያ ፊደል ከአርመን ተዋሰች ይባላል? ኢትዮጵያ ከአርመን በፊት ፊደል እንደነበራት ቢካድ እንኳ የኦሮሞና የአማራ ሊቃውንትን ጨምሮ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ይጽፉበት የነበረው ቀደም ሲል በተጨባጭ ያቀረብኩት የሱባ ቋንቋ እና ፊደል እንዴት ይካዳል?

ምንም እንኳ የሱባ ሆሄያት ቅርፅ የሳባዊ/ግዕዙን ባይመስልም ሳባዊ/ግዕዙ በጊዜ ሂደት የተከሰተውን ለውጥ ስመመጠን እንደ ሱባው አስር ሳይሆን ሰባት አናባቢዎች ከመጠቀሙ በስተቀር ድምጾቹ አንድ

ከኃይሌ ፊዳ በተቃራኒ፣ አርቆ አሳቢና ሃገሩን ይወድ የነበረው ኦናሲሞስ ነሲብ የኦሮሞ ሚሲዮናዊና መምህር በአውሮጳ ተምሮ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን በግእዝ ፊደል ወደ ኦሮምኛ የተረጎመ እንዲሁም አስቴር ጋኖ ከተባለች አንዲት የኦሮሞ ሴት ጋር ሆኖ የኦሮምኛ መዝገበ-ቃላትን የጻፈና መዝሙራትንና ምሳሌያዊ አባባሎችን የሰበሰበ ሊቅ ነበር። ፓስተር ኦናሲሞስ ነሲብ የተረጎመውን መጽሐፍ ቅዱስ “መጽሐፈ ቁልቁሉ” ብሎታል። ያ ጠሊቅ ምሑር ኦናሲሞስ ነሲብ የግዕዝ ፊደላትን ተጠቅሞ በ19ነኛው ክፍለ-ዘመን ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ በኦሮምኛ ከጻፈ እኛ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን እንደሱ የማናደርግበት ምክንያት ምንድነው? የተከበረው ፓስተር ኦናሲሞስ ነሲብ እና ጌፍቲ አስቴር ጋኖ የኢትዮጵያ ፊደላት ለኦሮምኛ ቋንቋ መጻፊያነት ከላቲኑ ይበልጥ የተመቹና ተስማሚ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

የኦሮሞ ምሁራን ከኢትዮጵያውያን ፊደል ይልቅ የላቲን ፊደልን የመረጡባቸው ሁለት ምክንያቶች የግእዙ ፊደል ‹‹dh›› ለሚለው የኦሮምኛ ድምጽ መወከያ ምልክት የሌለው መሆኑና ሰባቱ የግእዝ አናባቢዎች አሥር አናባቢዎች ላሉት ለኦሮምኛ ቋንቋ የሚመጥኑ ባለመሆናቸው ነው ይባላል። የሚያስገርመው ነገር ቀደም ሲል እንዳልኩት የሱባ ፊደል ግን ‹‹dh›› የሚለውን የኦሮምኛ ድምጽ የሚወከልበት ፊደል ያለው መሆኑና ሥርዓተ-አናባቢዎቹም ቁጥራቸው አሥር መሆኑ ነው። ከላይ በተቀመጠው የሱባ ፊደል ላይ በ‹‹ዲ›› ተራ የቀረበውን ይመልከቱ እስቲ፤ ‹‹dh›› ከአሥሩ አናባቢዎች አንፃር የሚነበብባቸው ፊደሎች አሉት። የጥንት ኦሮሞዎችና ጥንታውያን አባቶቻችን እንዲህ አሟልተው መጠቀማቸው የሚያስገርም ነው።

ስለ ኦናሲሞስ ነሲብ እና አስቴር ጋኖ እንደገና ለመናገር እነዚህ ሁለቱ ብቻ አይደሉም በግዕዝ ፊደል መጽሐፍት የጻፉ። ከአስቴር ጋኖ እና ከኦናሲሞስ በፊትም ኦሮምኛ በግዕዝ ፊደል ስመጻፉ የተመዘገበ መረጃ አለ። ቋንቋው ኦሮምኛ ሆኖ በግዕዝ ፊደል የተጻፈውን አንድ ጥቅል ቀጥሎ ይመልከቱ። የጥቅሉን እድሜ በትክክል ልነግርዎ አልችልም፤ እንደሚያዩት ግን እድሜ- ጠገብ





ይመስላል። ቢያንስ አንድ ሺ ዓመት እገምተዋለሁ። በአንድ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ነው የተገኘው።



መስላል። ቢያንስ አንድ ሺ ዓመት እገምተዋለሁ። በአንድ ጥንታዊ ኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ነው የተገኘው።





ጥንታውያን ኦሮሞ ምሁራን በግዕዝ ፊደል መጻፍ ከቻሉ ልጆቻቸውም ፍላጎቱ ቢኖረን ኖሮ እንዲሁ መጻፍ እንችል ነበር። ቁቤን ያስጀመሩ ምሁራን ያንን ርምጃ የወሰዱት የኢትዮጵያ(ሳባዊ ፊደላት የአማራና የትግሬ ብቻ ስለመሰላቸው በአማራ፣ በአማርኛ እና በግእዝም ላይ በነበራቸው ጥላቻና ቁጣ ተገፋፍተው ነው። ነገር ግን ግለሰቦቹ በዚህ ነጥብ ላይ ፍጹም ተሳስተዋል። ከሁሉ አስቀድሞ የኢትዮጵያ/ሳባዊ ፊደላት ባለቤቶች ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው

አገው ቋንቋ ሆኗል። የሚያስገርመው ይህ ቋንቋ በሰቆጣ እና በላስታ ከሚኖሩ አገው ህዝቦች ቋንቋ ጋር የማይመሳሰል መሆኑ ነው። አገው የከፍለ-ጦር ስያሜ ከሆነ በነዚህ አካባቢዎች /በሰቆጣ እና በላስታ/ አገው የሚሠኝ ማህበረ-ሰብ እንዴት ሲኖር እንደቻለም ይገርመኛል። በመሆኑም ክፍለ-ጦሩ ከላስታ እና ከሰቆጣ ስለመጣ ያንድ ጎሣ ስም ወርሶ ይሆናል አገው የተባለው ብዬም አገምታለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ "አገው ሲለደድ፣ አማራ ሲለምድ" የሚለው የግጥም እንጉ እንደሚያረጋግጠው አማራ በነዚህ ቦታዎች ከመስፈሩ በፊት አገው ተብሎ የሚጠራ ጎሳ መኖር አለበት። ከአማሮች በፊት አገዎች የአካባቢው ኗሪ ካልሆኑ ግጥሙ እንዴት አገው ተሰደደ፣ አማራ ለመደ ሲል ይችላል? አማሮችን ወደነዚህ አካባቢዎች ያመጣቸው እና ለቋንቋቸው መስፋፋትም ትልቅ ሚና የተጫወተው አጼ ላሊበላ መሆኑን በደንብ እናውቃለን። በመሆኑም ነባሮቹ አገዎች መገፋታቸው ተሰምቷቸው እድላቸውን ለመሞከር ወደ ሌላ ቦታ ተሰደው ሊሆን ይችላል። የብሌን ቋንቋ ከሆነው ከጎጃም አገውኛ የተለየ የራሳቸው የሆነ ቋንቋ እንደነበራቸው እገምታለሁ። ለዚህ ነው የጎጃም አገው ተወላጅ የሆነው ጓደኛዬ ከሰቆጣ አገው ጋር በቋንቋው መግባባት የተሳነው።

ቀደም ሲል እንዳነሳሁት ይኩኖ-እምላክ የዛጉዬ ሥርወ-መንግሥትን ለማስወገድ በአማሮች ተጠቅሟል። ለሰሞናዊው ሥርዎ-መንግሥት እንደገና ሊመሰረት የቻለው በዋንኛነት በአማሮች ድጋፍ ነው ሲሉ አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ ጽፈዋል።(50) የአማራ ወታደሮች የሰሰሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት እንደገና በማስመለስ ረገድ ቁልፍ ሚና ለመጫወታቸው ሌሎች ምንጮችም አሉ። መደባይ-ኦሮሞ እና ሌሎች ነገዶችም በዚህ ጉዳይ ውስጥ እጃቸው እንዳለበት በጽሁፍ ተመዝግቧል። (51) ለዚህ ማረጋገጫው ደግሞ ለሰሞናዊው ሥርወ-መንግሥት እንደተመለሰ አማርኛ መንግሥታዊ የመግባቢያ ቋንቋ እንዲሆን መደረጉ እና ተጉለት፣ ሸዋም የመንግሥቱ መቀመጫ መሆንዋ ነው። ከግዕዝ ይልቅ በአማርኛ ውስጥ የወታደራዊ ማዕረግ ስሞች እና ደረጃዎች ሰፋ ባለ መልኩ መገኘታቸውም ሌላው ማስረጃ ነው። ለምሳሌ በንጉሠ-ነገሥት ይኩኖ-እምላክ ዘመነ-ግዛት የሚከተሉት የአማርኛ የማዕረግ ስሞች ገናና ነበሩ።

| ግዕዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ሃሢኒ | አቤቶ፣ቢትወደድ |
| ኡቱ | እቴጌ |
| ጃንደረባ፣ ሄጌኖ | ኡቴጌ |
| ቀስ፣ አዬ | እጬጌ |
| እራቅ-ማስሬ | ርዕሰ-መኳንንት |
| ቀለብሳ | አዛዥ፣ አጋፋሪ |
| ደልካሚ | ደጀን፣ አዝማች |
| ዲልግሀን | ራስ |
| ደረስጌ+ ሰርግዋይ | አማካሪ |
| ብሀት | ቢትወደድ |
| ሰራዌ | ክብርዘብ |
| ሃሀፊ ላህም | ፀሀፊ ትዕዛዝ |
| ጌዋ+ጨዋ(ሸዋ) | የንጉሥ ሰራዊት |
| መስፍን | ፊትአውራሪ |
| መኮንን | አዝማች |
| ብላቴን | የንጉሥ ልጅ አማካሪ |
| ሊጋባ | ባለሟል |
| አቃቤሰዐት | ህግ አስከባሪ |
| የማነሃራሁ | ቀኛአዝማች |

ላይ አብረው በርካታ ጦርነቶችን በጀግንነት ተዋግተዋል፡፡ እስካሁን እንዳደረጉት ያለፈውን መከፋፈላቸውንና መጋጨታቸውን ረስተው በጋራ በሚያስተሳስሯቸው እሴቶች ላይ በማተኮር ወደፊት በስምምነት፣ በእኩልነት፣ በመከባበር፣ በኩራት እና ክፍ ባለ አስተሳሰብ አብረው ለመኖር መቻል አለባቸው፡፡ በስላምና ብልጽግና ጎዳና ለመጓዝ ያለፈውን ቅሬታ መቆፈር ሳይሆን በመጪው ብሩህ ተስፋ ላይ ማተኮር ነው የሚያስፈልገው፡፡

ባመዛኙ በማርክሳውያንና በዳርዊናውያን ተጽዕኖ ምክንያት እኔና የኔ ትውልድ በእግዚአብሔር መኖር አናምን ይሆናል፡፡ እንደዚህ ብናስብም መብታችን ነው፡፡ ሆኖም በእግዚእብሔር መኖር የሚያምኑትንና ህይወታቸውም በፈጣሪያቸው ዙሪያ የተሽከረከረውን የአባቶቻችንን እውነታ ቅንጣት ታህል አይለውጠውም፡፡ የሳባ ንግሥት ራስዋን ንግሥተ-ነገሥታት ብላ ከመጥራቷ በፊት ሁሉም የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥቶች ባንድ ጊዜ ንጉሦችም ሊቀ-ካህናትም ነበሩ፡፡ በዚህም ምክንያት ፈሪሃ-እግዚእብሔር በየልቦናቸው ያደረ፣ ባመራራቸውና በፍትህ አሰጣጣቸው ህቀኞች፣ ፍርድ አስተካካይዎች እና ቸሮች ሆነው ያለፉ ነበሩ፡፡ ታሪካቸው ይህንን ሀቅ ያረጋግጣል፡፡ ለኛ እምነት እንዲገጥም ብለን ይህንን እውነታ ልንቀይረው አንችልም፡፡ እንቀይር ብንልም እርባናቢስነት ነው፡፡ የዚያ እውነታ ውጤቶች በመሆናችን በዛሬው እኛነታችን ላይ የሚያሳርፈውን ተጽእኖውን ልናስቀይረው የማንችለው ያለፈ ታሪካችንን ትምህርት አድርገን ልንቀበለው ይገባል፡፡ በነዚህ ዓመታት ሁሉ ስለ ታሪካችን እውነታውን ተነፍገን በጨለማ ውስጥ ኖረናል፡፡ ይህ ጨለማም በላያችን ላይ ሊስላ የማይችል ጉዳት፣ ጥፋት፣ ውድመት፣ ስቃይ፣ መከራ እና ቁጣ አድርሶብናል፡፡ ሀቁን ማወቂያና ነፃ መውጫ ጊዜ አሁን ነው፡፡ እኔ በበኩሌ የአባቶቻችንን እና የናቶቻችንን ሽጋውን ውርስና ቅርስ አፈቅራለሁ፣ አከብራለሁ፣ እንክባከባለሁ፡፡ ራሴንም የዚያ ውርስና ቅርስ አንድ አካል አድርጌ እቆጥራለሁ፡፡ ያባቶቼንና የናቶቼን ታሪክ የዛሬውን ማንነቴን ይበልጥ እንዳውቅና እንዳደንቅ ያደርገኛል፡፡ ያለፈው ያባቶቼና የናቶቼ ክብርና ዝና ወኔዬን እንዳድስና በወቅታዊ ችግሮቼ ሳቢያ በንቀት በምትመለከተኝ በዚች ዓለም ውስጥ ለራሴ ያለኝን ክብር ከፍ አድርጌ እንዳይ ያደርገኛል፡፡

በምዕራብ አገራት ለበርካታ ዓመታት የኖረ አንድ ኦሮሞ ጓደኛዬ ‹‹ኢትዮጵያ›› የሚለው ስም አይመቸውም። ኢትዮጵያ በነበረበት ወቅት ባዳበረው ዘረኝነት ወይም ስላሰፈው የኦሮሞ ታሪክ በለማው ወይም ባነበበው በጥላቻ የተሞላ መራራ አፈ-ታሪክ የተነሳ በግሉ በኢትዮጵያ ላይ፣ በሰንደቅ ዓላማዋና ከኢትዮጵያ ጋር በተያያዘ በማናቸውም ነገር ላይ ጥላቻና ንቀት አድሮበታል። እየቆየም በጣም ስሜታዊ እየሆነ መጥቷል። ይህ ከቁጥጥር የወጣ የስሜት ግንፈላውና ምሬቱም ኢትጵያዊነቱን እስከሚጠላና እስከሚክድ ድረስ የማገናዘብ ችሎታውን አጥፍቶበታል። ምንም እንኳ አያት-ቅድመ አያቶቹ ለኢትዮጵያ ስልጣኔና ነጻነት ብዙ ያበረከቱ ኩሩ እና የተከበሩ ኦሮሞዎች ቢሆኑም ቅሉ እሱ ግን ኢትዮጵያዊነቱን የጠላና የካደ ሰው ሆኗል። ይህ መቸም አሳዛኝ ድምዳሜ ነው። በጤናማ አእምሮው በሚሆንበት ጊዜ ግን ኢትዮጵያዊ መሰረቱን ይቀበል ይሆናል። ይለማው የነበረው ማንኛውም ኢፍትሃዊ የሆነ ስሜት ሁሉ ዝርያዎቹ በሆኑ በኦሮሞዎች ነገሥታት እና ንግሥተነገሥታት በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ ሁሉ በግድ የተጫነባቸው መሆኑን ሲረዳ ለዛሬዋና ለነገዋ ኢትዮጵያ የተሻለውን መንገድ ለመጥረግ ጥረት ማድረጉ አይቀርም።

የኔን ጉዳይ እንደ አብነት እንውሰድ፤ በሺዎች የሚቆጠሩ አማሮች በቤንች ማጂ እና በቤንሻንጉል ዞኖች ከመሬታቸውና ከመኖሪያቸው ያለ አግባብ ሲፈናቀሉ፤ መሬታቸው፣ ንብረታቸው እና ገንዘባቸው (ይህ ርዕስ በሚጻፍበት ወቅት በፌደራሉ መንግሥት ታስረው በመመርመር ላይ ባሉ) በአካባቢው ባለስልጣኖች ሲወረስባቸው በጣም አዝኜ ነበር። ደርግ ሥልጣን ከያዘበት ከዛሬ 40 ዓመት ጀምሮ አማሮች ስለተገለሉ እና ሥልጣን አልባ ስለሆኑ ለማንም ስጋት አለመሆናቸውን እውቃለሁ። ይህንን ኢ-ፍትሓዊነት በመቃወም አንድ ግጥም ጻፍሁ። ለተበደሉ አማሮች መቆርቆሬን ያልወደደ አንድ ሰው ኦሮሞነቱን አስታውሶ ሙልጭ አድርጎ በኢ-ሜይል ሰደበኝ። በጋጠወጥነትም እንዲህ አለ፦ ‹‹ከተማረ ጋላ መሀይም ጉራጌ ይሻላል›› ይህን የጻፈው ትክክለኛ ስሙን ደብቆ ነው። እንዲህ ስል በጥሞና ጻፍኩለት፦ ‹‹እባክህ መሀይም ጉራጌ ከተማረ ጋላ መብለጡን በማስረጃ አረጋግጥና አሳምነኝ፤ ይህን ማድረግ ካልቻልክ ከሰብአዊነት ደረጃ ዝቅ ያልክ ተራ እንስሳ ነህ። ንግግርህ ኦሮሞዎችን ብቻ ሳይሆን ብልሆቹን ወንዞቻችንን ጉራጌዎችንም ያዋርዳል።

የኢትዮጵ፣ እንዲሁም ሙት ታስነሳ የነበረችውና የደሸት ወላጅ እናት የሆነችው የታላቅዋ ነቢይት የሸምሸል እና የነቢዩና የጠቢቡ የደሸት የራሱ ተወላጆች ናችሁ። እንዲሁም የኦሮሞ እና የአማራ ምንጭ የሆነው የታላቁ ፈላስፋ እና ነቢይ የደሸት ልጆች ናችሁ። ምንጫችንን ይበልጥ ራቅ ስናደርገው ደግሞ አይሁዶች ገና ወደ አካባቢው ከመምጣታቸው በፊት የኢየሩሳሌም ገንቢ እና ንጉሥ የነበረው ከሃሊውን ግዚአብሄርን በምድር ላይ የወከለው፥ የካህናቶች ካህናት፥ የንጉሦች ንጉሥ የመልከፃዲቅ ዝርያ ነን። ለዚህ ለትልቁ አባታችን የአይሁዶች አባት የሆነው አብርሃም ታላቅነቱን አክብሮ ይሰግድለት እና ምርቃቱን ለማግኘት አሥራት ያገባለት ነበር። ይህንንም አባታችንን፥ እንዲሁም ኢትዮጵን እና ደሸትን፥ አማሮችና ሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ዘመዶቻችን ከኛ ጋራ ይጋሩአቸዋል።

ኢትዮጵያን ለምን በጣም እንደማፈቅራት እና ኢትዮጵያዊነቴንም ለምን እንደምወድ አንዳንድ ኦሮሞ ወዳጆቼ ይገርማቸዋል። ኢትዮጵያን አፈቅራታለሁ፤ ምክንያቱም የኦሮሞ እና የሁሉም ኢትዮጵያውያን መገኛ የሆነውን የታላቁን አባታችንን የኢትዮጵን ስም ይዛለች። ኢትዮጵያዊነቴንም እወደዋለሁ፤ ምክንያቱም አያት ቅድመ-አያቶቼ በዓለም መድረክ ላይ የተጫወቱት ሚና ያኮራኛል። አያት ቅድመ-አያቶቼ ልዩ የሆነውን ቅርሳቸውን የተውልን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር አዘልለው መሆኑን አውቃለሁ። ስለዚህ ራሴን "ኦሮምያ" በምትባል ጠባብ ቦታ ላይ ብቻ መወሰን አልፈልግም። ምክንያቱም ጠቅላላዋ ኢትዮጵያ በመላው ቁመትዋ እና ስፋትዋ የኔ፣ የኦሮሞ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ እንዲሁም የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ናት። እሰዋንም ለማትረፍ እና ለኛ ለማስተሳለፍ ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰዋልና። በሕዝቦቿ ቅርፀ-መልክ፣ በቋንቋዎቿ ብርቅነት፣ በሙዚቃዋ ጥልቀት፣ በጭፈራዋ አማላይነት፣ በስነ-ቃልዋ፣ በታሪኳ፣ በፍልስፍናዋ እና በስነ-ጽሑፍዋ እማረካለሁ። በቤተክርስቲያን ስነ-ሥርዓትዋ እና በሃይማኖትዋ፣ በዜጎቿ መልካም ጠባይ፣ በጨዋነታቸው፣ ለሕይወት ባላቸው አመለካከት እና በእእምሮኣቸው ረቂቅነት እና ጥልቀት እሳባለሁ። በክብራቸው አስፈሪነት፣ በንግግራቸው ተራቃቂነት፣ በጥበባቸው ውስብስብነት፣ ከችግራቸው ባሻገር በአለው ኩራታቸው ጥልቀት እና ተወዳዳሪ በማይገኝለት ገርነታቸው እና በተቅለመለመው ብዙሐንነታቸው እሸነፋለሁ። የኦሮሞዎችን እና የአማሮችን ጨምሮ ይህን እና ይህን

መሳዩ የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን ባህርይ እና ማንነት ለኢትዮጵያ እና ለልጆቿ ስሜታዊ እንድሆን ያስገድዱኛል።

ስለዚህ እኔ ፍቅሬ ቶሎሳ (ቶለሳ) ጂግሳ፣ የሳሌም ንጉሥ እና የእግዚአብሔር ከፍተኛ ካህን የነበረው የመልከጼዴቅ ልጅ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት እና የዐለማቱ ፈጣሪ ከፍተኛ ካህን የነበረው የኢትዮጵ ልጅ፣ እንዲሁም ነቢይ እና ፈላስፋ የነበረው የጎጃም ንጉሥ የደሸት ልጅ ነኝ። አዎ! ኦሮሞዎችን፣ አማሮችን፣ ሃድያዎችን፣ ከምባታዎችን፣ ሶማሊዎችን አፋሮችን፣ ጉራጌዎችን እና ሌሎቹንም ኢትዮጵያውን ጨምሮ እንደ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ እኔም የነዚህ ሁሉ ልጅ ነኝ።

የኢትዮጵ ልጆች መሆን እና በዚህም ኢትዮጵያዊ መሆን የሚታፈርበት ሳይሆን የሚኮራበት ነው። የመልከጼዴቅ እና የኢትዮጵ ተወላጅ መሆን የሚያስገርም እና በእጅጉ የሚያኮራ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው እየሱስ ክርስቶስ ወደፊት በኢየሩሳሌም በሚገዛበት ወቅት በመልከጼዴቅ ሥርዓት መሰረት ነው የሚገዛው። (53) በርግጥ የሚታየውን እና የማይታዩትን ዐለማት የፈጠረ እየሱስ ክርስቶስ የሙሴ ወንድም እና የአይሁድ ከፍተኛ ካህን በነበረው በአሮን ስርዐት አይደለም የሚገዛው። የአሮን ካህንነት ከመልከጼዴቅ እና ከኢትዮጵ እጅግ ዝቅ ያለ ነው። እንዲሁም የንግሥተ-ሳባ እና የንጉሥ ሰለሞን ልጅ እስከ ሆነውና ከእናቱ ሃይማኖትና ባሕል ይልቅ የአባቱ ሃይማኖትና ባሕል በልጦበት ሊቀ-ካህናትነትን በአይሁድነት እለከለወጠው እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ድረስ ለአንድ ሺ አመታት ባንድ ጊዜ የነገሥታት ንጉሦች እና የካህናት አለቆች ከነበሩት ስፍር ቁጥር ከሌላቸው ከኢትዮጵ ወራሾች ካህንነት በጣም ያነስ ነው።

ልድገመውና የመልከጼዴቅ፣ የኢትዮጵ እና የተከታዮቹ ንጉሠ-ነገሥትነት እና ሊቀ-ካህናትነት ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ልንኮራበት የሚገባን ትልቅ ነገር ነው።

የኢትዮጵ ልጆች በመሆናችንም ልንኮራ ይገባናል፤ ምክንያቱም ከ4000 ዓመት በፊት የኢትዮጵያን ግዛት መሰርቶልናል፤ መጻህፍትም ጽፏል፤ ስለ መንግሥት መዋቅር እና ስለ ህገ-መንግሥት ተከታዮቹን አስተምሯል፤ ፊደላችንን አሻሽሏል።(54) ባለፉት ጊዜያት መላው

አፍሪቃ ኢትዮጵያ እየተባለ እንዲጠራ ምክንያት ሆኗል፤ እንዲሁም ታላቅነቱንና ምርቃቱን ለልጆቹ አስተላልፎ ነገሥታት፤ ከፍተኛ ካህናት፣ ነቢያት፣ ፈርኦኖች እና ህንደኬዎች እየሆኑ ኢትዮጵያን፣ እስያን፣ አረቢያን፣ ኒጀርን፣ ናይጀሪያን፣ ግብፅን፣ ኑቢያን፣ ሱዳንን፣ ታንዛኒያን፣ ሞሪታኒያን እና ሊቢያን በጽድቅና በፍትህ አስተዳድረዋል። የኢትዮጵያን ሥልጣኔንም አስራጭተዋል። ከታላላቅ ንግሥታት መካከል ፋሲላ እኖኒ በሚል ስያሜ የምትጠራውና በአጼ ፈንታሌ ተሾማ 13ኛዋ ህንደኬ የነበረችው መደባይዋ ኦሮሞ ትጠቀሳለች።(55)

ቀደም ሲል እንደዘረዘርኩት ከ2000 አመታት በኋላ አጼ ባዚን ንጉሠ-ነገሥት በነበረበት ወቅት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “የምሥራቅ ጠቢባን” የተባሉት 12ቱ የኢትዮጵ ዝርያዎች አሥራ ሁለት ነገሥታት እና ጠቢባን ሆነዋል። እጆቻቸውን ለእግዚአብሔር ዘርግተውም “ዮጵ” በመባል የሚታወቀውን ልዩዉን የኢትዮጵያን ቢጫ ወርቅ፤ ከርቤ እና እጣን ሥጦታ አበርክተዋል። የእየሱስ የሥጋ ዘመዶች የሆኑት አይሁዳዉያን መወለዱን እንኳ ገና ሳይሰሙ ነው እንግዲህ በትንቢቱ መሰረት እነዚህ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ትንቢቱን የፈፀሙት። ትንቢቱም “ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች” የሚለው ነው(56)። እነዚህ አሥራ ሁለት “ወንድማማች ንጉሦች” ሁሉንም የኢትዮጵያን ሕዝቦች ይወክላሉ። ለምሳሌ ንጉሥ መጋል፣ ንጉሥ ሙርኖ፣ ንጉሥ መቃዲሺ እና ንጉሥ አጎጃ ጀባን እንደ ቅደም ተከተላቸው ኦሮሞን፣ አፋርን፣ ሶማሌን እና አማራን ይወክላሉ።

ከ3500 ዓመት በፊት ሌላው የኢትዮጵ ተወላጅ የሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምድያም ሊቀ ካህናት እና የሙሴ አማት፣ እኛ ኢትዮጵያውያን የትሮ-አብ ብለን የምንጠራው ትልቅ ሰው ነው። ሙሴን በእግዚአብሔር ሥርዓት ለ40 ዓመት ያሰለጠነው። ከዚህም በላይ፥ በአይሁዳውያን መካከል ይነሳ የነበረውን ፀብና ውዝግብ ሙሴ ለብቻው ለመዳኘት ሲደክምና አይሁዳውያኑም ሲጉላሉ ዐይቶ ሙሴ የፍትህ እና የፍርድ ሥርዓት እንዴት መዘርጋት እንደ አለበት የመከረው እሱው ነው። (56)

እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ነጻ ለማውጣት የተጠቀመበት እና ቃል በቃል በቀጥታ እያነጋገረው አሥርቱ

ትዕዛዛትን የሰጠው ብቸኛው ሰው ሙሴ በመሆኑ ሙሴ እንደ ታላቅ ሰው ይታይ ነበር። የኛ የኢትዮጵያውያን ጥንተ-እባት የትሮአብ ግን ከሙሴ እጅግ የሚልቅ ታላቅ ሰው ነበር። ምክንያቱም ቃለ-እግዚአብሄርን፣ መንገደ መለኮትን እና የፍትህ ሥርዓት አዘረጋግን ለሙሴ ያስተማረ የታላቁ እግዚአብሔር ሊቀ ካህን ነበርና። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተገለጸው ሙሴ ለየትሮአብ ባክብሮት ቢያጎነብስለት እያስገርምም። የትሮአብ የመልከፀዴቅ እና የኢትዮጵ ዝርያ ስለነበረ እሥራኤላውን ከባርነት ነፃ ከወጡ ከ3 ዓመታት በሑዋላ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሆነ። አይሁዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሃባብ ብለው የሚጠሩት የየትሮአብ ልጅ አባ-ብሄር በታላቁ ካህን ልጅነቱ ቃለ-እግዚአብሄርን በደንብ ያውቅ ስለነበር በጉዞአቸው ላይ ህዝቡን በማስተማር ረገድ ሙሴን ለብዙ አመታት ረድቶታል። (57)

የጥንተ-አባታችን የኢትዮጵ ዝርያ ከሆኑ ታላላቅ እንስቶች መካከል፤ የንጉሥ ሰለሞንን ጥበበ-እውቀት ሽታ ከኢትዮጵያ ኢየሩሳሌም ድረስ በመጓዝዋ እየሱስ ያሞገሳት ኤትያኤል (ንግሥተ-ሳባ) (58)፣ በዘራቸው ኢትዮጲያውያን የነበሩት የንጉሥ ዳዊት አያት ሩት እና ሐብሴ እያልን የምንጠራት ወላጅ እናቱ አደሲያ ይጠቀሳሉ። ሩት ዓለምን የሚያድነውን ኮከብ (የእየሱስን) መወለድ የተነበየው የነቢዩ በልአም የልጅ ልጅ ስትሆን እርሷ ራሷም ስለ ኮከቡ መወለድ ራዕይ ዐይታ ስለ ነበር ያየችውን ራዕይ ለማሰብ የኮከቡን ቅርፅ ስርታ በልጅዋ በአቤድ አንገት ላይ አስራላት ነበር። ውሎ አድሮ ንጉሥ ዳዊት ያንን የኮከብ የእጅ-ሥራ ከእናቱ ወረሰ። ዛሬ ድረስ የአይሁድ ሕዝቦች እና መላው ዓለም ያንን የኮከብ ቅርፅ "የዳዊት ኮከብ" እያሉ ይጠሩታል። ስለ ኮከቡ ሠራተኛ ስለ ሩት ግን ምንም አይነሳም። እየሱስ ክርስቶስ "የዳዊት ልጅ" እየተባለ ስለሚጠራ እና እናቱ የኛዋ ኢትጵያዊትዋ አደሲያ (ሐብሴ) በመሆንዋ(59) በእየሱስ ክርስቶስ ደም ውስጥ ኢትዮጵያዊ ደም ስላለ እየሱስ ክርስቶስ የስጋ ዘመዳችን ነው ብንል ያስኬዳል። ታዲያ ይህ ሁሉ በኢትጵያውነታችን የሚያኮራን አይደለምን?

የስንደቅ ዓላማን ጉዳይ በተመለከተ ከኦሮሞ የነፃነት ተዋጊዎች ጋር የተያያዘ ስንደቅ ዓላማ አለ። አራት ወይም ሶስት የተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎች ነበሯቸው። በቀይ እና በአረንጓዴ ቀለማት ያጌጠውንና ማሕሉ ላይ ዋርካ ዛፍ ያለበትን እመርጠዋለሁ። ምክንያቱም የኦሮሞ

አዛውንት አካባቢያቸውን እና ሕይወታቸውን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለመምከር ሲሰበሰቡ ከሚጠለሉባቸው ዛፎች አንዱ የተወከለበት ስለሆነ ነው። ባለፈው ጊዜ ስለነበረው የኦሮሞ ዴሞክራሲ ብዙ የሚናገረው አለ። አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለማት ያሏትን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማም እወዳታለሁ። እስዋንም የምወድበት በቂ ምክንያት አለኝ፤ ከ3400 ዓመት በፊት የፈጠራት የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የአፋር፣ የሶማሊ፣ የሀዲያ እና የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት የሆነውና በንግሥና ስሙ "ሰንደቅ አልማ" ይባል የነበረው እጼ ወይም እሴ በመሆኑ ነው።(60) ሰንደቅ-ዐላማ የተባለችው ለዚህ ነው። እሴ የኢትዮጵ ዝርያ ሲሆን እኔ እስከማውቀው ድረስ ፍፁም አቻ የሌለው እጅግ ታላቅ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ነበር። በመልከጼዴቅ እና በኢትዮጵ ስርዐት መሰረት መንፈሳዊውንና ዓለማዊውን ሥልጣናት አጣምሮ የያዘ ሊቀ-ካህናት እና ንጉሠ-ነገሥት ነበር። እንደ አባቶቹ እሱም ሁለት ታላላቅ ሥልጣኖች ነበሩት ማለት ነው፡- መንፈሳዊ እና ፖለቲካዊ። ከፍ ያለ ዝናን ያተረፈ፣ እንደ ጥንታዊያን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የረጂም ዕድሜ ባለፀጋነትን ምስጢር ተረድቶ 480 ዓመት የኖረ፣ ሩቅ ምሥራቅን አስገብሮ በክህነት ስሙ "እስያ" ብሎ ሰይሞ(61) እስከ ዛሬ አህጉሩ "እስያ" እየተባለ የሚጠራለት እጅግ ታላቅ ንጉሠ-ነገሥት ነበር።

እሴ ልዩ ችሎታ የነበረው ሳይንቲስትም ነበር። አዝዕርትንና እፅዋትን እንዲሁም እንስሳትን እያዳቀለና አዳዲስ እፅዋትንና የእንስሳት ዝርያዎችን እያስገኘ በቤተ-መንግሥቱ ያኖር የነበረ የመጀመሪያው በራሄ-ጂን/ዘረ-መል/ መሐንዲስ (Genetic Engineer) ነበር። በሰው በራሄ-ጅን DNA ላይም ምርምር ያደርግ ስለ ነበር ኢትዮጵያውያንን ከእስያውያን፣ እና ከመካከለኛው ምሥራቅ ምርኮኞቹ ጋር እያጋባ ዛሬ ያለን ልዩ የሆነው ቅይጥይጥ የቆዳ ቀለም፣ የፊት ቅርጽ፥ የተለያየ የጸጉር አሠራር እና ልዩ ልዩ የነገድ አካላዊ ቅርፀ-መልክ እንዲኖረን አስችሏል። የተለያዩ ቀለማት እንዳሉት ውብ አበባ በልዩነት እንድናምር ያደረገን እሱ ነው። የቋጥኞችን ተፈጥሮ የተረዳ ጂኦሎጂስት እና አንዳንድ እንስሳትን ከሌሎች ጋር እያዳቀለ አዳዲስ እንስሳት እንዲፈጠሩ ያደረገ ታላቅ ሳይንቲስትም ነበር። በፈልሳፊነቱም ገና በጥንቱ ዘመን የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዐላማ ፈጥሮ የመንግሥት ባለሥልጣናት በየሥራ ቦታዎቻቸውና በየ ሰረገላዎቻቸው ላይ

እንዲሁም ከሰራዊቶቻቸው ፊት እና ኋላ እንዲያውለበልቧት በሕግ ደንግጓል፡፡ ይህን ሲያደርግ ምናልባት በዐለም የመጀመሪያው መሪ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የሰንደቅ ዓላማው ቀለም አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ ነበር፡፡ በጥቁር አባይ መነሻ ላይ ሆኖ የሰንደቅ-ዐላማዋን መፈጠር ባወጀበት ዕለት ለዜጎቹ ንግግር ሲያደርግ እግዚአብሔር ምድርን ዳግመኛ በውሀ እንደማያጠፋት ለኖኅ ቃል እንደገባለት እና ለቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተ-ዳመናን እንዳቆመ፤ የቀስተ-ደመናው ቀለማትም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንደሚወክሉ አስታውሶ በተመሳሳይ መንገድ አጼም በነገሥታት እና በሕዝቦች፣ በሱ እና በተወዳጅ ዜጎቹ መካከል ያለውን ፍቅር ለማሰብ ሰንደቅ-ዐላማዋ ከፍ ብላ እንደምትውለበለብ ማድረጉን ገልጾ ነበር፡፡ በገለጸው መሰረት አረንጓዴ ምድራዊነትን፣ ቢጫ ፍቅራችንን፣ ሰማያዊ ደግሞ መንፈሳዊነታችንን ይወክላሉ፡፡ የመስቀያው አናት በወርቅ እና በብር የተሰበጠ የኮከብ ቅርፅ እንዲሆንና ሰንደቅ-ዐላማዋን ያላውለበለበ ማንኛውም ባለሥልጣን በጥብቅ እንዲቀጣ ደንግጎ ነበር፡፡(62)

እንግዲህ ሰንደቅ-ዐላማችን በአጼ አስያኤል ለመፈጠርዋና የ3300 ዓመት እድሜ ባለጸጋ ለመሆንዋ ማስረጃው አጼ በዚህ ዘመን መግዛቱ የተመዘገበ መሆኑ እና “ሰንደቅ-ዐልማ” ስመ-መንግሥቱ እንደነበረ መረጋገጡ እንዲሁም ሰንደቅ-ዐላማችን የዚያን ልዕለ-ሰብ መሪ ስም ይዛ እስከዛሬ “ሰንደቅ-ዐላማ” እየተባለች መጠራትዋ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ከውጪ ወራሪዎች ሲከላከሉ ያፈሰሱትን እና የሚያፈሱትን ደም ለመወከል ታስቦ ከጊዜ በኋላ ሰማያዊው በቀይ ተተክቷል፡፡ ከ700 ዓመታት በፊት ይኩኖ አምላክ (የኦሮሞው ዝርያ ንጉሠ-ነገሥት) እና ነአኩቶ ለአብ (የዛጉዌው ንጉሠ-ነገሥት) በአቡነ ተክለሃይማኖት ሽምጋይነት የዛጉዌን ሥርወ-መንግሥት ለሠለሞን ሥርወ-መንግሥት አባላት ለማስተላለፍ ሲስማሙ ይቺ ሰንደቅ-ዐላማ እንደገና ተጠቅሳለች፡፡ (63)

አዎ! በርካታ ኦሮሞዎች፣ አማሮች፣ አፋሮች፣ ሀዲያዎች፣ ትግሬዎች እና ሌሎችም ኢትዮጵያውን ይቺ ሰንደቅ-ዐላማ በነፃነት አየር ላይ በክብር እንድትውለበለብ ደማቸውን አፍሰስዋል፡፡ ከ24 ዓመት በፊት አንዱ ከእሷ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ግለሰብ ባርቆበት እንደነበረው ላባቶቻችን ይቺ ሰንደቅ-ዐላማ ተራ “ጨርቅ” አይደለችም፡፡ የሚገርመው ያ ግለሰብ ሞቶ ወደ መቃብር ሲወርድ

አስክሬኑ ይቺኑ የጠላትንና "ጨርቅ" ብሎ ያናናቃትን ሰንደቅ-ዐላማ ለብሶ መታየቱ ነው።

በቅርቡ ያገራችን ታሪክ በአድዋ፥ በማይጨውና በደፈጣ ውጊያ ጦርነቶች እንኳዋ ለዚች ሰንደቅ-ዐላማ ከተፋለሙ ኦሮሞዎች ጥቂቶቹን ለማስታወስ፣ የአጼ ምኒልክ ባለቤት ንግሥት ጣይቱ ብጡል፣ ፊታውራሪ ሃብተ-ጊዮርጊስ ዲነግዴ፣ ፊታውራሪ ባልቻ አባ-ነፍሶ፣ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ጄኔራል ጃጋማ ኬሎ፣ እና ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ፣ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፣ ኮሎኔል አብዲሳ አጋ፣ ራስ አበበ አረጋይ፣ ደጃዝማች ገብረ-ማሪያም ጋሪ እና ወይዘሮ ልክ የለሽ በያን የሚጠቀሱ ናቸው። የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዐላማ በነጻነት ዓየር ላይ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ በጀግንነት የተዋጉትንና ያልተዘመረላቸውን የኦሮሞ ጦረኞች በሙሉ እዚህ መዘርዘር ያስቸግራል።

አባቴ ቶሎሳ(ቶለሳ) ጂግሳ ዋኬኔ ሰላማዊ ዜጋ እንጂ ጦረኛ አልነበሩም። ዳሩ ግን የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዐላማ በኢትዮጵያ ዐየር ላይ ለማውለብለብ ከጣልያን መፋለም ነበረባቸው። በወለጋው ገዢ በቢትወደድ መኮንን ደምሴ ስር ሆነው በ1928 ዓ.ም በማይጨው ጦርነት ከፋሺስት ጣልያን ጋር ተዋግተዋል። የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዐላማ ለኢትዮጵያውያን የነጻነት ምልክት ነበረች፤ ነችም። በኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዐላማ ቀለማት የተሠራ ያንገት ልብስ አንገቴ ላይ ጣል አድርጌ ያየኝ አንድ ወጣት ኦሮሞ ባንድ ወቅት አንባረቀብኝ። ሰንደቅ-ዐላማዋ ከ3300 ዓመታት በፊት በራሱ ቅድመ አያት የተፈለሰፈች እና በርካታ አባቶቹ እና እናቶቹ ለህልውናዋ የተዋደቁላት መሆንዋን ቢያውቅ ኖሮ ይህን ያህል ጠላትዋ አይሆንም ነበር። በቅርቡም አረብ አገር በሠራተኛነት የምታገለግል አንዲት ኦሮሞ ሴት የኢትዮጵያን ባንዲራ በጥላቻ አቃጥላለች። ጥንተ-አባትዋ አጼ ወይም አሴ እና ለሰንደቅ-ዐላማዋ ሕልውና የተዋደቁ እነዚያ ሁሉ ታላላቅ ኦሮሞዎች ድርጊትዋን ቢያዩ ኖሮ በመቃብር ውስጥ አጽማቸው በህዘን በተገላበጠ ነበር።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዐላማ በሌሎች እልፍ አእላፍ ኢትዮጵያውን ግን እጅግ ትፈቀራለች። ለምሳሌ አርቆ አሳቢው የአፋሮች መሪ ክቡር ደጃዝማች ዓሊ ሚራህ ባንድ ወቅት "እኛ ቀርተን ግመሎቻችን እንኳዋ የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዐላማ ያውቋታል" ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያውያንን በሙሉ የሚወክል ብሔራዊ ምልክት መኖር ስላለበት ሁሉም ኢትዮጵውያን ይቺን ሰንደቅ-ዐላማ ከፍ አድርገው ማውለብለብ ይገባቸዋል። ይህ ሀቅ የተለያዩ ጎሳዎች ልዩ የሆነውን ቅርሳቸውን እና ባሕላቸውን የሚያንጸባርቅ የራሳቸው የጎሳ አርማ እንዳይኖራቸው የሚያግድ አይደለም። ለምሳሌ የኦሮሞ ነጻነት ተፋላሚዎች መካከሉ ላይ የዋርካ ዛፍ ያለበት አርማ አላቸው። ይህንን አርማ ካገራቸው ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዐላማ ጋር በየአካባቢያቸው ከፍ አድርገው ማውለብለብ ይችላሉ። ይሁንና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምልክት የሆነችው ሰንደቅ-ዐላማ ከሁሉም አካባቢያዊ አርማዎች ቀድማ መውጣት፣ ልቃ መታየት አለባት። ምክንያቱም የሁላችንም የሆነችዋን አንዲት አገር የምትወክል የአንድነት ተምሳሌት ናትና። አንድ ቡድን በሌሎች ጎሣዎች ላይ የራሱን አርማ ብቻ ልጫንባችሁ ቢል ኢ-ፍትሀዊነት እና ጭቆና ነው። አርማው በማይወክላቸው ጎሳዎች ላይ፣ ለምሳሌ ሠንደቅ-ዐላማችንን “ግመሎቻችን እንኳ ያውቋታል” በሚሉት በአፋሮች ላይ ብሄራዊው ሰንደቅ-ዐላማ ቀርቶ ያንድ ጎሳ አርማ ብቻ ይውለብለብባችሁ ማለት አግባብ አይደለም። አሁን የእለችው ባለ አረንጓዴ፥ ቢጫ፥ ቀይ ቀለም ሰንደቅ-ዐላማ ለበርካታዎቹ ኢትዮጵያውያን ጥልቅ ትርጉም አላት። ትርጉሙ ከኦሮሞዎችም ጋር ይያያዛል። አረንጓዴው የኢትዮጵያን ልምላሜ ብቻ ሳይሆን የኦሮሞንም ምድር አረንጓዴነት ያመላክታል። ኦሮሞዎች የሚወዱአቸውን ጨፌዎች እና ዛፎችን ጭምር። ቢጫው መንፈሳዊነትን ሲገልፅ፥ የጥንቶቹን ከኢትዮጵና ከደሸት በቀጥታ የወረዱትን የኦሮሞ ነቢያት እና ካህናት መንፈሳዊነትንም ጭምር ያንፀባርቃል። ቀዩ ደግሞ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከውጪ ወራሪዎች ለመከላከል፥ ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ሆነው ኦሮሞዎች ያፈሰሱትን ደም ይዘክራል። ስለዚህ ስስቱም ቀለማትና ሰንደቅ-ዐላማዋ ራሷ ከኦሮሞዎች ጋር የቀጥታ ግንኙነት አላቸው። የጎሣ አርማንና የሀገር ሰንደቅአላማን አስመልክቶ የምለው ይህንኑ ነው።

የሀረሩ እውሳ አዳል ግራእጁ አህመድ ኢብራሂም መሀመድ ምንም እንኳን መፃህፍትና አብያተክርትያን ቢያቃጥልም፥ የሚመሰገንበት ገድል ነበረው። ከሁሉ አስቀድሞ በኢትዮጵያዊነቱ፥ በኢትዮጵያ ሰንደቅአላማና በኢትዮጵያ አንድነት አይደራደርም ነበር። ቱርኮችና አረቦች ኢትዮጵያን እንዲያጠፉ ሊጠቀሙበት የጦርመሳሪያና

የራሳቸውን ወታደሮች ቢሰጡትም፥ ሙሉ በሙሉ አሸንጉሊታቸው ሆኖ ፍላጎታቸውን አላሙዋላላቸውም። አብረውት የነበሩት ሱማሌዎች የእኛ ግዛት ከአዋሽ ማዶ አይደለም ሲሉት፥ ቱርኮቹም ያንተ ግዛት ከአዋሽ በታች ነውና ከዛ አትለፍ ተመለስ ሲሉት፥ የእሱ እቅድ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ መግዛት ብቻ ሳይሆን የጥንትዋን ኢትዮጵያን ክብርና ዝና ለማስመለስ ግብፅ'ን የመንን እና ሱዳንን ጭምር ለመቆጣጠር ስለነበር አሻፈረኝ አላቸው። ሱማሌዎቹንም ፈጃቸው።

እላይ በተጠቀሰው ምክንያት በተሰለፈበት ቦታ ሁሉ የኢትዮጵያን አረንጓዴ፥ ቢጫ ቀይ ሰንደቅአላማ እና አረቦች የቸሩትን የእስልምና ሃይማኖቱን የሚወክለውን ግማሽ ጨረቃ ያሰበትን አረንጓዴ አርማ በኩራት ያውለበልብ ነበር። የሁዋላ ሁዋላ መላውን ኢትዮጵያን እጠቀልላለሁ ቢልም በመጀመሪያ አነሳሱ ከንጉሠነገሥቱ፥ ከኦሮሞው ተወላጅ ከአፄ ልብነድንግል እውቅና አግኝቶ የንጉሡን ሴት ልጅ አምራ-ፅዮንን አግብቶ ከአዋሽ መለስ እስከ ሀረር ለመግዛት ነበር ። ስለዚህም ንጉሡን፥ ልጅህን አምራ-ፅዮንን ዳርልኝና አስልሜ አግብቻት፥ ተዛምደን ከአዋሽ በታች እየገዛሁ ግብሬን እያገባሁልህ ላገልግልህ፤ ፍቅራችንም ይፅና፤ ብሎ ደብዳቤ ፃፈለት። ክርስትያኑ ንጉሥ ግን አልባሌ ነው ብሎ የሚያስበውና ክርስትያን ያልሆነው ሰው ልጅህን ላግባ በማለቱ እንደ ድፍረት ቆጥሮት የዛቻ ደብዳቤ መለሰለት። ግራኝ አህመድም በዚህ ተናዶ ጦርነቱን ቀጥሎ ንጉሡን እና ቤተሰቡን እስከመጨረሻው አሳደዳቸው። ልእልት አምራ-ፅዮንም እንኳን ልታገባው ቀርቶ፥ ግራኝን በጀግንነት ተዋግታው ሞተች።

ግራኝ አህመድ ግን ያን ሁሉ ጦርነት ያኪያሂድ የነበረው በሙስሊም ሰራዊት ብቻ ታጅቦ አልነበረም። ከሙስሊሞቹ ጋር የተደባለቁ የአማራ ክርስትያን፥ የኦሮሞና የሌሎችም ጎሳዎች ለሱ ይዋጉለት ነበር። በማእረጋቸውም እስከ ደጃዝማች ያደርሳቸው ነበር። ቢሆንለት ኖሮ የእስላም መንግሥት መስርቶ፥ ሃበሻ ያላትን መላዋን ኢትዮጵያን በስነስርአት ለማስተዳደር ያስብ ነበር እንጂ ቅዋሚ ያላኪያሄዱበትን ዜጎቹን ወይም በግዛቱ ስር የወደቁቱን ወገኖቹን የግድ ስለሙ ብሎ አያስጨንቅም ነበር። እኔን ካልተቃወማችሁኝ በመሬታችሁና በሃይማኖታችሁ እንድትፀኑ እፈቅድላችሁአለሁ።

ከተቃወማችሁኝ ግን፥ማስለም ብቻ አይደለም ባርያ አድርጌ ለአረቦች አሸጣችሁአለሁ ብሎ አውጆ ነበር። ያለውንም አድርጎታል።

እንግሊዞች በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ላደረጉት የመጨረሻ ውድቀት ተጠያቂ አፄ ዮሃንስን ብቻ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ። ስለ እውነት እንነጋገር ከተባለ፥ እሳቸው ብቻ ተጠያቂ አይሆኑም። እሳቸው በአፄ ቴዎድሮስ ላይ የነበራቸው የግል ቂም ብቻ ነው። እሱም አንደኛ፥ እሳቸው ካሳ ምርጫ ተብለው በሚጠሩበት ሰዐት የአፄ ቴዎድሮስ ወታደር ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተው አምባቦ ላይ ከደጃዝማች ውቤ ጋር አፄ ቴዋድሮስ ሲዋጉ፥ ካሳ ምርጫና የእናታቸው ወንድም አጎታቸው አርአያ ድምፁ ተሳትፈው ነበር። አርአያ ድምፁ ከደጃዝማች ውቤ ተጣልተው፥ ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር አድመው፥ በዚሁ በአንባቦ ጦርነት ላይ ጀብድ በመሥራታቸው ከድል በሁዋላ ራስ ብለው ሾመው የትግራይ ገዢ አደረጉዋቸው። ካሳ ምርጫ ግን ምንም ልዩ ጀብድ ባለማሳየታቸው ባላምባራስ ብለው የመጨረሻ ዝቅተኛ ማእረግ ዳረጉዋቸው። ይህ ካሳ ምርጫን አስቆጣቸው። በሞግሼአቸው በካሳ ኃይሉ ላይ ቂም እንዲይዙም አስገደዳቸው። ይህ በእንደዚህ እያለ አፄ ቴዎድሮስ ሸዋን በወረሩበት ሰዐት በሰላም የተቀበለንን አትዝረፉ ብለው ለወታደሮቻቸው አወጁ። የባላምባራሰ ካሳ ምርጫ ሰራዊት ግን አዋጁን ጥሶ ከመንደር ገበቶ ሲዘርፍ ባላገሩ የአፄ ቴዎድሮስን ትእዛዝ ሰምቶ ስለነበር ዘራፊዎቹን ተቃውሞ አሳደዳቸው። ዘራፊዎቹ ሲሮጡ ያዩት አፄ ቴዎድሮስ የሚሮጡበት ምክንትያት ሲነገራቸው ሲሆን አዋጁን አክብረው ባላገሩን አለመዝረፍ ነበረባቸው። ከዘረፉ ደግሞ ቆመው መጋተር ነበረባቸው እንጂ ወታደሮች ሆነው እንዴት ይሸሻሉ፥ ብለው በንዴት እጅ እግራቸውን ቆረጡአቸው። በላምባራሰ ካላ በዚህ ተበሳጭተውና ይበልጥ ቂም ይዘው ወደ ሀውዜን ሄደው አገው ንጉሴ ከተባለ አንድ እልህ አስጨራሽ የአፄ ቴዋድሮሰ ጠላት ጋር አብረው ሸፈቱ። ከዛም ከእንግሊዞችና ፈረንሳይዎች ጋር ደብዳቤ እየተላላኩ በንጉሠነገሥቱ ላይ እያሴሩና እርዳታ እየጠየቁ ከረሙ። እንግሊዞች አፄ ቴዎድሮስን ሊቀጡ በመጡ ጊዜ ባላምባራሰ በአጋጣሚው ተጠቅመው ከእንግሊዞች ተመሳጠሩ። ይሄው ነው። ይሀንንም ተንኮል ባላምበራሱ ብቻ ሳይሆኑ በአፄ ቱዎድሮስ ላይ ቂም የያዙ ሁሉ መሳፍንት ፈፅመውታል።

ለኦሮምያ ካርታም ያለኝ አመለካከት እንዲሁ ነው፤ በቅርቡ በማሕበራዊ ድረ-ገጽ በቀስቀስኩት ውይይት ላይ ኦሮሞው ጠባብዋን “ኦሮምያን” ሳይሆን ጠቅላላዋን ኢትዮጵያን እንደ ቤቱ ሊያይት ይገባል ብዬ ላቀረብኩት ሀሳብ አንድ የኦሮሞ ብሔርተኛነት አራማጅ “ጠቅላላዋን ኢትዮጵያን “ኦሮምያ” ብለን እንጥራና ይህን አጀንዳ እንዝጋው” ሲል አስተያቱን ሰጥቷል። የዚህን ሀሳብ ተተግባሪነት በኂላ እናያለን፤

አንዳንድ ኦሮሞ ጓደኞቼ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ነገር እንደሌለ እና ኢትዮጵያውያን እንዳልሆኑም ይነግሩኛል። ኦሮሞዎች ኢትዮጵያውያን ካልሆኑ ምን ሊሆኑ ነው ታዲያ? በኔ አስተያት ኢትዮጵያዊነቱን የሚክድ ማንኛውም ኦሮሞ፣ ኦሮሞዎች በ16ኛው ክፍለ-ዘመን በማደጋስካር በኩል ከእስያ የመጡ የውጪ ወራሪዎች ናቸው የሚል ሃሳብ በስህተት ከሚያራምዱ ጋር የሚስማማ ነው። ኦሮሞዎች ከውጪ የመጡ ወራሪዎች ከሆኑ በየትኛው መብታቸው ነው ካንዲት አገር ላይ “ኦሮምያ” የምትባል ግዛት የሚቆርሱት? ያንተ ያልሆነውን ዳቦ እንዴት ትበላዋለህ? ኦሮሞዎችስ ፍፁም ኢትዮጵያውያን ነን። አማሮች፣ አፋሮች፣ ሀዲያዎች፣ ጉራጌዎች፣ ጋምቤላዎች፣ ከምባታዎች፣ ወላይታዎች፣ ሶማሊዎች እና ሁሉም ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵ ልጆች እንደሆኑ ሁሉ ኦሮሞዎችም የኢትዮጵ ልጆች ናቸው። ለኢትዮጵያዊነት ሥነ-ልቡና፣ ለታሪክዋ፣ ለባሕልዋ፣ ለቋንቋዋ፣ ለሥነ-ጽሑፍዋ፣ ለማሕበራዊ ሳይንስዋ፣ ለአንትሮፖሎጂዋ እና ለጆኦግራፊዋ እንደሌሎቹ ዜጎች የድርሻቸውን ብዙ አበርክተዋል። በተጨማሪም ባለፉት 3500 ዓመታት ውስጥ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከልክ በላይ ነው። ይህን ሁኔታ *“ኦሮሞ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከተው አስተዋጽኦ”* በሚለው ጽሁፌ አብራርቸዋለሁ። ምንም እንኳ ወታደሮች እና ቀሳውስት ሆነው የተጫወቱትን ሚና ባለፉት 3000 አመታት ውስጥ ቀላል ባይሆንም በለለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ውስጥ በጋብቻ ገብተው የኢትዮጵያን የታሪክ አቅጣጫ ላለፉት 700 ዓመታት ሲወስኑ መኖራቸው የማይታበል ሀቅ ነው። ይኸውም ለለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት በሸዋ እንደገና ከመስረተው ከአዛዥ ጫሳ የልጅ ልጅ እና ከጊፍቲ ሀዊ መንዲያ ልጅ ከተስፋ-እየሱስ የግዛት ዘመን ጀምሮ ነው።

ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ አዲስ መጥ ባዕዳን አለመሆናቸውን ይህ በሚገባ ያረጋግጣል። ኦሮሞዎች ባዕዳንም አይደሉም፤ ታሪክ ሳይኖራቸው የሚጮሁ ድመቶችም አልነበሩም፤ የታላቁን አባታቸውን የኢትዮጵን ደማቅ ታሪክ አንግበው የሚያገሱ አንበሶች ነበሩ እንጂ። ናቸውም። ኦሮሞዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው አሳው ግሩም ድንቅ ታሪክ የሠሩ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የማይቀበል ማንኛውም ኦሮሞ አንድም የገዛ ታሪኩን የማያውቅ ወይም ክቡር ማንነቱን አሽቀንጥሮ የጣለ፥ የሚያሳዝን ሰው ነው።

------------------------//------------------------

# መደምደሚያ

ከዚህ በላይ በቀረበው ጽሁፍ ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ ባእዳን እንግዶች ሳይሆኑ ልክ እንደ አማራና እንደሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አገር በቀል ኗሪዎች መሆናቸውን ተምረናል። ከዚህም አልፎ ኦሮሞና አማራ በደም የተዛመዱና ላለፉት 3500 ዓመታት በማህበራዊ አኗኗር፣ በባሕል፣ በቋንቋ፣ በሐይማኖትና በመንፈሳዊ ሕይወት የተቀላቀሉ እና የተዋሃዱ መሆናቸውንም አውቀናል። ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ አመራር ውስጥ ቁልፍ ሚና የተጫወቱ እና ለኢትዮጵያ ስልጣኔም ጉልህ ድርሻ ያበረከቱ ዜጎች ናቸው። ያበረከቱት አስተዋፅኦም በስነ-ልሳን፣ በፍልስፍና፣ በመንፈሳዊ ባህል በወታደራዊ ሳይንስ፣ በቅኔ፣ በቤተ ክህነት አገልግሎት፣ በዳንኪራ፣ በሙዚቃ እና በእደ-ጥበብ ዘርፎች ተዘርዝሮ ቀርቧል። የኦሮሞና የአማራ ግንኙነት በብዙ መልኮች በርስበርስ መፈቃቀድ፣ መፈቃቀር እና መከባበር ላይ የተመሰረተ እና በርግጥም በአርአያነት የሚታይ መሆኑን ተገንዝበናል። ባለፈው ታሪካቸው ብቻ ሳይወሰኑ ለወደፊትዋም ኢትዮጵያ አንድነት፥ እድገት እና ሰላም ምሰሶ እንደሚሆኑ አልጠራጠርም።

ስለ ኦሮሞና አማራ የዘር ሃረግ ምንጭ ስንመረምር፥ ምንጩ አንድ መሆኑን ተገንዝበናል። ከሌላው ሁሉ ማስረጃ ይበልጥ አንዱ ላይ ብቻ እንኳ ብናተኩር በቂ ነው። ኦሮሞና አማራ በአባይ ዙርያ በጎጃም ከአንድ ምንጭ ለመቀዳታቸው ሶስት የማይነቀነቁ ማረጋገጫዎች አሉ። አንደኛ፥ አበው ኦሮሞዎች ስነፍጥረትና አባታችን (ደሸት) ከውሃ ውስጥ ፈለቀ ብለው ማውጋታቸው፥ ሁለተኛ፥ በዛው በምስራቅ ጎጃም ውስጥ ከውሃ የፈለቁ እነማይ ወይም የውሃዎቹ ሰዎች የሚባሉ አማሮች አሁንም መኖራቸው፥ እና ሶስተኛው ደሸት የሚባል ሰው እና ዘረ-ደሸት የሚባሉ ሰዎች በዛው በጎጃም እንደነበሩ መታወቁ ነው። ለምሳሌ በ *ውዳሴ ማርያም* አንድምታ ላይ ስለ ዘረ-

ደሸት የተመዘገበ ከትውልድ ትውልድ ወደ እኛ የተላለፈ እውነት አለ። በዚህ መፅሃፍ ውስጥ ደሸትን ዘረደሸት ብለው በመጥራት፥ ዘረ-ደሸት ከአባይ ምንጭ አጠገብ ሆኖ በኀሊናው ሲመስጥ፥ ድንግል ማርያም ወደ ፊት የምትወልደውን እየሱስን አቅፋ፥ በእነሱ ላይ ደግሞ እየሱስ ሲወለድ ወደ ፊት የኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ ወጥታ የደሸትን ልጆች ሰብአሰገልን ወደ ቤተልሄም የምትመራቸውን ኮከብ በቅድሚያ ዐያት። እሱ የዐያትን ኮከብ ከዐያት ከ 1600 ዐመታት በሁዋላ እውነትም ከኢትዮጵያ በተጨማሪ፥ ሱዳን እና የመን ይደርስ የነበረው የኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ ታየች። በአፄ ባዜን ንጉሠነገሥትነት ስር በዛን ጊዜ 12 ነገሥታት የነበሩት የደሸት ልጆች ወንድማማቾች የኦሮሞን፥ የአማራን፣ የትግሬን እና የሌሎቹንም ጎሳዎች ወክለው፥ የኢትዮጵያን ቢጫ ወርቅ፥እጣን እና ከርቤ ይዘው፥ በኮከብዋ እየተመሩ ወደ ቤተልሄም አምርተው ለህፃኑ መሲህ ለእየሱስ ክርስቶስ ገፀበረከት አቅርበዋል። ለምሳሌ ከኦሮሞ ንገሦች አንዱን፥ ከአማራዎቹ ደግሞ ዐራቱን በስም ለመጥቀስ ያህል ኦሮሞው፥ የደርዲና፥ የስገል፣ የኦርመን (የኦሮሞ)፥ እና የማጂ ንጉሥ፥ አማሮቹ የጎጃም እና የጣና ውስጥና ዙሪያ፥ በደሸት ከተማ ተቀማጭነት የጎንጂ እና ጉንዳጉንዲት ነገሥታት አጎጃ ጀባን፤ አቦል፤ቶና እና በረካ ነበሩ። የኦሮሞው ንጉስ መጋል ወደ ቤተልሄም ከመጓዙ በፊት የመደባይ-ኦሮሞ ካህናትን ይዞ እና የኦሮሞ ወታደሮችን ከተት ብሎ፣ በአፋሮች ድንቅ መርከብ ተሳፍሮ፥ ባህር ተሻግሮ፥ ስፔንን እና ፖርትጋልን ቅኝ እንደ ገዛ እዚህ ፅሁፍ ከላይ መቀመጡን ተገንዘበናል። እንግዲህ እውነተኛው እና ትልቁ ታሪካችን ይህንን ይመስላል። ይህም ሲባል፥ ዘመዳሞቹ ኦሮሞዎችና አማሮች ባለፈው ታሪካቸው ብቻ ሳይኩራሩና ሳይገቱ፥ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋራ በመተባበር ለወደፊትዋ ኢትዮጵያ አንድነት፥ እድገት እና ሰላም ምለሶ እንደሚሆኑ አልጠራጠርም።

# Notes:

## The True Origin of the Oromo and Amara

1. Getachew Haile, *Ye Aba Bahriy Dersetoch,* p. 76.

2. Bairu Tafla. *Asma Giyorgis and His Work,* p.308.

3. Bairu Tafla. ibid., p. 309.

4. Bairu Tafla. ibid., p. 311.

5. Bairu Tafla. ibid. p. 138.

6. Aleka Taye Gebremariam, *Ye Ethiopia Hizb Tarik,* pp. 60-61.

7. Tekle Tsadik Mekuria, Ke Atse Libine-Dengil Iske Atse Tewodros, p. 94

8. Yilma Deressa, Ye Ethiopia Tarik Basra Sidestengaw Kifle Zemen,pp. 214-215.

9. Mohammed Hassen, *The Oromo of Ethiopia*, p. 4

10. Getachew Haile. ibid., pp. 26-27.

11. Bonnie K. Holocomb and Sisai Ibssa, *The Invention of Ethiopia ,p.5.*

12. Harold Marcus. *A History of Ethiopia,* pp. 34-35.

13. Tekletsadik Mekuria, ibid., p. 9.

14. Bairu Tafla, ibid., p. 204.

15. Bairu Tafla, ibid., p. 879.

16. N.Y, Saturday, October 21, 2006.

17. Aman Belai, Metsehafe Abrihit, p. 490-492.

18. Bairu Tafla. ibid., p.202.

19. Merigeta Lisane Work Gebre Giorigis, *Tintawi Sirate Mahlet Ze Abune Yared Liq,*

pp. 14-16.

20. Aman Belai, *Metsehafe Subae Ka'le.* p. 309.

21. Aman Belai. Ye Tintwa Ye Ethiopia Tarik. p. 350.

22. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik. p. 41.

23. Aman Belai, .ibid. p. 43.

24. Aman Belai. ibid. p. 57.

25. Aman Belai, pp. 306-308.

26. *Strong's Greek Lexicon.* #2739 and #4028, available on line.

27. Psalm 68: 31.

28. Aman Belai, Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik, p.10

29 Aman Belai. Metsihafe Subae Zebeaman Kale, pp. 320-334.

30. Aman Belai. ibid., p.324.

31. Psalms, 72:10.

32. Aman Belai, locit., p. 324.

33. Getachew Haile, ibid., p.76.

34. G.W.B. Huntingford, in *The History of The Galla of Ethiopia,* p.12.

35. Aman Belai. Hizbaw Kedamawi Mestawet Tarik, p. 28.

36. *The Holy Bible,* Numbers 21, 14.

37.Bairu Tafla, Asmagiyorgis and His Works, p. 310.

38. Aman Belai. Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, p. 30.

39. Aman Belai,*Metsihafe Abrihit*, p.479.

40. Aman Belai. Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik. p. 202.

41. Aman Belai. Ye Tinatwa Ethiopia Negestat Tarik, pp. 53-55.

42. Aman Belai, *Metsehafe Abrhit*, p. 4.

43. Ye Ethiopia Tarik, Ke Atse Libine-dengil iske Atse Tewodros, p. 21

44. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, p45.

45. Aman Belai. *Yetintwə Ethiopia Tinsae Tarik,* p.320.

46. Belai, Aman, Metsehafe Subae, p.59.

47. Aman Belai, *Metsehafe Abrihit*, p.308.

48. Aman Belai, ibid., pp.485-487.

49. Aman Belai, Metsihafe Subae Zebemaman Kale, pp.127-128.

50. Bairu Tafla, Asma Giyorigis and His Works, p. 202.

51. Aman Bela. *Mtesehafe Abrhit*, p. 521.

52. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, pp. 34-35.

53. 101 Psalm 110, 4

54. Aman Belai. Mesehafe Subae Kale Zebeaman, pp. 58-59

55. Aman Belai, ibid. p. 309.

56. Psalms 68: 31.

57. Numbers, 10, 29--32

58 Luke, 11, 32.

59. Fikre Tolossa, The Hidden and Untold History of the Jewish People and

Ethiopians, pp.39-43)

60. Aman Belai. *loc.cit. pp.*129, 150-152.

61. Aman Bela.loc.cit., p.128.

62. Aman Belai, loc.cit., pp.151-152.

63. Aman Belai, Ye Tinantinawa Ethiopia Tarik, p.199.

# ክፍል ሦስት

# በኢትዮጵያ ሥረወ-መንግሥታት ውስጥ የአማራው ተሳትፎ መጠን

ስለ ሥርወ-መንግሥት ስናወራ፥ ከሁሉ አስቀድሞ በአማርኛ ሥርወ-መንግሥት በእንግሊዝኛ 'dynasty' የሚለውን ቃል መተርጎም ተገቢ ይሆናል። እንደ መሪያም ዌብስተር መዝገበ-ቃላት "dynasty" ማለት ባንድ ሀገር ላይ "ሥልጣን እየተቀባበሉ የገዙ ያንድ ቤተሰብ አባላት" ማለት ነው። የሥልጣን ዘመናቸው በመቶዎች ወይም በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ሊዘልቅ ይችላል። በዚህ ፍቺ መሠረት " አማራው ኢትዮጵያን እንደ ሥርወ-መንግሥት ገዝቷል" ማለት ባለማወቅ አልያም በፖለቲካ መድልዎ ላይ የተመሰረተ አነጋገር ነው። በርግጥ፥ አማሮች እንደ ግለሰብ ንጉሥ በመሆን የየራሳቸውን ግዛት በሚገባ አስተዳድረዋል። ሆኖም የራሳቸውንም ሆነ የሌላ ስርወ-መንግሥትን ወክለው ንጉሠ-ነገሥት እና ንግሥተ-ነገሥታት በመሆን ድፍን ኢትዮጵያን አልገዙም። እዚህ ላይ ግልፅ መሆን ያለበት፥ አማሮች ብቻ ሳይሆኑ፥ ትግሬዎች እና ኦሮሞዎችም በየስማቸው ሥርወ-መንግሥት መስርተው ኢትዮጵያን አላስተዳደሩም። የአማራ፥ የትግሬ ወይም የኦሮሞ ሥርወ-መንግሥት የሚባል በኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም። ባለፉት 3000 ዐመታት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ሥርወ-መንግሥታት የሰለሞናዊ እና የዛግዌ ብቻ እንጂ። ሆኖም በርካታ ኦሮሞዎች በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ውስጥ በጋብቻ "ሰርገው ገብተው" ላለፉት 700 ዓመታት በሥልጣን ላይ ኖረዋል። በርግጥ ለኢትዮጵያ ህልውና እና ሥልጣኔ አማሮች ያበረከቱት አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው። ይህንን ጉዳይ በተገቢው ቦታ አነሳዋለሁ። ይህ ርእስ ዓላማው ግን አማራው ኢትዮጵያን እንደ ሥርወ-መንግሥት አለመግዛቱን አስመልክቶ አባባሉን በማስረጃ ለማረጋገጥ የኢትዮጵያን ሥርወ-መንግሥታት ታሪክ በዝርዝር መመርመር ነው። በመግቢያው ላይ ግልጽ እንዳደረግሁት አንዱን

ጎሣ የመካብ ወይም ሌላውን የማሳነስ ፍላጎት የለኝም። የታሪካችን እውነታው ክተረቱ ተለይቶ ሀቁ ፍንትው ብሎ እንዲታየን በጉዳዩ ላይ ብርሃን መፈንጠቅ ነው የኔ ተግባር። ለምሳሌ "በአክሱማይት ዘመን ፍጹማዊ የሆነ የፖለቲካ ሥልጣን እስከ ዘለቂታው ጨብጦ ኢትዮጵያን የገዛ ትግሬ ወይም ኦሮሞ ወይም አማራ ንጉሠ ነገሥት አልነበረም" ብል ትግሬን ወይም ኦሮሞን ወይም አማራን ማሳነሴ ሳይሆን ዝም ብዬ ታሪካዊውን እውነታ ማስቀመጤ ብቻ ነው።

ይህ ሁሉ ሆኖ አንድ ታሪካዊ ሃቅ ተመዝግቦአል።-- የዛሬ 1600 ዐመት ገደማ፥ ኦሮሞዎችን ሳይጨምር አማሮች በሰለሞናዊው/ኣግኣዚ/ ሥርወ-መንግሥት በአክሱም፥ ሥልጣን ላይ ላጭር ጊዜ የወጡበት አጋጣሚ አለ። እሱም ያው ኦሮሞዎች በሁዋላ በሸዋ እንዳደረጉት ሁሉ በጋብቻ አማካይነት ነበር። ላለፉት 700 ዓመታት በኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሰጡት ባመዛኙ የሰለሞናዊው/ኣግኣዚ ነገሥታት ነን የሚሉ የኦሮሞ ዝርያ ያላቸው ግለሰቦች ቢሆኑም ቅሉ አማሮች በቋንቋቸውና በባሕላቸው መስፋፋት ምክንያት፥ እንዲሁም በየሃገራቸው በንጉሥነት፥ በአስተዳዳሪነት፣ በአገረ-ገዢነት፣ እና በጦር አለቅነት በነበራቸው የተወሰነ ሥልጣን የተነሳ አማሮች ዘውዳዊውን ሥርዓት ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠሩ የመሳዋ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥታት እና ንግሥተ ነገሥታት መስለው ታይተዋል። በዚህ የተሳሳተ ግምት የተነሳ አማሮች አላግባብ የጥቃት ዒላማ ሆነው ሲሰቃዩ ኖረዋል፤ አሁንም እየተሰቃዩ ናቸው። በመግቢያዬ ላይ እንደጠቀስኩት አማሮች በየግዛታቸው በአስተዳዳሪነት እና በጦር አለቅነት የነበራቸውን ያንኑ ውሱን ቦታ አንኳ ካጡ ከ40 ዓመት በላይ ሆኗቸዋል። የዛሬ 43 ዐመት የደርግ ወታደራዊ መንግሥት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንግሥት ገልብጦ ሥልጣን ሲይዝ ነው አማሮችም የነበረቻቸውን ያችኑ ቦታ የአጡአት። በዱሮው መሰረተ-ቢስ ክሰና ቅሬታ ሰበብ እስከዛሬ ድረስ አማሮች እየተጠቁ ናቸው። ባሁኑ ወቅት አማሮች ስልጣን-አልባ መሆናቸውን ሁላችንም እናውቃለን። ስለዚህ በዛሬው ጊዜና ወቅት አማራን ጨቋኝ ብሎ የሚወነጅል ማንኛውም ሰው መሬት ላይ ካለው ከተጨባጩ እውነታ የራቀ ስህተተኛ ነው። ባሁኑ ጊዜ እንደዚህ ዓይነቱን ጉዳይ ማንሳት አፍራሽ ተግባር ነው። ይሁንና ያለፈውን የሚቆፍሩ አሁንም አንዳንድ ሰዎች አሉ። ስለዚህ ያለፈውን

መመርመር ተገቢ ነው። በስማቸው የመሰረቱት ሥርወ-መንግሥት ከሴስ ደግሞ በሰሰሞናዊው/ዛጉዌ ሥርዎ-መንግሥት ውሥጥ የነበራቸው ተሳትፎ መጠን ምን ያህል እንደነበረ እነመዝናለን። ይህንንም ለማድረግ፥ ባለፉት 4500 ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰቱትን ሥርወ-መንግሥታት መመርመር ተገቢ ይሆናል። በዚህ መንገድ በሥርወ-መንግሥታቱ ውስጥ አማራ ንጉሠ-ነገሥት እና ንግሥተ-ነገሥታት በመሆን ሙሉ ሥልጣን ኖሮት የገዛበት ጊዜ እንዳለ እንፈትሻለን።

"በቂ የፖለቲካ ሥልጣን ሳይኖረን የአማራ ታዛዮች ሆነን ኖርን" ከሚሉት ውስጥ አንዳንድ የኦሮሞ ፅንፈኞች ይገኙበታል። እነሱም ራሳቸውን "የአማራ ጨቋኞች ሰለባ" አድርገው ይቆጥራሉ።

እንደ እውነቱ ግን ኦሮሞ በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ሥልጣን አልነበረውምን? በኢትዮጵያ ታሪክ የኦሮሞ ዝርያዎች ዘውድ እየጫኑ ኢትዮጵያን የገዙበት ጊዜ የለምን? ቢያንስ ላለፉት 700 ዓመታት በኢትዮጵያ ሥርወ-መንግሥታት ውስጥ የተሻለ ሥልጣን የነበራቸው የአማራ ወይስ የኦሮሞ "ልሂቃን" ነበሩ? ይህ ምዕራፍ ለዚህ ጥያቄም እውነት ላይ የተንተራሰ መልስ ይሰጣል፡

በ1938 ዓ.ም ፍትሐ-ነገሥትን የተካውን ስባት ምዕራፎች እና 55 አንቀጾች የነበሩትን ህገ-መንግሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከመሰጠታቸው በስተቀር ኢትዮጵያ በታሪክ ዘመንዋ ሁሉ ፍጹማዊ ሰልጣን በነበራቸው ባለ ሙሉ ስልጣን ነገሥታት ስትገዛ ነው የኖረችው። ዊኪፔዲያ ነፃው ኢንሳይክሎፔዲያ እንዳሰፈረው "ንጉሠ-ነገሥቱ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ድረስ እንደ ቅዱስ የሚቆጠር፣ ክብሩ የማይዳሰስ፣ ሥልጣኑ የማይገሰስ፣ የሥልጣን ቅብብሉሹም ከሱ የዘር ሐረግ የማይወጣ መሆኑ በአዋጅ የተደነገገ ነበር። ይበልጥ ግልጽ ስመሆን በማእከላዊም ሆነ በክልሎች የሕግ አውጪነቱ፣ የዳኝነቱ እና የጦር ኃይሎቹ ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በንጉሠ-ነገሥቱ የተያዘ ነበር። ሕገ-መንግሥቱ ባላባቶቹን ለንጉሠ-ነገሥቱ ታማኝ በሆኑ ተሹዋሚዎች ለመተካት የህግ ሽፋን መሰጫ ነበር እንጂ የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አማካሪዎች (ሴናተሮች) የሚሰየሙት በቀጥታ በንጉሠ-ነገሥቱ በመሆኑ ዴሞክራሲያዊ ውክልና እንዲኖር ያስመ አልነበረም።" (ዊኪፔዲያ፤ 2015.) (1) ከላይ እንደተጠቀሰው የአጼ ኃይለሥላሴ ሕገ-

መንግሥት በስም ብቻ ያለ ነበር እንጂ እስከመጨረሻ ሕቅታቸው ድረስ የፍጹማዊው ሥልጣን ባለቤት እሳቸው እና እሳቸው ብቻ ነበሩ።

ርቀን ከመሄዳችን በፊት "absolute monarchy" የሚለውን ሐረግ እንተርጉም። ዊኪፔዲያን እንደገና እንጥቀስ፤--

"ፍጹማዊ የዘውድ አገዛዝ ወይም ፍጹማዊነት ማለት ንጉሠ-ነገሥቱ/ንግሥተ-ነገሥቷ/ ከሚቀርቡት/ቧት/ ሰዎች ጋር ፍጹማዊ የሆነ ሥልጣን የሚይዝበት/የምትይዝበት/ ዘውዳዊ የመንግሥት ቅርጽ ነው። ፍጹማዊ ንጉሠ-ነገሥት ባንዲት ሉዓላዊት ሀገር እና በዜጎቿ ላይ ገደብ የሌለው ሥልጣን ይኖረዋል። ፍጹማዊ ሥልጣን ብዙውን ጊዜ በዘር የሚወረስ አንዳንዴ በሌሎች ምክንያቶችም የሚያዝ ነው። ህገ-መንግሥታዊ የዘውድ አገዛዝ ከፍጹማዊው የዘውድ አገዛዝ የሚለየው የንጉሠ-ነገሥቱ ሥልጣን በሕግ የተገደበ ስለሚሆን ነው" 2 (ዊኪፔዲያ፤2015)።

ፊላጭ ቆራጭ ነገሥታት ህዝባቸውን ባልተገደበ ሥልጣን እንዲገዙ ከእግዚአብሔር እንደተሾሙ አድርገው ራሳቸውን ይቆጥራሉ። አጼው በሕይወት እስካለ ድረስ ንጉሳዊው ቤተ-ሰብ እንኳ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት መብት አልነበረውም። እንዳውም ልዑላን እና ልዕልታት በአመጽ ሥልጣን እንዳይነጥቁ እየተፈሩ "ወህኒ አምባ" በተባለ ቦታ በቁም እስር ይጠበቁ ነበር። ንጉሠ-ነገሥቱ ሲሞት ከእሥረኞቹ ልዑላን አንዱ ይፈታና በሟቹ እግር እንዲነግሥ ይደረግ ነበር። እንግዲህ እነዚያ ነገሥታት ባላቸው አቅም ሁሉ ዘውዳቸውን ከመጠበቅ እና የግል ፍላጎታቸውን ከማሟላት በስተቀር የራሳቸውን ጎሣና ነገድ ፍላጎትና ምኞት እንኳ የሚያስጠብቁ አልነበሩም። በሥልጣናቸው ከመጣባቸው ለማንኛውም ነገድ አባል ምህረት አልነበራቸውም። ስለዚህ አጼው ከዚህ ወይም ከዚያ ጎሣ ወይም ነገድ የወጣ ነው ስንል ጠቅላላው የጎሣው ወይም የነገዱ አባላት ተጠቃሚዎች ሆነዋል ማለት አይደለም። እንደ ኢትዮጵያ ባለች ጦረኛ ሀገር አጼዎቹ ቅድሚያ የሚሰጡት ሕልውናቸውን ለሚያስከብሩላቸው ለመሳፍንቶቻቸው፥ ለጦር አበጋዞቻቸው እና ለወታደሮቻቸው ነበር። ደሞዝ መክፈል ባልተለመደበት ወቅት ለወታደሮች እንደ ደሞዝ የሚሰጣቸው ተሰሪነት የመግባት መብት እና የእርሻ መሬት ነበር።

ተሠሪነት መግባትን ለማስቆም አዋጅ ያወጡ እና የብር ማዕድን እጥረት ስለገጠማቸው ተቋረጠ እንጂ ለወታደሮቻቸው ደሞዝ መክፈል የጀመሩ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ነበሩ። መሬት እንደልብ ስለነበረ ወታደሮች እንደማዕረጋቸው ለም መሬቶችን ሊይዙ ችለዋል። እንደዚህ ዓይነት የጦር አበጋዞች እና ወታደሮች "ነፍጠኞች" ተባሉ። ትርጉሙም "ጠብ-መንጃ ያለው፤ ባለ ጠመንጃ" ማለት ነው። ሁሉም አጼዎች የየራሳቸው ነፍጠኞች ነበሯቸው። በርግጥ ነገሩ ጊዜው የሚጠይቀው ሁኔታ ነበር። ከዚያ ክስተት ጥቂት ማየት እንችላለን።

ከ3 ሺ ዓመት በፊት ቀዳማዊ ምኒልክ "አቺ" የተባለና ከመደባይ/አሮሞ የተውጣጣ ጠንካራ ሰራዊት ነበረው። ቀዳማዊ ምኒሊክ ይህንን ጦሩን "ጨዋ" (ሸዋ) ብሎ ሰየመው እና የዛሬውን ማእከላዊ ኢትዮጵያን ወረረ። ከዚያም ጦሩን በወረረው በዚህ ቦታ ላይ አሰፈረና አገሩን በጦሩ መጠሪያ ‹‹ጨዋ›› (ሸዋ) ብሎ ጠራው። በዚህም ወንድማማቾቹ አማራ እና ጀማ ከወረራው ከ300 ዓመት በፊት ጀምሮ ይኖሩበት የነበረው ይህ ለም መሬት "ጨዋ" (ሸዋ) ለሚባለው ለቀዳማዊ ምኒሊክ ወታደሮች ተሰጠ። መሬቱ እንጂ ዘውድ አልተሰጣቸውም። ስለዚህ እነዚያ አሮሞ ወታደሮች እና ዝርያዎቻቸው ወታደራዊ ኃይል ስለነበራቸው በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ውስጥ ኢትዮጵያን ገዙ ማለት አንችልም።

በርካታ አማሮች እና ጥቂት የአሮሞ ጦረኞች በእናቱ ኦሮሞ የሆነው ይኩኖ አምላክ የመጨረሻውን የዛጉዌን ንጉሠ-ነገሥት ይትባረክን እንዲያሸንፍ እና ሥልጣን እንዲይዝ ረዱት። ይኩኖ አምላክ ውለታ ለመመለስ የረዱትን እና አብዛኞቹ አማሮች የነበሩትን ወታደሮች በለሙ ዐታ ላይ አሰፈረና ርስት ለጣቸው። ቀደም ሲል አጼ ላሊበላ ከአጼ ሀርቤ ጋር ሲዋጋ ላገዙት አማሮች አድርጎላቸው እንደነበረው ሁሉ ይኩኖ አምላክም አማርኛ የመንግሥቱ የሥራ ቋንቋ እንዲሆን አወጀ። ዳሩ ግን፣ ይህም ለአማሮች ምንም የፈየደላቸው ጉዳይ አልነበረም። ዘውድ የመቀዳጀት እድል ግን ለንጉሣውያን ቤተ-ሰብ የተጠበቀ መብት ሰለ ነበር ይኩኖ አምላክ ሲሞት ልጁ ነገሠ እንጂ አማሮች ስልጣን አልያዙም።

ቀደም ብሎም ቀዳማዊ ምኒልክ የእናቱ ወገን ከሆኑት ከኢትዮጵያውያን ጋር ሲዋጋ ያገዙት ወታደሮች አግአዚ የተባሉ ከጋዛ

የመጡ እሥራኤሎች ነበሩ። ቀዳማዊ ምኒሊክ በእግአዚ እማካይነት እና በወላጅ እናቱ በኢትያኤል(ንግሥት ሳባ) ድጋፍ ኢትዮጵያውያንን ድል ካደረገ በኂላ የሱባን ቋንቋ እና የሱባን ባሕል በአዋጅ አጥፍቶ በግዕዝ ቋንቋ እና በአግአዚ ባሕል ተካው። ለአግአዚዎች ሰፋፊ መሬት እና ታላላቅ ሥልጣን ለጣቸው። የመጨረሻውን ሥልጣን ንጉሠ-ነገሥትነቱን ብቻ ለራሱ እና ለዝርያዎቹ እንዲጠበቅ አድርጎ እስከ ንጉሥነት ድረስ ባለው ማዕረግ ላይ ሁሉ አግአዚዎችን ሾማቸው። ዳሩ ግን ንጉሠ-ነገሥትነትን አልቸራቸውም። እሱን ለልጆቹ ብቻ ነበር ያወረሰው።

በ15ኛው ክፍለ-ዘመን በልጅነቱ በጦርነት ላይ ተማርኮ በአንድ የኦሮሞ ባላባት ዘንድ በጉዲፈቻነት ያደገው አጼ ሱስንዮስም ስልጣን ለመያዝ የበቃው በመሰረተው ታላቅ የኦሮሞ ጦር ታግዞ ነበር። ያንን የኦሮሞ ጦሩን ያስፈረውም በእመጹበት አማሮች መሬት ላይ ጎንደር እና ጎጃም ነበር። ከሁሉም በላይ ደግሞ ማንኛውንም አማጺ አማራ እንዳሻቸው እንዲቀጡና በነፍጠኛነት እንዲገነባቸው ለወታደሮቹ ሙሉ ሥልጣን ሰጥቷቸው ነበር። ኦሮምኛም እንዲያብብ ተደረገ። ራሱ ሱስንዮስ ኦሮምኛ አቀላጥፎ ከመናገሩም በላይ የኦሮሞን ባሕልም ወርሶ ነበር። ይሁን እንጂ በንጉሠ-ነገሥትነት ኢትዮጵያን የመሩት የሱስንዮስ ዝርያዎች ነበሩ እንጂ ኦሮሞ የጦር አበጋዞቹ ወይም ኦሮሞ አገረ-ገዢዎቹ አልነበሩም።

በወቅቱ ለሀረር እና አውሳ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጦር መሪ የነበረው አህመድ ግራኝ ኦሮሞ የጦር አበጋዞቹን እና ደጋፊዎቹን በሸዋ በአማራው ይዞታ ላይ ነበር ያስፈራቸው። ያ መሬት ከ300 ዓመት በፊት በአጼ ይኩኖ አምላክ ለአማሮች የተሰጠ ይዞታቸው ነበር። በስሌ/ሳላሌ/ የተመደቡ የግራኝ ደጋፊ የነበሩ ኦሮሞዎች አማሮች "ግራርጌ" ይሉት የነበረውን ያንን ቦታ "ስላሌ" ወደሚለው ቀይረው ያዙት። እስከዛሬም በዚሁ ስያሜው ይጠራል።

ምንም እንኳ አማሮች ከኦሮሞ የሚወለደውን ንጉሠ-ነገሥታቸውን አጼ ልብነ-ድንግልን ለማዳን ሕይወታቸውንና ርስታቸውን አጥተው ብዙ ውለታ የሠሩ ቢሆንም አጼው እና ዝርያዎቹ ግን ዘውዱን ለራሳቸው ያዙ እንጅ ያካፈሏቸው ነገር የለም። በርግጥም አማሮች

ንጉሠ-ነገሥቶቻቸውን ለማዳን ደማቸውን አፍስሰው ለውለታቸው ምንም የተለየ ስልጣን አላገኙም።

ይህ ሁሉ የሆነው ኢትዮጵያ በስለሞናዊ ሥርወ-መንግሥት ነገሥታት በምትገዛበት ወቅት ነበር። በዘመነ-መሳፍንት ግን ሁኔታው ተቀየረ። እያንዳንዱ መሥፍን በየራሱ መንገድ እየሄደ የየራሱን ቅጽበታዊ ፍላጎት ያሟላ ነበር። ከወህኒ አምባ የመረጠውን ልዑል እያወጣና አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥት አድርጎ እያነገሠ ራሱ በቀጥታ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ይሆን ነበር። በውጤቱም ኢትዮጵያ ብዙ ቦታ ተበጣጥሳ አረፈች።

ካሳ ኃይሉ (አጼ ቴዎድሮስ) የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ እና ስለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት ለመመለስ እንዲሁም የሀገሪቱን ሉዓላዊነት እና የንጉሠ-ነገሥቱን ዓለማቀፋዊ ተጽዕኖ አሳዳሪነት ለማስጠበቅ ከነዚህ መሳፍንት ጋር መራራ ውጊያ አካሄዱ። ፊውዳሎቹ እና ቀሳውስቱ አበሳጭተው አቀወሱአቸው። ከዚያም ሁሉን ነገር አጥተው ልክ አጼ ሱስንዮስ ከ300 ዓመት በፊት የጎንደር መሳፍንት አንገብርልህም ባሏቸው ጊዜ በኦሮሞ ስራዊት እንደ ደመሰሱት፥ አጼ ቴዎድሮስም ጎንደር ከተማን አቃጠሏት። ወታደሮቻቸውም በየቦታው ተበታትነው ተንከራተቱ። አጼ ቴዎድሮስም ሊያሰባስቧቸውና አንድ ቦታ አስፍረው፣ ያመጹባቸውን ስዎች ርስት፣ አፄ ሱስንዮስ ለኦሮሞ ወታደሮቻቸው እንደ አደረጉት ሁሉ እየነጠቁ ሊሰጧቸው አልቻሉም።

አጼ ዮሃንስ ግን እድለኛ ነበሩ። ሁኔታው በራሱ ተመቻችቶላቸው ነበር። በስራቸው ሁለት ንጉሦች ነበሯቸው፤ የሸዋዉ ምኒልክ እና የጎጃሙ ተክለሃይማኖት። ሁለቱም ንጉሦች ላይ ላዩን ለንጉሠ-ነገሥቱ ታማኝ መስለው ውስጥ ውስጡን ግን ያሴሩባቸው ነበር። ቴዎድሮስ የጀመሩትን ኢትዮጵያን ወደ አንድነት የማምጣት ዓላማ አጼ ዮሃንስም ሳይፈጽሙት መተማ ላይ በመሃዲስቶች እጅ ወደቁ። ኢትዮጵያን ከዘመነ-መሳፍንት በፊት እንደነበረችው አድርጎ የማዋሃዱን እና የንጉሠ-ነገሥቱን የማይገሠሥ ሥልጣን የማስከበሩን ጅምር ዓላማ አዳር የማድረሱ ተግባርም በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ጫንቃ ላይ ወደቀ። ዳግማዊ ምኒልክም ለኢትዮጵያ አንድነት መገኘት ባለውለተኞች ከሆኑ ባመዛኙ ኦሮሞዎች ከነበሩ አበጋዞቻቸው ጋር ሆነው ይህን ሃላፊነት ተወጡ። አጼ ምኒልክ ይህን ግብ ለማስገኘት

የካሮት እና ዱላ/ carrot and stick/ ስልት ተጠቅመዋል። መጀመሪያ ነፃነታቸውን ላስከበሩ ክልሎች ባላባቶች እውቅና ሰጥተውና በመካከላቸው ጦርነት እንዳይነሳ እንዲተባበሩ አሳስበው መልዕክት ይልኩባቸዋል። የንጉሠ-ነገሥቱን የበላይነት ተቀብለው ግብር ለመገበር የሚስማሙትን ባላባቶች ግዛታቸውን ያጸድቁላቸውና በውስጥ አስተዳደራቸው ጣልቃ እንደማይገቡባቸው ቃል ይገቡላቸዋል። ለምሳሌ የወለጋ መሳፍንት የምኒልክን ንጉሠ-ነገሥትነት ተቀብለው በርቀት ሊያግዷቸው ችለዋል። ይህን ማድረግ ያልፈለጉ ደግሞ ጦርነት ውስጥ እየገቡ ሲሸነፉ ቀደም ሲል ይደረግ እንደነበረው የምኒልክ ሠራዊትም በየክልላቸው እየገባ ሠፍሮአል። ባብዞኞቹ ግዛቶች ግን መሳፍንቱ እየተዋጉአቸው ቢሸነፉም ምኒልክ ተሸናፊዎቹን መሳፍንት ምህረት እያደረጉላቸው፣ ወደ ሥልጣን እየመለሱአቸውና የውስጥ አስተዳደራቸውን ራሳቸው እንዲመሩ እየፈቀዱላቸው የበላይነቱን ማስፈን ችለዋል። እዚህ ላይ ንጉሥ ጦና የሚጠቀስ ነው። አጼ ምኒልክ ደም መፋሰስን እናስቀር ብለው ንጉሥ ጦናን ለመኑት። ንጉሥ ጦና ግን ኃይሉን አሟጦ መዋጋት ስለመረጠ በምኒልክ ሠራዊት ላይ ከባድ ጉዳት አደረሰ። በመጨረሻ ግን ቆሰለና ተማረከ። ዳግማዊ ምኒልክ ጦናን አይቀጡ ቅጣት ከመቅጣትና መንግሥቱንም አሽቀንጥረው ጥለው ሥልጣኑን ለጦር መሪዎቻቸው ከመስጠት ይልቅ ደግነት የተሞላበት ምህረት አድርገውለት እንደሚገብርላቸው ቃል ካስገቡት በኋላ ወደ ሥልጣኑ መለሱት። ምኒልክ ተበቃይ አልነበሩም። ይቅር ባይ፣ በተጨባጭ እውነታ ላይ የተመሰረተ ምክንያታዊ አስተሳሰብ የነበራቸው እና ራሳቸውን እንደ ጥሩ ክርስቲያን የሚያዩ ሰው ነበሩ። በጦርነት ላይ የሴት ልጅ ጡት መቁረጥ ፍጹም ከባሕሪያቸው ውጪ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ውንጀላ መሰረተ-ቢስ እና ከተንኮለኞች የመነጨ ነው። የጎጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት እምጸው ጦርነት አነሱና ቆስለው ተማረኩ። ምኒልክ የቆሰለውን ምርኮኛ ገድሎ በመጨረስ ፈንታ ቁስላቸውን ራሳቸው አክመው፣ አጠገባቸው አስቀምጠው አብረዋቸው እንዲመገቡ በማድረግ ፍቅር ነው ያሳዩአቸው። ሥልጣናቸውንም አልወሰዱባቸው፤ ያለማመንታት መልሰውላቸዋል። በርግጥ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ሩኅሩኅ ነበሩ። አገራቸውን ለመውረር የመጡ ምርኮኞች ጣልያኖችን እንኳ በርኅራኄና በደግ አያያዝ ነበር የያዟቸው። እኚህን ሰው ጡት ቆርጠዋል/አስቆርጠዋል/ ብሎ መፈረጅ አግባብነት የሌለው ትንሽ

የፖለቲካ ጠቀሜታ ለማገኘት የሚነዛ ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ነው። ምኒልክን ጡት ቆርጠዋል ብለው ለማስጠላት ሀውልት ያቆሙ አካላት በድርጊታቸው ማፈር እና ያንን አሳፋሪ ሀውልትም ማፍረስ ይገባቸዋል። ምኒልክ በግላቸው እንደዚያ ዓይነት ተግባር ጨርሶ አይፈጽሙም። ከወታደሮቻቸው አንዱ ቀደም ሲል የተፈጸመ በደልን ለመበቀል ሲል ፈጽሞት ከሆነም መወቀስ ያለበት ጥፋተኛው ወታደር ነው እንጂ ምኒልክ አይደሉም። ከዚህ ጋር በተያያዘ የዛሬው ትውልድ መገንዘብ ያለበት በዚያን ጊዜ የነበሩ ብዙዎቹ ነገዶች ጨካኞች እንደነበሩ ነው። አንዳንዶቹ እንዲያውም የወንድን ልጅ ብልት መስለብ የጀግንነት ምልክት እንደሆነ አድርገው ይቆጥሩ ነበር። ፍርጃ ሆነና ጥቂት ነገዶች ምንም ያልጠረጠሩ ዜጎችን ብልት አድብተው እየቆረጡ የጀግንነታቸው ማሳያ እና ልጃገረድ ማግቢያ ያደርጉት ነበር። ለኛ ለ21ኛው ክፍለ-ዘመን ሕዝቦች ያውሬነት ባሕሪ የሚመስለን ይህ ዓይነቱ የጭካኔ ተግባር በወቅቱ ጊዜው የሚጠይቀው የጀግነነት መገለጫ ነበር። የአፄ ምኒልክ ወታደሮች እብዛኞቹ ክርስትያኖች ነበሩ። ጡት መቁረጥ በሻሪያ የሚተዳደሩ የአረቦች ባህል እንጂ የኢትዮጵያውያን አይደለም። ስለዚህ ክርስትያኖቹ የአፄ ምኒልክ ወታደሮች የገዛ የሀገራቸውን የተከበሩ ሴቶች ጡት ቆረጡ ማለት ፍፁም የፈጠራ ወሬ እና ለሰሚው ግራ ነው። እኔ በአደረኩት ምርምር ይህን የሚያረጋግጥ አንድም ሰነድ አላገኘሁም። ርካሽ ጥላቻን ለመንዛት ይህን ለህዝብ ምንም ጥቅም የሌለውን ሃውልት የአቆሙት ፓለቲከኞች ይልቅየው ለህዝባቸው የሚፈይዱ ፋብሪካዎች ቢያቆሙላቸው ከድህነት ይላቀቃሉ። ይህን የጥላቻ ሃውልት ነቅለው ፋይዳ ያላቸው ፋብሪካዎች ለህዝባቸው እንዲተክሉላቸው በዚህ አጋጣሚ አመክራቸዋለሁ። ሌላው ስለ አፄ ምኒሊክም የተነዛ ሃሰት 5 ሚሊዎን ኦሮሞዎችን ፈጁ የሚል ነው። ይህም ከእውነት የራቀ ነው። በዛ ጊዜ የነበረው ጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ ግፋ ቢል 10 ሚሊዎን የሚደርስ ነበር። 5 ሚሊዎኑ ከተገደለ ምን ሰው ተረፈ? ደግሞስ ጀግናው የኦሮሞ ህዝብ ዝም ብሎ አንገቱን ለአርድ የሚጋብዝ ነበር እንዴ? ቢያንስ በአልሞት-ባይ ተጋዳይነት አይዋጋም ነበር እንዴ? የአሮሞ ህዝብ የማይበገር ጦረኛ እና ጀግና ስለነበር ተዋግቶ ለራሱ ይመክታል እንዲሁም ይገላል እንጂ በዝምታ እንደ በግ አይታረድም ነበር። ስለእዚህ የአፄ ምኒልክ ሰራዊት 5 ሚሊዎን ኦሮሞዎች ፈጅተዋል የሚለው ወሬም ለርካሽ ፕሮፓጋንዳ የተተረተ ነው። ልክ

እንደ የወላይታ ንጉሥ ጦና እና የከፋው ንጉስ ጋኪ ሼሮቾ ሰራዊቶች የሚኒልክን መስፋፋት በመቃወም የተቃወሙት ኦሮሞዎች ላይ ግድያ መፈፀሙ እሙን ቢሆንም 5 ሚሊዮኖች ተገደሉ ማለት ወሰን የሌለው አጋኖ ነው።

ቀደም ሲል እንዳነበብነው የወሎው ንጉስ ሚካኤል መሐመድ ዓሊ ይባሉ በነበረበት ወቅት አጼ ምኒልክን በተደጋጋሚ እየከዱ ሲዋጉዋቸው ምኒልክም በተደጋጋሚ እየማረኩ ምህረት አድርገውላቸዋል። መጨረሻ ላይ እንዳውም ልጃቸውን ሸዋረጋን ድረውላቸው ሊያለሰልሉአቸው እና መልካም ግንኙነት ሊፈጥሩ ችለዋል። በዚህ በምኒልክ ትዕግስት የተነሳ ነው ልጅ ኢያሱ ከመሐመድ ዓሊ አብራክ ሊወለዱ የቻሉት። የከፋው ንጉሥ ብቻ ናቸው ከምኒልክ ደግነት ተቋዳሽ ለመሆን ያልታደሉት። እሳቸውን እና ንጉሰ ጦናን በተመለከተ ቀጥሎ ተጨማሪ ነጥቦች አቀርባለሁ።

የከፋውን ንጉሥ ጋኪ ሼሮቾን በተመለከተ፣ እውቅና እንዲሰጧቸው እና በንጉሥነታቸው ግዛታቸውን ማስተዳደር እንዲቀጥሉ ምኒልክ ተማጸኗቸው። ጋኪ ሼሮቾ ግን ለመዋጋት ወሰኑና በመማረካቸው በሰንሰለት ታስረው ወደ አዲስ አበባ ተወሰዱ። መሬታቸውም ለምኒልክ ወታደሮች ተሰጠ።

ምንም እንኳ አጼዎቹ በማዕከላዊ ደረጃ ፍፁማዊ ሥልጣን ቢኖራቸውም በሰራቸው ያሉ ንጉሶች ግን ክልሎቻቸውን በነፃነት እንዲያስተዳድሩ የሚፈቅድ እንደ ፌዴራላዊ ዓይነት ሥርዓት ነበራቸው። ይኸውም ቋንቋን መሰረት ካደረገው ከዛሬው የስም ፌዴራሲዘም በጣም የተሻለ ነበር። ንጉሶቹ በየግዞቶቻቸው ውስጥ ሙሉ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ነበራቸው። በግዛታቸው ውስጥ በሰፈረው የአጼው ሠራዊት ላይ እንኳ ሥልጣን ነበራቸው። የንጉሠ-ነገሥቱ ሠራዊት በየሰፈረበት ክልል መሬት እንጂ በንጉሦቹ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት የፖለቲካ ሥልጣን አልነበረውም። ይህ ባይሆን ኖሮ ግጭት መከሰቱ አይቀርም ነበር። እውነተኛው ሥልጣን ዝቅ ሲል በየክልሎቹ ንጉሦች ከፍ ሲል ደግሞ በንጉሠ-ነገሥቱ እጅ ነበር። አጠቃላይ ግዛቱን በሚመለከት ጉዳይ ላይ መወሰን የሚችለው አጼው ነበር። በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ሁሉም ዜጎች የንጉሠ-ነገሥቱ ዜጎች ነበሩ። በንጉሦቻቸው ፍትሕ ተጓድሎብናል በደል

ተፈጽሞብናል ብለው ሲያስቡ በማናቸውም ጊዜ ንጉሠ-ነገሥቱ ዘንድ ቀርበው አቤት የማለት መብት ነበራቸው። በአማራም ሆነ በኦሮሞ ክልሎች ውስጥ የሰፈረ የንጉሠ-ነገሥቱ ወታደር በክፊል የክልሱ ንጉሥ አገልጋይም ነበር። አንዳንድ ጊዜ ንጉሡ ጠቃሚ መስሎ ከታየው የራሱንም ወታደሮች ከንጉሠ-ነገሥቱ ወታደሮች ጋር ይቀላቅል ነበር። ስለዚህ በክልል የሰፈሩትን የንጉሠ-ነገሥቱን ወታደሮች የክልሉ ንጉሥ የሚቆጥራቸው ሙሉ በሙሉ እንደ ወታደሮቹ አድርጎ እንጂ እንደ ፖስቲካ ሃይሎች አድርጎ አልነበረም።

ስዚህ ነው አማሮችም ሆኑ ኦሮሞዎች የንጉሠ-ነገሥቱን ወታደሮች የኢትዮጵያ ገዢዎች ነበሩ የማንለው። አጼዎቹ በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ስር ይሁኑ ወይም በዛጉዌው፣ ሀቁ ይኸው ነው፤-- ወታደሮቻቸው የነሱ አገልጋዮች እንጂ የኢትዮጵያ ገዢዎች አልነበሩም። ከላይ እንደተጠቀሰው በሰሰሞናዊውም ሆነ በዛጉዌው ሥርወ-መንግሥታት ፍጹማዊው ሥልጣን የተያዘው በራሳቸው በንጉሠ-ነገሥታቱ እና በንግሥተ-ነገሥታቱ ነበር። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወታደሮች እና የጦር አበጋዞች ያልተገደበ ሥልጣን ይዘው ክፊል ኢትዮጵያን የመሩበት ብቸኛው ጊዜ የሴሩ ዓንጉል ልጆች የነበሩት የየጁ ኦሮሞዎች ከትልቁ ራስ ዓሊ እስከ ትንሹ ራስ ዓሊ ድረስ አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥታት በዙፋኑ ላይ ስሰሙ እያስቀመጡ እነሱ ባስሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ነን እያሉ ፈላጭ ቆራጭ የሆኑበት ወቅት ብቻ ነው። ዘውድ እየደፉ በስስሞናዊው ዙፋን ላይ ራሳቸው ስመቀመጥ ያልደፈሩበት ምክንያት ከስስሞናዊው ሥርወ መንግሥት ጋር የሥጋ ዝምድና ስላልነበራቸው የንጉሥ ሰስሞን እና የዳዊት ልጅ ከሆነው ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር የስጋ ዝምድና የሌስው ሰው በስስሞናዊው ዙፋን ላይ ይቀመጥ ዘንድ ህጉ ስስማይፈቅድለትና ሕዝብ ስስማይቀበስው አመጽ ይነሳብናል ብለው ይፈሩ ስስነበረ ነው።

በርግጥ ከፍተኞቹ የጦር አበጋዞች አንዳንድ ክልሎችን አልገዙም ማስት አይደስም። የእስት ጉርሳቸውን የሚያገኙት በዚህ መልክ ስስነበረ እንደ ማዕረጋቸው ተዋረድ ስየራሳቸው ግዛት እየያዙ አስተዳድረዋል፤ ገዝተዋል። ዝቅተኞቹ "ባላምባራስ" ሲባሉ ከፍተኞቹ "ራስ" ይባሉ ነበር። ከ"ራስ" በላይ ያለው "ንጉሥ" ሲሆን ከንጉሡ በላይ ደግሞ "ንጉሠ-ነገሥቱ"/ "አጼው"/ ነበር። የግዛታቸው መጠን እንደ ማዕረጋቸው ይስያያል። ከንጉሡ ቀጥሎ ስፋፊውን ግዛት ራሶቹ

ይይዛሉ፡፡ እነዚህ አገሬ-ገዢ የሚሆኑት ባላባቶች በሙሉ የጦር አለቆች የነበሩ ናቸው፡፡ በአውሮጳ ግን መሳፍንቱ እንደ ኢትዮጵያው የግድ ክጦር አበጋዞች መደብ አልነበሩም፡፡ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ አጼያዊ አስተዳደር ወታደራዊ ስርዐት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ከባላምባራስ እስከ ራስ ባለው መካከል ወደ ላይ ስንዘረዝር ግራዝማች፣ ቀኛዝማች፣ ፊታውራሪ እና ደጃዝማች የሚሉ ማዕረጎች ነበሩ፡፡ ሁሉም ለንጉሡ ታዛዦች ናቸው፡፡ የየክልሉ ንጉሦች ደግሞ ተጠሪነታቸው ለማዕከላዊው ንጉሠ-ነገሥት ነበር፡፡ ንጉሡ ራሶችን ጨምሮ ከሱ በታች ያሉትን ሹማምንት የመሾም ስልጣን ነበረው፡፡ የጦር አበጋዞቹ የሚሾሙት በንጉሠ-ነገሥቱ ቢሆንም ከክልሉ ንጉሥ ጋር መተባበር ግዴታቸው ነበር፡፡ ለምና ወርቅ ሆነው ነበር የሚሰሩት፡፡ አንዳንዶቹ እንዲያውም እስከ መዋሃድ ይደርሱ ነበር፡፡ ባመዛኙ የክልሉን ንጉሥ ነበር የሚያገለግሉት፡፡ በርግጥም ንጉሠ-ነገሥታቱ ማሀል አገር ተቀምጠው የአንድነት ኃይል በመሆን ሲያገለግሉ በነሱ ሥር የነበሩ ንጉሦች ደግሞ በየክልሎቻቸው ህዝቦቻቸውን ያስተዳድሩ ነበር፡፡ ይህ ሥርዓት በኢትዮጵያ ውስጥ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ነው፡፡ ለምሳሌ ክ3900 ዓመት በፊት "ሞረሽ" በመባል ይገዛ የነበረው የኢትዮጵ የልጅ-ልጅ-ልጅ የሆነው "ሳቢ" በ45 አገሮች ላይ ያነገሳቸው 21 ንጉሦች ነበሩት ፡፡(3) ከ 3330 ዓመት በፊት እንደ ልዕለ-ሰብ/Super Man/ ይታይ የነበረው አጼ እስያኤል ደግሞ በስሩ 49 ንጉሦች ነበሩት፡፡ ታማኝነታቸውን ለመፈተንና ግንኙነታቸውን ለማደስ አሰበና በኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሥር የነበሩትን ሁሉንም ንጉሦች ወደ ዋና ከተማው ወደ ሱባ እንዲመጡ ጠራቸው፡፡ ጥሪውን አክብረው የመጡትን እንደገና እያነገሠ ሲሸልማቸው ያልመጡትን ግን እየቀጣ በሌሎች ንጉሦች ተክቷቸዋል፡፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከእስያ፣ ከግብጽ፣ ከሰሜን አፍሪቃ፣ እና ከአረቢያ ጭምር ወደ 49 ንጉሶች ሥጦታ እየያዙ መጥተዋል፡፡ በአባይ ወንዝ ውሀ እንዲለቃለቁ አድርጎ ራሱ አጼ እስያኤል ካነገሳቸው በኋላ ውድ ስጦታዎችን ሸልሟቸዋል (4) ፡፡ ኢትያኤል(ንግሥት ሳባ)፣ ልጇ ቀዳማዊ ምኒልክ፤ የሱ ልጅ ቶማይ ፣ የሱም ልጅ ዘግዱር፣ የዘግዱርም ልጅ አክሱማይት እና ሁሉም የአክሱማይት ተወላጅ ነገሥታት ከሜሶፖታሚያ ድረስ ግብር የሚያመጡላቸው ንጉሦች በስራቸው ነበሯቸው፡፡ በ13ኛው ክፍለ-ዘመን ይኩኖ አምላክ ሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት እንደገና ሲመሰርት እንኳ ከኢትዮጵያ ውስጥ ታማኝነታቸውን የገለጹለት 10 ንጉሦች

ነበሩ። እነሱም የጎጃም ንጉሥ፣ ባህረ-ነጋሽ፣ የዳሞት ንጉሥ፣ የኪንዶ ንጉሥ፣ የዘይላ ንጉሥ፣ የላስታ ንጉሥ፣ የእናርያ ንጉሥ፣ የአዳል ንጉሥ፣ የናግራን(የመን) ንጉሥ፣ እና የትግሬ ንጉሥ ነበሩ።(5)

በአጼ ቴዎድሮስ ጊዜ ግን ሲናቁ የማይችሉ አንድ ንጉሥ ብቻ ነበሩ፤ የሸዋ ንጉሥ እና የዳግማዊ አጼ ምኒልክ አባት የሆኑት ንጉሥ ሃይለ-መለኮት። አጼ ቴዎድሮስ ሳይወጉዋቸው ቀደም ብሎ በልብ ድካም አርፈዋል።ንጉሥ ተክለ-ሃይማኖት ሲያርፉ አጼ ቴዎድሮስ ክልብ አዝነው ልጃቸውን ምኒልክን እንደ ልጃቸው አድርገው ለማሳደግ ወሰዱት። ወደፊት ምኒልክ ጥሩ እድል እንደሚኖረው በደንብ የተገነዘቡት አጼ ቴዎድሮስ ልጃቸውን አልጣሽን ዳሩለት። በኋላ ምኒሊክ ከቴዎድሮስ አምልጠው ራሳቸውን "የአቢሲኒያና የጋላ ንጉሥ" በማለት ለይመው እስከነገሡበት ጊዜ ድረስ ንጉሥ አልነበረም። "ጋላ" የሚለው ቃል በወቅቱ የጠቢብነት መጠሪያ እንደነበር ከዚህ በፊት ጠቁሜአለሁ። ምኒልክ ከመቅደላ አምባ ማምለጡ ሲነገራቸው ቴዎድሮስ መጀመሪያ የጠየቁት ጥያቄ "አልጣሽን ይዟት ሄዷል?" የሚል ነበር። ቴዎድሮስ ይህን የጠየቁት ምኒልክ እንደሚነግሥና መልካምጊዜ እንደሚኖረው ስለሚያውቁ ለልጃቸው የወደፊት አጣ-ፈንታ ደጉን በማሰብ ነበር። አጼ ቴዎድሮስ በሞቱም ጊዜ ምኒልክ ተንሰቅስቀው አልቀሰዋል፣-- ተንከባክበው የአሳደጉዋቸው አባታቸው ነበሩና።

በአጼ ዮሃንስ 4ኛ ጊዜም አፄ ዮሃንስን የሚያስጉዋቸው ንጉሦች ሁለት ብቻ ነበሩ፤ የጎጃሙ ንጉሥ ተክለ-ሃይማኖት እና የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ። ራስ አዳልን ንጉሥ ተክለ-ሃይማኖት ብለው ያነገሷቸው አጼ ዮሐንስ ሲሆኑ ምኒልክ የነገሠው ግን በገዛ ራሱ ጠመንጃ ነበር።

ኃይለሥላሴ እንደ ንጉሠ-ነገሥት ቢገዙም በዘመናቸው ንጉሥ አልነበረም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክሊሉ ህብተወልድ ሥልጣን አልባ እስከሚሆኑ ድረስ ኃይለሥላሴ እያንዳንዷን ቅንጣት የመንግሥት ሥልጣን ይቆጣጠሯት ነበር። አክሊሉ ህብተወልድ መንግሥትን በሚመለከት ሁነኛ ውሳኔ ሲሰጡ ቀርቶ በውጪ አገር እና ባገር ውስጥም እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር መንቀሳቀስ አይችሉም ነበር። ለኢትዮጵያ ነፃነት እና ደህንነት እውቀትና ችሎታቸውን መሰዋዕት

ያደረጉ እኚያ ብልህ ሰው በኃይለሥላሴ ተጨቁነው ነበር የኖሩት። ካለ ጥሩ ነገራቸው ኃይለሥላሴ የማይረካ የሥልጣን ጥማት ነበራቸው። ወደ ተነሳንበት ርዕሰ-ጉዳይ እንመለስ።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ላለፉት አራት ሺ አምስት መቶ ዓመታት ያስተዳደሯትን አራት ሥርወ-መንግስሥታትን ታውቃለች። የመጀመሪያው ኩሻዊ-ሥርወ-መንግሥት፣ ሁለተኛው የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት፣ ሶስተኛው ሰለሞናዊ ሥርወ-መንግሥት እና አራተኛው የዛጉዬ ሥርወ-መንግሥት ይባላሉ። አማራ እንደ ዘር እና ጎሳ የተከሰተው የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት ከተቋቋመ ከ 400 ዐመታት ጀምሮ ስለነበር ኩሻዊ ሥርወ-መንግሥትን አልደረሰበትም። እሱ የደረሰበትን ሌሎቹን ሶስቱን ግን እያነሳሁ አማራ እንደ ሥርወ-መንግሥት መግዛት አለመግዛቱን እመረምራለሁ።

ከአራት ሺ አምስት መቶ ዓመት በፊት እንደ ንጉሥ ሆኖ ኢትዮጵያን ያስ ዘውድ የገዛ አንድ መሪ እንደ ነበር የተመዘገበ መረጃ አለ። ኩሻዊ ነው። ዝዮን /Zeyon/ ይባላል። ጥቂት ጊዜ መራና ሞተ። ኤባል/Ebal/ የተባለ ሰው ተካውና ንጉሥ ተብሎ ዘውድ ጫነ። ስመ-መንግሥቱ ሰበታህ/Sebtah/ ይባል ነበር። ዛሬ ኢትዮጵያውያን ተብለው ለሚጠሩት ኩሻውያን የመጀመሪያው ንጉሥ እንደሆነ ይገመታል። ለሰላሳ ዓመታት (2545-2515 B.C. ዐመተ ዐለም) ገዝቷል። ኩሻዊ ሥርዎ-መንግሥትን የመሰረተው እሱ ነው። (6)

ይህ ሥርወ-መንግሥት ለአምስት መቶ ዓመታት ያህል ገዛና በኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት ተተካ። የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት ከተመሰረተ ከአራት መቶ ዓመታት በኋላ አማሮች መታየት ጀመሩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሥልጣን ላይ የወጡ ነገሥታትንና ንግሥታትን ቀጥሎ እዘረዝራለሁ። በዚያውም ከመካከላቸው አማራ መኖር አለመኖሩን እንፈትሻለን።

ቀጥሎ የተዘረዘሩት የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥትን ለአንድ ሺ ዓመት የወከሉ ነገሥታት እና ንግሥታት ናቸው።

| የንጉሡ/ንግሥትዋ/ ስም | ዘመነ ንግሥና/በዓመት/ |
|---|---|
| ኢትዮጵ | 98 |
| አቲባ | 49 |
| አዜብ | 32 |
| ሞሪ-ስቢ | 77 |
| ልብና | 44 |
| መሊክ-መሰክ | 24 |
| ጋዝያ | 48 |
| አድያም | 83 |
| ታንዛን | 88 |
| የቶር-አብ /የሙሴ አማት/22 | 22 |
| አባ-ብሔር (የሱ ልጅ) | 10 |
| ኢትዮጵስ | 10 |
| ኤልካኖ | 25 |
| አጼ/እሴ/ | 10 |
| ታምሪያ | 10 |
| ሸምያ | 10 |
| አክናሁስ | 10 |
| ኩሳዮጺ | 10 |
| ቦኑ-ሰንካ | 10 |
| አሚን | 10 |
| አሪፌሪ | 10 |
| ዮጺዮሪ | 10 |
| አሞር | 10 |
| ብሌና (ንግሥት) | 10 |

| | |
|---|---|
| ዘግዱር | 10 |
| ሂርሂተር | 10 |
| እንጋቦ | 10 |
| አጋቦስ | 130 |
| ኩርፋን | 55 |
| ሰርፊ | 82 |
| አኪሳ | 80 |
| ጵርስቅላ (ንግሥት) | 40 |
| አቅጃቦ | 50 |
| አጋቦና (የንግሥተሳባ እያት) | 16 |
| ኢትያኤል (ማክዳ፣ንግሥተ ሳባ) | 51 |

‹‹አጼ›› ወይም ‹‹እሴ›› ስመ-ክህነቱ ‹‹እስያኤል›› የተባለው ልእለ-ሰብእ ንጉሠነገሥት 480 ዓመት በህይወት ኖረ ሲባል ያሥገርም ይሆናል። የሰው ዘር መነሻ የሆነውን አዳምን ጨምሮ አንዳንድ ሰዎች እስከ 930 አመት ድረስ በሕይወት እንደኖሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። መጀመሪያ ወጣት ሳለ አጼ ወይም እሴ ተብሎ በሳባ ከተማ ራሱ ባወጣውና ባከበረው ደንብ መሰረት ለ10 ዓመት ብቻ መራና ሥልጣኑን ለቀቀ። የእድሜ ባለ ጸጋ በመሆኑ ምክንያት ከ130 ዓመት በኋላ መጣና አጋቦስ ተብሎ እንደገና ሥልጣን ያዘ። እናትዋ ልዕልት እዝሚና ከሰዋ ጋር ለእሴ ይዘምርለት ከነበረው ጃንደርባ ተራ ሰው በሚስጥር ፀንሳ ኢትያኤልን (ንግሥተ ሳባን) በመውለድዋ ተደፈርኩ ብሎ ወላጆችዋን ገድሎ ስለነበር ኢትያኤል በሽምግልናው በበቀል እስከገደለቸውና በዙፋኑ እስከተቀመጠች ድረስ ስልጣኑን እየለቀቀ እና መልሶ እየያዘ ብዙ ዐመታት ኖሮአል። እዚህ ላይ ምናልባት የዘመን መፋለስ ያለ ቢመስለን እሴ ወይም አጼ እድሜው ብዙ በመሆኑና ሥልጣኑን እየለቀቀ እና መልሶ እየያዘ በመግዛቱ ምክንያት መሆኑን መገንዘብ ይገባል። በቀረበው ዝርዝር ላይ "አጋቦስ" ከሚለው ስም በታች የተጠቀሱት በሱባ ከተማ ላይ የተፈራረቁ ንጉሶች ሲሆኑ እሱ ግን በበላያቸው ንጉሠ-ነገሥት ነበር። ለምሳሌ በዝርዝሩ ላይ ስሙ

ከኢትያኤል በላይ የሚገኘው፣ የኢትያኤል አያት አጋቦና የሳባ ከተማ ንጉስ ሲሆን እስያኤል ግን የመላው የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ነበር። ልጁ አዝሚና በቤተ-መንግሥት ውስጥ ከዝቅተኛ ሰው ጋር ዝሙት ፈጽማ ስለተገኘች መገደልዋን ለመበቀል የልጅ ልጁ ኤትያኤል እሴን እንድትገድል ያገዛት አጋቦና ሲሆን የኢትዮጵያ ህዝብ የኢትያኤልን ወደ ሥልጣን መምጣት በተቃወመ ጊዜም ጦሩን አሰልፎ የተዋጋላት እና ሥልጣን እንድትይዝ የረዳትም ይኸው አያትዋ አጋቦና ነበር። አባትዋ ትንሽ ሰው ስለነበር ትጠራ የነበረውም በዚሁ የሳባ ከተማ ንጉሥ በነበረው አያትዋ በ አጋቦና፣ ኢትያኤል አጋቦና ተብላ ነበር። የአያትዋን ግዛት ሳባን በሁዋላ በመውረስዋ ምክንያት ነበር የሳባ ንግሥት (ንግሥተ-ሳባ) ወይም ሳባ የተባለችው እንጂ እናትዋ አዝሚና ከመገደልዋ በፊት ያወጣችላት ስም ኢትያኤል ነበር። ትርጉሙም በጥንቱ ሱባ ቋንቋችን እግዜር ሰጠኝ ማለት ነው። "ያ" የሚለው ፊደል የእንስትነትን ፆታ ሲያመለክት ኢትኤል ከተባለ ግን የተባእትን ፆታ ይጠቁማል። ለአባታችን ለኢትዮጵ ገናናው አባቱ የሳሴም ንጉሥ ያወጣለት ስም ኢትኤል (እግዜርሰጠኝ ነበር)። በእግዚአብሄር ትዕዛዝ ከአየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ (ያኔ ምድረ-ኩሽ ነበር የሚባለው) ተጉዞ አባይ ወንዝ እናት ጎጃም ላይ በሰፈረ ጊዜ ግን ወደፊት መሲሁ ሲወለድ ልጆቹ ወደ ቤተልሄም የሚወስዱለትን "ዮጵ" የተሰኘውን ቢጫ ወርቅ ስጦታ ለመጠቆም እና ለማስታወስ "ኢትዮጵ" ተባለ እንጂ። "አቴጌ" የሚለውም ንግሥተነገሥትነትን የሚያመለክተው ቃል እና ‹‹እትዬ›› ከ "ኢትያኤል" ጋር ኅብር አለው።

አማሮች ህልውናቸው የጀመረው የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት ከተመሰረተ ከአራት መቶ ዐመት በኋላ ነው። አንዳንዶቹ ንጉሦችና ንግሥቶች የአማራ ስም ቢይዙም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዳቸውም አማራ አልነበሩም። የአማራ ሥርወ-መንግሥት ብሎ የገዛም ሰው አልነበረም። የኢትዮጵ ዝርያዎች ለየትኛውም ነገድ ወገናዊነት ሳይኖራቸው በኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት ስር ለአንድ ሺ ዓመታት አስተዳደሩ። ይኸውም የኢትያኤል(የንግሥት ሳባ) እና የንጉሥ ሰለሞን ልጅ ቀዳማዊ ምኒልክ ሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት እስከመሰረተበት ጊዜ ድረስ ነው። ይህንን ሥርወ-መንግሥት መርምረን በሱ ውስጥ አማራው የነበረውን ሚና እንይ፤

ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ እና ስለዙፋኑ ዳራ ጥቂት ብርሃን መፈንጠቅ ታላቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት የሁሉም ኢትዮጵያውያን አባት ኢትኤል ወይም ኢትዮጵ፣ ከኢየሩሳሌም ወደ ዛሬዋ ኢትዮጵያ ሲመጣ ተልዕኮ ይዞ ነው የመጣው። በጥንቱ የሳባ ቋንቋ ‹‹ኢት›› ማለት ‹‹ስጦታ›› ማለት ሲሆን ‹‹ኤል›› ደግሞ እግዚአብሔር ተብሎ ተተርጉሟል። ልክ ‹‹ዳን-ኤል›› ወይም ‹‹ገብር-ኤል›› ሳይ እንዳስው ማስት ነው።

የኢትኤል ተልዕኮ ወደፊት ኢትዮጵያ ላይ የሚወለዱትን ልጆቹን ለአንድ የተቀደሰና መለኮታዊ ተግባር ማዘጋጀት ነበር። ተግባሩም፥ የኢትዮጵያ ምርጥ ምርት የሆኑትን፥ ‹‹ዮጵ›› የተባለውን ልዩ ቢጫ ወርቅ፣ ከርቤ እና አጣን ለሰላሙ ንጉሥ ለእየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በቤተ-ልሔም ሲወለድ ገፀ-በረከት ማቅረብ ነበር። (7)

ኢትኤል በጣና ሐይቅ ደሴቶች ከሰፈረ በኋላ ‹‹ኢት-ዮጵ›› እየተባለ መጠራት ጀመረ። ኩሽ ትባል የነበረችው አገርም ‹‹ኢትዮጵያ›› ትባል ጀመር። በዚህም ‹‹ኢትዮጵ›› እና ‹‹ኢትዮጵያ›› ማለትም ፍችው ‹‹ለእግዚአብሔር የቢጫ ወርቅ ሥጦታ›› ማለት ነው። ስለ ኢትኤል ያልነውን ለማጠቃለል በምድር ላይ ሰው ሆኖ ሲወለድ ምልክት ይሆናቸው ዘንድ ለዝርያዎቹ በሰማይ ላይ ኮከብ እደሚያሳያቸው እና ኮከቡም ከኢትዮጵያ ግዛት እሱ ወደ ሚወለድበት ወደ ቤተ-ልሔም እየመራ እንደሚወስዳቸው እግዚአብሔር ለኢትኤል ቃል ገባለት። ከሁለት ሺ ዓመታት በኋላ እየሱስ በቤተ-ልሔም ሲወለድ ይህ ትንቢት ተፈጸመ። በዚያን ወቅት የኢትዮጵ ዝርያዎች የሆኑ በርካታ ነገዶችን የሚወክሉ አሥራ ሁለት ንጉሦች በኢትዮጵያ ግዛቶች ላይ ነግሰው ነበር። መቀመጫውን አክሱም ያደረገው ባዚን ንጉሠ-ነገሥት በነበረበት ወቅት በትንቢቱ ሲጠበቅ የነበረው ኮከብ በኢትዮጵያ ሃገሮች ላይ ታየ። የኢትኤል ወይም የኢትዮጵ ዝርያዎች የነበሩት አሥራ ሁለቱ የኢትዮጵያ ንጉሦች በኮከቡ እየተመሩ ወደ ቤተ-ልሔም ተጉዘው ለሕጻኑ እየሱስ ለግደው ይጠብቀው የነበረውን የኢትዮጵያን ምርጥ ምርት ቢጫውን ወርቅ፣ ከርቤውንና አጣኑን አበረከቱለት።

ኢትዮጵ እና ዝርያዎቹ ስለ ኮከቡ የተነገረውን ትንቢት ስለሚያውቁ የሚከሰትበትን ጊዜ በታላቅ ጉጉትና ትጋት ይጠባበቁ ነበር። የኢትዮጵ ልጅና የኦሮሞና የአማራ ቅድመ-አያት የሆነው ነቢዩ ደሸት/ደሴት/

እየሱስ ከመወለዱ ከ 1400 ዐምታት በፊት፣ ከእለታት አንድ ቀን የአባይ ወንዝ መነሻን እያየ ሲቆዝም ተመስጦ ውስጥ ገባና ኮከቡን፣ ሕጻኑን እየሱስንና እናቱን ማርያምን አንድ ላይ ምስሎቻቸውን በውሃው አረፋ ላይ አያቸው። ያየውንም በወርቅና ብር ሰሌዳ ላይ ሳለው። ስዕሉንም ከሱ በኋላ ለልጆቹ አስተላለፈው። ይህ ራዕይ ስለኮከቡ የነበረውን ትንቢት አጠናከረው። የደሸት ዝርያዎች የእየሱስን መወለድ ለማስብ የኮከቡን ምስል በየዘውዶቻቸው፥ በየዙፋናቸው፥ በየ ሰንደቅ-ዐላማቸው ዘንግ ራስ ላይ እና በየበትረ-መንግሥቶቻቸው ላይ ያስቀርፁ ነበር።

የዚህ መጽሐፍ ደራሲ እስከሚያውቀው ድረስ በምድረ-ገፅ ላይ ተወዳዳሪ ጨርሶ ያልነበረው እጅግ ታላቁ ንጉሠ-ነገሥት እስያኤል /አጼ/እሴ/ የኢትዮጵ ሥርው-መንግስት የመጨረሻው ንጉሠ-ነገሥት ነው። አጼ /እሴ/ም የመሲሁን መወለድ የሚያመለክተውን ኮከብ ቅርፅ ራሱ በፈለሰፈው፥ እስከ ዛሬም በአለው ሰንደቅ-ዐላማ ዘንግ እራሱ፥ እንዲሁም በዘውዱ፥ በዙፋኑ፥ እና በበትረ-መንግሥቱ እናት ላይ አኑሮት ነበር። ይህ ትልቅ ንጉሠ ነገሥት ከሶስት ሺ ዓመት በፊት ነበር እጅግ ረጅም ዕድሜ ጠግቦ መኖር ስልችቶት እንዲሞት እግዚአብሄርን ለምኖ በኢትያኤል (በሁዋላ ማከዳ በተባለችው) ተገድሎ ይህችን ዐለም የለቀቀው። ‹‹ማክዳ›› (የከዳ) ማለትም ‹‹ከሃዲ›› የተባለችው የገዛ ወገኖቿን የራያና አዘቦ ጎሳዎችን ከድታ የያዕቆብ ዘር ነን የሚሉትን እስራኤላውያንን እና አግአዚያንን የውጪ ዜጎችን ወደ ኢትዮጵያ ካመጣውና በሥርወ-መንግሥቱ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ከሾማቸው ልጇ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ወግና በመውጋትዋ ነው። በነገራችን ላይ በተለምዶ እንደሚባለው እሷን ‹‹ሳባ›› ወይም ‹‹አዜብ›› ብሎ መጥራት ስህተት ነው። ምክንያቱም ሁለቱም ቃላት የሚነገሩት ለተባዕታይ ጾታ ሲሆን የሚወከሉትም በአጼ እና በአንድ ነገድ የተመሰረተን አንድ ከተማ ነው። ሴትን ልጅ ‹‹ማከዳ›› ማለትማ ጭራሽ የባሰ ስህተት ነው። እላይ የተባለውን ለመድገም ወይም ለማብራራት ያህል፥ ‹‹አጼ›› የሚለው ሥያሜ አጼን ወይም እሴን ለማስታወስ በእክሱማይት ንጉሠ-ነገሥት ለታላላቅ ነገሥታት በይፋ የሚሰጥ የማዕረግ ስም እንደነበረ ሁሉ ‹‹ኢትዮ-፥ እቴጌ›› ወይም ‹‹እትዬ›› ከ‹‹ኢትያ-ኤል›› የተወሰደ ለታላላቅ ንግሥታት የሚሰጥ የማዕረግ ስም ሆኖአል። (8)

ልጃገረዲቱ ኢትያኤል ስለምን ሽማግሌውን አጼን እንደገደለችው ለማብራራት ያህል፣ የአጼ የሩቅ ዘመድ እንደነበረች መግለጽ ያሻል። ታሪኩ እንደዚህ ነው። ለኢትያኤል አዝሚና የተባለች ልዕልት እናት ነበራት። አዝሚና ድምጺ-መረዋ ስለ ነበረች ከሌሎች ወጣት መዘምራን ጋራ ሆና በዘማሪነት አጼን ታገለግለው ነበር። ሙቺ ሲላት አብሮአት ይዘምር ከነበረ ከአንድ ጃንደረባ ጋር ፍቅር ይዞአት እየተሻሹ ሲፈጋፈጉ ዘሩ በአፈ-ማህፀንዋ ዘልቆ ኢትያኤል ተፀነሰች ። (9) በዚህ ምክንያት፥ አዝሚና ከጃንደረባ ጋር የዝሙት ተግባር ፈጽማ በቤተ-መንግሥቱ ውስጥ ውርደት አምጥታለች ተብሎ በአጼ እስያኤል የቁጣ ትዕዛዝ የኢትያኤል እናት አዝሚና፥ አባትዋ እና ህፃኒቱ ራስዋ ኢትያኤል ጭምር ይገደሉ ብሎ አጼ አዘዘ። ህፃኒቱን ኢትያኤልንም እንዲገሉ የታዘዙት ሰዎች የእናትዋ ጎሳዎች፥ የአዘቦ ሰዎች በመሆናቸው፥ ሌላ ህፃን ሰርቀው አምጥተው በእስዋ ቦታ ተከተው እስዋን የሳባ ንጉሥ ለነበረው ለአያትዋ ለ አጋቦና አስረከብዋት። አያትዋም አዬው እንዳያውቅ አድርጎ በምስጢር አሳደጋት። እንደ እናትዋ እንደ አዝሚና ድምፅ-መረዋ በመሆንዋም የ 15 ዐመት ልጅ በሆነች ጊዜ እስዋም የአፄ ዘማሪ ሆነችና ወድዶአት እስዋ ብቻ ታገልግለኝ አለ። አንድ ቀን በሽምግልናው ደክሞት ዙፋኑ ላይ ሸለብ አድርጎት ሳለ ገድላው ተበቅላው ከብዙ ረብሻ በሁዋላ በአባትዋ እርዳታ እና በአዘቦ ወገኖችዋ ድጋፍ እራስዋ ነገሠች። በአያትዋና በእናትዋ በኩል ከኢትዮጵ የወረደች የነገሥታት ዘር ስለሆነች በመጨረሻ የኢትዮጵያ ህዝብ እያንገራገረም ቢሆን ንግሥትነትዋን ተቀበለው። ይህን ጉዳይ በ እንግሊዝኛ ቋንቋ ***«ድብቁና ያልተነገረው የአይሁድ ሕዝብ እና የኢትዮጵያውያን ታሪክ»*** በተሰኘው መጽሐፌ ላይ ዘርዝሬዋለሁ። ረጅሙን ታሪክ ባጭር ለማስቀመጥ ኢትያኤል በቂም በቀል አጼን ከገደለች በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረው ግብታዊ አመጽ እና ሁካታ ሳያግዳት ዙፋኑን ወረሰች።

ሕስያ / ለሚባለው አህጉር ስሙን ያወረሰው፣ የኢትዮጵ እና የነቢዩ ደሸት ተወላጅ፣ ንጉሠ-ነገሥት አጼ (ስሙ-ክህነቱ እስያኤል) 480 ዓመት በህይወት ኖሯል ይባላል። ይህን ያህል ረጂም ዘመን በሕይወት በመኖር ከኢትዮጵያም ሆነ ከዓለም የመጀመሪያው ንጉሠ-ነገሥት ነው። ልዩ ችሎታ የነበረው ሳይንቲስትም ነበር። አዝዕርትንና አፅዋትን እንዲሁም እንስሳትን እያዳቀለና አዳዲስ አፅዋትንና የእንስሳት

ዝርያዎችን እያስገኘ በቤተ-መንግሥቱ ያኖር የነበረ የመጀመሪያው በራሂ-ጂ'ን/ዘረ-መል/ መሐንዲስ (Genetic Engineer) ነበር። በሰው በራሂ-ጅን እና DNA ላይም ምርምር ያደርግ ስለ ነበር ኢትዮጵያውያንን ከእስያውያን፣ ከአረቦች እና ከመካከለኛው ምሥራቅ ምርኮኞቹ ጋር እያጋባ ኢትዮጵያውያን ቅይጥይጥ የቆዳ ቀለም፣ የተለያዩ የነገድ አካላዊና ባሕላዊ ቅርፀ-መልክ እንዲኖረን አስችሏል።

ከሁሉም በላይ፣ በፊት እንደ አልኩት፣ ምናልባት በዓለም የመጀመሪያ የሆነችውን የኢትዮጵያ'ን ሰንደቅ-ዐላማ ከዛሬ 3300 ዓመት በፊት የፈጠረና ነገሥታት እና ልዑላን በየህንፃዎቻቸው እና በየሰረገላዎቻቸው ላይ እንዲያውለበልቧት ያወጀ ነው። ዛሬ "እስያ" እያልን የምንጠራውን እሕጉርም በጦር ኃይል አንበርክኮና አስገብሮ ‹‹እስያ›› ብሎ በሰሙ ሰይሞታል። ነገሥታት እና ንግሥታትም ባንድ ጊዜ ለአስር ዓመት ብቻ እንዲገዙ በሕግ ደንግጓል። ለዚህ ነው ከላይ በቀረበው ሰሌዳ ላይ ራሱን ጨምሮ አሥራ-አራት ነገሥታት እና አንዲት ንግሥት ለአሥር ዓመት ብቻ ነግሠው የምናየው። በሁዋላ ላይ ግን 158 አመት ሲሆነው እንደገና አጼ ተብሎና ስመ-መንግስቱን አጋቦስ አሰኝቶ በመንገሥ (ለ130 አመት) መርቷል። ልዑላኑንም ንጉሶች እያለ ዐስር ዐስር ዐመት እንዲነግሡ ሾሟል።

የንጉሥ ሰለሞንን ጥበብ ካንደበቱ ለመስማት ኢትያኤል(ንግሥተ-ሳባ) ወደ ኢየሩሳሌም መጓዝዋ በደንብ ይታወቃል። በርግጥ አካሄዷ ሰንጉሥ ሰለሞን እክብሮቷን ለመግለጽም ነበር። ከዚህም በላይ፥ የኢትዮጵ እና የደሸት ዝርያዎች ለብዙ ዓመታት የሚጠብቁት መሲህ፣ የሰላሙ ንጉሥ እሱ መስሏት በቶን የሚቆጠር ሥጦታ ይዛለት ነበር የሔደችው። ሁለት ሴቶች አጅበዋት ነበር። አንዷ የአዘበ፣ የቆቦ እና የራያ ንግሥት ሣሆይ ስትሆን ሁለተኛዋ በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ግዛት የነበረው የአረቢያ ልዕልት ቢልቂስ ነበረች። ቢልቂስን አረቦች እስከ ዛሬ ድረስ ከንግሥተ-ሳባ ጋራ ያምታቱዋታል። ሣሆይ የሥጋ ዘመድዋ ስትሆን ቢልቂስ ደግሞ በእናትዋ አዜብ ከተባለች ኢትዮጵያዊ ልዕልት የተወለደች ነበረች። አባትዋ የየመን ንጉሥ ነበር። ቢልቂስ በየመን ባል አግብታ ስትኖር ከባልዋ ተጣልታ ባልዋን ገድላ ኢትዮጵያ ትኖር ነበር። አባትዋ ከሞተ በኋላ በአባትዋ ዙፋን ተተክታ አረቢያን እንድትገዛ በኢትያኤል ፍቃድ በአግአዚ ጦር ኃይል የነገሠች የተከበረች ኢትዮጵያዊት ነበረች።

ንጉሥ ሰሎሞን ከኢትያኤል ቀዳማዊ ምኒልክን፣ ከሣሆይ ደግሞ በሁዋላ ወንድሙ ምኒልክ ‹‹ዛጉዌ›› የአለውን እናቱ ሳሆይ ግን ‹‹ዜጋዬ›› ያለችውን ልጅ ወለደ። ቢልቂሲንም ወደ አረቢያ ሄዳ ንግሥት እስከሆነችበት ጊዜ ድረስ ሰሎሞን እቁባቱ አድርጎአት በኢየሩሳሌም ትኖር ነበር።(10) ቀዳማዊ ምኒልክ በ 14 ዐመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ አባቱን ጎብኝቶ የአይሁዳውያንን ስርአትን አጥንቶ እና ነገረ-ሃይማኖት ተምሮ በ 17 ዐመቱ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ የቃል ኪዳኑን የምሥክር ታቦት እና 40,000 ወንዶች ቤተ እስራኤል ወታደሮችን ከኢየሩሳሌምና ከጋዛ ይዞ መጣ። በጉዞው ላይ ኢትዮጵያውያን በተለይም ራያና አዘቦ የኢትያኤል ጎሳዎች ክፉኛ ተዋጉት። ንግሥት ኢትያኤል ለልጆዋ አግዛ እና አርባ ሺዎቹ እስራኤላውያን፣ ማለትም ቀዳማዊ ምኒልክ ‹‹ኣግኣዚ›› ብሎ የጠራቸው ከጋዛ የመጡት አይሁዳውያን እና የዮቅጣን ጎሣዎች በለስ ቀናቸውና እና ቀዳማዊ ምኒልክ በድል አድራጊነት ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ከዚያም ከኢትዮጵ ሥርዓት ውጪ፣ ራሷም ንግሥተ-ሰባ ከነገሠችበትና አያት ቅድመ-አያቶቿ ይከተሉት ከነበረው ባሕል በተለይ በአይሁድ ካህን ተቀብቶ፣ በአይሁድ ልማድ መስረት ንጉሠ-ነገሥት ተብሎ በኢትዮጵያ ላይ ነገሠ።

እንባቢው እንደሚያስታውሰው ይህ ንጉሠ-ነገሥት መጀመሪያ ያደረገው ኢትዮጵንና የዜጎቿን ወግና ልማድ ማጥፋት ነበር። የመሲሁን መወለድ የሚያበስረውን የኮከቡን ምልክት ከኢትዮጵያ ዙፋንና ከበትረ-መንግሥቱ ላይ አሽቀንጥሮ ጥሎ ‹‹የይሁዳ አንበሳ›› በሚለው ተካው። የኢትዮጵ ዝርያዎችና የሱባ ቋንቋ ጠቢባን የነበሩትን ነቢያትና ፈላስፋዎች አስቃያቸው። አንዳንዶቹ ሞቱ። የቀሩት መጽሐፎቻቸውን እየያዙ ተሰደዱ። አንዳንዶቹም ከፍርሃት የተነሳ ለመኖር ሲሉ የቀዳማዊ ምኒልክን መንግሥት ተቀላቀሉ። ቀዳማዊ ምኒልክ ጥንታዊና ብርቅዬ መጽሐፎቻቸውን አቃጠለ፤ የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥትን የሚወክለውን ማንኛውንም ነገር አወደመ። ከኢየሩሳሌም ያመጣቸውን አይሁዶች ግን በስፋፊ መሬት ስጦታ አከበራቸው፤ ንጉሦች እና ቀሳውስት እያደረገም ሾማቸው። ከጋዛ ለመጡት ጦረኞች ምስጋናውን ለመግለጽም ‹‹አግአዚ›› ብሎ ጠራቸው። ትርጉሙም ‹‹ነፃ አውጪዎች›› ማለት ነው። ከአሁን በኋላ ኢትዮጵያ ‹‹የአግአዚ መሬት ትባላለች፤ የአግአዚ መሬት መንግሥታዊ ቋንቋም ግዕዝ ነው!›› ሲል

አወጀ። የሱባ ቋንቋ በሥራ ላይ እንዳይውልም አገደ። ይህ ድርጊቱ ባጠቃላይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም ከእናቱ ነገድ ከራያና አዘቦ ሕዝብ ጋር ለየው እና አቃረነው።

ቀዳማዊ ምኒልክ የፈጸማቸው እነዚህ ጥፋቶች ህይወቱን አስከፈሉት። ገና በ39 ዓመት የጎልማሳነት ዕድሜው የራያና አዘቦ ሰዎች በረሀ ውስጥ ውሃ ተጠምቶና ተዳክሞ አገኙትና ገደሉት። ከአራት ትውልድ በኋላ የተነሳው የልጅ ልጅ ልጁ አርቀ አሳቢው ታላቁ አክሱማይት የቀዳማዊ ምኒልክን ስህተቶች ተገንዝቦ ከሱባ ቋንቋ በስተቀር የተለወጡት ነገሮች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ አደረገ። ለኢትዮጵ፣ ለእጼ እና ለደሽት ታላቅነትና ለሥርዓታቸው በይፋ እውቅና ሰጠና የመሲሁን መወለድ የሚያመለክተውን ኮከብ ምስል በጥንቱ ዘውድ እና በትረ-መንግሥት ላይ ተመልሶ እንዲሳል እና ከይሁዳ አንበሳ ምልክት ለጥቆ እንዲቀመጥ አደረገ። የዚህ ታሪክ ጸሐፊ እንደሚያምነበት ከኢትዮጵ እና ከእጼ እስያኤል ቀጥሎ ግዛቱ እስከ ሜሶፖታሚያና እስከ መካከለኛው ምሥራቅ ድረስ የተዘረጋው፣ ዓለምን ካካለለው ከዚህ ሰፊ ግዛቱ የሚጎርፍለትን አቤቱታ እየተቀበለ በሚሰጠው ፍትሐዊ ፍርድ ‹‹የዓለም እባት›› የነገሥታት እራስ ይባል የነበረው አክሱማይት የገናናዎች ገናና የነበረ እጅግ ታላቅ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ነበር። ከኢትዮጵ እና ከእጼ እስያኤል ቀጥሎ አክሱማይት ዓለም ካፈራቻቸው ሁሉ እጅግ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ንጉሠ-ነገሥት ነበር። በእውነትም እስከ ሜሶፖታሚያ እና መካከለኛው ምሥራቅ ድረስ በተንጣለለው ሰፊ ግዛቱ ባስፈነው ፍትህ እና መልካም አስተዳደር ምክንያት “የዓለም እባት” እየተባለ ይጠራ ነበር።

በዚህም ግዕዝ የእግእዚ የመንግሥት ቋንቋ ሆኖ እየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ከአንድ ሺ ዓመታት በፊት ጀምሮ አገለገለ። ኢትዮጵያ የክርስትና እምነትን ከተቀበለችበት ጊዜ ጀምሮም እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ሆኖ ቀጥሏል። ከዚህ ጋር በተያዘ መጠቀስ ያለበት ቀዳማዊ ምኒልክ ንጉሠ-ነገሥት ከሆነ በኋላ የእባቱን ልጅ ዜጋዬ ሰለሞንን ስሙን በመጠኑ ለወጥ አድርጎ ‹‹ዛጉዬ/ዛግዌ›› በማለት የዋግ፣ የላስታ፣ የራያና ቆቦ ንጉሥ አድርጎ አነገሠው። በዚህም ግማሽ ወንድሙን ታዛዡ አደረገው። ልጆቹ ጭምር ለቀዳማዊ ምኒሊክ ልጆች የበታች ሆነው ከነሱ ቀጥሎ ያለውን ሥልጣን እየያዙ ቀጠሉ።

የሚቀጥለው ሰሌዳ በቀዳማዊ ምኒልክ የተመሰረተውን የሰለሞንን ሥርወ-መንግሥት አባላት ስም ዝርዝር ይዟል። ሁሉም ንጉሦችና ንግሥታት የቀዳማዊ ምኒልክ ዝርያዎች ናቸው።

| ስም | ዘመነ ንግሥና |
|---|---|
| ቀዳማዊ ምኒልክ | 21 |
| ቶማይ | 13 |
| ዘግዱር | 41 |
| አክሱማይ (የአክሱም መስራችና ገንቢ) | 83 |
| አውሳብዮስ | 10 |
| አብራሊዮስ | 17 |
| ወረደ-ፀሓይ | 30 |
| ህንደር | 41 |
| ቲርሐቅ | 48 |
| አውስያ | 30 |
| ኤልሳልዮን (ታንታሙን) | 39 |
| ቶማጽዮን | 29 |
| ባስልዮስ | 70 |
| አውጥጥ | 42 |
| ፒያንኪሮ | 41 |
| ሰይፌ (ጃን ሸዋ) | 38 |
| ረመሓይ ረመሃይ (ደንቀዝ) | 60 |
| ሃንዲ (ዋዜባ) | 22 |
| ሶፎልያ | 51 |
| ግ እግልዑል | 49 |
| በዋውል | 70 |
| በወሪስ (ደግሓሬ) | 83 |
| መሓሲ (ኤንዛይቀሬ) | 27 |

| | |
|---|---|
| ናልክ | 47 |
| ባዚን (ኢየሱስ ሲወለድ የነበረው ንጉሥ) | 17 |
| ራስዳሺ | 22 |
| ገርላሞት (ንግሥት) | 08 |
| ሶሬን (አዜና) | 20 |
| ብልብላ (ንግሥት) | 22 |
| ክተብ (ባሕር -ሰገድ) | 24 |
| ግርማሰፌር | 60 |
| ሰርግዋይ | 40 |
| ዘርዓይ | 29 |
| ሰብዐሰገድ | 19 |
| ጽዮን-ግዛ | 22 |
| አግዱር | 19 |
| አልአሜዳ | 16 |
| ኢዛና | 40 |
| ኢካፍህ<br>አሰህ አስፍህ | 59<br>31 |
| አርፍድ | 11 |
| አምሲ | 10 |
| አልሚራስ | 12 |
| ቲዛናታዚና፥ | 10 |
| ካሌብ | 40 |
| ገብረመስቀል | 14 |
| ቆስጠንጢኖስ | 28 |

| | |
|---|---|
| ባዝጋር | 15 |
| ፍሬሁ | 23 |
| አድርእዝ | 20 |
| አክሰውድም (አርማሕ) | 08 |
| ግርማአስፈሪ (አል-ባሀር ነጋሽ) | 15 |
| ዝርጋዝ (ጻን አስፋሕ) | 10 |
| ድግና | 26 |
| ባህረኤክሳ | 19 |
| ጉም | 24 |
| አስጎምጉም | 05 |
| ልትም | 16 |
| ተሳተም | 21 |
| አድጉሺ | 13 |
| አይዙር | 6 ሰዓት(ያሳዝናል-በነገስበት ዕለት ሊያየው የሚጋፋው ህዝብ እንዳይከለከል በማድረጉ ተረጋግጦ ህይወቱ እንዳለፈ ተጽፏል። |
| ድ ድድም | 05 |
| - ውድድም<br>ውድምአስፈሬ | 10<br>30 |
| አርማሕ | 05 |
| ደንግዣን | 19 |
| ግደዝን (ሕዝበናኝ) | 09 |

| | |
|---|---|
| ውድም፥ አንበሳ-ሰገድ) | 20 |
| ድልነአድ | 20 በዮዲት ተሰዶ አልነገሠም። ወደ ሸዋ ሸሸ። |

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ የተዘረዘሩት ሁሉም ንጉሦችና ንግሥቶች የሰለሞናዊውን ስርወ-መንግሥት ይወክላሉ። ምንም እንኳ አንዳንዶቹ የአማራ ስም እና ስመ-መንግሥት ቢኖራቸውም አንዳቸውም አማራ ነን ብለው አያውቁም። ከነዚህ ውስጥ እናቶቻቸው አማሮች መሆን አለመሆናቸው ባይታወቅም አባቶቻቸው ግን የሰለሞን ዝርያዎች ናቸው፤ ወይም የዘር ሐረጋቸውን ሲመዙ ከዚያ ጀምረው ነው የሚቆጥሩት።

እንደ አውነቱ ከሆነ በ3ኛው ከፍለ-ዘመን መጨረሻ የአግአዚ/ሰለሞናዊ ሥርወ-መንግሥትን በጋብቻ የተዛመዱ ሁለት የአማራ ሴቶች ታሪክ በግልጽ ተመዝግቧል። አንዷ ሙሉ በሙሉ አማራ ስትሆን ሌላዋ ግማሽ አማራ ነበረች። ከክርስቶስ ልደት በሁዋላ በ275 ዓመተ-ምሕረት የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሆኖ የነገሠውና ዘግዱር ይባል የነበረው አጼ ጃን-ሰገድ በጣም የሚወዳት ሚስት ነበረችው። ልጅ ስትወልድ በምጥ ላይ አንዳለች አረፈች። አጼ ጃን ሰገድ ኃዘኑን እንዲረሳ ባለሟሎቹ ያንድ ገበሬ ሚስት ነጥቀው አመጡና ሰጡት። "ማርብላ " ትባል ነበር። ካካባቢው ሴቶች ሁሉ አጅግ በጣም ውብ ነበረች። ንጉሠ-ነገሥቱ ያለፈ ታሪኳን ስለማያውቅ ሚስቱ አደረጋትና "ንግሥት ብርሃን ለዓለም" ብሎ አነገሣት። በኋላ አጼ ሰይፈ-አርዕድ ተብሎ የነገሠውን "አልአሜዳ" ብለው የጠሩትን ወንድ ልጅ ወለደችለት። ይሁንና ማርብላ አዲሱ ባልዋ የሆነውን ንጉሠ-ነገሥቱን አትወደውም ነበር። የመጀመሪያ ባልዋን ድሃውን ገበሬ ነበር የምትወደው እና የምትናፍቀው። ንጉሠ-ነገሥቱ ከምትወደው ባልዋ ተቀምታ መምጣትዋን ሲያውቅ ለመጀመሪያው ባልዋ መልሶአት በቤ-ተመንግሥቱ ውስጥ ከቀድሞ ባልዋ ጋር ተቀምጣ ልጃቸውን አልአሜዳን እንድታሳድግ ፈቀደላት እና ደግ ዋለላት። አልአሜዳ ሲያድግ "ኦሃየ" የተባለችውን በከፊል አማራ የሆነች ሴት አገባ እና "ንግሥት አብረሂት ዘ ኢትዮጵያ" አሰኝቶ አነገሣት። ኦሃየ የኦሮሞ ተወላጅ ከነበረው ከታላቁ መጋል የሚወለደው የአዘቦው ንጉሥ የከሀለ

የነበሩ የኦሮሞ ንጉሶች ነበሩ። የአጼ ዋዜባ ሚስት የንጉሶቹ የፌንታሌ እና የጭላሎ ዝርያ ስለነበረች ይሆን ልጁ እና የልጅ ልጁ የታላላቆቹን ኦሮሞዎች ስሞች ስመ-መንግሥታቸው ያደረጉት? አጼ ፍንታሌ የኦሮሞዋን ልዕልት ፋሲላ አኖኒን የኑቢያ ንግሥት አድርገው ያነገሷት በኦሮሞ ዝምድናቸው ነውን? አባትና ልጆቹ የጥንት ታዋቂ እና ዝነኛ ኦሮሞ ነገሥታት ስሞችን ሥመ-መንግሥታቸው እያደረጉ ራሳቸውን ያነገሡት የኦሮሞ ደም ቢኖራቸው ይሆን? እናቶቻቸው ግን ኦሮሞዎች ናቸው ብለን በርግጠኝነት መናገር አንችልም።

ቀዳማዊ ምኒልክ የመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አድርጎ ከሾማቸው ጊዜ ጀምሮ አግአዚዎቹ በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ውስጥ ጠንካሮች ነበሩ። በአገሪቱ ውስጥ አመጽ እያስነሱ የጠሉትን ንጉሠ-ነገሥት ከዙፋን የሚያወርዱ፣ የወደዱትን ወደ ዙፋን የሚያወጡ ኃይለኞች እንደነበሩ ታሪክ መዝግቦታል። ለምሳሌ የአክሱማይት አባት ዘግዱር በገዛ ልጁ እንዲገደል እና ገዳዩም ወደ ዙፋን እንዲወጣ አድርገዋል። አባቱን የገደለውን ወንድሙን እና አባቱን እንዲገድል ያነሳሱትን አግአዚዎችን ለመበቀል አክሱማይት ግብጽ ውስጥ በነበሩ አማሮች ወታደሮቹ ድጋፍ ወንድሙ የግብጽ ፈርኦንነቱን እንዲለቅ አስደርጓል። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ9ኛው ዓመተ-ዓለምም ወንድሙን ገድሎ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሆኗል። በአንደኛው ክፍለ-ዘመን እቴ ህንደኬ ጻን በቅዱስ ማቲዎስ እጅ ተጠምቃ ክርስቲያን ሆና ነበር። አይሁድ አግአዚዎች በአክሱም ተሰሚዎች እና ኃይለኞች በመሆናቸው እሷን (ሕንደኬን)፣ ልጇን እና ባሏን ገድለው በእሳት አቃጥለዋል። ወንድሟን ኬቴብን አጼ ባሕር-ሰገድ በሚል ስመ-መንግስት በዙፋኗ ላይ አስቀምጠው አሻንጉሊታቸው አድርገውታል። (13) አግአዚዎቹ መጀመሪያ ቲጋሩዎቹ እስከሚደመስሷቸውና ቀጥሎም ዮዲት ጉዲት የምትባለው ፈላሻዋ አስቴር የመጨረሻ ምት እስርፋባቸው ፈጽማ እስከምታጠፋቸውና በ9ኛው ክፍለ-ዘመን ንግሥት ተበላ በዙፋናቸው ላይ እስከምትቀመጥ ድረስ አግአዚዎቹ ያን ያሕል ኃይለኞች ነበሩ። ቋንቋቸው ግዕዝ በአል-ነጋሽ ዘመን በ7ኛው ክፍለ-ዘመን ከእስልምና ተጽዕኖ የተነሳ በአረብኛና በሶርያ ቋንቋ ሲተካ ተዳከመ። አግአዚያኑ ራሳቸውም እንዲሁ በአሌክሳንደሪያ እየተመረጡ በኢትዮጵያ በሚሾሙ የግብጽ ፓትርያሪኮች ክፉኛ ተጎዱ። አንዳንዶቹ ከግብጽ የሚመጡ

ፓትርያሪኮች አረቦች በመሆናቸው አይሁድን ስለሚጠሉ አግአዚዎች "የክርስቶስ ገዳዮች" ናቸው ብለው እንዲፈርጇቸውና እንዲያስቃዩአቸው የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች አነሳሱባቸው። ቀደም ብሎም ቲጋሩዎች በጭካኔ ወጉአቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ቲጋሩዎች እና አግአዚዎች አንድ ዘር አለመሆናቸውን መግለጽ በጣም አስፈላጊ ነው። እንዲያውም አንዱ ለሌላው ፀር ነው። አግአዚ እስራኤላውያን ናቸው። ከክርስቶስ ልደት1000 ዓመት በፊት ቀዳማዊ ምኒልክን አጅበው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ቋንቋቸው ግዕዝ ነው። ትግሬዎች ወይም ተጋሩ የሚባሉት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ330 ዓመተ-ዓለም አካባቢ በታላቁ እስክንድር ከዛሬው ኢራቅ ከጥንቱዋ ባቢሎን እና ከሶርያ ስደአቸው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ናቸው። ታላቁ እስክንድር ከአክሱም ንጉሠ-ነገሥት ከአጼ ዋዜባ ስለመልካም ግንኙነት የተሰጡትንና በኢትዮጵያዊ በጄኔራል ክሊንቶ የሚመሩትን 21000 ምርጥ ጦረኞች ተጠቅሞ ባቢሎንን (የዛሬዋን ኢራቅን) እና ሶርያን ከወረረ በኋላ ለኢትዮጵያው ንጉሠ-ነገሥት ለውለታው የተሰጡ ናቸው። ታላቁ እስክንድር "የዓለም ንጉሥ" ተብሎ የተሰየመበትን ቀን ሲያከብር በጄኔራል ክሊንቶ ላይ ሸር ሰራበት። የሻምላ ጨዋታ እየተጫወቱ ሳለ በስካር መንፈስ አቅሉን ስቶ ገደለው። የአጼ ዋዜባን ቁጣ ለማብረድ እና ይቅርታውን ለመማጸን አሌክሳንደር ከሶርያና ከኢራቅ የተውጣጡ 25000 ምርኮኞችን ላከለት። የአጼ ዋዜባ ልጅ አጼ ፊንታሌ ከነዚህ አንዷን የሶርያ ሴት ወልቃ የምትባል አገባና በዋውል የተባለ ወንድ ልጅ ወለደ። አጼ ፊንታሌ ሲሞት በዋውል "አጼ ናግሽሬ" ተብሎ ነገሠ። አጼ ናግሽሬ የእናቱን ወገኖች ሶርያዎቹንና ከባቢሎን ከኢራቅ የመጡትን በመንግሥቱ አስተዳደር ከፍተኛ ቦታዎች ሁሉ በስለሞናዊ አግአዚዎች ላይ ሾማቸው። በተጨማሪም መሬት ሰጣቸውና ከነባሮቹ፥ ከአገሬዎቹ ከሚከሮቢያ፣ ኩሳ፣ ቤንኣሚር እና ከሌሎቹም ነገዶች ጋር እንዲጋቡ በህግ ደነገገላቸው። በዚህም ክብራቸውንም ከሁለተኛ ደረጃ ዜጋነት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ዜጋነት ከፍ አደረገላቸው።(14) ሶርያዊትዋ የአፄ ናግሽሬ እናት አዴር ወልዱ የሚባል አንድ ወንድም ነበራት። የእህቱ ልጅ ንጉሠነገሥት ስለ ነበር እሱም በመንግሥቱ ውስጥ ሙሉ ስልጣን ነበረው። ሶሪያዊ አዴር ወልዱም፥ የስልጣን ተቀናቃኞቹን ድሮ በአክሱም መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወቱ የነበሩትን አግአዝያኑን እየአሳደደ አጠፋቸው። (15) ይህ አዴር ወልዱ የተባለው

ሶርያዊ ሰው ስሙ የተሰየመው፥ ሶርያውያን ወገኖቹ ወደ ኢትዮጵያ ከመጋዛቸው ከጥቂት መቶ ዐመታት በፊት ወልደ አዴር ተብሎ ሶርያን ይገዛ የነበረውን ንጉሥ ስማስታወስ ይመስላል። በእርግጥም ወልደ አዴር የሚባል የሶርያ ንጉሥ መኖሩ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ ተረጋግጦአል። የኢትዮጵያ መፅሃፍ ቅዱስ ማህበር አኤአ በ2007 ዐመተ ምህረት ባላተመው የአማርኛ መፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ፥ በ መፅሃፈ ነገሥት ቀዳማዊ፥ በምዕራፍ 21 ብቻ ወልደ አዴር የሚስው ስም ዐራት ጊዜ ይነሳል። ስምሳሌ እንዱን ብናይ፥በምዕራፍ 21 መጀመሪያ ላይ እንዲህ ይላል፤--

‹‹የሶርያ ንጉሥ ወልደ አዴር ሠራዊቱን ሁሉ ሰበሰበ፤ወጥቶም ሰማርያን ከበባት። አየጠበቃቸውም ተቀመጠ።›› ከዚህ የሶርያዊ ስም እና የሶርያ ንጉሥ የምንገነዘበው አዴር ወልዱ፥ ንግሥቲትዋ እህቱ ወልቃ እና ወገኖችዋ በአሌክሳንደር ትልቁ ትዕዛዝ ስአዌ ዋዜባ በገፁ በረከትነት ተሰጥተው በእውነትም ከሶርያ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ መሆናቸውን ነው።

ከአጼ ናግሽሬ ሞት በኋላ ሶርያዊት ሚስቱ እና ወንድምዋ አዴር ወልዱ ይዘውት የነበረው ለሶርያውያን ያደላ ሥልጣን ቀስ በቀስ ከእጃቸው አፈተለከ። አጼ ናግሽሬ 70 ዓመት ነው የገዛው። እነዚያ ከሶርያ እና ከጥንቱ ባቢሎን ከዛሬው ኢራቅ መጥተው የተከማቹ፣ በኋላም ቲጋሩ የተባሉ ስዎች ቢያንስ በነዚያ 70 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በጣም ኃይለኞች ነበሩ። በኋላ ግን አግአዚዎቹ ቀስ በቀስ አንሰራርተው የበላይ ሆኑና የበፊት ክብራቸውን መልሰው ጨበጡ። አጼ ባዚን የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት በነበረበት ወቅት በ1ኛው ከፍለ-ዘመን በክርስቲያንዋ አገር ላይ አግአዝያን እንደገና ከፍተኛ ሥልጣን ያዙ። ከዚያ በኋላ ዮዲት ጉዲት (አስቴር) እስከተነሳችበት ጊዜ ድረስ ስ800 ዓመታት በአክሱም ዙፋን ላይ እውጪ አውራጅ ሆነው ጉልህ ተጽዕና አሳዳሪዎች ሆኑ። እልፈው ተርፈው እቴጌ ሕንደኬን ከልጅዋ እና ከባልዋ ጋር ገድለው በእሳት እስከማቃጠል ደረሱ። ያንን ያደረጉት ንግሥተ-ነገሥታት ሕንደኬ ክርስትናን በመቀበልዋ እና አግአዝያን ደግሞ እምነታቸው አይሁዳዊ ስስነበረና ፀረ-ክርስቶስ ስለነበሩ ነው። ዝቅ ብዬ ስለ ትግሬ ሕዝብ ስጽፍ ተጨማሪ መረጃ እስጣስሁ።

አጼ ጊዳጃን በአክሱም በስለሞናዊው ዙፋን ላይ በተቀመጠ በሃያኛው ዓመት እ.ኤ.አ በ878 ዓ.ም አስቴር ወይም ዮዲት ጉዲት የተባለች የአገው ፈላሻ አይሁዳዊት ሴት አክሱምን ወረረችና ንጉሡን አጼ ጊዳጃንን ገደለችው፡፡ የዓሥር ዓመት ዕድሜ የነበረው ልጁ አንበሳ ውድም ከዘመዶቹ ጋር ሸሽቶ ሸዋ ውስጥ መንዝ ተደበቀ፡፡ ንጉሣዊ ደም የሌላት፥ ሆኖም በርግጥ አይሁዳዊነት የነበረባት አስቴር እኔም የዳዊትና የሰለሞን ዘር ነኝ፥ እያለች በጎራዴዋ ኃይል 41 ዓመት ገዛች፡፡ የሚያስገርመው የአይሁድ ነገሥታትንና የእሥራኤሉን ንጉሥ ዳዊትን እየጠቀሰች እስራኤላዊ ደም አለኝ ብትልም የራስዋን ሥርወ-መንግሥት አልመሰረተችም፡፡ ልጅ ሳትወልድ ገደልዋት፡፡ ከዛግዌ ነገሥታት የተወሰደው ባልዋ መራ-ተክለሃይማኖት ከ እስዋ ልጅ ወልዶ ቢሆን ኖሮ እሱ ዳግማዊ ዛግዌ ነኝ ብሎ ከነገሠ በሁዋላ ከእስዋ የወሰደውን ልጅ እሱ ዙፋኑን ሲለቅ እንዲነግሥ ያመቻችለት ነበር፡፡

እሷ እንደሞተች ማን እንደተተካ እርስ በርሱ የሚቃረን መረጃ ነው ያለው፡፡ አንዳንዶች መንዝ ተደብቆ የነበረው የጊዱ-ጃን ልጅ አንበሳ-ውድም ወደ አክሱም ተመልሶ በመራ ተክለ-ሃይማኖት እስከተገለበጠበት ጊዜ ድረስ ለ20 ዓመት ገዛ ይላሉ፡፡ ሌሎች የአገውና የአክሱም ሕዝቦች የተነጠቀውን የአባቱን ዙፋን መልሶ እንዳይዝ ከለከሉት ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአገው ልዑል የነበረው የንግሥት ዮዲት ባል መራ ተክለ-ሃይማኖት ዮዲት ስትሞት ነገሠ፤ ስመ-መንግሥቱንም የንጉሥ ሰለሞን እና የኤትያ-ኤል /ንግሥተ-ሳባ / ዘመድ የነበረችው የአዘቦ ንግሥት የሣሆይ ልጅ የሆነውን ቀዳማዊ ዛግዌን ለማስታወስ ‹‹ዳግማዊ ሞራራ-ዛግዌ ›› ብሎ ራሱን ሰየመ ይላሉ፡፡ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ኢትያኤል እና ንግሥት ሣሆይ ንጉሥ ሰለሞንን ለማየት ኢየሩሳሌም በሄዱበት ወቅት ሁለቱም ንግሥቶች ከሰለሞን ፀንሰው መጥተው እንደ ቅደም ተከተላቸው ምኒልክ እና ዜጋዬ የተባሉ ወንዶች ልጆች ወልደዋል፡፡

የዳግማዊ ዛጉዌ/መራ ተክለ-ይማኖት/ መቀመጫ ላስታ አጠገብ ቡግና ነበር፡፡ ከዳግማዊ ዛጉዌ ጀምሮ ያሉትን የዛጉዌ ሥርወ-መንግሥት አባላትን ዝቅ ብዬ እዘረዝራለሁ፡፡ መራ ተክለ-ሃማኖት ስመ-መንግሥቱን ዳግማዊ ዛጉዌ ብሎ የሰየመው ባበስጡኝ አልነበረም፡፡ ዛጉዌም የንጉሥ ሰለሞን ልጅ እና ለቀዳማዊ ምኒልክ ከፊል ወንድሙ በመሆኑ እሱና ተተኪዎቹ ባጠቃላይ ለንግሥና በተለይ ደግሞ

ለሰለሞናዊው *ሥርወ-መንግሥት* ዘውድ *ያገባናል* ለማለት ነበር፡፡ ቀዳማዊ ምኒልክና ወንድሙ ዜጋዬ በኖሩበት ዘመን በልጅ ልጆቻቸው ሁሉ የሚፀና አንድ ውል ተዋውለው ነበር፡፡ በወንድማማቾቹ በምኒልክ እና በዜጋዬ /በዛጉዌ/ መካከል ውይይት ተካሄደና ምኒልክ ዜጋዬን "ዛግዌ" ብሎ ሰይሞ ዛግዌን የላስታ ንጉሥ አድርጎ ሊያነግሰው፣ የምኒልክ ተወላጆች ብቻ ንጉሠ-ነገሥት እና ንግሥተ-ነገሥታት እየሆኑ ሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት በመወከል ዙፋን ላይ ሊቀመጡ ስምምነት ተደረገ፡፡ እናቱ ሳሆይ ልጅዋን "ዜጋዬ" የአለችው በአማርኛ ቋንቋ በመሆኑ አማርኛ ቋንቋ ቢያንስ 3000 ዐመት እንደሆነው ያረጋግጣል፡፡ ለነገሩማ ምኒልክ ምንይልክ የሚለውስ ቃል አማርኛ አይደል? ኢትያኤል የቀዳማዊ ምኒልከ እናት ንግሥተ-ነገሥታት ስለነበረች ልጇ ምኒልክም ነጉሠ-ነገሥት እንዲሆን ተደረገ፡፡ የዛግዌ እናት ንግሥት ሣሆይ የንግሥት ሳባ ታዛዥ ስለነበረች ዛግዌ ንጉሥ እንጂ ንጉሠ-ነገሥት መሆን አይችልም ነበር፡፡ በንጉሥ ሰለሞን ልጆች መካከል ይህ ስምምነት ቢኖርም የዛግዌ ወራሾች ክዮዲት ሞት በሁዋላ ሰለሞናዊው ዙፋን ባዶ ሆኖ ሲያገኙት ጊዜ እኛም የሰለሞን ዘር ነን ብለው ገብ አሉበት፡፡

አለቂኝ ቢመስልም የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ታሪክ ጸሐፊ ጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረ-መስቀል ዛጉዌን እንደ ንጉሥ ዳዊትም ሆነ እንደ ሰለሞን ዘር አይቆጥሩትም ነበር፡፡ ልጥቀሳቸው፤ *‹‹የእስራኤል ንጉሥ ግዛት ከድልነአድ መዳፍ ተፈልቅቆ ወጥቶ እስራኤላውያን ላልሆኑ ሌሎች ሰዎች ተሰጥቷል››(16)* (ጸሐፌ ትእዛዙ በግልጽ የነገሩን የድልነአድ ግዛት የእስራኤል ሲሆን የዛጉዬ ግዛት ግን የአሰራኤል አይደለም ብለው ነው፡፡ ሀቁ ግን የሰለሞን ዘር በመሆናቸው የቀዳማዊ ምኒሊክ ልጆች እና ግዛታቸው እስራኤላውያን ከሆኑ ዛጉዬም የሰለሞን ልጅ በመሆኑ ልጆቹና ግዛቶቹ አሰራኤላውያን የማይሆኑበት ምክንያት አለመኖሩ ነው፡፡

ቡግና፣ አዳፋ እና ሮሃ ተቀምጠው የገዙ የዛጉዬ *ሥርወ-መንግሥት*

አባላት ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ስም | ዘመነ-ንግሥና (ዓመት) |
|---|---|
| መራ ተክለ-ሃይማኖት | 13 |
| ጠጠወ-ደም | 40 |
| አኮቴት | 20 |
| በዕምነት | 20 |
| መይራራ | 49 (አንዳንዶች 15 ዓመት ይላሉ) |
| ሐርቤይ | 49 (አንዳንዶች 8 ዓመት ይላሉ) |
| እሴዳ | 40 |
| ሓርቤ | 40 |
| ላሊበላ | 40 |
| ነኣኩቶ ለኣብ | 40 |
| ይትባረክ | 10 |

የዛጉዌ/ዛጉዬ/ ሥርወ-መንግሥት ኢትዮጵያን ለ343 ዓመታት ገዝቷል፡፡ መይራራ የገዛው 15 ዓመት ብቻ ከሆነና ሀርቤ ደግሞ ለ8 ዓመት ብቻ ከሆነ የነገሠው 286 ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡ የዛግዌ ስርው-መንገሥት መስራች መራ ተክለሃይማኖት ለወራሾቹ እያንዳንቸው ከ40 ዐመት በላይ እንዳይነግሡ ደንግጎ ስለነበር ከዛ ዘመን በላይ የነገሠ አልነበረም፡፡

ከዛጉዬ ነገሥታት ውስጥ የአማራን ሥርወ መንግሥት አወክላለሁ ያለ አንድም ንጉሠ-ነገሥት የለም፡፡ የሚልበትም ምክንያት አልነበረም፡፡ ይህ ግን አማሮች በዛግዌ ሥልጣን ዙሪያ አልነበሩም ማለት አይደለም፡፡ በትክክል በሥልጣኑ ዙሪያ ነበሩ፡፡ ታሪካቸውም እንደሚከተለው ነበር፤

በዛጉዬ ቤተሰብ የሥልጣን ሽኩቻ እና መራራ ፀብ ምክንያት እንዲሁም ላሊበላን በመርዝ ለመግደል ሀርቤ በጠነሰሰው ሤራ የተነሳ ላሊበላ ህይወቱን ለማትረፍ ወደ ኢየሩሳሌም ሸሽቶ ሄደ፡፡ ኢየሩሳሌም ጥቂት ዓመታት ቆይቶ ግብፅ ውስጥ አማርና ደልታ ወደሚባለው ቦታ መጣ፡፡ ይህ ቦታ በርካታ አማሮች የሰፈሩበት ቦታ ነው፡፡ አማሮቹ ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ የሄዱት ከአንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ዓመት በፊት ሲሆን አክሱማይት በሕፃንነቱ ራምሴስ በሚል ስም የግብፅ ፈርዖን ሆኖ ሲሄድ እሱን ሊጠብቁ አጅበው ሄደው ነው እማርና በተባለው ቦታ ሰፍረው የቀሩት፡፡ እነዚህ አማሮች በግብፅ እስላም መሪዎች በመስቃየት ላይ ነበሩ፡፡

ጎልማሳው ላሊበላም ከሱ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ሄደው ሃርቤን በመጣል እንዲረዱት እና ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ዘመዶቻቸው ጋር በሰላም እንዲኖሩ አሳመናቸው፡፡ በዚህም አሥር ሺ የሚሆኑ አማራ ጦረኞችና ባለእጆች ከላሊበላ ጋር በሱዳን በኩል ዓባይ ወንዝን ተከትለው መጡና ከሃርቤ ጋር ጥቂት እንደተዋጉ ሃርቤ ፈርቶ ስልጣኔን እለቃለሁ አለ፡፡ መልካሙ የእግዚአብሄር ሰው ላሊበላም አባታችን መራ ተክለሃየማኖት የደነገገውን ህግ አላፈርስም፡፡ 40 ዐመትህን ጨርስና እነግሣለሁ፣ አለው፡፡ በዚህ ምክንያት የሃርቤ 40 ዐመት ከእለቀ በሁዋላ በ1172 ዓ.ም (አንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር)

ገብረ-መስቀል በሚል ስም ላሊበላ ነገሠ። አማሮች ለዋሉለት ውለታ አጼ ገብረ-መስቀል በከፍተኛ የመንግሥቱ ሥልጣን ቦታዎች ላይ ሾማቸው። አማርኛም የመንግሥቱ የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ፈቀደ። በዚህም ከግብፅ የመጡት እና አገር ውስጥ የነበሩት አማሮች የአጼ ገብረ-መስቀል አስተዳደር የጀርባ አጥንት ሆኑ። ከግብፅ ከመጡት መንፈሳውያን መሃል በሁዋላ አቡነ ገብረ-መንፈስቅዱስ የተባሉት ትልቅ ፃድቅ ነበሩበት። እሳቸውም የአፄ ላሊበላ የመንፈስ አባትና ወዳጅ ነበሩ። እነዚህን ከግብፅ የመጡትንና የአገር ውስጥ አማሮችን እንዲሁም አገዎችን እና የእጅ ሙያ ያላቸውን ሌሎችንም ኢትዮጵያውያንን በመጠቀም ላሊበላ፡ ከዓለም አስደናቂ ነገሮች አንዱ ለመሆን የበቁትን የላሊበላን ፍልፍል አብያተ-ክርስቲያናት አነፀ። የላሊበላን ፍልፍል አብያተ-ክርስትያናት ያነፁት ኢትዮጵያውያን አይደሉም የሚል አፈ-ታሪክ እያቀረቡ የኢትዮጵያውያንን አስተዋጽኦ ዋጋ ለማሳጣት የሚጥሩ አንዳንድ ግለሰቦች አሉ። እነዚህ የገዛ ሕዝባቸውን ክብር ለሌሎች ለመስጠት ሽንጎ የሚቀመጡ ግለሰቦች ናቸው። እውነታው በተቃራኒው ስለሆነ ትክክል አይደሉም።

ከዛጉዌ ነገሥታት አራቱ ቅዱሳን ይምርሃነ-ክርስቶስ፣ ገብረ-ማርያም፣ ላሊበላ እና ነአኩቶ-ለአብ ካህናትም ነበሩ። በርግጥ ቅዱስ እስከመባል የበቁ ጥብቅ ክርስቲያኖች እና ጥልቅ መንፈሳውያን ነበሩ። ይህ ክስተት ለኢትዮጵያውያን ነገሥታት አዲስ ነገር ነው እንዴ? በፍፁም አይደለም።

ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ከኢትያኤል/ንግሥተ-ሳባ/ በፊት የነበሩ ነገሥታት በዚች ዐለም ላይ የካህናት ካህን እና የንጉሦች ንጉሥ ሆኖ በኢየሩሳሌም ነግሦ ከነበረው ከመልከ ጼዴቅ ልጅ ከኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት መሥራች ከኢት-ኤል/ኢትዮጵ/ ጀምሮ እስከ እሴ/አጼ/ ድረስ በመልከ ጼዴቅ ሥርዓት መሰረት ሁሉም ባንድ ጊዜ ነጉሠነገሥታትም ሊቀካህናትም ነበሩ። እግዚአብሔርን ስለሚያመልኩ እና ስለሚፈሩ በትክክል ያስተዳድሩ፣ በጽድቅም ይመሩ ነበር። በሌላ አባባል የኢትዮጵ ዝርያዎች የነበሩና የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥትን የመሰረቱ ነገሥታት እያንዳንዳቸው ድርብ ሥልጣን ነበራቸው፤ ፖለቲካዊ እና መንፈሳዊ /ንግሥና እና ቅስና/። ሁለቱን ሥልጣኖች አጣምረው ነበር የሚመሩት። ይህ ነበር የአያት ቅድመ-አያቶቻችን እውነተኛው ታሪክ። ብንወደውም ብንጠላውም፤

ብንቀበለውም ባንቀበለውም ልጆቻቸው ስለሆንን ይህ ነበር ታሪካዊ ዳራችን። ልብ ከአለን ግን በዓለም ታሪክ ውስጥ ባለው ልዩ ቦታ በዚህ ታሪካችን ልንኩራበት ይገባል።

ምንም እንኳ አጼ ገብረ-መስቀል/ላሊበላ/ አማሮችን ወታደሮቹ አድርጎ ቢቀጥር፣ አማርኛን ልሳነ-መንግሥቱ ቢያደርግ እና አንዳንዶቹን በከፍተኛ የመንግሥት ቦታዎች ላይ ቢሾማቸውም ቅሉ ፍጹማዊው ሥልጣን በራሱ በላሊበላ እና በልጁ በይትባረክ እጅ ነበር። አማራው ከነሱ ጋር አብሮ አልገዛም። ለዚህ ማስረጃው ይትባረክን ሲገለብጥ በእናቱ ኦሮሞ የነበረውን ይኩኖ-እምላክን ባብዛኛው የረዱት አማሮች መሆናቸው ነው። በአመክንዮ ለመናገር፥ አማሮች በዛጉዌ ሥርወ-መንግሥት ውስጥ ቢገዙ ኖሮ ምንም ቢሆን ተጠቃሚ የሆኑበት ሥርወ-መንግሥት ተገልብጦ ስለሞናዊው ሥርወ-መንግሣት ተመልሶ እንዲመጣ ተባባሪዎች አይሆኑም ነበር።

እሴ/አጼ/ ቆየት ብሎ ስመ-መንግሥቱ "ስንደቅ ዓልማ" የተባለው ከኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት የመጨረሻው ንጉሠ-ነገሥት እና ሊቀ-ካህናት ነበር። ኢትያ-ኤል/ንግሥተ-ሳባ / የዚህን የንግሥና፣ እና የክህነት ሥርወ-መንግሥት ስንስለት በጣጥላ ጣለችው። ሽማግሌውን ንጉሠ-ነገሥት ገደለችና በዙፋኑ ላይ ጉብ አለችበት። ሴት ካህን መሆን ስለማይፈቀድላት አለዋም ያንን ወግ ጠብቃ ንግሥተ-ነገሥታት ብቻ ሆነች። ልጇ ቀዳማዊ ምኒልክም ንጉሥና ካህን መሆን ሲገባው አልሆነም። የክህነት ስልጣኑን ከእስራኤል ላመጣቸው አይሁዳውያን ለእነ ሳዶቅ አሳልፎ ሰጠ። ከመልከጼዴቅና ከኢትዮጵ የወረዱትን ኢትዮጵያውያን ቀላውስትን አዋርዶ እና አሳዶ ከእስራኤል ወደ አመጣቸው ወደ አሪት የአይሁድ ካህናት ተጠጋ። ከዚህም በላይ፥ በኢትዮጵ አና በዝርያዎቹ ልማድ መሰረት በኢትዮጵያዊ ካህን ተቀብቶ መንገሥ ሲገባው እሱ ግን የአስራኤልን ሊቀ-ካህን ሳዶቅን አክብሮ በእሱ እጅ ሥርዓተ-ንግሥናውን በመፈፀሙ ለኢትዮጵያ ወግና ሥርዓት ንቀትን አሳየ። ከዚህ በተጨማሪ የአይሁድ ምናምንቴ ቅራቅንቦዎችን ለቃቅሞ አምጥቶ ንጉሦችና ካህናት እያደረገ ሾማቸው። ከፍ ባሉ ቦታዎች ላይ ምኩራቦችን እያሠራ አሥርቱ ቃላትን የያዙ ታቦታትን አስገባላቸው። ርስት ሰጣቸው። ወታደሮች መደበላቸው። እንዲሰብኩ፣ እንዲያዙና እንዲናዝዙ ፈቀደላቸው። የዐስርቱ ትዕዛዛት ታቦት ግን ለኢትዮጵያውያን አዲስ ነገር አልነበረም። ከምኒልክ ዘመን

500 ቀደም ሲል፥ ሙሴ ራሱ በህይወት እያለ ዐስርቱን ትዕዛዛት በሌላ ፅላት አስቀርፆ ቀይ ባህርን የከፍለበትን በትር ጨምሮ በአንድ ሳጥን ከትቶ ለሚስቱ ወንድም ለአባ-ብሄር ማስታወሻ ስጥቶት፥ አባ-ብሄር እነዛን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ፤ ዳግማዊ ኢትዮጵ ተብሎ ነግሦ ነበር። ይህ ታቦት እና በትረ-ሙሴ ሳባ በተባለው ከተማ ውስጥ በአንድ ዋሻ ውስጥ በክብር ተቀምጠው ሲኖሩ፥ የሳባ ከተማ በመሬት ንቅናቄ ስትጠፋ አብረው ጠፍተዋል።

ጌታ እየሱስ ክርስቶስ እሥራኤል ውስጥ ራሱን ለአይሁድ ከመግለጡ በፊት እድሜው ከ22 እስከ 25 ዓመት በነበረበት ወቅት ለ3 ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ኖሮ እንደነበር የተጻፈ *ዜና ማርቈር* የተባለ ማስረጃ ተገኝቷል። በኋላም በርቶሎሚዎስ፣ ማቲዎስ፣ማትያስ፣ ናትናኤል፣ የአልፌዎስ ልጅ ያዕቆብ እና ቶማስ የተባሉ 6 ደቀ-መዛሙርቱን ወደ ኢትዮጵያ ልኳል። ምንም እንኳ አንባቢው ያስማስረጃ የስድስቱን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ለመቀበል ቢቸገር እንኳን፣ ወንጌላዊው ማቴዎስ ኢትዮጵያውንን እንዳስተማረና ክርስቶስን እንደሰበከ መካድ አይቻልም። አውሮፓውያን ወንጌላውያን በሞላ ይህን ሃቅ ይቀበላሉ። ጌታ እየሱስ ክርስቶስ እንደ አረገ ቅዱስ ማቴዎስ ንግሥት ሕንደኬ ጃንን፣ ቤተ-ሰቧን እና የጦር ስራዊትዋን በዓባይ ወንዝ አጠመቃቸው እና ሁሉንም ክርስቲያን አደረጋቸው። ከዐመታት በኋላ ግን በአክሱም የነበሩ በዚያን ጊዜ ስልጣን የነበራቸው አግአዚ አይሁዳውያን ሕንደኬን፣ ልጇን እና ባሏን ባሳዛኝ ሁኔታ ገደሏቸው። እየሱስ ክርስቶስ በቤተ-ልሔም ሲወለድም ልደቱን ሲጠባበቁ የነበሩ 12 የኢትዮጵያ ጠቢባን ንጉሦች የአማራን፥ የኦሮሞን፥ የአፋርን፥ የሶማሌን የኑብያን እና የሌሎቹንም የኢትዮጵያ ጎሳዎች ወክለው ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዘው፣ ስግደውለት ስጦታ አበርክተውለታል። እነሱም በዓለም ላይ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ነበሩ። ይህ ሁሉ የሚያረጋግጠው ኢትዮጵውያን ከዓለም ሕዝብ ቀድመው ክርስትናን መቀበላቸውን ነው። በበርጠሎሚዎስ እጅ ብቻ በርካታ የኢትዮጵያ ነገዶች ተጠምቀዋል። ከነሱም ውስጥ አማሮች፣ ጋፋቶች፤ ቦሮዎች፣ ካፎቶች፣ ቦጮቶች፣ ኢብራዎች፣ ዘይላዎች፣ ኢሳዎች፤ የበረንታ አዳሎች፣ ሐረሬዎች፣ እነማዮች፣ ጎጃሞች፣ ሸበሎች፣ ሊኮዎች፣ቋራዎች፣ እናሪያዎች፣ ቤተ-መራዎች፣ ስገነቴዎች፣ ወይዞች፣ ዲሆ-ዳሞቶች፣ ፈጢጋሮች እና ገበታኖች ይገኙበታል። (17)

በ 333 ዓ.ም ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችበት ጊዜ ሳይሆን ክርስትና መንግሥታዊ ሃይማኖትዋ መሆኑን በይፋ ያወጀችበት ዓመት ነው። እንደዚህ ደፍሮ ያወጀ አንድም ሌላ አገር በዐለም ላይ የለም። ታላቁ ቆስጠንጢኖስም ቢሆን ክርስቲያኖች ባገሩ ውስጥ ክርስቶስን በነፃነት እንዲያመልኩ ነው የፈቀደላቸው። በርግጥ እናቱ እሌኒ ክርስቲያን ነበረች። ቆስጠንጢኖስ ራሱ ግን ሊሞት ትንሽ ሲቀረው በ332 ዓ.ም. ዘግይቶ ነው ክርስቲያን የሆነው።(18) ስለዚህ ፍሬሚናጦስ እና እዴሲዩስ የተባሉ ሁለት የግሪክ ልጆች ክርስትናን ለኢትዮጵያውያን እንዳስተዋወቁ መቁጠር ስህተት ነው።

ሁለቱ ወንድማማቾች ልጆች ፍሬሚናጦስ እና አዴሲዩስ ካንዲት መርከብ ላይ ተማርከውና ለአክሱም መንግሥት ተሰጥተው የኢትዮጵያን ባሕል፥ የክርስትና ሃይማኖትንና የቤትመንግሥቱን ወግና ሥርዓት እየተማሩ በቤተ-መንግሥት አደጉ። ሰይፈ-አርእድ ተብሎ ይገዛ የነበረው አልአሚዳ እና አሮሞ እና አማራ የነበረችው ንግሥት አብርሂት ዘ ኢትዮጵያ የምትባለው ባለቤቱ ሶሃዬ እነዚህን ሁለት ልጆች ሊያሳድጉ ከመቀበላቸው በፊት ጀምሮ ጽኑ ክርስቲያኖች ነበሩ። ንግሥት አብርሂት ክርስትናን ለማስፋፋት እጅግ ከፍተኛ ጉጉት ነበራት። በሷ ጉጉት እና ሁለቱን ልጆቿን እብርሃና አጽብሃን በማትጋት ነበር እናትና ልጆች ክርስትና የመንግሥታቸው ሃይማኖት እንዲሆን በይፋ ያወጁት። ማደጎሞቹ ልጆች ፍርሚናጦስ እና አዴስዩስ ብልሆች መሆናቸውን የተገነዘበችው ንግሥት አብርሂት ፍሬምናጦስን የእብርሃና አጽብሃ አማካሪ አደረገችው። ክርስትና የኢትዮጵያ ሃይማኖት ሆኖ በይፋ እንዲታወጅ ታስላስል በነበረበት ወቅት የአይሁድን ሃይማኖት ለ1300 አመታት ሲያመልኩ የኖሩት አይሁዶች የክርስትና ሃይማኖትን በመቃወም የኢትዮጵያን ህዝብ ቀስቅሰው አመጽ ያስነሱ ይሆናል ሲል የአክሱም ሊቀ-ካህናት ስጋቱን ገልጾላት ነበር። በዚህ ምክንያት የግሪክ ቋንቋ የሚችሉትን ፍሬምናጦስንና እዴሲዩስን ወደ ግብጽ አሌክሳንደሪያ ልካ ከፓትርያሪኩ ከአትናቲዎስ ጳጳስ እንዲሾምላት እንድትጠይቅ ሃሳብ አካፈላት እና ሁለቱ ወጣቶች ተላኩ። አትናቲዎስም በሃሳቡ ደስ ተሰኝቶ ፍሬምናጦስን "ሰላማ" በሚል ስም ጳጳስ አድርጎ ሾሞ ላከው። በኋላ ከሳቴ ብርሃን የተባሉት አቡነ ሰላማ ኢትዮጵያውያን ቀሳውስትንና ረዳት ጳጳሳትን ለመሾም ሥልጣን ተሰጥቷቸው መጡና ባሳደጋቻቸው አገር ክርስትናን

ለማስፋፋት ትልቅ መሳሪያ ሆኑ። ባጭሩ የፍሬምናጦስ ሚና ይህ ነበር።ፍሬምናጦስ እና አዴሲዩስ በእድሜ 10 ዓመት እና ከዚያም በታች ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ክርስትናን ከኢትዮጵያውያን ተምረው መልስው አስተምረዋል። እውነቱ ይህ ነው እንጂ የተገላቢጦሹ አይደለም። ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ትንንሽ ልጆች ስለነበሩ ክርስትናን ለመስበክ የሚያበቃ ቃሰ-ወንጌል ያውቁ ነበር ማለት አያስኬድም። ከነሱ የሚበልጡ እና በእምነቱ የተካኑ ኢትዮጵያውያንን ወደ ክርስትና እምነት ሊሰውጡ ቀርቶ ራሳቸውም ሃይማኖቱን በወጉ ማወቃቸው ያጠራጥራል:::: ፍሬምናጦስ የአሌክሳንደሪያን ኮፕቲክ ቤተ-ክርስቲያን ስለማይወክል ሰሷ ይሠራ ነበር ማለትም አያስኬድም። የወከለውም ያገለገለውም ተንከባክባ ያሳደገችውን ኢትዮጵያን ነው። እንደ ኢትዮጵያዊነቱ ታማኝነቱም ለኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ነበር። ደሞም የኢትዮጵያ ሕዝብ የክርስትና ዘር ሊዘራበት ለም መሬት ሆኖ ዘሩን ባይቀበል ኖሮ ንግሥት አብርሂትም ሆነች አብርሃና እጽብሃ ወይም ፍሬምናጦስ ስር የሰደደ ክርስቲያናዊ ዘር ማብቀል ባልቻሉም ነበር።

ይህ ሁኔታ ኢትዮጵያ በይፋ ክርስቲያን እስከሆነችበት እስከ አራተኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ የነበረው ነው። "በይፋ" ለሚለው ቃል አፅንኦት እሰጣለሁ፤ ምክንያቱም ከዚያ በፊት በግለሰብ ደረጃ በሐዋርያው ፊሊጶስ ተሰብኮ የተጠመቀውን ጃንደርባውን ጨምሮ የሃይማኖቱ መሰበክ ከተጀመረበት ከአንደኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ እንደተሰበከላቸው የክርስትና እምነትን የተቀበሉ በርካታ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት እና ንግሥታት አሉ።

ኢትዮጵያ አዲሱን ሃይማኖት በመንግሥት አዋጅ በይፋ በተቀበለች ባጭር ጊዜ ውስጥ በመንፈሳዊው መድረክ ላይ ሌላ ሽሚያ እና ቅሚያ ታዩ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በራሷ ፓትርያሪክ ሳይሆን በግብፅ ኮፕቲክ ፓትርያሪክ ብቻ እንድትመራ እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር በ325 ዓ.፣ም. በተካሄደው የኒቂያ ጉባኤ ተወስኗል ሲል የግብፅ ሊቀ-ጳጳስ በሃሰት አወጀ። ኢትዮጵያውያን ካህናት፥ እነሱ በሌሉበት በማንም የተወሰነን ማንኛውንም ውሳኔ እንደማይቀበሉ ከመከሩ በሁዋላ የኢትዮጵያ ቀሳውሰት እና ዲያቆናት በአክሱም ከተማ በውሳኔው ላይ ተቃውሞ አነሱ። ሆኖም በህመም ላይ የሚገኘው ጡረተኛው ንጉሠ-ነገሥት ዋዜባ፣ ቅመም የተባለች ሚስቱ እና ንእሰ-ሰላማ በተባለው በአስመሳዩ ግብፃዊ ጳጳሥ እጅ ተቀብቶ መንገሥ

ይፈልግ የነበረው ልጁ አጼ ኤል-ስሚሪሴዮስ ከኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ይልቅ ለግብፅ ጳጳሳት የበለጠ ክበሬታ ይስጡ ነበር። በመሆኑም ስዚያ ጮሌ የግብፅ ጳጳስ ሰንዑስ-ስላማ አባሪ ተባባሪ ሆነው የራሳቸውን ቅዱሳን ጨፍጭፈው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን መንፈሳውያን ያልሆኑ ህገ-ወጥ የግብፅ ኮፕቲክ ፓትርያሪክ ተብየዎች እንዲመሯት ፈቀዱ።

በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን እ.ጎ.አ. ከ325 ዓ.ም. እስከ 1951 ዓ.ም. ድረስ ስአንድ ሺ ስድስት መቶ ዓመታት በነቀዙ፣ መንፈሳዊነት በሌላቸው አልፎም አንዳንዴ ሙስሊም በሆኑና ከቤተክርስቲያን ይልቅ መስጊድ ማሠራት በሚቀናቸው አስመሳይ የግብጽ ፓትሪያርኮች ተመራች። ግዕዝን በማዳከም እና አረብኛን በማስፋፋት እንዲሁም የጥንት መጻሕፍትን እያወደሙ የኢትዮጵያ ታሪክ የአረቦችን ፍላጎት እንዲያሟላ እያደረጉ እንደገና በመጻፍ ገናና ታሪካችንን አበላሹ። ራሷን በራሷ የሾመችውና ብዙም ደህና ነገር የማይነገርላት ዮዲት እነዚህን ጳጳስ ተብዬ አፍቃሬ-አረቦች ባታስቆማቸው ኖሮ ግዕዝ ሙሉ በሙሉ ይጠፋ ነበር። እነዚያ የግብፅ “ጳጳሳት” እና “ፓትሪያሪኮች” የኢትዮጵያን ነገሥታት በሴራ እያጠመዱና እየተቆጣጠሩ፣ ለነሱ ታዛዥ ካልሆኑ በስተቀር ግንኙነት እንደሚያቋርጡባቸው እያስፈራሩና የፈሩ ነገሥታትን እየተጠቀሙ፣ የተማሩ ኢትዮጵያውያንን በተስይም ቅዱሳን ቀሳውስትን፣ ሊቃውንትን፣ ከያኒያንን፣ የታሪክ አዋቂዎችንና ፈላስፎችን አረዱ፣ ጨፈጨፉ፣ እካለ-ስንኩለ አደረጉ፣ አጠፉ።

የኢትዮጵያን ክብረ-ዝና ከፍ የሚያደርጉ መጻሕፍትንም እየሰበሰቡ አቃጠሉ። ከተቃጠሉት መጻሕፍት ውስጥ “መጽሐፈ ሉባኤ” በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ተካትቶ የነበረው እየሱስ ክርስቶስ ማንነቱን ስራሱ ሕዝብ ለአይሁድ ከመግለጡ በፊት እድሜው ከሃያ ሁለት እስከ ሃያ አምስት በነበረበት ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ሰሶስት ዓመታት እንደኖረና እንዳስተማረ የሚያትተው መጽሐፍ *ዜና ማርሄር* ይገኝበታል። ይህን መጽሐፍ ለማጥፋት እና መጽሐፉ የተገኘባቸውንም ምሁራን ለማስወገድ የግብፅ ፓትሪያርኮች ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ለዚህ የነበሩአቸው ምክንያቶችም ብሩህ የቆዳ ቀስም የነበረው እየሱስ ክርስቶስ በግብፅ ውስጥ ኖሮ ይሆናል እንጂ እንዴት የጥቁር አገር በሆነችው በኢትዮጵያ ይኖራል የሚሉ ንቀትና ቅናት

ነበሩ። እነዚያ ደናቁርት የግብፅ ጳጳሳት ያላወቁት ወይም ለማመን ያልፈለጉት ነገር ኢትዮጵያውያን ፈርኦኖች አስልጣኞቻቸውና ጌቶቻቸው እንደነበሩ እንዲሁም ኢትዮጵያ በዓለም ገናና በነበረችበት በዚያ ወቅት ፈርዖኖች እየሆኑ ግብፅን ካስተዳደሩ አሥራ ዐራት የኢትዮጵያ አንስት ንግሥታት ውስጥ ሁሉንም ባይሆንም አራቱን ብልሆች እና እጅግ የተዋቡ ንግሥቶችን ግብፆች የፍቅር አማልክት ናቸው እያሉ ያመልኳቸው እንደነበረ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አኩሪ ታሪካችን ለዘመናት ተሰውሮብን ሊኖር የቻለው አንዱም በነዚያ ፓትሪያርክ ተብዬዎች ምቀኞች ግብፃውያን ተንኮል ነው።

ስለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት በዛጉዬ ሥርወ-መንግሥት ቢተካም ከሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ዓባላት የፀዳ አልነበረም። የአጼ ጊዳ-ጃን ዝርያዎች ነን የሚሉ ርዝራዦች በሸዋ ነበሩ። እጼ ጊዳ-ጃን በንግሥት አስቴር ወይም በዮዲት የተገደለ የሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት የመጨረሻው ንጉሥነገሥት ነው። ለአራት መቶ አመታት በተጉለት ተደብቀው የኖሩ የሰለሞናዊ ሥርወ-መንግስት ርዝራዦች የሚከተሉት ናቸው፡-

አንበሳ ውድም

ድል-ነዓድ

እግባጽዮን

ፀገፌ-አርዕድ

ነጋሺ-ዛሬ

አስፍሃ

ያዕቆብ

ባሀር-ሰገድ

እድም-አሰግድ

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት እድም-እስግድ፣ ህዊ ጊፍቲ መንዲያ ከተባለች የቦረና ኦሮሞ ስመ-መንግሥቱ ይኩኖ-አምላክ የተሰኘውን ተስፋ-እየሱስን ወለደ። ይኩኖ-እምላክ በ1262 ዓ.ም ስለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት እንደገና እንዲመሰረት ያደረገ ነው። አያቱ፣ የህዊ ጊፍቲ መንዲያ አባት አዛዥ ጫላ የተባሉ፣ በሸዋ የሚኖሩ የኦሮሞ ባላባት ነበሩ።

ተክለ-ጻድቅ መኩሪያ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ይኩኖ አምላክ እስከ አጼ ልብነ-ድንግል* በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 11 ላይ የጣልያን ምሁርና የፋሺስት ሞሶሎኒ ደጋፊ የነበረው ኮንቲ ሮዚኒ "ስቶሪያ ዴ ኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ከጻፈው ጠቅሰው ስለ ይኩኖ አምላክ (ተስፋ ኢየሱስ) ጽፈዋል። ኮንቲ ሮዚኒ በጻፈው መሰረት ተስፋ እየሱስ የእድም እስግድ አባት ነው። የተስፋ እየሱስ እናት ጊፍቲ ሃዊ መንዲያ ደግሞ የአዛዥ ጫላ ልጅ ሳትሆን አገልጋይ ነበረች። ኮንቲ ሮዚኒ ላቀረበው ታሪክ ስሙ ባልተጠቀሰ ምንጭ እና ባልታወቁ አዛውንቶች ላይ መመስረቱን አምኗል። በሌላ አባባል የሰነዘረው ሀሳብ አጠራጣሪና ግምት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ምንጮች ለምሳሌ ስርግው ሀብለሥላሴ፣ *ጥንታዊ እና የመካከለኛ ዘመን ታሪክ እስከ 1270* ፤ ገጽ 289፣ በሪሁን ከበደ፤*የአጼ ኃይለሥላሴ ታሪክ*፤ገጽ133፣ አማን በላይ፤*የትናንትዋ ኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ* ፤ ገጽ 18፣ እና የኢትዮጵያ ነገሥታት የዘር ሐረግ ዛፍ እንደሚያረጋግጡት እድም አስግድ የተስፋ-እየሱስ (ንጉሠ-ነገሥት ከሆነ በኋላ ይኩኖ አምላክ የተባለው) አባት ነው። ስለዚህ ኮንቲ ሮዚኒ ፍጹም ተሳስቷል። የተሰፋ-ኢየሱስ እናት ጊፍቲ ሃዊ መንዲያ የአዛዥ ጫላ ልጅ ሳትሆን አገልጋይ ናት ያለውም ስህተት ነው። የአዛዥ ጫላ ልጅ ወይም አገልጋይ መሆንዋ ብዙም አስፈላጊ ባይሆንም የኮንቲ ሮዚኒ ምንጭ አስተማማኝ ስላልሆነ ጊፍቲ ሃዊ መንዲያ የአዛዥ ጫላ ልጅ መሆንዋን በሚያረጋግጡ *ታሪክ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያን* በመሰሉ በኢትዮጵያውያን በተጻፉ መረጃዎች ላይ እናተኩራለን። የላሊበላ ልጅ የሆነውን ይትባረክን ከሥልጣን ለማውረድ እና ይኩኖ አምላክን ለማንገሥ የተዋጉ ወታደሮችን ማንነት ጨምሮ ስለ ይኩኖ አምላክ ይህ ምሁር-ተብዬ ፋሺስት ጣልያን በሰነዘራቸው ባብዛኞቹ ሀሳቦች ላይም ተሳስቷል። የእሱን ስህተት ተከትለው ተስፋ እየሱስን እንደ አባት፥ እድምስገድን እንደ ልጅ አድርገው አማራው ለተስፋ እየሱስ

መንገሥ የአደረገውንም ወታደራዊ አስተዋፅኦ አሳንሰው የፃፉ እና የተናገሩም አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ምሁራን አሉ። ይሁንና ከርዕሴ ላለመውጣት የእነሱንም ስሞች ሳልጠቅስ አልፌዋለሁ።

ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች የንጉሥ ሰለሞንና የንግሥተ-ሳባ ዝርያዎች ናቸው ተብሎ ይታመናል። ከተሰፋ-አየሱስ እናት በስተቀር የሌሎቹን የእናቶቻቸውን ስም እና ነገድ ጨርሶ አናውቅም ይሆናል። አንድ ነገር ላይ ግን ርግጠኞች ነን፤--ተስፋ-ጽዮን በግዕዝ ቋንቋ "ይኩኖ-አምላክ" የሚል የክርስቲያን ስም የያዘ በእናቱ የኦሮሞ ተወላጅ ነበር። የይኩኖ-አምላክ መንግሥት በግልጽ "የኦሮሞ ሥርወ - መንግሥት" አልተባለም እንጂ በተግባር ግን የኦሮሞ መንግሥት ነበር። ከሱ በኋላ የነገሱ ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ነገሥታትም የኦሮሞ ወይዛዝርትን እያገቡ ስለነገሱ ኦሮሞዎች ከ1262 እስከ 1965 ዓ.ም. ድረስ ለ700 ዓመታት የሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ነገሥታት እና ንጉሳውያን ቤተሰብ አባላት ሆነው ኖረዋል። ሥርወ-መንግሥቱ ለትንሽ ጊዜ መደናቀፍ የገጠመው በዘመነ-መሳፍንት ወቅት በኦሮሞ መሳፍንት፣ በአጼ ቴዎድሮስ፣ በአጼ ተክለ-ጊዮርጊስ እና በአጼ ዮሐንስ 4ኛ ነው።.ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የመጨረሻው ንጉሠ-ነገሥቱ አድርጎ ሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት በ1967 ዓ.ም. ግብአተ-መሬቱ ተፈጸመ። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ቢሆኑ፤ በእናታቸው በወይዘሮ የሺእመቤት አሊ ጋምጬ በኩል የወረዒመኑ ኦሮሞ ነበሩ። ኦሮምኛንም አቀላጥፈው ይናገሩ ነበር።

እንደገና የተመሰረተውን ሰለሞናዊ ሥርወ-መንግሥት አባላት ከመዘርዘሬ በፊት ይኩኖ-አምላክ ሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት መልሶ የተከሰበትን ሁኔታ መግለጽ አግባብ ይሆናል።

ሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት እንደገና እንዲመሠረት ጉልህ ሚና የተጫወቱት በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍ ያለ ክብር የነበራቸውና አሁንም ያላቸው አቡነ ተክለ-ሃይማኖት ናቸው። የዛጉዌ ነገሥታት ቀማኞች ስውድ ነጣቂዎች/ መሆናቸውንና የሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ህጋዊ ወራሽ እሱ (ተስፋ-እየሱስ) መሆኑን ባጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ ደግሞ ለአማራ ጠረኞች በማስረዳት ካሳመኑስትና ወደ ሥልጣን እንዲወጣ ከረዱት የግዛቱን ሲሶ ለኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን እንደሚሰጥ ማስላቸው። መነኩሴውም ተልዕኳቸውን

በደንብ ፈጸሙ። አማራው፣ መደባይ/ኦሮሞና ሌሎቹም ነገዶች ተስፋ-እየሱስ (ይኩኖ-አምላክ) የንጉሥ ሰለሞን እና የንግሥት ሳባ ህጋዊ ወራሽ መሆኑን እንዲያምኑ ብቻ ሳይሆን በሥልጣን ላይ የነበሩት የዛጉዌ ንጉሠ-ነገሥት ነዓኩቶ-ለአብ፣ ዛጉዌ እና ቀዳማዊ ምኒልክ በፈጸሙት ስምምነት መሰረት የበላይ ሆኖ መግዛት ያለበት የምኒልክ ዘር መሆኑን አምነው እንዲቀበሉም አደረጉ።

ንጉሠ-ነገሥት ነአኩቶ ለአብ መንፈሳዊ ሰው ስለነበሩ መነኩሴው ያቀረቡትን ሃሳብ ተቀብለው እስከ ወሰነ-ንግሥናቸው ብቻ ገዝተው ሥልጣናቸውን ለምኒልክ ዘር ለመልቀቅ ተስማሙ። ቀደም ብዬ እንዳልኩት፣ የመጀመሪያው የዛግዌ ንጉሠነገሥት መራ-ተክለሃይምኖት ለልጆቹ በደነገገው ስርዐት መሰረት፥ እያንዳንዱ የዛግዌ ንጉሠ-ነገሥት ለ40 ዓመታት ብቻ ነበር የሚገዛው። አጼ ነአኩቶ ለአብ ዘመነ-ንግሥናቸውን የሚፈጽሙ ከሆነ ተረኛው ንጉሠ-ነገሥት የላሊበላ ልጅ ይትባረክ ስለሆነ ይትባረክ የመነኩሴውን ሃሳብ ውድቅ አደረገው። *"የንጉሥ ነአኩቶ ለአብ ጋሻጃግሬ (የጦርመሣሪያ ተሸካሚ ወይም ያዥ) ለነበረና ምንም የንግሥና ደም ለሌለው ለአንድ መደባይ* (ኦሮሞ) *ለተስፋ-ኢየሱስ የንግሥና ተራየን አልለቅም"* ብሎ ድርቅ አለ።(19) የሚገርመው ነገር፥ አፄ ቴዎድሮስም በዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያን ስለመርዋት የኦሮሞ መሳፍንት ይህን መሰል ነገር ተናግረው ነበር። ለንግሥት ቪክቶርያ በፃፉት ደብዳቤ ላይ፥ እግዚአብሄር የአባቶቼን መንግሥት ከጋሎች መለሰልኝ፤ ብለው። ይትባረክ እና አላቸው ባሉት ላይ ብንመረኮዝ፥ ይኩኖአምላክም እነራስ አሊም ኦሮሞዎች መሆናቸውን እናረጋግጣለን። ምንም እንኳ መነኩሴው ከሁለት ሺ ሁለት መቶ ዓመት በፊት በቀዳማዊ ምኒልክ እና በክፉል ወንድሙ በዛጉዌ መካከል የተፈፀመውን፣ የቀዳማዊ ምኒልክ ዝርያ ብቻ ንጉሠ-ነገሥት ይሆናል የሚለውን ስምምነት ቢያስታውሱትም ይትባረክ አልተበገረም። ንጉሠ-ነገሥት ነኝ ብሎ ዘውድ ደፋና ተስፋ-እየሱስ ባመዛኙ በደንብ የሰለጠኑትን የአማራን ወታደሮችና የኦሮሞን ጦረኞች ይዞ ጦርነት አስክገጠመውና እስከደመሰሰው ድረስ ነገሠ። አቡነ ተክለሃይማኖትም ተናደው ተለዩት። ከዛም ይከበሩና ይደመጡ ስለነበር፥ የአማራን ጭዋ ጦር አስነሱበት። አማራዎቹም የተሰባሰቡት ከወግዳ፥ ከደምቤ፥ ከመገር፥ ከወረብ፥ ከፅላልሽ የዛሬው ቡልጋ፥ ከሙአል፥ ከመራቤቴ፥ ከመንዝ፥

ከተጉለት፥ ከአማራ ሳይንት ሲሆን ከአነሱም ውስጥ በርካታ መደባይ ኦሮሞዎች ነበሩበት። ከነዚህ በተጨማሪ የተስፋ እየሱስን የሰለሞን ዘርነት የአመኑ የላስታ አማሮች የትባረክን ከድተው ተቀላቀሉእቸው። ከዛም በኃይንት፥ አንሰታ ከሚባል ቦታ ይትባረክን ጦርነት ገጥመው ድል አድርገውት ሸሸ። ተሰፋ አየሱስ አሳዶ ገደለውም ይላሉ። ይትባረክ ከተሸነፈ በኂላ የኦሮሞው ዝርያ ተስፋ-ኢየሱስ ‹‹ይኩኖ አምላክ›› ተብሎ ነገሠ እና የሰለሞን ዙፋን በሚባለው ላይ ተቀመጠ። የእሉም ተወላጆች ባብዛኛው ኦሮሞ ሴቶች እያገቡ ለ 700 ዐመታት ኢትጵያን ገዙ።

ነገር ለማላጠር፤ በርግጥ ይኩኖ አምላክ የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ነው? አዎ! በአባቱ በኩል የቀዳማዊ ምኒልክ ዝርያ አለው። በእናቱ በኩል ግን ሐዊ ጊፍቲ መንዲያ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ኦሮሞ ናት። ከይኩኖ-አምላክ ልጆች አንዳንዶቹ የአናታቸውን የዘር ሐረግ ተከትለው በኦሮሞነታቸው የቀጠሉ አሉ። ምንም እንኳ በሥልጣን ላይ ለመቆየት የክርስቲያን ግዕዝ ስም በመያዝ  የሰለሞን ዘር መሆናቸውን ማጣቀስ ቢኖርባቸውም በደም ሥራቸው ውስጥ የሚዘዋወረው ደም ኦሮሞነታቸውን ያረጋግጣል። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አንኳ የእናታቸውን (የወ/ሮ የሺእመቤት ዓሊ ጋምጮን) የዘር ሐረግ ሳያነሱ ባባታቸው በኩል የንጉሥ ሰለሞን 225ኛው ተወላጅ መሆናቸውን ነው ወደ አደባባይ ያወጡት። ምክንያቱም የሺእመቤት አሊ ጋምጮ፥ ከኦሮሞነታቸውም በላይ, በአባታቸው ሙስሊም ነበሩአ። የሰለሞናዊ የሚባለው ዙፋን ላይ ለመቀመጥ አይሁዳዊ-ክርስትያን ነኝ ማለት ግድ ነበር። ወጣቱ ልጅ እያሱ ከሰልጣኑ የተፈነገለው ዋናው ምክንያት በሙስሊምነት ስለተጠረጠረ ወይም በምስጢር ሰልሞአል ተብሎ በጠላቶቹ እና በተቀናቃኞቹ ተወርቶበት ስለነበረ ነው።

እነዚያ ንጉሠ-ነገሥቶች ከንጉሥ ሰለሞን ተወልደናል የሚሉት ሌላው ምክንያት ምን ነበር? ልክ ቀዳማዊ ምኒልክ እንዳደረገው ማድረጋቸው ነዋ! በእርግጥ ቀዳማዊ ምኒልክ ከዚያም አለፍ ብሎ ራሱን ‹‹የንጉሥ ዳዊት ልጅ›› በማለት በአውነትም አያቱ የሆነውንም ጠቅሷል። የንጉሥ ዳዊት ልጅ መሆን ያኮራዋል፤ ምክንያቱም ንጉሥ ዳዊት ታላቅ ነቢይና (በእግዚአብሔር ፈቃድ የተቀባ) ንጉሥ ስለነበረ ነው። በዚያ ላይ ጎልያድን ያህል ኃይለኛ ግዙፍ ሰው ባንዲት የወንጭፍ ጠጠር የገደለ ብሔራዊ ጀግና ነበር። ወላጅ አባቱ ንጉሥ ሰለሞንም

በምድሪቱ ላይ አቻ የሌለው እጅግ ዝነኛና ጠቢብ ሰው ነበር። ስለዚህ ኩሻዊት በሆነችው ኢትዮጵያዊት እናቱ በኢትያ-ኤል /ንግሥተሳባ / ከመኩራት ይልቅ ሴማውያን በሆኑት አባቱና አያቱ ይበልጥ ስለታበየ «የንጉሥ ዳዊትና የሰለሞን ልጅ» ተብሎ መጠራትን መረጠ። ሴማዊው የሰለሞን ደም ተብየው ከ 2260 ዓመታት በኋላ የኦሮሞ ዝርያ በሆነው በይኩኖ-አምላክ ደም ስር ውስጥ ሲደርስ የሟሟ፣ የተበራረዘ፣ የተከላለሰ፣ የደካከመ ነበር።

አሁንም ኩሻውያን የሆኑት የኦሮሞ ተወላጅ ነገሥታትም ሰለሞናዊ እና ሴማዊ ነን የሚሉት ለምንድነው? መልሱ ቀላል ነው፤ ሴማዊው የሰለሞን ዘር ተገዢ በሆኑት ህዝቦች ዘንድ ከመጠን በላይ የሚከበር በመሆኑ ንጉሥ፣ ንግሥት እና ንጉሠ-ነገሥት ለመሆን የሰለሞን ዘር ነኝ ማለት ተቀባይነት ያስገኝ ስለነበረ ነው።

ያም ሆነ ይህ ንጉሠ-ነገሥት ይኩኖ-አምላክ ዋና ከተማውን ሸዋ ውስጥ ተጉለት አድርጎ፣ የሥራ ቋንቋውን አማርኛ እንዲሆን ወሰኖና ራሱንና መንግሥቱን በአማራ ወታደሮችና በኦሮሞ ዘመዶቹ አጥሮና አጠናክሮ ቃሉንም በማክበር ሲሶ መሬት ለቤተክርስቲያን ሰጥቶ፤ የኦሮሞይቷ ልጅ በሰለሞናዊው ዙፋን ላይ ተደላድሎ ጉብ አለበት ። በዚህ መልክ አማራው ለሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት አንደገና መመለስ ድጋፍ መሰጠት ብቻ ሳይሆን በውስጣቸውም ሆኖ ሰለሞናዊ ነኝ ይል የነበረውን የኦሮሞ ዝርያ ንጉሣዊ ቤተሰብ ሰሚቀጥሉት 700 ዓመታትም ደግፎና ጠብቆ አኑሮታል። በዚህ ድርጊቱ ግን ቋንቋ ተስፋፋለት እንጂ አማራው ከመከራ በቀር በግሉ ያተረፈው ነገር የለም። የአማራ ጦረኞች በይኩኖ-አምላክ ሥር ማገልገላቸው ለጦር ሰራዊቱ ይፈቀዱ በነበሩት የማዕረግ ስሞችም የሚረጋገጥ ነው። አማሮች በይኩኖ-አምላክ ጦር ሠራዊት ውስጥ ማገልገል ከጀመሩ በኋላ ነው የቀድሞዎቹ የግእዝ የማእረግ ሰሞች በይፋ ቀርተው በሚከተሉት የአማርኛ ስሞች የተተኩት፡፡--

አቤቶ፣ ቢትወደድ፣ እቴጌ፣ አፈ-ንጉሥ፣ ርዕሰ-መኳንንት አጋፋሪ፣ አዛዥ፣ የክብር-ዘብ፣ ፀሃፊ-ትዕዛዝ፣ ፊታውራሪ፣ አዝማች፣ ባለሟል፣ ሕግ-አስከባሪ፣ ቀኝ-አዝማች፣ ግራ-አዝማች፣ አልጋ-ወራሽ፣ ራስ እና በመሳሰሉት።

ይህ ሁሉ ሲሆን አማራው በስሙ የሚጠራ የይስሙላም ሆነ የምር የራሱ የሆነ ሥርወ-መንግሥት አልነበረውም። ይህ እውነታ ቲጋሩዎቼንም ይመለከታል። ርግጥ በመጀመሪያው ላይ እንዳልኩት ኦሮሞዎችም በስማቸው የሚጠራ ሥርወ-መንግሥት አልመሰረቱም። ሆኖም በተዘዋዋሪ መንገድ በዙፋኑ ላይ ላለፉት 700 ዓመታት ተቀምጠው ሠለሞናዊውን ስርወ-መንግሥት በንጉሠ ነገሥትነትና በንግሥተ ነገሥታትነት ተቆጣጥረውታል። አማሮች ግን የየሀገራቸው ንጉሦች፣ ጠንካራ የጦር መሪዎች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ አስተዳዳሪዎች፣ አገረ- ገዢዎች፣ አስተማሪዎች፣ ምሁራን እና ቀሳውስት፣ እንዲሁም ገበሬዎች እና ነጋዴዎች ሆነው ነው እንደገና በተመሰረተው ሰለሞናዊ ሥርወ-መንግሥት ውስጥ ያገለገሉት። በላስታው በዛጉዌ ሥርወ-መንግሥት ውስጥም እንዲሁ ነው። በሸዋና በጎንደር ፍጹማዊው ሥልጣን የተያዘው ቀደም ሲል እንደተገለፀው፥ የኦሮሞ ዝርያዎች በሆኑ የሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ንጉሠ-ነገሥታት ነን በሚሉቱ ነበር። በርግጥ አማሮች የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ እንዲቀዳጁ ላስቴዎቹ ዛጉዌዎችም ሆኑ ሰሎሞናዊዎቹ ኦሮሞዎች ፈቃደኞች አልነበሩም። ደግሞስ አማሮቹ ተዋግተው ዘውዳቸውን ካልቀሙዋቸው በስተቀር ለምን ይሠጧቸዋል? በዘር ካልወረሱ ወይም ተዋግተው ካላሸነፉ ንጉሠ-ነገሥት አይኮንም አልነበር? እነዚያ የኦሮሞ ዝርያ ንጉሠ-ነገሥቶች ሠፊውን የኦሮሞ ሕዝብ እንደማይወክሉም ግልጽ መሆን አለበት። ንጉሣውያን ቤተሰቦቻቸውን ብቻ ነበር የሚወክሉት። ስለዚህ የኦሮሞ ዝርያዎች የሆኑ ነገሥታት ስልጣን ላይ በመውጣታቸው ብቻ ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ ያገኘው ልዩ ጥቅም አልነበረም።. ነገሥታቱ የሚተጉት ለራሳቸውና የነሱ ለሆኑቱ ምቾት እና ድሎት ብቻ ነበርና።

ከላይ እንደጠቀስኩት የኦሮሞ ሴቶችና ወንዶች ልጆቻቸው በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ውስጥ የኦሮሞ ዘራቸውን የሚሸፍን የክርስቲያን ግዕዝ ስም ይዘው ነበር የሚገዙት። ለምሳሌ ከሴት ኦሮሞ ንግሥታት መካከል የቱሉ በዴላ ልጅ "ፅዮን ሞገሳ"፣ የሐረር ኦሮሞ የገራድ መሐመድ በንቲ ሴት ልጅ "ንግሥት ቀኝ ባልቲሃት ) እሌኒ." (የንጉሠ-ነገሥት በእደ-ማርያም ሚስት)፣ የታላቁ አምደ-ፅዮን ባለቤት ጊፍቲ ዳዲ "ጃንሞገሳ" (ንግሥት ሰብለ-ወንጌል)፣ የገብረ-መስቀል ጀተማ ሴት ልጅ (የአጼ ልብነ-ድንግል ባለቤት) እና ንግሥት ወለተ-

በርሳቤህ (የአጼ ዳግማዊ ኢያሱ ሚስት) ሁለቱም "ውቢት" ተብለዋል። ከዚህ ለየት ባለ መልክ የአጼ ልብነ-ድንግል ባለቤት ብቻ ወላጆችዋ ባወጡላት የኦሮሞ ስም እቴጌ (ንግሥት) "ላሎ ጃሬ" ተብላ ነበር የምትጠራው። የነዚህ እና የሌሎችም ኦሮሞ ንግሥታት ወንዶች ልጆችም የአማራ እንጂ የኦሮሞ ስም አልነበራቸውም። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል ይኩኖ-አምላክ፣ ልብነ-ድንግል፣ እቤቶ ፊቅጦር፣ አጼ ሚናስ፣ አጼ ዮስቶስ፣ አጼ አዲያም ሰገድ ኢያሱ፣ አጼ ቴዎፍሎስ፣ እና አጼ ኢዮኣስ ይጠቀሳሉ።

በርግጥ እነዚህ ነገሥታት በእናቶቻቸው ዘር ኦሮሞዎች ናቸው። ቢሆንም ያፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ከሆነ ጎሣቸው አማራ ይሆናል። ጥንተ-አባታቸው አጼ ይኩኖ አምላክ እንደሚለው አባቱ የአግአዚ ተወላጅ ከሆነ ዘሩ ከፊል ኦሮሞ እና ከፊል አግአዚ ቢሆንም ቋንቋ በመልመጃ ጊዜው ከኦሮሞዋ እናቱ ከጊፍቲ ሃዊ መንዲያ ጋር ስለነበረ ያፍ መፍቻ ቋንቋው ኦሮምኛ በመሆኑ በዘሩም በጎሣውም ኦሮሞነቱ ግልጽ ነው። አባቱ እድም-አሰግድ ከአማሮች ጋር ተጉለት ውስጥ በመኖሩ አፉን የፈታው በአማርኛ ከሆነ ጎሣው አማራ ነው የሚሆነው። እናቶቻቸው ኦሮሞ የሆኑ ዝርያዎቹ አፋቸውን በየትኛው ቋንቋ እንደፈቱ ርግጠኛ አይደለሁም። ግን በህፃንነታቸው በእናቶቻቸው እጅ ስለሚያድጉና የመጀመሪያ ቋንቋቸው ኦሮምኛ ስለሚሆን ጎሣቸውም፣ በከፊል ዘራቸውም ኦሮሞ ነው የሚሆነው። አፋቸውን በአማርኛ ፈትተው ከሆነ ግን ጎሣቸው አማራ ይሆናል። ዘራቸው በናታቸው በኩል ምንም ኦሮሞ ቢሆንም። የጎሣ መስፈረቱ ቋንቋ ነውና። ለንግሥና መስፈርቱ ግን ቋንቋ ሳይሆን የዘር ሐረግ ነው። አንድ ሰው የንጉሣዊ ደም ያለው መሆን አለመሆኑን ማወቅ ሲፈልጉ የሚጠይቁት "ምን ቋንቋ ትናገራለህ?" ብለው ሳይሆን "የማን ዘር ነህ?" ብለው ነበር። የኦሮሞ ነገሥታት በአባት በኩል በዘራቸው የሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት አባላት ነን ቢሉም ቅሉ ሰለሞንነቱ እጅግ እሩቅ በመሆኑ ወሳኙ የቅርቡ ኦሮሞናታቸው ነው። በእውነትም ንጉሣዊ አባልነትን ለማረጋገጥ ቋንቋ መስፈርት አይደለም።

ይህ ማለት ታዲያ እነዚህ የኦሮሞ ዝርያ ነገሥታት ሁልጊዜ ከራሳቸው ነገድ ብቻ ያገባሉ ማለት አይደለም። አልፎ አልፎ ከኦሮሞ ነገድ ውጪም ያገቡ ነበር። ለምሳሌ የአጼ ሰርጸ-ድንግል ሚስት (ማርያም ስና )፣ የአጼ ፋሲለደስ (አደይ ገብረ-አምላክ)፣ የአጼ ዮሐንስ

(ንባበ-ወንጌል)፣ የእጼ እዲያም-ሰገድ ኢያሱ (መለኮታዊት)፣ የአጼ በካፋ (ምንትዋብ) ሚስቶች ኦሮሞዎች ሳይሆኑ የቡግና-ዛጉዌ፣ የላስታ፣ የበሲያ-እገው፣ የትግሬ እና የቋራ ተወላጆች ነበሩ። በአጋጣሚ ይሁን ሆነ ተብሎ ከነዚህ ውስጥ አንዳቸውም አማራ አይደሉም።

ከነዚህ ንግሥታት ውስጥ የአጼ በካፋ ባለቤት ንግሥት ምንትዋብ ብቻ በጣም ተከባሪና ተደማጭ ነበረች። የፖርቹጋል ደም ያላቸው የቋራው ባላባት የግራዝማች እሸቴ ልጅ ናት። ከበሲያ እገው የተገኘችው ንባበ-ወንጌል ቀደም ሲል ቡለን የምትባል የሸናሻ ንግሥት ስትሆን ከንስሐ አባታቸው ጋር በፈፀመችው ዝሙት በፃድቁ ቀዳማዊ ዮሐንስ ተዋርዳ የተፈታች ናት። የገዛ ልጆቿን እንኳ በድርጊትዋ ስላሳፈረቻቸው ዐይንሽን ላፈር ብለዋታል። የአክሱማይት ባለባት ልጅ የሆነችው እቴጌ መለኮታዊት በባለቤትዋ በእጼ ኢያሱ አዲያም ሰገድ ግድያ ከእንጀራ-ልጅዋ ከእርጉም ተክለ-ሃይማኖት ጋር አባሪ ተባባሪ በመሆንዋ ባደባባይ ተለቅላለች። እነዚህ ንግሥታት ሁሉም የንጉሣውያን ቤተሰብ ዓባላት እንደነበሩ ግልጽ መሆን አለበት። ኦሮሞ ሆኑም አልሆኑም የባላባቶች እና የንግሥቶች ልጆች ነበሩ። ማህበራዊ ደረጃቸውን "ዝቅ ላለማድረግ" መሣፍንቱ ከተራው ሕዝብ ጋር አይጋቡም ነበር። ጋብቻ ሁልጊዜ ፖለቲካዊ ዓላማ ነበረው። ገዢ መደቦች የሥልጣን ሽኩቻቸውን ለማርገብና መንግሥታቸውን ለማደላደል እርስ በርሳቸው በጋብቻ ይተሳሰራሉ። ጠንካራ መሳፍንት ወይም አደገኛ ጠረኞች ሲነሱባቸው ነገሥታቱ ሴት ልጆቻቸውን ወይም የቅርብ ዘመዶቻቸውን ልጆች ይድሩላቸውና ያለሰልሱእቸዋል። አንዳንድ ጊዜማ ሴት ልጆቻቸው ወይም የዘመዶቻቸው ሴቶች ልጆች ደከም የሚሉ ገራም ባሎቻቸውን ፈትተው ለአልጋው እስጊ የሚሏቸውን ሃይለኞች እንዲያገቡ ያስገድዷቸው ነበር። በንጉሣውያን ቤተሰብ ዘንድ ለፖለቲካዊ ጥቅም እንጂ ለፍቅር እና ለስሜት ቦታ አልነበረም። ሴቶች ፖለቲካዊ ትስስሮሽን ለማጠንከርና አጣብቆ ለማኖር ደህና መሳሪያ ነበሩ። ከዛሬ 2850 ዓመት በፊት ከእጼ አክሱማይት ዘመን ጀምሮ እስከ 1967 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ፍጻሜ ድረስ ሁሉም ነገሥታትና መኳንንት ሴት ልጆቻቸውን ለሃይለኛና ዝነኛ ወንዶች ያለምንም ማስታጎል ድረዋል። የኢትዮጵያ ታሪክ ጠባይ እንደዚያ ነበር።

ወደ ኦሮሞ ንግሥቶች ስንመለስ፤ የቅርብ ወዳጆቻቸውን እና ዘመዶቻቸውን ወደ ዙፋኑ በማቅረብ፣ ንጉሥ እና ራስ እያሉ በመሾም

ነው እንጂ በራሳቸው ብቻ አልገዙም። ሁለት ንግሥቶችን፣ ጽዮን ሞገሳ ሣልሳዊትን እና ወለተ-በርሳቤህን በማንሳት ይህንን ነጥብ ላብራራው። ሳልሳዊ ንግሥት ጽዮን ሞገሳ ከ500 ዓመት በፊት ፈይሣ ቱሉ/ዶሪ/ የተባለውን ወንድሟን አንግሣ የኤርትራ ክፍለ-ሀገር ገዢ አድርጋ ሾማለች። አባትዋ ቱሉ በዴላም በመላ ግዛትዋ በጣም ተደማጭነት ነበራቸው።

ንግሥት ወለተ-በርሳቤህ ኢትዮጵያን ከ1723 እስከ 1747 ዓ.ም የገዛውን ንጉሠ-ነገሥት ዳግማዊ ኢያሱ ብርሃን ሰገድን ካገባች በኋላ ባልዋ ሲሞቱ የ17 ዓመት ልጅ የነበረውን ኢዮአስ የተባለውን ልጅዋን ይዛ ኢትዮጵያን መግዛት አሰበች። ልክ እቴጌ ምንትዋብ እጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ በህጻንነቱ አባቱ ሲሞቱበት ራስዋን ለመጠበቅና ሥልጣንዋን ለማጠናከር ወንድሞቿን ከቋራ አምጥታ ዙሪያዋን እንዳጠረችው እሷም አደረገች። በሁለቱ እቴጌዎች መካከል የሥልጣን ሽኩቻ ፈነዳ። የእቴጌ ወለተ-በርሳቤህ ኦሮሞ ወንድሞች ባልጋዳ ሊቦ እና ብርሌ እህታችንን እንጠይቃለን በሚል ሰበብ በ1900 ፈረሰኞች የታጀበ ጦራቸውን ይዘው ከየጁ ወደ ጎንደር መጡ። ንግሥት ወለተ-በርሳቤህ ለወንድሞቼ ማረፊያ ቦታ ይሰጥልኝ ሲሉ ለባላቸው ለንጉሠ-ነገሥቱ አመለከቱና ከቅማንት መሬት ላይ ቆርሰው ስለሰጧቸው እዚያ ሰፈሩ። ከዚያን ጊዜ በኋላ ያ ቦታ ‹‹የጋላ መሬት›› ተባለ።(20) ንግሥት ወለተ-በርሳቤህ እንዴ ሥልጣንዋን ካጠናከረች በኋላ አባትዋን ‹‹የእንደርታ አዛዥ››፣ ወንድሞቿን ሊቦንና ብርሌን እንደ ቅደም ተከተላቸው ፊታውራሪ እና ቀኛዝማች አድርጋ ሾመች። ራስ ወልደ-ሥላሴን ከባለ ሙሉ ሥላጣን እንደራሴነት ሥልጣናቸው ከሻረች በኋላ ወንድሟን ፊታውራሪ ሊቦን ተካች። ሆኖም ከፍ ባለ ተቃውሞ ተደናቀፈ። በወላጅ እናቱ እና በአያቱ መካከል የተነሳውን ረብሻ ለማስቆም አጼ ኢዮአስ ራስ ሣህለ-ሚካኤል ስሁልን ከትግራይ አስመጥቶ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴው አድርጎ ሾማቸው። ቆይቶ ግን ራስ ሣህለ-ሚካኤል ሥሁል (በጦር ሜዳ ላይ ሊያስገድለኝ ሞክሯል በሚል ሰበብ፥ ደግሞም እውነትም ሊያስገድላቸው በማሴሩ) አጼ ኢዮአስን በአድርባይ ቀሳዋስት አስፈርደው በሻሽ አሳንቀው ገደሉት እና ሥልጣኑን ወስደው አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥት አነገሡበት። ይህም ድርጊት ‹‹ዘመነ-መሣፍንት››ን አስከተለ። በላቸው እግር የተተኩት የኦሮሞ ባለሙሉስልጣኖች እንደዚሁ አሻንጉሊት ሰለሞናዊ ነገሥታትን

ለወጉ አልጋው ላይ አያስቀመጡ በተከታትይ ራሳቸው ከ 60 ዐመታት በላይ ዘመኑን የመሳፍንት አድርገው ገዙ።

ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ኦሮሞዎች ከሌላው ይልቁ የነበረው በጎንደር ብቻ ሳይሆን በሱስንዮስ ዘመን በጎጃምም ጭምር ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በጎንደር በአጼ ሱስንዮስ ዙሪያ በርካታ የኦሮሞ ሹማምንት ነበሩ።

ስለ ልዑል ሱስንየስ ጥቂት ለማለት፣ በ1571 ዓ.ም የተወለዱት ልዑል ሱስንዮስ በወጣትነታቸው ባንድ ጦርነት ላይ በቦረን ጎሣ ተማርከው አንድ የኦሮሞ ባላባት እንደ ልጁ አድርጎ አሳደጋቸው። ልዑል ሱስንዮስ የኦሮምኛ ቋንቋ እየተማሩ በኦሮሞ ባሕል ሥርዓት መሰረት አደጉ። ኦሮሞዎች በወዳጅነት እንደ ልዑል ተንከባከበው አሳደጓቸውና 18 ዓመት ሲሞላቸው የምርኮኛ ልውውጥ ሲደረግ ልዑሉ ከዘመዶቻቸው ጋር ተቀላቀሉ። በ1597 ዓ.ም አጼ ሰርፀ-ድንግል ሲሞቱ ሱስንዮስ ይነግሣል ብለው የሰጉ ዘመዶቻቸው ሊገድሏቸው ሲያደቡ ወጣቱ ሱስንዮስ ከለላና ጥበቃ ለማግኘት ወደ ቀድሞ ወዳጆቻቸው ወደ ኦሮሞዎቹ ተመለሱ። ኦሮሞዎቹም ሱስንዮስን እንደገና እንደ ልዑል ተቀበሏቸውና ከዚያም በላይ መሪያቸው አደረጓቸው። የኦሮሞ ወታደሮችን ይዘው ለዙፋኑ ከዘመዶቻቸው ጋር በርካታ ጦርነቶችን ካካሄዱ በኋላ በ1604 ዓ.ም ጎጃም ውስጥ ሞጣ ቀራንዮ ላይ ነገሡ። ከዚያም ኢልማና እና ዴንሳ የተሰኙ ሁለት የጦር ሰፈሮችን ጎጃም ውስጥ መሰረቱ እና የኦሮሞ ወታደሮችን/ጨዋዎችን (ነፍጠኞችን ማለት ነው) በአማራ ጭሰኞች ላይ ተሰሪነት አስገቡባቸው። ከኦሮሞ ነገድ ውስጥ ሱስንዮስ ነፍጠኞች ያደረጓቸው የሜጫን፣ የቅሮን እና የባሶ ኦሮሞዎችን ነበር። (21) ኢልማና እና ዴንሳ የተባሉት ሁለት የኦሮሞ የጦር ክፍሎች ሰፈሮች ዛሬ በጎጃም ውስጥ ሁለት መንደሮች ሆነው በታሪክነት ቅርስ ይኖራሉ።

የጎንደር አማሮች በመጀመሪያ ለሱስንዮስ የገቡ መስለው አንገብርም ብለው ሲያሞኙት ጎንደር ከተማን እንዲያጠፏት የኦሮሞ ጦሩን እንደገና አዟል። ይህንን ሦስት ጊዜ ፈጽሞታል። ይህን የቁጣ ድርጊት አጼ ቴዎድሮስም በዘመናቸው በጎንደር ላይ ያለርህራሄ አካሂደውታል።

አጼ ሱስንዮስ ጊዜ የፈተናቸውን የኦሮሞ ወታደሮቻቸውን ብቻ ነበር የሚያምኑት። ከነሱ መካከል በርካታዎችን ወደ ከፍተኛ ማዕረግ አሳድገው ቤተ-መንግሥታቸውን በነሱ ሞሉት። በጊዜ ሂደት ውስጥ ግን ከአዲሶቹ ኦሮሞ ወዳጆቻቸው ጋር ብቻ መሆን አበዙና ለጥንት ኦሮሞ ወዳጆቻቸው፣ ለአማሮች እና ለሌሎችም ነገዶች አባላት የሚሰጡት ጊዜ ታጣ። በዚህ ምክንያት እንደመሪያቸው ይመለከቷቸው የነበሩትን የፊት የኦሮሞ ተከታዮቻቸውን ቀስ በቀስ ችላ እያሉዋቸው ስለመጡ እነዚያ የቀድሞ ወዳጆቻቸው እንደተካዱ ቆጥረውት ታማኝነታቸውን ሲቀንሱ ሌሎቹ ግን በታማኝነት ማገልገላቸውን እስከመጨረሻው ቀጥለዋል።

የሚከተለው ሰሌዳ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከኦሮሞ ጋር ተያያዥነት የነበራቸውንና የኦሮሞ ስም ሳይኖራቸው እንደገና በተመሰረተው "ሰለሞናዊ ሥርወ-መንግሥት" ውስጥ ኢትዮጵያን የገዙ ባብዛኛው የኦሮሞ ዝርያ የሆኑና ከሌሎችም የተካለሱ ነገሥታትን ዝርዝር የያዘ ነው። በሸዋ እና በጎንደር ከመጀመሪያው (አጼ ይኩኖ-አምላክ የኦሮሞእዋ የጊፍቲ ሃዊ መንዲያ ልጅ) እስከ መጨረሻው፥ እስከ ፍፃሜ-መንግሥት ኢዮአስ፥ (የወሎዋ ኦሮሞ የዋቢ ወይም እቴጌ ቤርሳቤህ ልጅ) እና እስከ ዘመነ-መሳፍንት መጀመሪያ ድረስ የነበሩ ነገሥታት በዝርዝሩ ተካትተዋል። ከእነዚህ በርካታዎቹ የኦሮሞ ዝርያዎች ቢሆኑም ሁሉም የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን እምነት ተከታዮች ነበሩ።

| ስም | ዘመነ-ንግሥና (ዓመት) |
|---|---|
| ተስፋ-ኢየሱስ (ይኩኖ-አምላክ) | 15 |
| አግባፅዮንአ | 09 |
| ባሕር-አስግድ | 01 |
| እንስ-ጽዮን | 01 |
| ጽንፈ-አሰግድ | 01 |
| ፍሬሃይማኖት | 01 |
| ኪድመ-አሰግድ | 01 |
| ኢሙን (ጃን አሰግድ) | 01 |
| አር'እድ | 07 |

| | |
|---|---|
| እምደ-ጽዮን ፤ | 30 |
| ንዋዬ-ክርስቶስ (ሰይፍ-አርእድ) | 28 |
| ንዋዬ-ማርያም (ውድም-እስፍሪ) | 10 |
| ቀዳማዊ ዳዊት | 29 |
| ቀዳማዊ ቴዎድሮስ | 04 |
| ይስሐቅ (ገብረ-መስቀል) | 15 |
| እንድርያስ (ጻን-ሀርቤ) | 6 ወራት |
| ተክለ-ማርያም (ሕዝበ-ናኝ) | 04 |
| ሥርወ-ኢየሱስ (ምህርቃነ ናኝ) | 4 ወራት |
| እምደ-ኢየሱስ(በድል-ናኝ) | 8 ወራት |
| ዘርአ'ያእቆብ (ቆስጠንጢኖስ) | 34 |
| በ'እደ-ማርያም | 10 |
| እስክንድር | 17 |
| እንድርያስ (ዳግማዊ አምደ-ጽዮን ) | 6 ወራት |
| ናኦድ | 18 |
| ልብነ-ድንግል | 32 |
| ገላውዴዎስ | 19 |
| ሚናስ | 04 |
| ሰርፀ-ድንግል | 34 |
| ያቆብ | 07 |
| ዘድንግል | 01 |
| ሱስንዮስ | 28 |
| ፋሲለደስ | 34 |
| ቀዳማዊ ዮሐንስ | 15 |
| ቀዳማዊ ኢያሱ | 24 |
| ዳግማዊ ተክለ-ሃይማኖት | 02 |
| ቴዎፍሎስ | 03 |
| ዮስቶስ | 05 |

| | |
|---|---|
| ዳዊት (አድባር-ሰገድ) | 05 |
| በካፋ | 10 |
| ዳግማዊ ኢያሱ | 25 |
| ኢዮአስ | 14 |

ባለፈው ጊዜ እንዳመለከትኩት፥ የይኩኖአምላክ አባቱ እድምአስግድ ከአማሮች ጋር ተጉለት ስለኖረ የመጀመሪያ ቋንቋው አማርኛ ከሆነ ‹‹በዘሬ ሰለሞናዊ-አይሁዳዊ ነኝ፣›› ቢልም፥ ጎሣው አማራ ነበር ብለን እንገምታለን፡፡ እናቶቻቸው ኦሮሞ የሆኑ የይኩኖ አምላክ ተወላጆች በልጅነታቸው መጀመሪያ በየትኛው ቋንቋ እንደተናገሩ አሳውቅም። መጀመሪያ የተናገሩት ኦሮምኛ ከሆነ ጎሣቸው ኦሮሞ ነበር፡፡ መጀመሪያ የተናገሩት ኦሮምኛ ይሆናል ብዬ አገምታለሁ፤ ምክንያቱም የሚያድጉት ከእናቶቻቸው ጋር ስለሆነ፡፡ የመጀመሪያ ቋንቋቸው አማርኛ ከሆነ ግን የጎሣ መስፈርት ቋንቋ ስለሆነ ጎሣቸው አማራ ነው የሚሆነው፡፡ ለንግሥና የንጉሥነት መስፈርቱ ግን ቋንቋ ሳይሆን የዘር ሀረግ ነው፡፡እላይ ጠቅሼው የነበረውን ለመድገም፥ አንድ ሰው የንጉሣዊ ደም ያለው መሆን አለመሆኑን ማወቅ ሲፈልጉ የሚጠይቁት “ምን ቋንቋ ትናገራለህ?” ብለው ሳይሆን “የማን ዘር ነህ?” ብለው ነበር። የኦሮሞ ነገሥታት በአባት በኩል በዘራቸው የሰለሞናዊው ሥርው መንግሥት አባላት ነን ይሉ ነበር፡፡ የንጉሣዊ አባልነትን ለማረጋገጥ ቋንቋ መስፈርት ባለመሆኑ ግን እነዚህ ልዑላን የይሁዳ ነገድ፣ ዘረ-እስራኤል ነን ለማለት ከጎሣ ይልቅ በነገድ ላይ ያተኩሩና ርቀው ይቆጥራሉ። ነገዶቻቸው ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን እናውቃለን። በዙፋኑ ላይ መቀመጥ የሚቹሉት የሰለሞን ዘር የሆኑ ናቸው ብለው በሚያምኑት ኢትዮጵያውያን ዘንድ ህጋዊነት እና ተቀባይነትን ለማግኘት ግን አልጋው ይገባናል የሚሉ ልዑላን የይሁዳ ነገድ፣ ዘረ-እስራኤል መሆናቸውን ዘራቸውን ቆጥረው ማስረገጥ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት የኦሮሞ ተወላጅነት ወይም ተያያዥነት ያላቸው ነገሥታት ሁሉም ቀደም ሲል እንደተገለፀው ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ የንጉሥ ሰለሞን እና የአግአዚ ዝርያዎች ነን ይሉ ነበር። በዝርዝሩ መጨረሻ ላይ የተጠቀሰው አጼ ኢዮአስ (የወሎዋ ኦሮሞ

የወለተ-በርሳቤህ ልጅ) በትግራዩ መስፍን በራስ ሣሕለ-ሚካኤል ሥሑል እስከተገደለበት እስከ 1748 ዓ.ም ድረስ እውነተኛ ፍፁማዊ ሥልጣን የነበረው የሰለሞን ሰርወ-መንግሥት የመጨረሻ ንጉሠ-ነገሥት ነበር። በዚህም ምክንያት ፍፃሜ-መንግሥት ይባል ነበር። ከእሱ መገደል በኋላ እስከ ዘመነ መሳፍንት ፍፃሜ፥ የግዛቱን ሉዓላዊነትና የገዢነቱን ፍፁማዊነት ሙሉ በሙሉ አስጠብቆ የመራ ንጉሠ-ነገሥት የለም። ቀደም ሲል እንዳልኩት የሱ ሞት ዘመነ-መሳፍንትን አስከትሏል።

# የዘመነ መሳፍንት ክስተት

በእናቱ በወለተ-ቤርሳቤህ (ዋቢ) በኩል ኦሮሞ የነበረውን አጼ ኢዮአስን ከገደሉ በኋላ ራስ ሣሕለ-ሚካኤል ሥሑል እሻንጉሊት ንጉሥ እንግሠው በቅርፁም ሆነ በይዘቱ ከዛሬው የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣን በጣም በሚበልጠው በ ‹‹ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴነት›› በጦርነት አስከሚባረሩ ድረስ አዛዥ ናዛዥ ሆነው ገዝተዋል፡፡ ዘውድ ያልደፉበት ምክንያት፣ ምንም እንኳ የአጼ ፋሲል ተወላጅ ቢሆኑም የሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ቀጥተኛ ዝርያ ነኝ የሚሉበት ምንም ስበብ ስላልነበራቸው ህዝቡን በመፍራታቸው ነው፡፡ የአጼ ኢዮአስን ሞት ተከትሎ የደረሰ ምንም ቀውስ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም "ባለ-ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መሆን ያለብኝ እኔ ነኝ" የሚል ማንኛውም ጉልበት ያለው መስፍን ሳልጋው ያስጋሉ ተብለው የሚታሰቡ የንጉሣውያን ቤተሰብ አባላት ተግዘው/ታስረው/ ከሚጠበቁበት ከ"ወህኒ አምባ" እሥር ቤት አንዱን ልዑል ጎትቶ አምጥቶ ለስሙ ዘውድ ጭኖለት በዙፋኑ ላይ ያስቀምጠውና ራሱን "ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ" ብሎ የእውነተኛው ሥልጣን ባለቤት በመሆን ኢትዮጵያን ማዘዝና መግዛት የሚችልበት ወቅት ስለነበረ ነው፡፡

ንጉሥ ሹዋሚና እና ሻሪ የሆኑት እንደራሴዎቹ ራሳቸው ዘውድ ደፍተው፣ ዙፋን ላይ የማይቀመጡበት ምክንያት ሰፊው ሕዝብ "ዘውድ ነጣቂ" ብሎ ይቀጣናል ብለው ይፈሩ ስለነበረ ነው፡፡ በፊውዳሏ ኢትዮጵያ የተለመደው የወቅቱ ስልት እንደዚያ ነበር፡፡-- ከወህኒአምባ አንዳንድ እቅመ-ቢስ ልዑላንን ጎትተው አያመጡ እነሱን ለይስሙላ አልጋው ላይ አስቀምጠው መግዛት፡፡ የእያንዳንዱ መስፍን ምኞትና ተግባር የዘመኑ ፊሊጥ ይኸው ነበር፡፡

ከነዚህ ገናና መስፍንት መካከል አንድ ቤተሰብ የሆኑ የየጁ ኦሮሞዎች ይገኙበታል። የሴሩ ጉዋንጉል ዝርያ የሆኑት እነዚህ የየጁ ኦሮሞዎች ከትልቁ ራስ ዓሊ እስከ ትንሹ ራስ ዓሊ ድረስ ያሉት፣ ካሳ ኃይሉ (ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ) ትንሹ ራስ ዓሊን ድል አድርገው ንጉሠ-ነገሥት ተብለው በ1847 ዓ.ም ዘውድ እስከ ደፉበት የትንሹ ራስ ዓሊ ዘመን ፍፃሜ ድረስ ‹‹ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ›› እየሆኑ በተከታታይ ኢትዮጵያን በከፊል የገዙ መስፍንት ናቸው። ኢትዮጵያን በከፊል ለ61 ዓመታት የገዙ 11 ‹‹ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴዎች›› አሉ። ከነዚህ ውስጥ ምንም እንኳ ሁለቱ የአማራ ስም ቢኖራቸውም ስምንቱ ኦሮሞዎች ናቸው። አንዱ ቀደም ሲል የተጠቀሱት የትግሬው ሚሕስ-ሚካኤል ሥሑል ሲሆኑ ሁለቱ ከላስታ ነበሩ። የሁሉም መስፍንት ስም እንደ ቅደም ተከተላቸው ቀጥሎ ቀርቧል፤

ራስ ሚሕስ-ሚካኤል ሥሑል (ትግሬ)፤ ራስ ጎሹ (የቦረና ባላባት ኦሮሞ)፤ ራስ ዓሊና ራስ ዓሊጋዝ (ኦሮሞ)፤ ራስ ዓሥራት እና ራስ ወልደ-ገብርኤል (ላስታ አገው ወይም አማራ)፤ ራስ ጉግሳ ራስ ይማም (ኦሮሞ)፤ ራስ ማርዬ (ኦሮሞ)፤ ራስ ዶሪ (ኦሮሞ)፤ ራስ ዓሊ ትንሹ (ኦሮሞ)። ሁለቱ ላስታዎች አማራ ካልሆኑ ከነዚህ ገዢዎች መካከል አንድ እንኳ አማራ የለም ማለት ነው። አገውም እንዲሁ። ምንም እንኳ የየጁ ቤተ-ኦሮሞ የሆኑት የሴሩ ጓንጉል ልጆች የአረብ ስም ያላቸው ቢሆኑም ጥብቅ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን አባል ነበሩ። የአረብኛዎቹ ስሞቻቸው ያሳስታሉ። አንድ ሰው በአረብኛዎቹ ስሞች ተመርቶ ስዎቹ ሙስሊሞች ናቸው ብሎ መደምደም የለበትም። አብያተ-ክርስቲያናትን የሚያስገነቡ፥ ገንዘባቸውንና ርስታቸውን ለቤተ-ክርስቲያናት የሚቸሩ ጥብቅ ክርስቲያኖች ነበሩ። ትንሹ ራስ ዓሊ ብቻ በዋና ከተማቸው በደብረ-ታቦር አምስት ቤተ-ክርስቲያኖችን አሠርተዋል። እነዚህ የኦሮሞ ዝርያ ያላቸው መስፍንት ኦሮምኛን ቢያቀላጥፉም አማርኛ አጥርተው የሚናገሩ፣ በግዕዝ ፊደል የሚፅፉ፤ ለብዙሃኑ መግባቢያ የአንድ ብሔራዊ ቋንቋ አስፈላጊነት የገባቸው ብልሆች ስዎች ነበሩ። አማርኛ ብዙ የተሰራጨና ተወዳጅ መሆኑን በመረዳታቸው የመንግሥታቸው ቋንቋ አድርገውታል። ፍጹማዊ ሥልጣን ስለነበራቸው ኦሮምኛን ብህዝቡ ላይ መጫን ይችሉ ነበር። እነሱ ግን ያንን ማድረግ ጠቃሚ መስሎ ስላልታያቸው አማርኛን መንግሥታዊ ቋንቋ አደረጉት።

ትግሬው አጼ ዮሐንስ ዐራተኛውም እንዲሁ ነበር ያደረጉት። ለንግግርም ሆነ ለጽሑፍ በአደባባይ በአማርኛ፣ በግላቸው ደግሞ በትግርኛ ይጠቀሙ ነበር። የወቅቱ ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ መንግሥትም አማርኛን የመሥሪያ ቋንቋው በማድረጉ፣ አጼ ዮሐንስ ዐራተኛ ያደረጉትን ነው እየተገበረ ያለው። የኢህአዴግ መንግሥት ለህልውናውና ለጥቅሙ ሲል እስካሁን ያደረገው ብልህነት ሲሆን ለወደፊቱም የሌሎች ነገዶች ቋንቋዎችን በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ በአብሳጨው ህዝብ የሚነገረውን ኦሮምኛን ከአማርኛ ጎን ለጎን እንዲበለጽግ እሱም ሆነ እሱን የሚተካው መንግሥት ማበረታታት ይኖርበታል። የማይናቅ ጉልበት ስለነበረው ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ቢፈልግ ኖሮ ትግሪኛን ብሄራዊ ቋንቋ ለማድረግ ምንም የሚያግደው ኀይል ባልነበረም ነበር። ለቀለጠፈ አስተዳደር ነገሩ እንደማያዋጣ በብልህነት በመገንዘቡ እና የማያስፈልግ ቅዋሜንም ለመጋበዝ ስላልፈለገ ግን የተለመደውን እና አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚናገርበትን ከተወለደ ከ 3600 ዐመታት የማያንሰውን አማርኛን እንዲቀጥል አደረገ። ወደፊት የሚመጣውም መንግሥት ሥራውን ሊያቀላጥፍ የሚችለው ይህን ከአደረገ ብቻ ነው። አላይ እንዳልኩት እንደ ሁለተኛ የሥራ ቋንቋ ከአማርኛ ጎን ለጎን ቀስ በቀስ ኦሮምኛንም ማዳበር ይቻላል።

የተከበሩትን ታላቁን የኦሮሞ መሪ ትልቁ ራስ ዓሊን መሪው እንዲሆኑ ያጫቸው የጎንደር ሕዝብ ሲሆን የሳቸው ዘመድ የሆኑት እዛዥ ጉግሳም የተሾሙት በላስታው ራስ ወልደ-ገብርኤል ነበር። ትልቁ ራስ ዓሊ እስከ ዛሬ ባለው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በለፊው ሕዝብ መልካም ፈቃድ ሥልጣን የያዙ የመጀመሪያው መሪ ሳይሆኑ አይቀሩም። አጼ ተክለ-ጊዮርጊስ ለስሙ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት በነበሩበት ወቅት ከባድ ግብር በመጫንና ሌሎች በደሎችንም በማድረስ የጎንደርን ሕዝብ ያለ ርኅራኄ ጨቁነውት ነበር። እንደራሴያቸው ትልቁ ራስ ዓሊ ግን የጎንደር ሕዝብ በንጉሠ-ነገሥት ተክለ-ጊዮርጊስ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ እንዳች ለመወሰን ባደረገው ምስጢራዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተው የንጉሠ-ነገሥቱን ኢፍትሐዊነት ተቃውመው ለሕዝቡ ያላቸውን ድጋፍ ገለፁ። ሕዝቡም ሥልጣኑን ራሳቸው ወስደው እንዲታደጓቸው ትልቁ ራስ ዓሊን ተማፀናቸው። በዚህ የተነሳም ትልቁ ራስ ዓሊ ‹‹የጁ ሄጀ የታመሙ እናቴን ለመጠየቅ ፈቃድ ይሰጠኝ፣››





ብለው ንጉሠ-ነገሥቱን ለመኑ። ተፈቅዶላቸው ሄዱና ከየጁ በሺ የሚቆጠሩ ፈረሰኞችን አምጥተው ቤተ-መንግሥቱን አስከበቡና አጼ ተክለ-ጊዮርጊስን ከሥልጣን አወረዷቸው። ራስ ሚካኤል ሥሑል እንዳደረጉት አሻንጉሊት ንጉሥ እንግሠው ባለሙሉ-ሥልጣን እንደራሴ ሆኑና ከፊል ኢትዮጵያን ራሳቸው ማስተዳደር ጀመሩ። ይህም የኦሮሞ መሳፍንት ሥርወ-መንግሥት ጅማሮም ሆነ። ቢሆንም ኦሮሞ ያልሆኑት የሴት ዘመዳቸው፣ የከፊይ ሴሩ ጓንጉል ልጅ ራስ ጉግሳም በሴሎች ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነው ተሹመው ነበር። ራስ ወልደ-ገብርኤል በሚል ስም የተሾሙ ላስቴ ነበሩ። ራሱ ከገዛ ወንድማቸው ከራስ እሥራት ጋር ጦርነት ውስጥ ከመግባታቸው በፊት እህታቸውን ወ/ሮ ሎሚትን ለእዛዥ ጉግሳ ዳሩና ተጠባባቂ ባለ-ሙሉ ሥልጣን እንደራሴያቸው አድርገው ሾሟቸው። ጦርነቱ በዚህ ቀረ።(23) እድል ከራስ ወልደ-ገበርኤል ወደ እዛዥ ጉግሳ ፊትዋን አዙራ ራስ እረፉ እና እዛዥ ጉግሳ ራስ ተብለው አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥቶችን በኢትዮጵያ ላይ እንደፈለጉ የሚሾሙ የሚሽሩ ኦሮሞ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆኑ።ቀድሞ እናቱ ኦሮሞ በነበረችው አፄ ኢዮአስ ላይ አብቅቶ የነበረው በሰለሞን ስርወ-መንግሥት ስም ኢትዮጵያን ያስተዳደረው የኦሮሞ አመራር፤ አዲስ ስልት ቀይሶ አሁን ደግሞ የኦሮሞ መሳፍንትን አስልጣን ማማ ላይ አስቀመጣቸው።

ኦሮሞዎች ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ እየሆኑ በኢትዮጵያ ላይ ሲያዙ ኦሮሞ ያልሆኑት ባላባቶች ቀኑባቸው፣ ጠሏቸው፣ ከሥልጣን ሊያወርዷቸውም አሰቡ። ምንም እንኳ ያልተሳካ ቢሆንም አንዳንነዶቹ ጦርነት አነሱ። እርስ በርሳቸውም ለሥልጣንና ለግዛት መሬት ብለው ይዋጉ ጀመር፤ ሁሉም ‹‹ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ›› መሆን አማራቸው። በባላንጣዎቹ ተጠላም ተወደደ የኦሮሞ መሳፍንት “ሥርወ-መንግሥት” ኢትዮጵያን ከ60 ዓመት በላይ በደንብ ገዝቷል። ለዚያ ስኬት ያበቃቸው ምስጢር ምንድነው? ምስጢሩ ሌላ ሳይሆን የነበራቸው ብልጠት እና ያስፈኑት መልካም አስተዳደር ነው። ብልጠታቸው ምንድነው? ያንዱን ግዛት ቆርሰው ለሌላው በመስጠት ታማኝ ከሆኑላቸው የበለጠ እንደሚሰጧቸው ቃል እየገቡ ተቀናቃኞቻቸውን እርስ በርሳቸው ማናከስ መቻላቸው ነው። ያስፈኑት መልካም አስተዳደርስ ምንድነው? የሚገዙትን ሕዝብ አለመጨቆናቸው፣ ዜጎቻቸውን ከጥቃት እየጠበቁ መንከባከባቸው፣

አብያተ-ክርስቲያናትን ማስራታቸው እና ለህዝቦቻቸው ደህንነት የሚያስቡ መሆናቸው ነው።

የሴሩ ጓንጉል ልጆች ሥርወ-መንግሥት በጎጃም፣ በጎንደር እና በትግራይ በሚገዛበት ወቅት ከነዚህ ክልሎች ውጪ በወሎ፣ በሸዋ እና በጊቤ ወንዝ ዙሪያ የነበሩ የኦሮሞ ባላባቶችና የጎሣ መሪዎች ግዛቶቻቸውን ለማስከበር እየታገሉ የየግል ኑሮአቸውን በመኖር ላይ ነበሩ። የሸዋ ኦሮሞዎች የተደራጀ የመንግሥት መዋቅር ስላልነበራቸው በእናቱ ከቱሉ በዴሳ ልጅ ከኦሮሞዋ ከንግሥት ናኦድ ሞገሳ ለሚወለደው ለአጼ ልብነ-ድንግል ልጅ ይገብሩ ነበር። አጼ ልብነ-ድንግል ከአህመድ ኢብራሂም መሐመድ ግራኝ ሸሽተው ወደ አማራ ሳይንት እና ወደ ትግራይ ከመሰደዳቸው በፊት አቤቶ ያቆብ የተባለ ልጅ ነበራቸው። በዘመነ-ግራኝ ነፍሱን ለማትረፍ ሌላ ሰው ተመስሎ በሸዋ ውስጥ ተደብቆ ይኖር ነበር። ወንድሙ አጼ ገላውዴዎስ አህመድ ግራኝን ድል ካደረጉ በኋላ ወደ ደንገዝ ሄዶ ከወንድሙ ከአጼ ገላውዲዎስ እና ከመደባይ/ኦሮሞ እናቱ ከንግሥት ሰብለ-ወንጌል ጋር ተገናኘ። ወንድሙ እና እናቱ አቤቶ ያቆብን ከፍ ባለ ሹመት ሾሙትና የመንግሥታቸው ተወካይ እንዲሆንላቸው መልሰው ወደ ሸዋ ላኩት። ሸዋ መጥቶ የንጉሥ ሣህለ-ሥላሴ፣ የሃይለ-መለኮት እና የዳግማዊ ምኒልክ ስሮች የሚሆኑ በርካታ ልጆችን ወለደ። እነዚህ ልጆችም ‹‹የኦሮሞይቱ የጊፍቲ መንዲያ እና የኦሮሞው ንጉሠ-ነገሥት የአጼ ልብነ-ድንግል ልጅ የአጼ ይኩኖ-አምላክ ዝርያ በመሆናችን ህዝባችንን መግዛት መብታችን ነው፤›› እያሉ የሸዋን ኦሮሞ እና አማራ ገባራቸው አደረጉት። ዳግማዊ አጼ ምኒልክም ይህንኑ የኦሮሞ-ሰለሞናዊ አግአዚ ደም ካርድ መዘውና "የይሁዳ ነገድ" ነኝ ብለው ነው የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ለመሆን የበቁት። የሸዋ መሳፍንትና ነገሥታት ግን በራቸውን ጥርቅም አድርገው ዘግተው ለጎንደሩ መንግሥት ምንም ሳይገብሩ በፍጹም ነጻነት ነው የኖሩ።





# የንግሥተ-ሳባ ማንነትና ስለ መኖር አለመኖርዋ

ወላጅ እናትዋ አዝሚና "ኤትያኤል" ያለቻትን ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘችውን ንግሥተ-ሳባን በተመለከተ አንዳንድ ሰዎች ከናካቴው መፈጠርዋንም ይክዳሉ። አንዳንዶች ደግሞ የአረቦች በተለይም የዛሬዋ የመን ንግሥት ያደርጓታል። አሁን ዋናው ጥያቄ ‹‹ብርግጥ ንግሥተ-ሳባ በሕይወት ነበረች ወይ?›› ነው። አዎ! በርግጥ ነበረች። እንደ ሃይማኖት የለሽ አረመኔ የሚቆጥሯትን በአረቦች የተከለሰውን *ክብረ-ነገሥት ን*ና አንዳንዶችንም የኢትዮጵያን ልዕልና የሚቀናቀኑ ዐረቦችን ፅሁፎች ቁምነገር ብለን ባንቀበላቸውም እንኳ ሌሎች አስተማማኝ ምንጮች ሊካዱ አይችሉም። በአንደኛው ክፍለ-ዘመን የነበረውን ጆሴፈስ የተባለውን አይሁድ-ሮማዊ የታሪክ ጸሐፊ እና መጽሐፍ ቅዱስንም ባናምን እንኳ በመግቢያዬ ላይ የተጠቀሰውን የልዑል አክሉማይ ሲራክ ሥራ የሆነውን "ታሪኩ-ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ" የተሰኘውን መጽሐፍ ግን እምነት የጣልኩበት አስተማማኝ ምንጭ ስለሆነ የምጠቅሰው ይሆናል። ከሁሉም በላይ ደግሞ እስከዛሬ ድረስ የሚመዘዘው የዘር ሐረግ ለሕልውናዋ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊት ለመሆኗም የማያወለዳ ማስረጃ ነው።

ከ 2000 ዐመት በፊት የኖረው የአይሁድ ደም የነበረው ዝነኛው ባለታሪክ ፍላቪዮስ ጆሴፈስ በመጽሃፉ ውስጥ ንግሥት ሳባ ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ስላደረገችው ጉዞ መታሰቢያ አንድ ሙሉ ገጽ ጽፏል። የኢትዮጵያና የግብፅ ንግሥት እንደነበረች ባንዱ ገጽ ላይ

ሁለት ጊዜ ከትቦአል፡፡ (F. *Josephus, Jewish Antiquities*, ed. J. Thaceray and R. Marcus, Loeb Classical Library, London, 1961, Vol. VIII, pp. 165-175)፡፡ የሱ አፃፃፍ ከኦሪት ዘ ፍጥረት አፃፃፍ ጋር ይገጣጠማል (I Kings X: 1-10)፡፡ ኦሪት ዘ ፍጥረት ንግሥት-ሳባ ብሎ ይጠራታል፡፡ ከሺ ዓመታት በኋላ ጆሴፈስም የኢትዮጵያ እና የግብፅ ንግስት መሆንዋን አረጋግጦ አመልክቷል፡፡ ይህም ፍፁም እውነት ነው፡፡ ጌታ እየሱስ ክርስቶስም ቢሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ለ ሦስት ዓመታት ስለነበረ እና ከ ክብረነገሥት ፀሐፊም ሆነ ከፍላቪዮስ ጆሴፈስ በላይ ኢትዮጵያን ስለሚያውቅ "የአዘቦ ንግሥት" በማለት ማንነትዋን በትክክል ገልጧል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እየሱስ ክርስቶስ ለሕልውናዋ እውቅና መስጠት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊት መሆኗንም አረጋግጧል፡፡ በማያሻማ አባባል "የአዘቦ ንግሥት" ሲል ጠርቷታል፡፡ "አዜብ" የሚለው ቃል ከየት የመጣ ነው? ከንግሥት ሳባ ህልውና 900 ዓመት በፊት ኢትዮጵያን ይገዛ የነበረ ንጉሥ ስም ነው፡፡ የዘር ሐረጉ እንደደሚከተለው ቀርቧል፤

የኢትዮጵያ መስራች እና ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ጥንተ-አባት የነበረው ቀዳማዊ ኢትዮጵ ከ4000 ዓመት በፊት ከጥንተ-እናታችን ከእንዮጳ-ግዮን አቲባን ወለደ፡፡አቲባ ከንግሥት ቂቂ አዜብን ወለደ፡፡ አዜብ አዛል/አዳል/ ይባላልም፡፡ የአዜብ ዝርያዎች ከዐእመታት በኋላ "አዜብ" ወይም "አዘቦ"ይባሉ ጀመር፡፡ አዜብ ከአባይ መነሻ ጀምሮ እስከ ሰዶም ድረስ ስተዘረጋው ሰፊ አገር ንጉሥ ተብሎ ሲነግስ የነገሠበትን ሰፊ አገር "አዜብ" ብሎ ጠራው፡፡ ልጆቹ እና የልጅ ልጆቹ እዚህ እንዲኖሩም በሕግ ደነገገ፡፡ ንግሥተ ሳባ ወይም በትክክለኛው እናትዋ አዝሚና ባወጣችላት መጠሪያዋ ኢትያኤል በምትገዛበት ዘመን አዜቦዎች ወይም አዘበዎች ትልቅ ነገድ ነበሩ፡፡ ራሷ የወጣችው ከዚህ ነገድ ነበር፡፡ የሳባ ንግሥት ሆና እንኳ የአዜብ ንግሥትም ነበረች፡፡ ሳባ ከአያትዋ የወረሰችው ከተማ ነው፡፡ የአዘቦ ህዝቦች እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ፡፡ ለዚህ ነው እየሱስ ክርስቶስ ስለ ኢትያኤል ማንነት ርግጠኛ ሆኖ "ንግስተ-አዜብ" ሲል በትክክል የጠራት(ማቴ.12፡2፣ሉቃ.11፡31)፡፡ የአማርኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ቢጠቀሙ የተሻለ ነው፡፡ የእንግሊዝኛው ቅጂ "የደቡብ ንግሥት" ብሏታል፡፡ ከእብራይስጥ ወደ እንግሊዝኛ የመለሰው ተርጓሚ "አዜብ" የሚለውን ቃል የተረዳው "ደቡብ" በሚል ነው፡፡ በአማርኛ ወይም





በግዕዝም ታዲያ "አዜብ" የሚለው ቃል ከምዕራብ እስከ ደቡብ ያለውን ቦታ ለማመልከትም ይውላል፡፡ የስርወ ቃሉ ፍቺ ግን የአዘቦ ህዝቦችን፣ የንጉሥ አዜብን ዝርያ እና የንግሥት ሳባን ዘመዶች የሚያመለክት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከእስራኤል በስተደቡብ ስለምትገኝ ተርጓሚው ያንን መጥቀሱም ይሆናል፡፡ ያም ሆነ ይህ ከላይ የቀረበው ገለጻ የኢትያኤልን ማንነት በተመለከተ በትክክል ያስቀመጠ ነው፡፡ እየሱስ "ንግስተ-ሳባ" ያላለበት ምክንያት በሱ ጊዜ ሳባ ከተማ ስላልነበረች ነው፡፡ በኃይለኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ከምድረ-ገጽ ጠፍታ ነበር፡፡ የአዘቦ ሰዎች በሱ ጊዜ ስለነበሩ "አዜብ" አለ፡፡ በተጨማሪም እየሱስ የኢትዮጵያን መልክአ-ምድር በዝርዝር ያውቀዋል፡፡ ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት እድሜው ከ22 እስከ 25 በነበረበት ወቅት በመላ ኢትዮጵያ በየብስ በባህርዋ፣ በወርድ በስፋትዋ ለ 3 ዓመት ተመላልሶባታል፡፡ ኢትዮጵያ አልሄደም ቢባልም እንኳዋን የዐለሙ ሁሉ ፈጣሪ ነውና ኢትዮጵያን ቀርቶ የድፍን ዐለምን ካርታ በመዳፉ ውስጥ ጨብጦ ይዞ ያውቃል፡፡

በፊት እንዳመለከትኩት፥ የብሉይ ኪዳኑ ኦሪት ዘ ፍጥረት ነገሥት ምዕራፍ 10 ቁጥር 1 ንግሥት ሳባ ሥጦታ ይዛ ንጉሥ ሰለሞንን ለማየት እንደሄደች ይናገራል፡፡ ነግሥተ-ሳባ ከኢትዮጵያ መሆኗን ይህ አመልካች ነው፡፡ በዚሁ ምዕራፍ ስንኝ 11 እና 12 ንግሥት ሳባ የኦፊር ወርቅ፤ ከርቤ፣ ሰንደል ሽቱ እና ውድ ሥጦታዎችን ይዛ መሄዷን ይዘረዝራል፡፡ በዓለም ላይ ምርጥ የሆነው የኦፊር (አፋር) ወርቅ ምንጩ አፋር፣ ኢትዮጵያ ነው፡፡ ኢትያኤል ለሰለሞን እስጭና ለወሰደችው የሰንደል እንጨቱም እንዲሁ ምንጩ ኢትዮጵያ ናት፡፡ እስዋ በግመል እስጭና ለለሰሞን ይዛ ከሄደችው ማናቸውም ሥጦታ በተጨማሪ የኦፊርን ወረቅ ጨምሮ ሌሎች ውድ ብርቅየ ሥጦታዎችንም በመርከብ አስጭና ወስዳለታለች፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ኢትያኤል ከመሄድዋ በፊትም ሰለሞን ቤቱን ለመሥራት እና ለማስዋብ እነዚህን ቁሳቁሶች እንዲሁም እንስሶችን ከኢትዮጵያ ይገዛ ነበር፡፡ ይህን እውነታ አስመልክቶ ኦሪቱ እንደሚከተለው ብሏል፤--

"ንጉሱ ከታርሲስ / አፋር፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረች የወደብ ከተማ/ ወደብ ከሂራም የጦር መርከቦች ጋር አብረው የሚነሱ የንግድ

መርከቦች ነበሩት። የታርሲስ የንግድ መርከቦች ወርቅ፣ብር፣ የዝሆን ጥርስ፣ ጦጣዎች እና ዝንጀሮዎች ጭነው በየሶስት ዓመቱ አንድ ጊዜ (ወደ ኢየሩሳሌም) ይመጣሉ። (መጽሐፍ ቅዱስ፤ ነገሥት 1:22) ንግሥት ሳባ ኢትዮጵያዊት ለመሆንዋ ይህ ሌላው ጠንካራ ማስረጃ ነው። ከሰለሞን በኋላ በጀሆሳፋት ጊዜም አፋር ወርቋን በንግድ መርከቦች እየጫነች ለኢየሩሳሌም ማቅረበዋን ቀጥላለች። ጀሆሳፋት ወርቅ ለመጫን ወደ ኦፊር የሚሄዱ የንግድ መርከቦችን አሠርቶ ነበር። ሆኖም ጨርሶ አልቀዘፉም። ምክንያቱም በኤዚዮን ገበር ስጥመው በመሰባበራቸው ነው" (1 ነገስት፤ 22:48)። ኤዚዮን ገበር ኢትዮጵያ ውስጥ የአፋር/ኦፊር/ የነበረች ወደብ ናት። ይህም እንዲሁ ንግሥተ-ሳባ የኢትዮጵያ ንግሥት እንደነበረች ያረጋግጣል። የሳባን እምነት በተመለከተ አረቦች ስሟን ለማጥፋት እንደሚሞክሩት ሃይማኖት-የለሽ አልነበረችም። በኖኅ፣ በሳሌም/ኢየሩሳሌም/ ንጉሥ በመልከጼዴቅ፣ ኢትዮጵያን በመሰረተው በኢትዮጵ እና ዙፋኑን በወረሰችው በታላቁ ንጉሠ-ነገሥት በአጼ/ኤስያኤል/ አምላክ ታምን ነበር። እነዚህ ንጉሶች ሁሉም ወደ እስራኤል ሄደው ስጦታ ሊያበረክቱለት የመሲሁን መወለድ የሚጠባበቁ ነበሩ። ሳባ በአጼ/ኤስያኤል/ ቤተ-መንግሥት እንደ እናትዋ እንደ አዝሚና እንደ መቆየትዋ እና የኢትዮጵ ዝርያ የሆነው አያትዋ ቤት ውስጥ እንደማደግዋ በዚህ እምነትና እውቀት ታንፃ ነበር። በመሆኑም ስለሰለሞን ዝና ስትሰማ መሲሁ መስሏት ነበር። ስለዚህ ወደ እስራኤል ተጉዛ ሥጦታ የማበርከቱን ክብር ተሽቀዳድማ ለመውሰድ ወሰነች። አማካሪዎቿ ግን ሰለሞን የንጉሥ ዳዊት ልጅ ነው እንጂ መሲሁ አይደለም ሲሉ ነገሯት። በዚህም ምክንያት ጉዞዋን አዘገየችው። በመጨረሻ ግን እውነቱን ራሷ ማረጋገጥ ስለፈለገች በመሄዷ ፀናች። ኢየሩሳሌም ስትደርስ ሰለሞን መሲሁ አለመሆኑን አረጋገጠች። ሆኖም በጥበቡ እና በ ስርዐተ ቤተመንግሥቱ ተደነቀች፥ ተማረከች እና አግብታው ቀዳማዊ ምኒልክን ፀንሳለት ተመለሰች። ስለዚህ በጨረቃ እና በከዋክብት የምታምን ጣኦት አምላኪ ነበረች የሚባለው ፍፁም ስህተት ነው።

ደቡብ አረቢያዎቹ "ቢልቂስ የኛ ንግሥት ነበረች" ሲሉ በከፊል እውነታቸውን ነው። በርግጥም የሁዋላ ሁዋላ የነሱ ንግሥት ነበረች። ነገር ግን የመንን በንግሥትነት የገዛችው አባትዋ ከሞተ ብዙ ቆይታና





በንግሥት ሳባ ፈቃድና በኣግኣዚዎች የጦር እገዛ ነበር። ታሪክዋ እንደሚከተለው ነው፤--

የቢልቂስ ዘረ ምንጭ ኢትዮጵያ ናት። በኛ መረጃ መሰረት አባትዋ አዲላዛር ይባላል። የየመን ንጉሥ ነበር። የመን የኖረ አንድ አውሮጳዊ እንደዘገበው እናትዋ ኤኬዬ/እትዬ?፣ አቴጌ?፣/ አዜብ፣ እንዲት የኢትዮጵያ ንግሥት ናት። በስመ ሞክሼነት እንጂ የንግሥተ-ሳባዋ አዜብ አይደለችም። (N.Pearn and V. Barlow, *Quest for Sheba*, London, 1964), pp. 250-251. የቢልቂስ እናት፥ ሌላ አዜብ ናት ማለት ነው። እምን ኢትያኤል አይደለችም።

ፕሮፌሰር ስርግው ሃብለስላሴም ኮማንደር ክራውፈርድ የተባለውንና የየመኑ ኢማም አማካሪ የነበረውን አውሮጳዊ አመልክተው እነዚህን ሁለት ጸሐፊዎች ይጠቅሷቸዋል። ኮማንደሩ ስለ ቢልቂስ የተወሰነ መረጃ የያዘ ጥንታዊ ጽሁፍ አግኝቻለሁ የሚል ነው። ፕሮፌሰር ስርግው ሃብለስላሴን እንጥቀስ፤

"ኮማንደር ክራውፈርድ ለየመኑ ኢማም የረጂም ጊዜ አማካሪ የነበረ ባንዲት ቆንጆ ንግሥት እየተመራ ወደ ንጉሥ ሰለሞን ስለሚተምም የግመሎች መንጋ የሚናገር እድሜ ጠገብ ጽሑፍ አግኝቻለሁ" ብሏል። ስምዋ ቢልቂስ ይባላል። የሻር ሃቢል ልጅ ናት። እናትዋ የኢትዮጵያ ንግሥት ኢኬዬ አዜብ ናት። በልጅነትዋ በእናትዋ አገር ብዙ ዐመታትን አሳልፋ አባትዋ ከመሞቱ ትንሽ ቀደም ብሎ ወደ ማሪብ ተመልሳለች። እንደታሪኩ ከሆነ ቢልቂስ ለሳቢያን ዘውድ የተወዳደረች የመጀመሪያዋ እንስት ናት።" (ስርግው ሃብለስላሴ፤ *የጥንታዊ እና መካከለኛ ኢትዮጵያውያን ታሪክ እስከ 1270* (ገጽ 38-39)።

ክራውፋርድ ካገኘው ጽሑፍ ቢልቂስ ከኢትዮጵያ ጋር ዝምድና እንዳላት እንረዳለን። ስዕለ-ሁኔታው አሁን ግልጽ ነው፤ ቢለቂስ ከእናትዋ ጋር በኢትዮጵያ ውስጥ አድጋለች። ይህም ኢትዮጵያ ውስጥ መወለድዋን ያሳያል። በርግጥ እናትዋ ኢትዮጵያ ውስጥ ከኖረችና ቢልቂስም ኢትዮጵያ ውስጥ እናትዋ ጋ ካሳደገች ሌላጋ የት ታድጋለች? እውነት ነው፥ አባትዋ በኢትያኤል /ንግሥት ሳባ/አዜብ/ ሥር ያለ ንጉሥ ነበር። ምክንያቱም ያን ጊዜ ደቡብ አረቢያ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበር። ንግሥት አዜብ ንጉሥ ሻር ሃቢልን

አግብታ ቢልቂስን ወልዳለች፡፡ የተጋቡት እሱ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ይሁን ወይም እሷ ወደ እሱ ሄዳ የታወቀ ነገር የሰም፡፡ አንድ ነገር ብቻ ግልጽ ነው፤ አብረው ብዙ አልቆዩም፡፡ ሳይፋቱ አልቀሩም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖረች ልጅዋን ቢልቂስን ታሳድግ ነበር፡፡ ቢልቂስ ራስዋም ባንድ ወቅት ካባትዋ ጋር አብራ ኖራለች፡፡ ማስረጃውም ደቡብ አረቢያ ውስጥ ባል አግብታ ነበር፡፡ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ባሏን ገድላ ወደ ኢትዮጵያ ኮበለለችና ከእናትዋ ከአዜብ ጋር ትኖር ጀመር፡፡ ባልዋን ገድላ ከየመን ሸሽታ ኢትዮጵያ ውስጥ ምትኖርበት ሰዐት የአዘቦና ቆቦ ንግሥት ከነበረችው ከሳባ ዘመድ ከንግሥት ሣሆይ ጋር ንግሥተ-ሳባን አጅባ ንጉሥ ሰለሞንን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳለች፡፡

ድንግል የነበረችው ኢትያኤል ንጉሥ ሰሰሞንን አገባችና የህግ ሚስቱ ሆነች፡፡ ዝሙት እንደፈጸመች ይህን መቁጠር ስህተት ነው፤ ምክንያቱም አግብታዋለች፡፡ ሌሎቹ ሁለቱ እንስቶች ቢልቂስ እና ሳሆይ የሰለሞን እቁባቶቹ ሆኑ፤ ምክንያቱም ሰለሞን ሴትን እማላይ ሰው ነበር፡፡ ቢልቂስን ያስረግዝ አያስረግዝ ማስረጃ የሰንም፡፡ ኢትያኤል እና ሣሆይ ግን ከሰሰሞን ጸንሰው እንደቅደም ተከተላቸው ቀዳማዊ ምኒልክን እና ዜጋዬን ወለዱ፡፡ በኋላ ቀዳማዊ ምኒልክ ዜጋዬን "ዛጉዬ" ሲል ጠራውና የእዘቦና የላስታ ንጉሥ አድርጎ በናቱ ዙፋን አነገሠው፡፡ ኢትያኤል እና ሣሆይ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ቢልቂስ ግን ሰመመለስ ምክንያት ስላልነበራት እዛው ቀርታ ስትኖር በኢትያኤል እና በቀዳማዊ ምኒልክ ትዕዛዝ አግአዚዎች ወደ የመን ወሰዷት እና አባትዋ ከሞተ በኋላ የመጀመሪያዋ የደቡብ አረቢያ ንግሥት አድርገው አነገሷት፡፡ ሰዚህ ነው አረቦች እንደ ንግሥታቸው የሚቆጥሯት እና ከኢትያኤል ወይም ከንግሥት ሳባ ጋርም የሚያምታቷት፡፡ ኢትዮጵያውያን የየመን ንግሥት አድርገው ባያነግሷት ኖሮ ወደ እረቢያ የመመለስ ተስፋ ሳይኖራት የሰሰሞን ቁባት ሆና በኢየሩሳሌም በቀረች ነበር፡፡ ምክንያቱም አረቦች እንደ ኢትዮጵያውያን ባለ ነፃ አእምሮ ሰላልሆኑ ሴት ልጅ ንግሥት እንድትሆን ፈጽሞ ስለማይፈቅዱላት ነው፡፡ ኢትያኤል ወይም ንግሥት ሳባ ራሷም አረባዊት ብትሆን ኖሮ ንግሥት ባልሆነች ነበር፤ ሀቁም፥ አረቦች በታሪካቸውም ሴትን አንግሠው አያውቁም፡፡ ኢትዮጵያ ናት ቢልቂሰን





እንዳነገሠችው ሁሉ በአረቦች ላይ ሴቶችን የምታነገሥባቸው፣ወይም የምታነግሥላቸው፡፡

ስሰዚህ ኢትያኤል(ንግሥት ሳባ) አረባዊት መሆን አትችልም፤ አልሆነችምም፡፡ ኢትያኤል (ንግሥት ሳባ) አረባዊት ሳትሆን ያሰጥርጥር ኢትዮጵያዊት ናት፡፡ ቢልቂስም እንዲሁ በናትዋ በኩል ኢትዮጵያዊት ነች፡፡ "ሳባ" ኢትዮጵያ ውስጥ በአጼ እስያኤል የተመሰረተች ከተማ ነበረች፡፡ አረቢያ ውስጥ ያለችው "ሳባ" ግን ኢትዮጵያውያን ደቡብ አረብን በቅኝ ገዢነት በሚገዙበት ወቅት ዋና ከተማቸውን ለማስታወስ የሰየሚት ሌላ ከተማ ናት፡፡ ሰመሆኑ መቸ ነው አረብ ኢትዮጵያን በቅኝ ገዢነት የገዛና ያሰለጠነው? በፍጹም ተደርጎም አያውቅ፡፡ ሀቁ የተገላቢጦሹ ነው፡፡ ይህ ነው ፣የንግሥት ሳባ (የኢትያኤል) እውነተኛው ታሪክ፡፡

ከኢትዮጵያ ታሪካውያን ሃውልቶች፣ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እና በየመን ውስጥ ከሚገኘው መረብ ወንዝ ጎን ለጎን ኢትዮጵያውያን በየመን ውስጥ ሰነበራቸው ተሳትፎ ሌላው ማስረጃ የመን ያን ጊዜ "ናግራን" መባልዋ ነው፡፡(ና በግራ በኩል፤ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የመንን ቅኝ በሚገዙበት ወቅት ወታደራዊ ማዘዣ ቃል ነበር፡፡ የመን የሚሰውም ቃል "የ ማን?" ከተሰኘው አማርኛ የፈለቀ ነው፡፡)

ቀዳማዊ ምኒልክንና ወንድሙን ዜጋዬን በተመለከተ በርግጥ በወላጅ እናቱ እግር የአዘቦና የላስታ ንጉሥ አድርጎ ሲያነግሠው ምኒልክ ነው ዜጋዬን "ዛጉዬ" ብሎ የሰየመው፡፡ (ከዚህ የተነሳ ነው የቀዳማዊ ዛጉዬ ተወላጅ፣መራ ተክለ-ሃይማኖት ዳግማዊ ዛጉዬ ተብሎ በላስታና ላሊበላ ላይ የነገሠው እና ይኩኖ አምላክ ዙፋኑን እንደገና ወደ ሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት እስከሚመልሰው ድረስ ኢትዮጵያን የገዛውን የዛጉዬ ሥርወ-መንግሥትን የመሰረተው፡፡)

ሴቶችን ንግሥት አያልን የማንገሥ ባሕላችን ደግሞ ተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸው ኢትዮጵያውያን በጾታ እኩልነት ያምኑ እንደነበረ ያሳያል፡፡ ሳባ ወይም ኢትያኤል የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ንግሥት አልነበረችም፡፡ ለምሳሌ ከሷ በፊት ንግሥተ-ነገሥታት የነበረች ንግሥት ነበረች፡፡ ኢቲግዝያ ትባላለች፡፡ የኢትዮጲስ 3ኛ ልጅ ነበረች፡፡ ስመ-መንግስትዋ ሰንደቅ-ጃን ይባላል፡፡ አባትዋ ኢትዮጲስ 3ኛ

በጣም ይወዳት ስለነበረ በመላ ኢትዮጵያ ንግሥተ-ነገሥት አደረጋት። ይኸውም ኢትያኤል ከመወለዷ ከብዙ ዐመታት በፊት ነበር። ለ45 ዓመት ገዝታለች። ከሷ በተጨማሪ ኢትዮጺስ ሌሎች ሁለት ሴቶች ልጆቹንም ንግሥቶች አድርጎ አንግሷቸዋል። አንዷ አሊና የተባለችው የኤደን ንግሥት ነበረች ። ከ 2900 ዓመት በፊት ደግሞ አክሱማይት የተባለው የንግሥት ሳባ የልጅ ልጅ ኢትዮጵያውያን ንግሥቶችን "ሕንደኬ" በሚል የማዕረግ ስም በኑቢያ፣ በግብፅ እና በሲቢያ ላይ ያነግሥ ነበር። በ1000 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከአክስቱ ጀምሮ የ13 ንግሥታት ታሪክ ተመዝግቧል። እነሱም፡-

1. አዚት (የአክሱማይት አክስት).

2. ኒኒ

3. ቅንዳቅስ

4. ሰማርታ

5. ካሺታ (የፈርዖን ቲሬሃቅ እናት)

6. ሙዝልብያ (ሴሳው መጠሪያዋ አሚን ሪትስ የነበረ፣ የፍቅር ዓምላክ ተደርጋ የተቆጠረች፣ 240 ባሎች የነበሯትእና 130 ዓመት የኖረች)

7. አንጥያ (የሙዝልብያ ልጅ)

8. አንስጥያ (የአንጥያ ልጅ)

9. አንስጣጥያ (የአንስጥያ ልጅ)

ከላይ የቀረቡት አራቱ እናቶች፣ ልጆች እና የልጅ ልጆች አጅግ ውብ ከመሆናቸው የተነሳ ፊታቸውን ያየ እና ድምፃቸውን የሰማ ማንኛውም ህመም ያለበት ሰው ከያዘው በሽታ ይፈወሳል ተብሎ ይታመን ነበር። ሁሉም እንደ አማልክት ተቆጥረው በግብፃውያን፣በኑቢያውያን እና በሊቢያውያን ይመለኩ ነበር።

10. የኔትሜር (ታላቅ የግብፅ ፈርዖን የነበረው የፒያንግሮ እናት፣)





11. ሃትሃር (የታላቁ ሂሚከስ ባለቤት)

12. ዳግማዊ ቅንዳቅስ

13. እቴ ህንደኬ ጻን (ለኢየሱስ፣ ለማርያም እና ለዮሴፍ ከሄሮድስ በሸሹበት ወቅት በግብፅ ውስጥ ጥገኝነት የሰጣቸውና የላይኛው ግብፅ ንጉስ የነበረው የንጉሥ አማናቱ ተትናይ እህት) ናቸው።

ዝርዝሩ ከዚህ ቢረዝምም ለጊዜው ይበቃናል። አረቦች እነዚህን የመሰሉ ንግሥቶች ጨርሶ አልነበሯቸውም። የኢትዮጵያ ንግሥቶች ነበሩ ሲገዟቸው የኖሩት። አረቦች በኢትዮጵያ ሴቶች መገዛታቸው ብቻ ሳይሆን እንደ ጣኦታት ያመልኳቸውም ነበር። የነዚያ አስደናቂ ንግሥታት ዝርያዎች የሆኑ ቆነጃጅት ኢትዮጵያውያት ዛሬ የማይረቡ አረቦች ገረዶች ሆነዋል። አይ ጊዜ! ይህ ለኢትዮጵያ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ክስተት ነው!

የንግሥት ሳባ የዘር ሐረግ ምን ይመስላል? ለመሆኑ ኢትያኤል ወይም ንግሥት ሳባ በገሀድ የነበረች ሰው ናት? ኢትዮጵያዊትስ ነች? አዎ! ፍጹም በሆነ ርግጠኝነት ንግሥት ሳባ በገሀዱ ዓለም የነበረች ገሃዳዊ ሰው ናት፤ ኢትዮጵያዊትም ነች። የሳባ ከተማ ንጉሥ የነበረው የንጉሥ አጋቦና ተብሎ ይጠራ የነበረው የ ተዋስያ ሳቢ የልጅ ልጅ ናት። ሳባ ከተማ የተመለረተቸው የንግሥናው ስም ሰንደቅ-ዐልማ ይባል በነበረው በኡሴ ወይም እስያኤል ነው። እስያኤል የቀዳማዊ ኢትዮጵ እና የሳልሳዊ ኢትዮጵ ተወላጅ ሲሆን የሳባ ከተማ የመጀመሪያው ንጉሥ ነው። የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሆኖ ረጅም ዘመን ከመኖሩም በላይ ልጆቹ እና ዘመዶቹ የሆኑ በርካታዎችን ንጉሦች እያደረገ ሾሟል። ከነዚህ ውስጥ አሞር ሳቢሳባ ተብሎ የነገሠው ልጁ ኩርፋን፣ ዣንዛቦ ተብሎ የገዛው የኩርፋን ልጅ ሰርፌ፣ የቆቦ ንጉስ ተብሎ የነገሰው የሰርፌ ልጅ አኪላዣን፣ እና የአኪላዣን ልጅ ሳባ፣ የሳባ ልጅ ጽርስቅላ አንዘቦ፣ የጽርስቅላ አንዘቦ ልጅ አቅጃቦ፣ እና ተዋስያሳቢ ተብሎ የነገሰው የአቅጃቦ ልጅ አጋቦና ይገኙበታል። አጋቦና የሚባለው ተዋስያሳቢ ልዕልት አዝሚናን ወለደ። ልዕልት አዝሚና ኢትያኤልን ወለደች። ኢትያኤል አያትዋ አጋቦና፣ ተዋስያሳቢ ተብሎ በነገሰባት ሳባ ከተማ ንግሥት ሳባ ተብላ ተጠራች። ስለዚህ ከዚህ የዘር ሐረግ ሳባ የኢትዮጵ ዝርያ የሆነች፣ አያትዋ የሳባ



አክሱም ውስጥ ጉሉ ማክዳ የሚገኘው የንግስት ሳባ መካነ-መቃብር

ሌላው የማያወላዳ ማስረጃ አመጣጥዋን የሚያሳየው የዘር ሐረግዋ ነው። ከኢትዮጵ ጀምሮ የወላጆቿን መገደል ለመበቀል አስከገደለችው አስከ እሴ ወይም አጼ እስያኤል ድረስ የሚዘረጋው የዘር ሐረግዋ። ከሷ በኋላ የመጣውን ዝርያዋን በተመለከተ ደግሞ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምረን እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ድረስ 225 ነገሥታትን እንቆጥራለን። ሁሉም እነዚህ ነገሥታት ራሳቸውን ከሰለሞን ዘር ጋር በማያያዝ "በእግዚአብሔር የተመረጠ ድል አድራጊው የይሁዳ አንበሳ" ሲሉ የኖሩ ህልውናቸው ሊካድ የማይቻል ደምና ስጋ የተዋሃዳችውና የለበሱ ገሃድ ሰዎች ነበሩ። የያንዳንዱን ንጉሥ የግዛት ቦታና ዘመንም ለይተን እናውቃለን። በዘመናችን ከነበሩት ከቅርቡ ንጉሠ-ነገሥት ከአጼ ኃየለሥላሤ ተነስተንም ወደ ኋላ እስከ ቀዳማዊ ምኒልከ እና ንግሥት ሳባም መቁጠር እንችላለን። የነዚህን ነገሥታት ህልውና መካድና አሽቀንጥረን መጣል ያስኬዳል እንዴ?





በምንም መንገድ። የቀዳማዊ ምኒልክ እናት ኢትያኤል፣ንግሥት ሳባ መሆኗን በትክከል እናውቃለን። አባቱ ንጉሥ ሰለሞን አይደለም የምንል ከሆነ ማነው ታዲያ አባቱ? እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ፍንትው ብሎ የሚታወቅ አባት አለው። ምኒልከ ያለ አባት የተወለደ ይሆን? ሰለሞን አባቱ ካልሆነ ለአያቱ ለዳዊት ይበልጥ ክብር በመስጠት እና በሱም በመኩራራት ራሱን እንዴት "የዳዊት ልጅ" ብሎ ሊጠራ ቻለ?

ንግሥተ-ሳባን እና ልጇን አፈ-ታሪክ ናቸው ብለን ብንወስዳቸው እንኳ የአግአዚን እና የቋንቋቸውን የግዕዝን በኢትዮጵያ ውስጥ መገኘት ምን እናደርገዋለን? የፈላሻዎቹን እና የታቦተ-ጽዮንንስ ጉዳይ እንዴት እናደርገዋለን? የቃል ኪዳኑ ታቦት ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩን ብንክድ እንኳ ኢትዮጵያ በያንዳንዱ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያንዋ ውስጥ በምሳሌው የተቀረጸ ጽላት ያላት በዓለም ብቸኛ አገር እንዴት ልትሆን ቻለች? በተጨማሪም 40,000 አግአዚዎች እና ብዛታቸው ያልታወቀ ፈላሻዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ገቡ? ቋንቋቸው ግዕዝስ በፊት የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ቋንቋ አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን መገልገያ ቋንቋ ሲሆን እንዴት ቻለ? ይቺ የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያንስ ልክ አይሁድ በሲናይ በረሃ ለክብረ-በዓላት ያደርጉት እንደነበረው ዲያቆኖቿ እና ቀሳውስቷ ልብሰ-ተክህኖ ለብሰው፣ ታቦት ተሸክመው፣ ልዩ ልዩ ቀለማት ያሏቸውን ዣንጥላዎች የሚያጠሉባት እና ውደት የሚዞሩባት በዓለም ላይ ብቸኛዋ አገር እንዴት ሆነች? እይሁድ ያደርጉት እንደነበረው እጣንስ እንዴት ሊያጤሱ ቻሉ? በአክሱም እና በጣና ደሴት እንስሳትን ይሰዉ የነበረውስ ለምንድነው? ቀዳማዊ ምኒልክ አግአዚዎችን ንጉሦች እና ካህናት እያደረገ በመንግሥቱ የሥልጣን ቦታዎች ላይ ከፍ አድርጎ ባይሾማቸው ኖሮ ኣግኣዚዎች በአክሱም ንጉሥ እና ንግሥት እስከ ማንገሥ እና ማውረድ ብቻ ሳይሆን ያልፈለጓቸውን ነገሥታት እስከ መግደልም የደረሰ ኃይል እንዴት ሊኖራቸው ቻለ? አግአዚዎች በ4ኛው ክፍለ-ዘመን ከንጉሠ-ነገሥት አብርሃ ጋር የተደራደሩት እና እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናት የሚሠራባቸውን የአይሁድ እምነት አሠራሮችን ወደ ኢትዮጵያ አስርገው ያስገቡት በምን ሥልጣናቸው ነበር? ንግሥተ-ሳባ ወይም ኢትያኤል ኢትዮጵያዊት ባትሆን፣ ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ሥጦታዎች ይዛ ባትሄድ እና

ቀዳማዊ ምኒልክን ጸንሳለት ባትመለስ ኖሮ ይህና፣ ይህ ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ እውን መሆን አይችልም ነበር። ንግሥተ-ሳባ ወደ እስራኤል ያደረገችውን ጉዞ አስመልክቶ ሌሎች በርካታ ዝርዝሮችን ማቅረብ ይቻል ነበር። ሆኖም በዚህ ጥናት ትኩረቴ የንግሥት ሳባ እና የንጉሥ ሰለሞን ታሪክ እውነተኛ ታሪክ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ስላልሆነ እዚህ ላይ አበቃለሁ። ሳባ በእውን የነበረች ኢትዮጵዊት ንግሥት ነበረች በሚለው ሀሳብ አጠንጥኛለሁ። አንባቢዎቼ ስለሷ እና ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ማግኘት ከፈለጉ "የተደበቁና ያልተነገሩ የአይሁድ እና የኢትዮጵያውያን ታሪኮች" የተሰኘውን መጽሐፌን እንዲያነቡ እጋብዛለሁ።መፅሃፉ ግን በእንግሊዝኛ ነው።

አህመድ ግራኝ ከሰለሞናዊው የኦሮሞ ሥርወ-መንግሥት ጋር ጦርነት ባደረገበት ጊዜ እና በዘመነ-መሳፍንት ወቅት አምስት የኦሮሞ ጊቤ መንግሥታት ማለትም፡- ሊሙ-እናሪያ፣ ጂማ፣ ጎማ፣ ጉማ እና ጌራ አንፃራዊ ሰላም፣ የውስጥ አገዛዝ ነፃነት እና የንግድ ብልፅግና አግኝተው ነበር። ሊሙ-እናርያ በጂኦግራፊያዊ አቀማመጡ የንግድ መስመር እምብርት ስለነበረ እና የወርቅ ክምችትም ስለነበረው ከሁሉም ጎልቶ የወጣ እንደ ነበረ እሙን ነው። በሸዋ ውስጥ ያሉ የሰላሌ ኦሮሞዎች ከአህመድ ግራኝ ጦር ጋር ተባብረው ‹‹ሰለሞናዊውን-ኦሮሞ-ስርወ-መንግሥት›› በሚወጉበት ወቅት የሊሙ-እናርያ ንጉሦች ግን ከመንግሥት ጋር ጥሩ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ነበራቸው። ይህ ዲፕሎማሲም እስከ ንጉሠ-ነገሥት ሰርፀ-ድንግል ዘመን (እ.ኤ.አ1563-1597) ድረስ እና ከዚያም ወዲህ ዘልቋል። የሊሙ-እናርያ ንጉሶች ለኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሌባ ያዥ በመሆናቸው የሌባ ያዥ ግብር ይገብሩ እንደነበረ ተመዝግቧል። ለምሳሌ ከእናርያ የሚከፈለው የወርቅ ግብር በሰርፀ-ድንግል ዘመነ-መንግሥት ሰማይ ነክቶ አምስት ሺ ወቄት ወርቅ ደርሶ ነበር።

ሁለቱ ብቁ የእናርያ መሪዎች አባ ጎሞል (እ.አ.አ.1800-1825) እና ተተኪያቸው እና ልጃቸው አባ ባጊቦ (እ.አ.አ.1825-1861) የሚጠቀሱ ናቸው። ወደ መሳፍንቱ ዘመን ማብቂያ አካባቢ አባ ጎሞል ከጎጃም እና ከከፋ መሳፍንት ጋር ዲፕሎማሲያዊና ንግዳዊ ትስስሮሽ ፈጠሩ። ተተኪያቸው አባ ባጊቦ በቡና፣ በወርቅ፣ በዝሆን ጥርስ፣ በጥርኝ፣ እና አልፎም በባሪያ ንግድ እጅግ ከመበልፀጋቸው የተነሳ ከአፄ ቴዎድሮስ





እያት ከራስ ጎሹ የጦር-ሠራዊት ጥበቃ እስከመጠየቅ ደርሰው ነበር። ይህንን ዓላማ ለማሳካት የዳሞት ገዢ ለነበሩት ለራስ ጎሹ ሴት ባሪያዎችን ጨምሮ የተለያዩ ሥጦታዎችን ልከውላቸዋል። በዓፋት ደብዳቤም ግንኙነታቸውን ለማጠንከር የደጃዝማቹን ሴት ልጅ ለጋብቻ ጠይቀው ነበር። ደጃዝማቹ ሥጦታውን ተቀብለው 30 ነፍጥ እና ስለመሳሪያው አጠቃቀም ስልጠና የሚሰጡ ባለሙያዎችን ጨምረው ልከውላቸዋል።

ምንም እንኳ እነዚህ መንግሥታትና መሪዎቻቸው ኦሮሞዎች ቢሆኑም ኦሮሞነታቸው እንዳቸው ባንዳቸው ላይ ወረራ እንዳይፈጽሙ አላቀባቸውም። ሁለቱም አባ ጎሞል እና አባ ባጊቦ ጉማን ገባራቸው ሊያደርጓት በርካታ ጊዜ ወረራ ፈጽመውባታል። አባ ባጊቦ ከደጃዝማች ጎሹ ጋር ወታደራዊ ስምምነት እና የንግድ ግንኙነት ማድረግ የፈለጉበት ሌላው ምክንያት የጉዱሩን ለም መሬት ለመቆጣጠር ነበር። ‹‹የጅማው ንጉሥ አባ ጂፋር (እኤአ 1830-1855) በጣም ጠንካራ ሆነው ሲወጡ በጊቤ ክልል እና በታዋቂው ሶዶ ገበያ መካከል ያለውን መሬት ተቆጣጠሩ›› ። ቆይቶ እኚሁ አባ ጂፋር ጃንጀሮ፣ ጎማ፣ ጉማ እና ጌራ የተባሉትን ግዛቶች ወርረው አንድ አደረጓቸው። የእባ ጂፋርና ቀደም ያሉትም የአባ ጎሞልና የአባ ባጊቦ ወረራዎች አጼ ምኒልክ እማራን፣ እፋርን፣ ትግሬን፣ ወላይታን እና የኦሮሞ ግዛቶችን በማዕከላዊ መንግስታቸው ስር ለማድረግ ካደረጉት ወረራ የሚለየው በአላማው ብቻ ነው። ኦሮሞዎቹ መሳፍንት አጎራባች መሬቶችን በመያዝ የግል ግዛታቸውን ለማስፋፋት ሲሆን የምኒልክ ግን ከዘመነ መሳፍንት በፊት የነበረችውን ትልቋን ኢትዮጵያ በአንድ ማእከላዊ መንግሥት ስር ለማሰባሰብ ነበር። በዚህ ምክንያት፥ ምኒልክ የኦሮሞ ግዛቶችን ብቻ አይደለም ወደ ግዛታቸው የቀላቀሉት፤ የጎንደርን እና የጎጃምን አማራም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው በማናቸውም ዘዴ አስገብረዋል። ሉዓላዊ ገዢነታቸውን ያልተቀበሉትንና ግብር መገበር እቁመው ያመፁባቸውን እማራ ሆኑም አልሆኑም ማንም ንጉሠ-ነገሥት እንደሚያደርገው በጽኑ ቀጥተዋል። ጎንደር አልገብርም በማለቱ፣ ከዚህ ቀደም በአፄዎቹ ሱስንዮስ እና ቴዎድሮስ ድምጥማጡ እንደ ጠፋ አስተውለናል። የእነዚህ ነገሥታት ቁጣ የጎንደርን ህጻናትና አሮጊቶችን እንኳን አልማረም።

ቴዎድሮስ ጀምረውት፥ አፄ ዮሃንስ ቀጥለውበት፥ አፄ ምኒልክ አስፋፍተውት አፄ ኃይለሥላሴ ፈረሳቸውን ጠቅል ብለው የጠቀለሉት ሀገር፥ በመጀመርያ ለደርግ፣ ቀጥሎ ለኢህአዴግ ተርፎለት እስከ ዛሬ ይገኛል። በአሁኑ ሰዐት የዚህ ሁሉ ጥረትና ድካም ፍሬ ተመጋቢ ኢህአዴግ ነው። ነገ ደግሞ ተረኛው ገዢ ነው። ከእለታት አንድ ቀን ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ተጠቃሚ ይሆን ይሆናል።

ዘር ግምት ውስጥ ሳይገባ ለሥልጣን እና ለግዛት መፋለም በልሂቃን ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ባሕሪ ነው። ልሂቃን ኃይላቸውን እስከሚያጠናክሩ እና ይገባናል የሚሉትን ግዛት እስከሚጠቀልሉ ድረስ ሁል ጊዜ እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ። የትግሬ የጦር አበጋዞች እንኳ ኃይላቸውን ለማጠናከር እና ግዛታቸውን ለማስፋት እርስ በርሳቸው ይዋጉ ነበር። ባለፉት ጊዜያት በመረብ ወንዝ ማዶና ማዶ ያሉት የትግራይ እና የትግረ ገዢ መደቦች ለሥልጣን እና ለግዛት ሲሉ ተዋግተዋል። ለምሳሌ፣ ከአጋሜ የአጋሜው የደጃዝማች ሰባጋዲስ አባት የሹም አጋሜ ወልዱ ገዢ ቤተሰብ፣ ከተንቤን የአፄ ዮሐንስ 4ተኛው አባት ሹም ተንቤን ምርጫ ፣ ከእንደርታ የራስ ወልደሥላሴ ቤተሰብ እና የከንቲባ ተስፋ እና ዘርኣይ ቤተሰብ፣ ደጃዝማች ወልደሚካኤል እና ደጃዝማች ኃይሉ ከህማሴን ሁል ጊዜ በሥልጣንና በመሬት ጥያቄ አምርረው የሚዋጉ ደመኛሞች ነበሩ።

አጼ ቴዎድሮስ፣ በዋናነት በኦሮሞ ራሶች ተወስዶ የነበረውን ሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት መልሶ መመስረት ከመለኮት የታዘዙት ተግባርና ግዴታቸው አድርገው ተመለከቱት። ስለዚህ፣ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መሆን በተጠናወታቸው ስተቻለም ንጉሠ-ነገሥት መባል በሚቋምጡ መሳፍንት ተከፋፍላና ብዙ ቦታ ተበጣጥሳ የነበረችውን ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ፣ ዘመነ-መሳፍንትን በማስቆምና ዳር ድንበርዋን እንደ ቀድሞው እስከ ቀይ ባህር እና እስከ ሕንድ ውቅያኖስ በማስፋት ኢትዮጵያን ወደ ቀድሞ ክብርዋና ገናናነትዋ የመመለስ ራዕይ ይዘው ተነሱ።

ይህንን ታላቅ ራዕያቸውን እውን ለማድረግ ከነዚያ ትናንሽ ዓላማዎች እና ጠባብ ግዛቶች ከነበሯቸው በርካታ መሳፍንት ጋር ጦርነት ማድረግ ነበረባቸው። አጼ ቴዎድሮስ አይቀሬ ጦርነት ከሚዋጉዋቸው የመጨረሻዎቹ መሳፍንት አንዱ ራስ ዓሊ ትንሹ ነበሩ። ከራስ ዓሊ





ትንሹ ጎን ደግሞ ኃይለኛዋ እቴጌ መነንን ነበሩ። እሳቸውንም መፋለም ነበረባቸው። እናትና ልጅ ሁለቱም የየጁው ሴሩ ጓንጉል እና የትልቁ ራስ ዓሊ ተወላጆች እንደ ነበሩ ይታወሳል። ልጃቸው ራስ ዓሊ ትንሹ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በነበሩበት ወቅት ቆንጆዋና ጮሌዋ መነን ንግሥት የመሆን ጽኑ ምኞት ስለነበራቸው ነበር የመጨረሻውን አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥት ሳልሳዊ ዮሓንስን ያገቡአቸው።

ስሙ ካሳ ኃይሉ የነበረው ቴዎድሮስ ገና እንደተነሳ ራስ ዓሊ እና እቴጌ መነን ለሥርወ-መንግሥታቸው ስጋት መሆኑንን ወዲያው ተገነዘቡ። በዚያን ወቅት ለአልጋው የሚያሰጋ ኃይለኛ ሰው ሲነሳ በጋብቻ አስሮ በቀዬው መግታት የተለመደ ስለነበር የራስ ዓሊን ልጅ ልዕልት ተዋበችን ለካሳ ኃይሉ በጋብቻ ሰጡ። ካሳ ኃይሉ ተዋበችን ከልብ ስላፈቀራት ሽፍትነቱ ለጊዜው በጋብቻው ረግቦ ነበር። ሆኖም መርገቡ ብዙ አልቆየም። እናትና ልጅ፣ ሁለቱም ተዋጉትና ተሸነፉ።

ከዚያም የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥታት ሥልጣናቸውን መጀመሪያ በትግሬው ራስ፣ ቀጥሎ በኦሮሞ መሳፍንት ከተቀሙ ከ66 ዓመት በኋላ ካሳ ኃይሉ እውነተኛ ፍፁማዊ ሥልጣን ይዞና እውነተኛ ንጉሠ-ነገሥት ሆኖ የካቲት 5 ቀን 1847 አጼ ቴዎድሮስ ተብሎ ነገሠ። ኦሮሞዋ ባለቤቱ እቴጌ ተዋበችም እውነተኛዋ ንግሥተ-ነገሥታት ሆና የካቲት 12 ቀን 1847 ዓ.ም. ዘውድ ተቀዳጀች።

ካሳ ኃይሉ ከአጼ ልብነ-ድንግል ጋር ዝምድና አለኝ ቢልም በእናቱ በወይዘሮ አትጠገብ አብተው በኩል ነው እንጂ በአባቱ በኩል አይደለም በሚል የጎንደር ሕዝብ ስንግሥና በዓሉ ጥቂት ቀደም ብሎ ተቃውሞ አነሳበት። በህጉ መሰረት በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ቀደም ካለው ንጉሠ-ነገሥት ጋር አለ የሚባለው ዝምድና መቆጠር ያለበት በሴትዋ ወላጅ (በእናት) በኩል ሳይሆን በወንዱ ወላጅ (በአባት) በኩል ነው። ‹‹እየሱስ ክርስቶስ እንኳ ዓለምን ለማዳን የተወለደው ከሴት ነው›› በማለት ቴዎድሮስ እንደ ንጉሳቸው እንዲቀበሉት የጎንደርን ህዝብ አሳመነ። ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለማዳን የተነሳ በመሆኑ በሱነቱ ሊቀበሉት ይገባል። ሆኖም በቴዎድሮስ ደም ስር ውስጥ ጠብታ የንጉሣውያን ደም ባትኖር ኖሮ የቱንም ያህል በጦር ኃይለኛ ቢሆንም በሰለሞናዊው ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ያነሳውን ጥያቄ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ያደርግበትና ይብስ

ችግር ውስጥ ይክተው ነበር፡፡ በዚህ በሕዝብ ውድቅ የመደረግ ፍራቻ ስለተያዙ ነበር ክትልቁ ራስ ዓሊ እስክ ትንሹ ራስ ዓሊ ድረስ የነበሩት የየጁ ኦሮሞዎች በሰለሞናዊው ዙፋን ላይ በገዛ ፈቃዳቸው ፊጥ ለማለት ያልደፈሩት፡፡ ስለዚህም፥ አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥት እንዳሻቸው እየጎለቱና ፍፁማዊ የውክልና ሥልጣን እየያዙ ኢዮጵያን ሲገዙ ኖረዋል፡፡

የቴዎድሮስ አማት ትንሹ ራስ ዓሊ ከቴዎድሮስ ጋር ጦርነት ገጥመው ሲሸነፉ ሸሽተው ደምበጫ (ዳሞት) ገቡና የደጃዝማች ብሩ ጎሹን ክለላ ጠየቁ፡፡ ሆኖም በአባታቸው ሞት ስለጠረጠሯቸው ተጣሉና ወደ ደራ ሲያቀኑ ኦሮሞው ግራዝማች ዋቄ ዲቦ ለቴዎድሮስ አሳልፈው ሊሰጧቸው አሰሯቸው፡፡ ቴዎድሮስ ግን ራሩላቸውና ወደ አባቶቻቸው አገር ወደ የጁ እንዲሄዱ ይለቃቸው ዘንድ ደጃዝማች ዋቆ ዲቦን አዘዙ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ግን የዳግማዊ አጼ ምኒልክ አባት ንጉሥ ኃይለ-መለኮት ናቸው ግራዝማች ዋቆ ዲቦን ወግተው ያስለቀቋቸው ይላሉ፡፡ የዚህ መፅሐፍ ፀሃፊ ግን በመጀመሪያው ሀሳብ ነው የሚስማማው፡፡ ምክንያቱም ቴዎድሮስ ራስ ዓሊን ለመያዝ ቢፈልጉ ኖሮ እስክ ዕለተ-ሞታቸው ያሳድዱአቸው ነበር እንጂ ወደ የጁ ሲሄዱና በእዚያም ጭራሽ ያንዲት ትንሽ አገር ገዢ ሲሆኑ ዝም ብለው አያዩአቸውም ነበር፡፡ የሚያሳዝነው ራስ ዓሊ ትንሹ የእንግሊዙን ጄኔራል ናፒየርን ጦር በመርዳት በመቅደላ ምሽግ ላይ የቆመውን ቴዎድሮስን መበቀላቸው ነው፡፡ ራስ ዓሊ የዳግማዊ ምኒልክን ዘመነ-መንግሥት እስክሚያዩ ድረስ በሕይወት ኖረው የዕድሜ ባለጸጋ ሆነዋል፡፡ ምንም እንኳ ራስ ዓሊ ከልጃቸው ከተዋበች ቢለያዩም በሚችግራቸው ሁሉ በምሥጢር ትረዳቸው ነበር፡፡ ተዋበች ላባትዋ የምታደርገውን ልግስና ቴዎድሮስ ቢያውቁም ጣልቃ አልገቡም፡፡ ራስ ዓሊ የተዋበችን ሞት መራራ መርዶ ሲሰሙ በጣም አዝነው በተባ አማርኛቸው ቅኔ ተቀኙላት፡፡ በዚህም ምንም እንኳ ኦሮሞ ቢሆኑም አማርኛ ቋንቋን ለመንግሥታዊ ሥራ ማክናወኛ ብቻ ሳይሆን ጥልቅ ውስጣዊ ስሜታቸውን ለመግለጽም ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ በድጋሚ አስመስክሩ፡፡ ጥልቅ ውስጣዊ ስሜትን በግጥም እና በቅኔ መግለጽ በኢትዮጵያውያን መሳፍንት እና ነገሥታት ዘንድ የተለመደ ወግ ነበር፡፡ ተክለጻድቅ መኩሪያ *ዐፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት*





በተሰኘው መጽሐፋቸው ገጽ 186 ላይ ያሰፈሩት የራስ ዓሊ ግጥም / ቅኔ / ቀጥሎ ቀርቧል፤

*ጠጅ አማረኝ ስላት ማሩን ታስጭናለች*

*ራበኝም ስላት አህሉን ታስኝጭናለች*

*በረደኝም ስላት ሸማ ትሰዳለች*

*ሌባዬ ተይዛ ባልጋ ትሄዳለች፡፡*

*የት አባትዋን አውቃ ታሳዝነኛለች፥*

*የጣቴን ቀለበት አንተ አድርገው ካሳ፥*

*በኔማ ጣት (በኔ ማጣት) ገብቶ አሰጨነቀኝሳ፡፡*

ቴዎድሮስ ለራስ ዓሊ እናት ለእቴጌ መነንም ምህረት በማድረግ ርኅራኄ አሳይተዋል፡፡ በሰባት ደጃዝማቾች እየተመራ የመጣውን ጦራቸውን እስክዚያን ጊዜ ድረስ በዚያች አገር ላይ ታይቶ በማይታወቅ የጦር ስልት ብትንትኑን አውጥቶት ክማረካቸው በኋላ ወደ ጎንደር ተመልሰው እንዲሄዱ እና ክባላቸው ክአጼ ሳልሳዊ ዮሐንስ ጋር እንዲቀላቀሉ ማድረጋቸውትልቅ የርኅራኄ ተግባር ነበር፡፡ ምላሰኛዋ ሴትዮ ‹‹ይህ ፍየል ጠባቂ ቆለኛ›› ብለው የሰደቡአቸውንም ይቅር ብለዋቸዋል፡፡ ልጃቸውን ካገቡ በኋላ እንኳ በብዙ መልኩ ሲያዋርዱአቸው አልተበቀሏቸውም፡፡ ይህ መሀሪነታቸውና ይቅር ባይነታቸውም የጎንደርን ሕዝብ አድናቆት አትርፎላቸዋል፡፡

ቆየት ብሎ ቴዎድሮስ ወደ ወሎ ሲያቀኑ ወርቂት እና መስተዋት ክተባሉ ሁለት ኦሮሞ ባላባት ወይዛዝርት ተቃውሞ ገጠማቸው፡፡ ወይዘሮ ወርቂት ከቴዎድሮስ ጋር ተዋግታ ድል ሆነችና ወደ አንድ ተራራ ሸሸች፡፡ እዚያ ሆና ለመስተዋት መልዕክት ላክች፡፡ መልእክቱም በራስዋ ዋና ክተማ በጊምቢያ-ወረሂመኑ አጼ ቴዎድሮስን ድግስ ደግሳ እንድትቀበላቸውና አዘናግታ እንድትገድላቸው የሚያሳስብ ነበር፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት የወርቂት ሠራዊት ዓባላት እና ልጆቿ አግደው ዓሊ እና አምዴ ዓሊ በቴዎድሮስ ሠራዊት ውስጥ ሰርገው እንዲገቡ

ተደረገ። ሆኖም ሌራው ከሸፈና መስተዋት እና የወርቂት ልጅ አምዬ ዓሊ ሸሽተው ሲያመልጡ አግደው ዓሊ እና ሌሎች መኳንንቶች ተይዘው መቅደላ ታስሩ። የአቀባበል ግብዣ አስመስለው ሲገድሉአቸው በማሌራቸው የተናደዱት ቴዎድሮስ የማረኩአቸውን ወታደሮችና ህዝባዊ ጦር አንዳንድ እጃቸውን አስቆርጠው በወርቂት እና በመስተዋት ቦታ ወይዘሮ ተመኙን ሾመው ወደ ሸዋ አቀኑ።

አጼ ቴዎድሮስ እንደነገሡ ያረቀቁትን የሥራ መመሪያ ለኢትዮጵያ ህዝብ አነበቡ። በመመሪያውም የባርነት ሥርዓት እንዲቀር ደነገጉ። የመንግሥትን ወታደሮች በደሞዝ ለማሳደርና በጭሰኛው ላይ ሸክም የሚሆኑበትን የተሠሪነት አሠራር ለማስቀረት ቃል ገቡ። በየቤተ-ክርስቲያኑ የሚያገለግሉትን ካሕናት ቁጥር ከ10 በታች ዝቅ ለማድረግና የቤተ-ክሕነትን አስተዳደር ለማሻሻል እንደሚሞክሩ አስታወቁ። ሌሎቹ ካህናት በእርሻ ሥራ ላይ ተሰማርተው በላባቸው እንዲተዳደሩ አሳሰቡ፡ ይህ የመመሪያ አዋጃቸው ከካህናቱ ጋር ቅራኔ ውስጥ አስገባቸው። ቴዎድሮስን ለመጉዳት ሲሉም የሚወዱአቸውን ባለቤታቸውን እቴጌ ተዋበችን በቤተ-ክርስቲያን ተገኝተው ሥጋ-ወደሙ ሲቀበሉ መርዝ ቀላቅለው ሰጧቸውና ገደሉባቸው። በዚህ የተበሳጩት ቴዎድሮስ በቀኝም በግራም ካሉ መሳፍንት ጋር ጦርነት ውስጥ እየገቡ የሚቃወሙአቸውን ሁሉ ወደ መግደል የእብደትና የቀቢፀ-ተስፋ ድርጊት ውስጥ ገቡ።

የየጁውን ራስ ዓሊ ትንሹን፣ የወሎዋን ወርቂት ይማምን፣ የላስታውን ዋግ ሥዩም ጎበዜ ገብረ-መድህንን (ቴዎድሮስ እንደ ወደቁ ንጉሠ-ነገሥት ተክለ-ጊዮርጊስ ተብሎ ነገሷል፤)፣ የትግሬውን በዝብዝ ካሣ ምርጫን (አጼ ተክለ-ጊዮርጊስን ከያዘና ዐይናቸውን ጎርጉሮ አውጥቶ ከገደለ በኋላ አጼ ዮሐንስ 4ኛ ተብሎ ነግሷል)፣ ጨምሮ ሁሉም ጠላቶቹ ተባበሩና የእንግሊዝን ጦር እንደየ አቅማቸው ይረዱ ጀመር። አጼ ቴዎድሮስ ግን በናፒር ተማርከው ከሚዋረዱና አገራቸውንም ከሚያዋርዱ ይልቅ የራሳቸውንና የአገራቸውን ክብር እንደጠበቁ መሞትን መርጠው ሽጉጣቸውን ጠጥተው ወደቁ። ህዝቡም የሚከተለውን ቅኔ እየተቀኘ ህዘኑን ገለፀላቸው፤--

*ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኟቸው፤*





*ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው፤*

*ለወሬ አይመቹም ተንኮለኛ ናቸው፤*

*ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው።*

በሌላ አንፃር ግን ቴዎድሮስ በኃይል ስለ ገዙዋቸው በቴዎድሮስ ሞት የፈነጠዙም ብዙ ነበሩ። አንድዋ አልቃሽ በሚከተሉት ስንኞች ይህን ሁኔታ ገለጠች-

*ባለድባብ ንጉሥ ባለ ጥና አቡን*

*አየዞሩ ፈትዋት ኢትዮጵያን።*

*መላ የጎጃም ሰው፥ መላ የበጌምድር፥*

*መላው የትግሬ ሰው፥መላው የሸዋ ሰው ተይዞ በምጥ፥*

*የእንግሊዝ ሃኪሞች መጥተው ቢይዙት፥*

*ተገላገለ አሉ ይህ ሁሉ ፍጥረት።*

አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ እንደጻፉት አጼ ቴዎድሮስ በዘር አማራ አልነበሩም። ቋራ {ቁዋሬ} ናቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለአማራ አልወገኑም። ታማኝ አገልጋይዎቻቸው እነደ ጃዝማች ገልሞ እና ደጃዝማች ጠህዩ ቅማንት ነበሩ። ከአማራዎች ይልቅ እነሱን ያምኑ ነበር። አማርኛ አቀላጥፈው ይናገሩ ነበር። አማራ ሆኑ አልሆኑ አጼ ቴዎድሮስ ፈጽሞ የአማራን ሥር-መንግሥት እወክላለሁ አላሉም ወይም በፍፁም የአማራ ሥርወ-መንግሥት የሚል አልመሰረተም። በሠራዊቱ ውስጥ በርካታ አማሮች እንደነበሩ ግን እሙን ነው። የንጉሥ ሰሎሞን እና የቀዳማዊ ምኒልክ ደም አለኝ ያለው በእናቱ በወይዘሮ አትጠገብ አብተው በኩል ሲሆን በርግጥም የአጼ ቴዎድሮስ እናት የሰም ንጉሠ-ነገሥት የነበሩትና ስለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት እንደገና ሲመሰረት ዙፋን ላይ የተቀመጡት የአጼ ዮሐንስ ሳልሳዊ ዝርያ ነበሩ። የሆነው ሆኖ የዘር ሐረጋቸውን ጠበቅ አድርገን ስንመዝ

የሰለሞን ደም በደም ሥራቸው ውስጥ እናገኛለን፡፡ የአጼ ልብነ-ድንግል ዝርያ ናቸው፡፡



ምንም እንኳ በአባታቸው በኩል ዘራቸው ቋራ ቢሆንም የአጼ ቴዎድሮስ እናት ያፍ መፍቻ ቋንቋ አማርኛ ከሆነ (ይሆናል ብዬም አስባለሁ) እና ቴዎድሮስ በአማርኛ አፋቸውን ከፈቱ በጎሣ ትርጉም መሰረት ጎሣቸው አማራ ይሆናል፡፡ በዘራቸው አማራ እንዳልሆኑ ግን አለቃ አፅመጊዮርጊስ ግልጥ አድርገው አስቀምጠውታል፡፡ አጼ ልብነ-ድንግል በእናታቸው ከቱሉ በዴሳ ልጅ ከኦሮሞይትዋ ከጽዮን ሞገሣ ነው የሚወለዱት፡፡ ከፍ ሲል አጼ ቴዎድሮስ ከእሳቸው አብራክ ይፈልቃሉ፡፡ የአጼ ቴዎድሮስን ማህተም ስንመረምር የተለመደውን የይሁዳ አንበሳን ምሥል ይዟል፡፡ ለንግሥት ቪክቶሪያ እና ለሌሎችም





በጻፉአቸው ደብዳቤዎች ላይም የአባቶቻቸውን ንጉሣዊ ግዛት (ሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት) እግዚአብሔር ከኦሮሞዎች እጅ አውጥቶ እንደመለሰላቸው ጠቅሰዋል፡፡ (በአጼ ቴዎድሮስ ደም ስር ውስጥ የኦሮሞ ደም መኖሩን ያስታወሰ አንባቢ መቸም ፈገግ ማለቱ አይቀርም) ከሁሉም በላይ ደግሞ በደብዳቤዎቹ አናት ላይ ‹‹የእግዚአብሔር ባሪያ፣ የዳዊት እና የሰለሞን ልጅ›› የሚል ማስታወቂያ ይነበብ ነበር፡፡ አሟሟታቸው አሳዛኝ ቢሆንም አጼ ቴዎድሮስ እውነተኛ የንጉሠ-ነገሥትነት ሥልጣን ይዘው ኢትዮጵያን እንደገና አንድ አድርገው ለማዋሃድ ያደረጉት ብርቱ ጥረት ከንቱ አልቀረም፡፡ ከእልፈተ-ሕይወታቸው በኋላ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በእግራቸው የተተኩት አጼ ተክለ-ጊዮርጊስ፣ከዛም አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክ፣ አጼ ኃይለ-ሥላሴ የልፋታቸው ውጤት ተቋዳሾች ሆነዋል፡፡ በዘመነ-መሳፍንት ከነበረችዋ ኢትዮጵያ ይበልጥ የሰፋች አገር መውረስ ችለዋል፡፡ እላይ ጠቆም እንዳደረግኩት፥ ወታደራዊው ደርግ የገዛት እና ሕወሃት ኢህአዴግም ዛሬ እየገዛት ያለችው ኢትዮጵያ ዳር ድንበርዋ የተፈጠረ በአጼ ቴዎድሮስ፥ በአፄ ዮሃንስ፥ በአፄ ምኒልክ እና በአፄ ኀይለሥላሴ ጥረት ነው፡፡ ኢሕአዴግም ቢለቅና ማንኛውም ዓይነት መንግሥት ቢመሰረትም መጪውም መንግሥት የሚረከበው ያሁኗን ኢትዮጵያን ነው፡፡

የተከፋፈለች ኢጣሊያንን ለማዋሀድ እና የተበታተነች ጀርመንን አንድ ለማድረግ እንደ ቅደም ተከተላቸው ጋሪባልዲ እና ቢስማርክ ለየአገሮቻቸው ብዙ ደክመዋል፡፡ የጣልያንና የጀርመን ሕዝቦች ያን ጊዜ አስተዋዮቹ መሪዎቻቸው በሠሩላቸው የውህደት እና የአንድነት ሥራ ዛሬ በዓለም መድረክ ኃያላን ሕዝቦች ለመሆን በቅተዋል፡፡ ያን ጊዜ ጋሪባልዲ እና ቢስማርክ ለውህደት ባካሄዷቸው ጦርነቶች ዛሬ የጣልያንና የጀርመን ሕዝቦች ዕድለኞችና ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡ ብልሆቹ የወቅቱ የአውሮጳ መሪዎችም አውሮጳን ያለምንም ደም መፋሰስ አንድ እያደረጓት ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም ላለፉት 60 ዓመታት በፍጥነት እያደገ የመጣው የፖለቲካ ብስለት አውሮጳን ወደ ውህደት ለማምጣት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል፡፡ አሁን አውሮጳ 300 ሚሊዮን ሕዝብ ይዛ አሜሪካንንና ቻይናን የምትፎካከር አንድ ጠንካራ አገር እየሆነች ነው፡፡ አብርሃም ሊንከን በተገንጣዮቹ በደቡቦቹ ላይ አስከፊና አውዳሚ ጦርነት በማካሄድ የተዋሀደች አሜሪካንን ፈጥሯል፡፡ በደቡብ

ተገንጣዮች ላይ የተቀዳጀው ድል ዛሬ የዓለም ኃያል አገር የሆነች አሜሪካንን አስገኝቷል፡፡ ከባድ ዋጋ ተከፍሎ በተገኘው አንድነት ሳቢያ የተፈጠረውን ዴሞክራሲና ብልጽግና ክደቡብም ክሰሜንም ያሉ ሁሉም አሜሪካኖች በመቋደስ ላይ ናቸው፡፡ እንኳን እነሱ በሃገራችን ውስጥ በደረሰብን መከራ እና ሰቆቃ እኛም ወደ አሜሪካ ሸሽተን ጥጋት አግኝተን የአሜሪካን አንድነት ባስገኘው ነፃነት እና ብልፅግና ተሳታፊ ለመሆን በቅተናል፡፡ አንድነትንና መልካም አስተዳደርን እስመልክቶ የኢትዮጵያ ሁኔታም ከዚህ የተለዩ አይሆንም፡፡ ኢትዮጵያ ጠንካራ ልትሆን እና ልትበለጽግ የምትችለው በእኩልነት ላይ በተመሰረተ እውነተኛ አንድነት፣ በጋራ መከባበር እና በሕግ የበላይነት መስፈን ብቻ ነው፡፡ ሕገ-መንግሥታዊት ሪፑብሊክ አገር ሆና ለግለሰብ እና ለብዙሃን መብቶች፣ ለሁሉም ዋስትና ሲሰጥ፣ ብሔሮች በትልቋ ኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው የውስጥ ነጻነታቸው ተክብሮ እውነተኛ የራስ-ገዝ የውስጥ አስተዳደር መብት ሲኖራቸው ነው፡፡

እሮሞ እና አማራ በማናቸውም ምክንያት እርስ በርሳቸው ቂም ቢያያዙም ያለፈውን መቆፈር ለዛሬው አጣዳፊ ችግር መፍትሔ አይሆንም፡፡ ወይም በማንኛውም መንገድ ለነገው አይበጅም፡፡ መፍትሔው ይቅር መባባል እና እርቅ ማውረድ ብቻ ነው፡፡ አርቆ አሳቢው እና ይቅር ባዩ ኔልሰን ማንዴላ ምሳሌያችን ሊሆን ይገባል፡፡ ዘረኞቹ ነጮች እሱን በአካል ለ27 ዓመታት በእስር ቤት አጉረው ምን ያህል እንዳሰቃዩት እና በህዝቡ ላይም ምን ያህል ጉዳት እና ሰቆቃ እንዳደረሱ መታወስ አለበት፡፡ ባለፈው ጊዜ ውስጥ ሆኖ ላጥፊዎች ተገቢ የሚባል ቅጣት ከማስጠት ይልቅ ማንዴላ ከፈላጭ ቆራጮች ነጮች ጋር ለመታረቅ እና ይቅር ለመባባል ወሰነ፡፡ ይህን ያደረገው በቀጣይ የሚደርሰውን የደም መፋሰስ እና የህገሩን ውድመት ለማስቀረት ሲል ነው፡፡ በውጤቱም ሥልጣን በሰላማዊ መንገድ ወደሱ ሕዝብ ተላለፈና ያላግባብ ይደርስ የነበረው የህይወት እና የንብረት ውድመት ተረፈ፡፡ ከጥቁሩ የደቡብ አፍሪቃ ሕዝብ ጋር በዘር፣ በባሕል፣ በኤክኖሚ፣ በፖለቲካ፣ እና በንግድ እንኳ ሳይቀር ለመነካካት ከሚፀየፉ ክለየላቸው ዘረኞች ነጮች ጋር እንኳ መታረቅ እና ይቅር መባባል ክተቻለ ኢትዮጵያውያን ተቀላቅለው፣ ተጋብተው፣ ተዋልደው፣ ተዛምደው፣ አንድ ዓይነት ደም፣ መልክ፣ አመለካከት እና ሥነ-ልቦና፣ ኖሮአቸው፣ ተመሳሳይ ወግ፣ ባሕል፣ ታሪክ እና አገር





ተጋርተው ለ4000 ዓመታት እንደኖሩት ሁሉ አሁንም እርስ በርሳቸው ይቅር የማይባባሉበትና ሌላ አዲስ ሕይወት የማይቀጥሉበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ አርቆ አሳቢነት፣ ቅን ልቦናና በጎ ፈቃደኛነት ካሉ ይህንን የተከበረ ዓላማ በርግጠኝነት ማሳካት ይቻላል፡፡

ገብረ-መድህን ይባል የነበረው፣ የዘውድ ስሙን ተክለ-ጊዮርጊስ ያለው፣ የላስታውና የዛጉዌው ጎበዜ በ1861 ከአጼ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ላሊበላ ተብሎ ነገሠና በሰለሞናዊው ዙፋን ላይ ተቀመጠ፡፡ ካሳ ምርጫ ባይማርከውና በ1864 ዮሐንስ 4ተኛ ብሎ ራሱን በአክሱም ባያነግሥ ኖሮ (ላሊበላ) የዛጉዌን ሥርወ-መንግሥት እንደገና ሳይመሰርት አይቀርም ነበር፡፡

አጼ ዮሐንስም እንዲሁ የሰለሞን ሥርወ-መንግሥት ተወካይ ነኝ አሉ፡፡ በዚያ ሥርወ-መንግሥት ውስጥ አራተኛው ዮሐንስ መሆናቸው ነው፡፡ ከእርሳቸው በፊት በዚያ ሥርወ-መንግሥት ውስጥ ሦስት ዮሐንሶች ነግሠዋል፡፡ የትግሬ ሥርወ-መንግሥት ልመስርት ግን አላሉም፡፡ እንደዚያ ብሎ ነገር ከዚያ በፊት በትግሬ መኳንንቶች ታሪክ ቀርቶ በአማራውና በኦሮሞው እንኳ አልነበረምና፡፡ ቢሆንም ቅሉ ኦሮሞዎች ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ በጋብቻ አማካይነት የሰለሞን ሥርወ-መንግሥት አባላት መሆን ችለዋል፡፡ አጼ ቴዎድሮስ እና አጼ ዮሐንስ ከሰለሞናዊው /እሥራኤል/ አግአዚ መኳንንት ጋር በአጼ ፋሲል በኩል የደም ዝምድና ነበራቸው፡፡ በሪሁን ከበደ፤ "የአጼ ኃይለ-ሥላሴ ታሪክ፤" በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 147 ላይ እንደ ፃፉት ራስ ሚካኤል ስሑልም ከጎንደሩ አጼ ፋሲል ጋር ይዛመዳሉ፡፡

እንደ አቶ በሪሁን ከበደ የአጼ ዮሐንስ አግአዚ-ሰለሞናዊ ደም ከአጼ ፋሲል እስከ ሹም ተምቤን ምርጫ ወደ ታች ፈስሷል፡፡ አጼ ፋሲል የራስ አንስጣትዮስን እናት ንግሥት እህተ-ማርያምን ወለደ፡፡ ራስ እንስጣትዮስ ቢትወድድ ጊዮርጊስን ወለደ፡፡ ቢትወደድ ጊዮርጊስ ወይዘሮ ወለተ-ዮሐንስን ወለደ፡፡ ወይዘሮ ወለተ-ዮሐንስ ወይዘሮ መና-እስራኤልን ወለደች፡፡ ወይዘሮ መና-እስራኤል ሹም ተንቤን ምርጫን ወለደች፡፡ ሹም ተንቤን ምርጫ ካሣ ምርጫን ወለደ፡፡ ካሣ ምርጫ በንግሥና ስሙ አጼ ዮሓንስ 4ተኛ የተባለው ነው፡፡ አጼ ዮሐንስ 4ተኛ ለአግአዚ-ሰለሞናዊ ሐረጉ የሚጨነቅ አልነበረም፡፡ በዚህም ምክንያት እንደሌሎቹ አግአዚ-ሰለሞናዊ ነገሥታት በማህተሙ ላይ

"ድል አድራጊው የይሁዳ አንበሳ" የሚል ጽሁፍ አሳስቀረፀም፡፡ *ሆኖም ራሱን የጽዮን ንጉስ ብሎ ይጠራ ነበር፣ በማሕተሙ መካካልም ዘውድ የደፋ አንበሳ ነበረው፡፡*

የአጼ ዮሐንስን ማሕተም ይመለከቷል፡ ማህተሙ የአረብኛ ጽሑፍ ነበረው፡፡ ጽሑፉ "ንጉሠ ነገሥታት ዮሐንስ ንጉሠ ፅዮን ዘ ኢትዮጵያ፥ ዘ አምነገደ እስማኢል" የሚል ነበር፡፡ "ዘ እምነገደ-እስማኢል" የሚለውን ጽሁፍ ሳይ ዐይኖቼን አላመንኩም ነበር፡፡ የገዛ ዐይኖቼን ተጠራጠርኳቸው፡፡ ሌሎች ሰዎች እንዲያነቡልኝ እስከመጠየቅም ደረስኩ፡፡ ሁሉም "ነገደ እስማኤል" እያሉ አነበቡልኝ፡፡ እስካሁን አልተዋጠልኝም፡፡ ዐይኖቼ ቢሳሳቱ እመርጣለሁ፡፡ አጼ ዮሐንስ የአረብ ዝርያ ያላቸው ይመስል በማህተማቸው ላይ ለምን "ነገደ እስማኤል" የሚል ጽሁፍ አስቀረጹ? አጼ ዮሐንስ ሙስሊም እንኳ አለመሆናቸውን እናውቃለን፡፡ እንዲያውም በርካታ ሙስሊሞችን በጉልበት ጭምር ወደ ክርስትና እምነት የመለሱ አክራሪ ክርስቲያን ነበሩ፡፡ ፍጹም የተጉ ክርስቲያን ነበሩ፡፡ ከእስራኤል ሰለሞናዊ የዘር ሐረግ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ስለማያውቁትና እስማኤልም የአብርሃም ልጅ ስለሆነ፣ አብርሃምም የእስራኤላውያን ሁሉ አባት ስለሆነ ከእስማኤል ጋር የነበረውን ዝምድና መቀበላቸው ይሆን? ከአብርሃም ዘር ማፈግፈጋቸውና ከአብርሃም እስራኤላውያን ልጆች ጋር ያላቸውን ዝምድና በተዘዋዋሪ ማወጃቸው ይሆን? ማሕተሙን አሳስተን ካላነበብነው በስተቀር ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ እስካሁን የነበሩ የታሪክ ጸሐፊዎች ይህን ክስተት ለምን ሳያነሱ እንዳለፉትም ይገርመኛል፡፡ ምናልባት በየግል ምክንያታቸው ዝምታን መርጠው ይሆናል፡፡









አጼ ዮሐንስ - የራስ ሚካኤል ስሑል ዝርያ በመሆናቸው ይሆናል አቶ በሪሁን ከበደ የጠቀሱት፡፡ አጼ ዮሐንስ ከሰለሞናዊው የደም መስመር ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ባኖራቸውም እንኳ እርሳቸው ግን በማህተማቸው ላይ ‹‹የይሁዳ አንበሳ›› የሚል ምልክት አስቀርፀው ዝምድናው ያላቸው አስመስለዋል፡፡ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ይሠራበት እንደነበረው ‹‹በእግዚአብሔር የተሾመ፤ የጽዮን ንጉሥ፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት›› የሚል ግልጽ አርማም ነበራቸው፡፡ የመንግሥታቸው የሥራ ቋንቋም ትግርኛ ሳይሆን አማርኛ ነበር፡፡ እላይ የሰፈረውን ከማህተማቸው ስር የአለው ቁራጭ ደብዳቤያቸው እንደሚመሰክረው፡፡ ቀደምት ዝርያዎቻቸው ሰለሞናዊያን /እሥራኤላውያን/ ኣግኣዝያን ያደርጉት እነደነበረው ደብዳቤ ሲጽፉ በግዕዝ ይጀምሩና በአማርኛ ይቀጥሉ ነበር፡፡

እላይ ከተጠቀሰው ጋር በተያያዘ አግአዚዎች ትግሬ አለመሆናቸውን ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከተው እግአዚዎች ከእሥራኤልና ከጋዛ የመጡ አይሁዶች እና የዮቅጣን ጎሣ ዓባላት ናቸው፡፡ ትግራይ የሚለውን ስያሜ ያስገኙት ቲጋሩዎች ምንጮቻቸው ‹‹ቲክሪት›› የተባለች ከተማ እና ጥንት ሜሶፖታሚያ ይባል የነበረው የዛሬው ኢራቅ ውስጥ ያለው ‹‹የጤግሮስ/ቲግሪስ/›› ወንዝ ሸለቆ

መንግሥት እጃቸው ከተቱ። ዳግማዊ አጼ ምኒልክም ከአጼ ልብነ-ድንግል ጋር ከአህመድ ግራኝ ሸሽቶ መንዝ ተደብቆ በነበረው ትንሹ ልጃቸው በያቆብ በኩል ይዛመዳሉ። (‹‹ሞአ አንበሳ ዘ-እምነገደ ይሁዳ ድል እድራጊው የይሁዳ ነገድ አንበሳ››) ተብለው ነገሡ። ዳግማዊ ምኒልክ ብቻ ሳይሆኑ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ-ሥላሴ ፍፃሜ ድረስ ሁሉም ንጉሠ-ነገሥቶች ለአይሁድ ነገድ እውቅና ለጥተዋል፤ ከአይሁድ ነገድ ነን እያሉም አውጀዋል። ከአይሁድ ነገድ፣ ከአግአዚና ከሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ጋር ምንም የደም ዝምድና ያልነበረው የገናናው፣ የኢትዮጵና የደሸት ልጅ አማራው ለኢትዮጵያ ስልጣኔ በተለያዩ የእውቀት ዘርፍ እና የሥራ ጥበብብ ከማበርከቱ በተጨማሪ በነበረው ታላቅ የጦር ብቃት እና ችሎታ የሀገሩን የኢትዮጵያን ዳርድንበርና መንግሥት በታማኝነት ና በቅነነት በመጠበቅ ና እባክህ ለመንገሥ እርዳን ሲሉት ያመነበትን እና የሚወደውን በማንገሥ፣ እንዲሁም ተባበረን ሲሉት ጥያቄው ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ሲመስለው ከዙፋን መውረድ ይገባዋል የአለውን ሲያወርድ ኖረ። አማራው ሚናውን ጠንቅቆ የተረዳ፣ ፍጹም ታማኝነት የተካነ ስለ ሆነና የስልጣን ጥማት ስላልነበረው እንጂ ቢፈልግ ኖሮ የማይበገር የጦር ኃይል ስለነበረው ሌሎችን በማንገሥ ፈንታ ራሱን እንዳይነግሥ ምንም የሚያግደው ነገር አልነበረም። በዚህ የተአማኝነት ጠባዩና ለስልጣን ባለመስገብገቡ የማራ ልጅ አማራ ሊወደስ እና ሊደነቅ ይገባዋል። እድሉ መጥፎ ሆኖበት ግን ለኢትዮጵያ ለዋለው ውለታ ተገቢውን ካሳ ካለመከፈሉ ም በላይ በመሸለም እና በመመስገን ፈንታ እሱ ባልዋለበት ና ባላጠፋው ነገር ፥ ቋንቋው የመንግሥት አፍ በመሆኑ ብቻ እንደ ገዢ መደብ ታይቶ በየአቅጣጫው መጠቃቱ ነው።

ስለ አጼ ምኒልክ ቤተሰብ ጥቂት ለማለት ያህል፣ የዳግማዊ ምኒልክ እናት እጅጋየሁ ለማ አዲያሞ ከላስታ ነበሩ፤አገው ሳይሆኑ አይቀሩም። አያታቸው ደጃዝማች አዲያሞ የላስታ ባላባት ሲሆኑ አባታቸው ለማ ደግሞ ፊታውራሪ ነበሩ። የምኒልክ ባለቤት እቴጌ ጣይቱ ብጡል የኦሮሞ ደም አላቸው። የወንድማቸው ልጅ ኦሮሞው ጉግሳ ወሌ አባትዋ ንጉሠ-ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ሲሞቱ ንግሥተ-ነገሥታት የሆነችውን ዘውዲቱ ምኒልክን አግብቶ ነበር። ጣይቱ ፥ በዘመነ-መሳፍንት ጎንደር ሆኖ ኢትዮጵያን ከገዛው የኦሮሞ ቤተ-ሰብ





ከሆነው ከየጁው ሌሩ ጓንጉል ይዛመዳሉ። አጼ ምኒልክም በኦሮሞ ሹማምንት ነበር የተከበቡት። ለምሳሌ ገበየሁ ጎራ፣ ባልቻ አባ ነፍሶ፣ ሃብተ-ጊዮርጊስ ዲነግዴ፣ አሉላ ብጡል፣ ወሌ ብጡል እና ምንም እንኳ ሰለሞናዊውን/የኦሮሞ/ ሥርወ-መንግሥት እንደገና ለመመስረትና ለማጠናከር በተደረገው ጦርነት በርካታ የኦሮሞ ግዛቶችን በመውጋታቸው በአንዳንድ የዘመኑ ተራማጆች ዘንድ የተጠሉ ቢሆኑም ራስ ጎበና ዳጨም የሚጠቀሱ ናቸው።

የንግሥት ጣይቱ ወንድሞች አሉላና ወሌ ከምኒሲክ ጋር በመቅደላ የአጼ ቴዎድሮስ እስረኞች ነበሩ። ከዚያ አምልጠው ወደ ሸዋ መጡና ቀደም ሲል ከቴዎድሮስ አምልጦ መጥቶ ንጉሥ የሆነውን ምኒልክን ተቀላቀሉ። ሁለቱ ኦሮሞ ወንድማማቾች ከምኒልክ ጋር በመቅደላ እስር ቤት ለዓመታት አብረው ስለቆዩ የጠበቀ ወዳጅነት ነበራቸው። ለዚህ ነበር ከቴዎድሮስ አምልጠው ወደ ሸዋ መጥተው በደስታ የተቀበሉአቸውን ምኒልክን የተቀላቀሉት። ጣይቱ ወንድሞቿን ልትጠይቅ ስትመጣ ከምኒሊክ ጋር ተዋወቀች።

ከቴዎድሮስ እና ከዮሐንስ በኂላ የቀድሞውን የኢትዮጵያን አንድነት እንደገና የመመለሱና እንዲት ሉዓላዊት አገር የመፍጠሩ ሃላፊነት በምኒልክ ትከሻ ላይ ወደቀ። ለፋፊ ግዛት ከያዙት ውስጥ አብዛኞቹ ምኒልክ የዮሐንስ ወራሽ መሆኑን ተቀብለው በሰላም ገቡላቸው። እነሱም የጎንደር፣ የጎጃም፣ የወሎ፣ የትግሬ፣ የኤሉባቦር፣ የሲዳማ እና የወለጋ መሪዎች ነበሩ። የወለጋ ባላባቶች ኩምሳ ሞረዳ እና ጆቴ ጦርነት ውስጥ ቢገቡ እንደሚሸነፉ ስላወቁና የውስጥ አስተዳደር ነፃነታቸው እንደሚከበርላቸው በምኒልክ ቃል ስለተገባላቸው አስተውለው ወሰኑና ለምኒልክ ገቡ። በመሆኑም ለነሱም የውስጥ አስተዳደር መብት ተጠበቀላቸው፤ ላገሪቱም የግዛት አንድነቷ ሰመረላት።

የተወሰኑትን የጊቤ ግዛቶች ወርሮ ያጠፋቸው የኦሮሞው ንጉሥ አባ ጂፋርም እንዲሁ በሰላም ለምኒልክ ገባና የግዛቱን ደህንነትና ብልፅግና አስከበረ። ምኒልክም በክብር እና በእንክብካቤ ያዙት። ጠፍቶ የነበረውን ያገሪቱን አንድነት እንደገና ለመመለስ ምኒልክ የተጠቀሙበት የራሳቸው ለላማዊ ብልሃት ነበራቸው። መጀመሪያ ለባላባቱ ምክር አዘል መልዕክት ይልኩበታል፤ ‹‹አሁን ንጉሠ-ነገሥትህ

እኔ ነኝ፤ እውቅና ስጠኝና የኔን የበላይ ገዢነት ተቀበል፤ በዚህም የደም መፋሰስን እናስወግድ፤ ግብሬን አስገባልኝ!›› ይሉታል፡፡ ባላባቱ በዚህ ሀሳብ ከተስማማ ምኒልክ ማእረጉን አሳድገው ይሾሙትና በያዘው ግዛት ላይ ሌላ ግዛት ይጨምሩለታል፡፡ ወይም የያዘውን ያፀድቁለታል፡፡ ባላባቱ በደረሰው መልዕክት ካልተስማማ ግን ደም መፋሰስንና የጦርነት ውድመትን ባይጋብዝ የተሻለ መሆኑን በድጋሚ ያስገነዝቡታል፡፡ አሁንም አሻፈረኝ ካለ ምኒልክ ጦርነት ገጥመው ያሸንፉታል፤ ከዚያም በሚገርም ሁኔታ ተሸናፊውን ምህረት አድርገውለት መልሰው በሥልጣኑ ላይ ያስቀምጡትና የበላይነታቸውን በተጨባጭ ያሳዩታል፡፡ የወላይታው ንጉሥ ካኦ ጦና ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ ይህ ሰው ምኒልክ ደም መፋሰስንና የንብረት ውድመትን እናስቀር እያሉ በተደጋጋሚ ቢያስገነዝቡትም፣ ቢማጠኑትም አልሰማ ብሎ ወደ ጦርነት ውስጥ ገባና ቆስሎ ተማረከ፡፡ ምኒልክ ግን በቀድሞ የወላይታ ንጉሥነት ሥልጣኑ ላይ መልሰው አስቀመጡት፡፡ የምኒልክ ይቅር ባይነት፣ ትዕግሥት እና መሓሪነት ብዙውን ጊዜ አፀፋውን አስገኝቶላቸዋል፡፡

የተወለኑት ባላባቶች ለምሳሌ ይማም መሐመድ ዓሊ (በኋላ የወሎው ንጉሥ ሚካኤል የተባለው)፣ ይማም አባ ዋጠው (የወሎዋ የንግሥት መስተዋት ልጅ)፣ መርእድ አዝማች ኃይለ-ሚካኤል እና የሸዋው ደጃዝማች መሸሻ ሰይፉ፣ የትግራዩ ራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ እንዲሁም የበጌምድሩና የሰሜኑ ራስ ዘውዴ በምኒልክ ላይ ሁለት፣ ሦስት ጊዜ አመፁባቸው፡፡ ምንም እንኳ አንዳንዶቹ የሞት ፍርድ ቢገባቸውም ምኒልክ ግን ደጋግመው ማሩአቸው፡፡ የሚያስገርመው ነገር ሁለቱም የወሎ ይማሞች፣ መሐመድ ዓሊ፣ እና እባ ዋጠው በተደጋጋሚ ሲያምፁባቸው ምኒልክ ግን ደጋግመው ምህረት ከማድረጋቸውም በላይ ክርስትና እያስነሱ (ይማም አባ ዋጠው፣ ኃይለ-ማርያም የሚል የክርስትና ስም ተሰጥቶታል፤) የክርስትና አባት እየሆኑእቸው በሹመት ያሳድጉአቸው ነበር፡፡ ክርስትና ከተነሳ እና ራስ ሚካኤል ከተባለ በኋላ ምኒልክ ልጃን ሸዋረጋን ለይማም መሐመድ ዓሊ መዳራቸውም እርግጥ ነው፡፡ የምኒልክ ተተኪ ልጅ ኢያሱ የተወለደው በዚህ ጋብቻ ነበር። ምኒልክ በዚህ መልክ ያገሩን አንድነት አንፃራዊ በሆነ ሰላም እና መረጋጋት ማስጠበቅ ችሎ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ እነዚህ የጦር አበጋዞች እና የ ሀገር መሪዎች በ1896 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ወቅት





ወራሪዋን ጣልያንን ድባቅ በመምታት ረገድ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል፡፡ በዚህ ወቅት እንደ እናት ተወደው ‹‹እምዬ›› እስከ መባል ከደረሱት ምኒልክ ጋር ትብብር የቸሩት አንዱም በአፄ ምኒልክ የቻይነት ፀባይ እና መልካም አስተዳደር ሰኬት ነው፡፡ ትናንሽ ግዛቶች በማእከላዊው መንግሥት ስር መጠቃለላቸውን የተቃወሙትን ግን ምኒልክና ተባባሪዎቻቸው ክፉኛ ቀጥተዋቸዋል፡፡ የጡት መቁረጡን ማስረጃ - ቢስ ክስ እንኳን ብንተወው፣ ለምሳሌ የሜጫና የአርሲ ኦሮሞዎች የምኒልክን መስፋፋት ሲቃወሙ አምነው እስከሚገቡ ድረስ ያለርኅራኄ ተመትተዋል፡፡ እነሱም ግን እጃቸውን እጣጥፈው አልተቀመጡም፡፡ ጠንክረው በጀግንነት ተዋግተው የምኒልክ ሰራዊት ላይ ከፍተኛ እልቂት ፈፅመዋል፡፡ ከዚያ በኋላም አምነው በሰላም ስላልገቡላቸው ምኒልክ የራሳቸውን የጦር አበጋዞች ገዢ እያደረጉ በእነሱ ግዛት ላይ ሾመውባቸዋል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በሰላም አምነው ለገቡት ግን የየራሳቸው መሪዎች እንዲያስተዳድሯቸውና እና የውስጥ አስተዳደር ነፃነታቸው እንዲጠበቅላቸው ነው የተደረገው፡፡ ያም ለነሱ መልካም ነበር፡፡

አፄ ምኒልክ ንጉስ ጋኪ ሸሮቾን ከፋ ለዳግማዊ ምኒልክ እንዲገብር እና ግዛቱ እንዲከበርለት በተደጋጋሚ ቢጠይቁትም አልገብርም ብሎ ኃይለኛ ጦርነት ተነሳና የምኒልክን ጦር 9 ወር ገትሮ በመያዝ ከባድ ጉዳት አደረሰበት፡፡ በመጨረሻ ንጉሥ ጋኪ ሸሮቾ ተማረከና በሰንሰለት ታሰረ፡፡ ግዛቱም ለምኒልክ ጭቃሹሞች ተሰጠ፡፡ (አለቃ ገብረ-ሥላሴ፤ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ*፤ ገጽ 277)

ቀደም ሲል እንዳልኩት ፣ አጼ ምኒሊክ የወላይታ ንጉሥ የነበረውን ጦናን እንዲገብርላቸውና ደም መፋሰስን እንዲያስቀር ለመኑት፡፡ ጦና ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ለጥቂት ቀናት በጀግንነት ተዋግቶ ክፉኛ ቆስለና ተማረከ፡፡ ምኒልክ ጦናን ከመጨረስ ይልቅ ማሩትና ገባሪያቸው አድርገው ወደ ቀድሞ ስልጣኑና ግዛቱ መለሱት፡፡ (አለቃ ገብረስላሴ፤እላይ በተጠቀሰው. ገጽ 220) ጦና ባይዋጋም ኖሮ የምኒልክን ንጉሠ-ነገሥትነት እስከተቀበለ ድረስ ግዛቱን ማስተዳደር ይቀጥል ነበር፡፡ ምኒልክ ኢትዮጵያን እንደገና ባንድ ሉዓላዊ ንጉሠ-ነገሥት ሥር ሲያዋህዱ ጥበባዊ አመራራቸው እንደዚያ ነበር፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከምኒልክ የጦር አበጋዞች መካከል በሰላምም ይሁን በኃይል ኢትዮጵያ እንድትሰፋ እና አንድነቷ እንዲጠበቅ ምኒልክን የረዱት ክኦሮሞ ወታደሮቻቸው ጋር የኦሮሞ ባላባቶች መሆናቸው መታወስ ይኖርበታል። ለምሳሌ ንጉሥ አባ ጂፋር፣ የወሎው ንጉስ ሚካኤል፣ ራስ አሉላ ብጡል፣ ራስ ወሌ ብጡል፣ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ (አባ ነፍሶ)፣ ፊታውራሪ ገበየሁ ጎራ እና ፊታውራሪ ሀብተ-ጊዮርጊስ ዲነግዴ ይጠቀሳሉ። ይህ እንግዲህ ራስ ጎብና ዳጨን ክዝርዝሩ ውስጥ ሳናስገባ እንኳ ነው። እነዚህ ሁሉ የጦር አበጋዞች ለኢትዮጵያ አንድነት ቆርጠው የተነሱ ነበሩ። ምክንያቱም እነ ጋሪ ባልዲ በጣልያን፥ እነ ቢስማርክ በጀርመን እና እነአብርሃም ሊንክን በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ታላቅ መስዋእትነትን ክፍለው የየሀገራቸውን አንድነት እንዳስጠበቁት ሁሉ እነዚህም ታላላቅ ኢትዮጵያውያን ክንጉሣቸው ጋር ተባብረው የሀገራቸውን አንድነት መጠበቅ ለኢትዮጵያ የሚጠቅማት መሆኑን በመገንዘባቸው በዘመናቸው ላገራቸው ሊያደርጉላት የሚችሉት የላቀ ነገር ያ ነው ብለው ስላመኑበት ነው። ያለነሱ ቁርጥ ውሳኔና ትብብር አጼ ምኒልክ በዘመነ መሳፍንት ተበጣጥሳ የነበረችውን ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ወደጥንት ቦታዋ ለመመለስ የነበራቸው ራዕይ ባልተሳካም ነበር።

አንዳንድ ሽማግሌዎች እንደሚሉት ዳግማዊ ምኒልክ በጠና በታመሙበት ወቅት አባቱን የወሎውን ራስ ሚካኤልን ንጉሥ-ጽዮን ብሎ (ጽዮንን ለማስታወስና የሰለሞናዊውን ሥርዎ-መንግሥት ለመጥቀስ ነው) ያነገሠው የምኒልክ የልጅ፣ ልጅ፣ ኢያሱ ለህዝብ ይፋ አልሆነም እንጂ በ1906 ዓ.ም በአዲስ እበባ በምስጢር ኢያሱ 4ተኛ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ተብሎ ነግሶ ነበር። ንግሥናው ለህዝብ ይፋ ያልሆነበት ምክንያት በክርስቲያን ሥርዓተ-ንግሡ ላይ ኢያሱ ሙስሊሞች ፀሎት ሲያደርሱና ድቤ እየመቱ ነቢያቸውን መሐመድን ሊያወድሱ እንደሚያደርጉት ሁሉ ራሱን እየወዘወዘ ሙስሊም መስሎ ስለነበር ነው። ይህ ታሪክ እውነት ይሁንም አይሁን ንጉሠ-ነገሥታዊ ሥልጣን ባይኖረው ኖሮ አባቱን ንጉሥ ብሎ ባልሾመም ነበር። ምክንያቱም ከንጉሠ-ነገሥትነት ያነስ ሥልጣን ያለው ሰው ንጉሥ ብሎ መሾም አይችልም። ቢሾምም አይፀናም።

ኢያሱ የምኒልክን ልጅ ዘውዲቱንና ተፈሪ መኮንንን ወደ ሥልጣን ባመጣው መፈንቅለ-መንግሥት ከተገለበጠ በኋላ የዳግማዊ





አጼ ምኒልክ አያት የሸዋው ንጉሥ የንጉሥ ሣህለ-ሥላሴ የልጅ ልጅ-ልጅ የሆነችው ዘውዲቱ በ1909 ዓ.ም በምኒልክ ዙፋን ላይ ተቀመጠች። ተፈሪ መኮንን በነበረው የማስገደድ ኃይል ባንድ ጊዜ ልዑልና ንጉሥ ሆኖ አደገ። ንግሥት ዘውዲቱ ለተፈሪ መኮንን መንገዱን ጠርጋለት እስከ ዕለተ-ሞቷ እስከ 1923 ዓ.ም ድረስ በሰለሞናዊው ዙፋን ላይ ቆየች እና ልክ እሷ ስታርፍ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ‹‹ንጉሠ-ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ-ሥላሴ፣ በእግዚአብሔር የተመረጠ አሸናፊው የይሁዳ አንበሳ›› ተብሎ ነገሡና 44 ዓመት ከገዛ በኋላ በ1967 ዓ.ም በህዝባዊ አብዮት ክሥልጣን ተወገዶ የመጨረሻው የሰለሞን /አግአዚ/ኦሮሞ/ ሥርወ-መንግሥት ንጉሠ-ነገሥት ሆነ። ኃይለ-ሥላሴ ባመዛኙ ኦሮሞ ነው። እናቱ የሺእመቤት ዓሊ ጋምጬ በአባትዋ በኩል የወረሂመኑ ኦሮሞ ናት። በአዲሱ ግኝት መሰረት ይብረሁልሽ በተባለቻው ስልጤ-ጉራጌ እናትዋ ‹‹ቂቶ›› ትባል የነበረችው አያትዋ ወ/ሮ ወለተ-ጊዮርጊስ የወሎው-ኦሮሞ ነቢይ የሼሕ ሁሴን ጅብሪል ልጅ ናት።( )

ይህ ማለት ሼኽ ሁሴን ጅብሪል የአጼ ኃይለ-ሥላሴ ቅድመ-አያት ናቸው ማለት ነው። ቅድመ አያቶቹ ሙስሊሞች የመሆናቸው ይህ እውነታ እስከ ዕለተ-ሞቱ ድረስ ትልቅ ምሥጢር ሆኖ እንዲያዝ ተደርጓል። የቀዳማዊ እና የዳግማዊ ምኒልክን ፈለግ ተክትሎ ራሱን ‹‹በእግዚአብሔር የተመረጠ፣ የነገሥች ንጉሥ፣ ድል አድራጊ የይሁዳ አንበሳ›› ብሎ የሰየመ በመሆኑ እስላምነቱ የሰለሞናዊ-ይሁዲያዊ - ክርስቲያን ዙፋኑን ይጎዳል ብሎ ሰለሰጋ ነው። ወንድ ቅድመ-አያቱ ባባታቸው በኩል ጉዲሳ የሚል የኦሮሞ ስም ነው ያላቸው። በኋላ እንደተረጋገጠው ጉዲሳ አሳዳጊያቸው ሲሆኑ ትክክለኛ ቅድመ-አያታቸው ግን ከትግራይ ተንቤን ወደ ሸዋ ዶባ የመጡ ወልደ-መለኮት የሚባሉ ትግሬ ነበሩ። ዶባ መጥተው የአንድ ባላባት ልጅ አገቡና ደጃዝማች ወልደ-ሚካኤልን ወለዱ። ደጃዝማች ወልደ-ሚካል ክዳግማዊ አጼ ምኒልክ አያት ክንጉሥ ሣህለ-ሥላሴ ልጅ ከልዕልት ተናኜ ወርቅ ራስ መኮንንን ወለዱ (የአጼ ኃይለ-ሥላሴ ባለቤት እቴጌ መነን አስፋውም እንዲሁ ከልጅ ኢያሱ በቅርብ የምትዛመድ የወሎ ኦሮሞ ደም ያለባት ናት ተብሎ ይታሰባል። የአህቱ የወይዘሮ ስሂን ሚካኤል ልጅ ናት።

እስካሁን ከቀረበው ሀተታ ተነስተን የሚከተለውን መደምደም እንችላለን፤ አማራው ኢትዮጵያን እንደ ሥርወ-መንግሥትም ሆነ እንደ ግለሰብ ንጉሠ-ነገሥት/ንግሥተ-ነገሥት/ በመሆን ወይም የአማራ ስርወ-መንግሥት በማቋቋዉዋም ፈጽሞ አልገዛም። ይህም ሲባል በራሱ ክፍለ-ሀገራት የራሱ ነገሥታት አልነበሩትም ማለት አይደለም። በተለያዩ ዘመናትና ግዛቶች ለራሱ ለአማራ፣ የአማራ ነገሥታት ነበሩት። የቅርብ የቅርቡን እንኳዋን ብንተወው፥ የዛሬ 2000 ዐመት በአንድ ጎጃም ላይ በጣና አካባቢ ብቻ 4 የአማራ ንጉሦች ነበሩ።-- በቅድመ-አባቱ በደሸት ከተማ የጎንጂ እና ጉንዳጎንዲት ንጉሥ የነበረው አጎጃ ጀባን፥ የጣና ደጋና የአካባቢው የነበሩ ሶስት ነገሥታት ወንድማማቾች፥ አቦል፥ ቶና እና በረካ የሚባሉ ነበሩ። ቡና ጠጪዎች አቦል፥ ጦና እና በረካ እያሉ የሚጠጡት ምናልባት እነዚህን ታላላቅ ነገሥታት ለማስታወስ ይሆናል። አጎጃ ጃባንን እና እነዚህን ሶስት የአማራ ንጉሦች ታላላቅ የሚያደርጋቸው ህዝባችውን በፍትህ እና ባስተዋይነት ማስተዳደራቸው ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት ግዛት ተነስተው የመሲሁን መወለድ የምታበስረውን ኮከብ ተከትለው ገፀበረከት ይዘው ቤተልሄም ድረስ ሄደው ለዐለሙ መድህን ለእየሱስ ክርስቶስ ከሰገዱለት 12 ኢትዮጵያውያን ወንድማማች ጠቢባን ነገሥታት መሃል በመሆናቸው ነው። ከዚህ በተቃራኒ ያለው ጭቅጭቅ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚዘወር የፈጠራ ታሪክ ነው። ያም ሆነ ይህ አማራ የጦር ኀይልም የፖለቲካ ስልጣንም በፍፁም አልነበረውም፣ በሰለሞናዊ-ኦሮሞ ሥርወ-መንግሥት ውስጥ አስተዳዳሪና ዳኛ ሆኖም አልሠራም ማለት አይደለም። በፊት እዳስረገጥኩት፥ በርግጥ አማሮች ንጉሦችን ደግፎ የማውጣት እና ዘርጥጦ የማውረድ የጦር ኃይል ችሎታ ነበራቸው። ከአመኑበት፥ ንጉሥ ለማንገስ እና ለመሻር አጋዥ ኃይሎች ነበሩ። በኦሮሞ ንጉሣውያን ቤተሰቦች ለሚመራው የኢትዮጵያ መንግሥትና ለፍትሕ ሥርዓቱም በነበራቸው የወታደራዊና የትምሕርት ችሎታ ብዙ አበርክተዋል። በየግዛታቸው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ለንጉሠነገሥቱ ተጠሪ የሆኑ የራሳቸው የአማራ ንጉሦች ቢኖሩአቸውም ፥ ባብዛኛው በራሳቸው ምርጫ ፀሀፍት ፥ ሊቃውንት፥ ባለቅኔዎች፥ ገበሬዎች፣ ባለእጆች፤ ነጋዴዎች፣ አዝማሪዎች፤ ካህናት ፥፣ ዳኞች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ምሁራን እና መምህራን ነበሩ። ይህ እውነታ





አማሮችን የገዢው መደብ አባላት ወይም ልሂቃን እንደነበሩ አያስቆጥራቸውም።

ከአስራ አራት ዓመት በፊት ወደ ጎጃም ስሄድ አባይን እና ደጀንን አልፈን ግርግዳቸው በጭቃ፣ ጣራቸው በሰንበሌጥ የተሰሩ ቤቶች ያሏት አንዲት ሥልጣኔ ያልጎበኛት የምትመስል መንደር ደረስንና ‹‹ደብረ-ማርቆስ ለመድረስ ምን ያህል ይቀረናል?›› ስል ሾፌሬን ጠየቅሁት። አየት አደረገኝና ‹‹ማርቆስ ይቺ ናት›› አለኝ።

‹‹ደብረ-ማርቆስን ማለቴ ነው›› አልኩት።

"እኮ! ይቺ ናት ደብረ-ማርቆስ" ሲል መለሰልኝ። አማራው እንደ ሥርወ-መንግሥት ኢትዮጵያን ሲገዛ ኖሯል ብዬ እንደአብዛኛው ሕዝብ አስብ ስለነበር ዘመናዊ ሕንፃዎች እና በርካታ መኪናዎች የሚርመሰመሱባቸው አስፋልት መንገዶች ለማየት ጠብቄ ነበር። ‹‹ተሞኘሁ!›› ስል አጉመተመትኩ። ‹‹ምን ጠብቀው እንደነበር አውቃለሁ››፤ ሾፌሩ አስተያየቱን ሰነዘረ፤ ‹‹እኔም መጀመሪያ ደብረ-ማርቆስ ስመጣ እንዲሁ ነበር የተሰማኝ›› አለ።

‹‹ኗሪዎቹ ያገሪቱ ገገሮች ናቸው። አማሮች ናቸው። እንዴት ይህን ያህል ጎስቋሎች ሆኑ!›› ተገረምኩ። ‹‹ትርኪ-ምርኪ ናት!›› መንዝን፣ ተጉለትን፣ መርሐ-ቤቴን፣ ቡልጋን፣ ጋይንትን፣ ላስታን፣ ጎንደርንና አማራ ሳይንትን ቢያዩ ምን ሊሉ ነው! የባሱ ናቸው። ሰው ሊኖርባቸው የማይችል፣ በድህነት የተመቱ ናቸው። እኔ በነዚህ ቦታዎች አልኖርም። አብዛኛው ሰው ባዶ እግሩን ነው የሚሄደው። አንዲት ልብስ ካለችው እሷኑ እላዩ ላይ ብጥሥጥስ እስክትል ይለበሳታል። ጥቂት የአማራ ልሂቃን ሥልጣን ላይ አሉ ማለት ሰፊው የአማራ ሕዝብ አልፎለታል ማለት አይደለም። በፍፁም! ሰፊው የአማራ ሕዝብ የስቃይ ኑሮ ነው የሚገፋው›› አለ። ትክክል ነበር።

ያ ሁኔታ ስለ አማራው ሕዝብ ለነበረኝ አስተሳሰብ መለወጥ አንድ ምክንያት ሆነ። በርግጥ ኢትዮጵያን የሚገዙ ከሆኑ ለምን ይህን ያህል ከልክ ያለፈ ጎስቋሎች ሆኑ? ስል ጠየቅሁ ራሴን። ይህ ጥያቄ መልሱን ራሴ እንድፈልግ አነሳሳኝ። በዚህ ጽሁፍ እንዳያችሁት አሁን መልሱን አግኝቸዋለሁ ብዬ አምናለሁ።

በ1967 ዓ.ም የአጼው ሥርዓት ከተወገደ በኋላ እንኳ ርእሰ-ብሔር ሆኖ የመራ ሙሉ በሙሉ አማራ የሆነ አንድም ግለሰብ የለም። ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ትግሬ፤ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ኦሮሞ፣ የቀድሞው ፕሬዝዳንቶች መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ባንድ በኩል ኮንሶ ማለትም ኦሮሞ፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ደግሞ ኦሮሞ፣ በፊት ፕሬዝዳንት በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው መለስ ዜናዊ በወላጆቹ ትውልድ ኤርትራዊ ነበር እንጂ ከነዚህ አንዳቸውም አማራ አልነበሩም። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአድዋ የተወለደ ሙሉ በሙሉ ኤርቴራዊ የሆነ ሰው ነው። አዲስ የተሾሙት የይስሙላ ፕሬዝዳንቶችም ቢሆኑ ግርማ ወልደ-ጊዮርጊስ ቅይጥ ብሔረ-ሰብ ሲሆን፣ የአሁኑ ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ኦሮሞ ነው። ስለዚህ ‹‹አማራ ገፋን፤ ጨቆነን›› የሚለው ጩኸት መሰረተ-ቢስ ውንጀላ እና ህዝቡን ለማነሳሳት እና ራሳቸውን ለማጠናከር የፈለጉ ፖለቲከኞች የፈጠሩት ‹‹ማታገያ ጠላት›› ነው። የእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች እንዲህ ዓይነቱን ፈጠራ “bogeyman” ይሉታል፤ የአማርኛ አቻው የልጆች ማስፈራሪያ ‹‹ጭራቅ›› እንደ ማለት ነው። በልጅነቴ ትንሽ ሞልቀቅ ብዬ እናቴን ሳስቸግራት አንድ ጋሼ አበበ የሚባል ሰውዬ ‹‹ ጎረዳማንን ነው የምጠራው!›› ሲለኝ እብረክረክ ነበር። ፡፡ጎረደማን የሚለውን ቃል ገና ሲጠራብኝ ሞት የተጠራብኝ ያህል ስለምፈራ ወዲያውኑ አዋቂዎቹ የሚፈልጉትን ፀባይ አሳይ ነበር። ቀድሞ ነገር አማራን ማስፈራሪያ ማድረግ እንደገና ወደ ሥልጣን የሚያወጣ መስሏቸው ከሆነ አስቂኝ ነው። ያም ሆነ ይህ አማራ ሥልጣን ቢኖረው እንኳ እንዲገለል ከተደረገ ከ40 ዓመት በላይ ሆኖታል። የሚያሳዝነው አማሮች የውጭ ዜጎች የሆኑ ያህል በገዛ አገራቸውና በገዛ ርስታቸው ከግራም ከቀኝም በፖለቲካ ጥላቻ ከመኖሪያቸው እያፈናቀሉ ሲያሰቃዩዋቸው ራሳቸውን ጥንት የኢትዮጵያን ዳርድንበር በውትድርና ያልጠበቁ ያህል አሁን ለራሳችው መከላከል እንኳ ያልቻሉ መሆናቸው ነው።

አማሮች የራሳቸው ሥርወ-መንግሥት ሳይኖራቸውና እንደ ሌሎቹ ርዕሰ-ብሔር ሳይሆኑ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሚናቸው በዋናነት መንግሥትን መጠበቅና ያገሪቱን የግዛት አንድነት እና ሉዓላዊነት ማስከበር፥ ከዚህ ሲያልፍም በየግዛታቸው በንጉሥነት፥ በእርሻ፣ በንግድ፣ በአስተዳደር፣ በቤተ-ክህነት እና በባህላዊ ትምህርት ቤቶች በመምህርነት ማገልገል ሆኖ ሳለ ‹‹ኢትዮጵያን እንደ ሥርወ-





መንግሥት በጭካኔ ገዝተዋል›› እያልን ያን ያህል እንዴት ልንዋሽ ቻልን?

ለዚህ መደናገር አራት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ቋንቋቸው ነው። በተረትና ምሳሌዎች፣ በዘይቤዎች፣ በቅኔ፣ በሰምና ወርቅ አባባል በኅብር አነጋገር የበለፀገው አማርኛ ቋንቋ። ይህ ቋንቋ ታዋቂ የሆነው የውትድርና እና የንግድ ተግባራቸውን ለማሟላት መላ ኢትዮጵያን ዳር እስከዳር ያካለሉ በነበሩ በአማራ ወታደሮችና በነጋዴዎች ነው። በተጨማሪ በሁለቱም በዛጉዬ እና በሰለሞናዊ ሥርወ-መንግሥቶች ነገሥታት ከዚያም አልፎ በ አፄ ዮሐንስ እና በወቅቱ የትግሬ መንግሥት ጭምር የሥራ ቋንቋ ሆኖ ስለሚ ሠራበት ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ አማርኛ ከአሥራ ሁለተኛው፣ አሥራ ሦስተኛውና አሥራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመናት ጀምሮ ነው በሦስት አበይት ንጉሠ-ነገሥቶች በላሊበላ፣ በይኩኖ-አምላክ እና በዳግማዊ ኢያሱ በይፋ የሥራ ቋንቋ ተደርጎና ፀድቆ እየተሠራበት ያለው። ላሊበላ የላስታ-አገው ተወላጅ ሲሆን ይኩኖ-አምላክ እና ዳግማዊ ኢያሱ ደግሞ ሁለቱም የኦሮሞ ዝርያዎች ናቸው። አማርኛ ብሔራዊና መንግሥታዊ ቋንቋ መሆኑ ፋይዳው ቁልጭ ብሎ ስለታያቸው ነው ያንን ያደረጉት። በተለይ ዳግማዊ ኢያሱ ግዕዝ በቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ እንዲወሰንና አማርኛ ግን በመላ ግዛቱ ለሁሉም መንግሥታዊ ሥራዎች መገልገያ እንዲሆን በሕግ ደንግጓል። እነዚህ ንጉሠ-ነገሥታት አንዳቸውም አማራ እንዳልሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ ‹‹የአማራ ነገሥታት አማርኛን አማርኛ ተናጋሪ ባልሆኑ ሕዝቦች ላይ ጫኑባቸው›› ብሎ መደምደም ጨርሶ አያስኬድም። ስዚያውም አማራውን ወክሎ አንድም የአማራ ንጉሠ-ነገሥት በሥልጣን ላይ ባልወጣበት ሁኔታ።

የተለያዩ ብሔረሰቦች አባላት በኢትዮጵያ ውስጥ አስተዳዳሪዎች እየሆኑ ለመሥራት አማርኛ ተማሩ። ብዙዎቹ ሥራቸውንና ማኅበራዊ ደረጃቸውን አስጠብቀው ለመኖር ከአማራ ጋር መቀላቀልና ራሳቸውን አማራ ማድረግ መረጡ። አማራ እንደ ገዢ መደብ የተቆጠረበት ሁለተኛው ምክንያት አማራነትና ክርስቲያንነት አንድ ቃል የሆኑ እስከሚመስል ድረስ እማሮች የተዋሕዶ እምነትን ከአግአዚ/ኦሮሞና

ዛጉዌ ነገሥታት ጋር መጋራታቸው ነው፡፡ ሦስተኛው ምክንያት አማሮች ኢትዮጵያን እንደ ሥርወ-መንግሥት መላዋን ኢትዮጵያን አስመግዛታቸው በወጉ አስመታወቁ ነው፡፡ አራተኛውና የመጨረሻው ምክንያት ከላይ ጠቆም እንደተደረገው ሆን ተብሎ የሚሠራጭ ውዥምብር እና የፖለቲካ ሰዎች አማራን እንደ የጋራ ጠላት አስቆጥረው ሠፊውን ሕዝብ በመቀስቀስና በማስተባበር የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት ያደርጉት የነበረው እንቅስቃሴ ነው፡፡ አማሮች በዚህ የተነሳ ስስቆቃ መዳረጋቸው፣ በተለያዩ ጊዜያት እንደ ገዢ መደብ እየታዩ ከቤት ንብረታቸው መፈናቀላቸውና መለቃየታቸው ያፀፅታል፡፡ ብዙሃኑ አማራ ግን ከጥንት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የገዢ መደብ ሳይሆኑ እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ዜጎች በውትድርና እና በተለያዩ ሙያዎች ተሰማርተው ደፋ ቀና ሲሉ የኖሩ ናቸው፡፡

የአማራን ትክክለኛ ማንነት በተመለከተ አንዳንድ የአውሮፓ ምሁራን ተብዬዎች እንደሚሉት አማሮች ሴማውያን አይደሉም፡፡ ኦሮሞና አማራ ካንድ ምንጭ ነው የተቀዱት፡፡ ቀደም ሲል እንደተረጋገጠው ኦሮሞና አማራ በዘርም አንድ ናቸው፡፡ ኦሮሞዎች ኩሻውያን ከሆኑ አማሮች እንዴት ነው ሴማውያን የሚሆኑት? አንድ ሰው ቋንቋቸውን ሴማዊ አድርጎ ስለመደበው አማሮችም ሴማውያን ተደርገው የሚመደቡ ከሆነ ግልብ ምደባ ነው፡፡ ቋንቋ ዘርን አይወስንም፤ ጎሳን ነው እንጂ፡፡ ቀድሞ-ነገር አማርኛን ‹‹ሴማዊ ቋንቋ›› ነው ብሎ መመደቡ አጠያያቂ ነው፡፡ ለምሳሌ እንደ ግዕዝ ባሉ ሴማዊ ቋንቋዎች ውስጥ የማይገኙ ድምጾች በአማርኛ

እና በኦሮምኛ ውስጥ አሉ፡፡ እነሱም ‹‹ ከ € ’ I µ Ê Û ›› ናቸው፡፡ እነዚህን በመሰሉ የአማርኛና የኦሮምኛ መሰረታውያን ድምፀ-ልሳናት ላይ የተደረገው ጥናት እንደሚያብራራው አማርኛ ከግዕዝ ይልቅ ለኦሮምኛ ነው የሚቀርበው፡፡ እነዚህ ድምፀ-ልሳናት የአማርኛ እና የኦሮምኛ ናቸው እንጂ የግዕዝ አይደሉም፡፡ እነዚህ የፊደላት ድምፆች የኩሽ ቋንቋዎች መስኪያና መሰረታውያን ጠባያት ናቸው፡፡ ወደፊት በአማርኛ እና በኦሮምኛ ቋንቋዎች ላይ የሚደረግ ጥልቅ የንፅፅር ጥናት አዲስ ውጤት ይሰጠን ይሆናል፡፡

የሙዚቃው ቃና /melody/ ወይም ባለ አራት ቅኝቱ የአማርኛና የኦሮምኛ ሙዚቃ እንኳ ከአረቡ ወይም በእብራይስጥ ምንም





ግንኙነት የለውም፡፡ የአማርኛና የኦሮምኛ አልፎም የኑቢያ (ከሥር ከመሠረቱ ጥቁሮች የሆኑ ኩሻውያን ሱዳኖች) ሙዚቃዎች ግን ተመሳሳይ ቅኝት ነው ያላቸው፡፡ የአረብና የእብራይጥ ሙዚቃዎች ግን አማሮችንና ኦሮሞዎችን ጨምሮ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ጆሮ እና ልቦና አይመስጡም፤ አይጥሙም፡፡ የኦሮሞና የአማራ ሙዚቃዎች ግን ተመሳሳይ ቅኝት እና ምት አላቸው፡፡ ይህም ሁለቱ ህዝቦች አንድ ዓይነት የነገድ እና የባሕል ዳራ ያላቸው ስመሆኑ ማረጋገጫ ነው፡፡

አማሮች ኩሻውያን ሆነው ሳለ ለምን ሴማዊና ሐበሻ ተብለው ተፈረጁ? ምክንያቱ ምንጫቸው እሥራኤል ከሆነ እግአዚያን ጋር ስለተምታቱ ነው፡፡ የንጉሥ ሰለሞን እና የንግሥት ሳባ ልጅ ቀዳማዊ ምኒልክ ከሦስት ሺ አመታት በፊት አባቱን ለመጠየቅ ወደ እሥራኤል ሄዶ የአይሁድን ሃይማኖትና ባሕል እየተማረ ጥቂት አመታት ከቆየ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ 40,000 ጠንካራ እያሁዳውያን እና በጋዛ የሚኖሩ ኢያቡሳውያን ወንዶችን ይዞ መምጣቱ መታወስ ይኖርበታል፡፡ ቀዳማዊ ምኒልክ እነዚያን 40,000 እሥራኤላውያን ‹‹አግአዚ/ነፃ አውጪ/›› ብሎ ስይሞ ሥልጣን ስለሰጣቸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለ3,000 ዓመታት የተጋቢቸውን ኢትዮጵያውያንን ማንነት ማስለወጥ አልቻሉም እንጂ በኢትዮጵያ ሃይማኖት፣ ቋንቋ ፖለቲካ እና ባሕላዊ ገጽታዎች ላይ ተፅእኖ ማሳረፍ ችለዋል፡፡ እነዚያ 40,000 እሥራእላውያን ወንዶች በኢትዮጵያ ሰፍረው ከአገር በቀል ነዋሪዎቹ ኩሻውያን አንስቶች ጋር ተጋቡ፡፡ ኢትዮጵያ በዋናነት ኩሻዊት አገር ነበረች፤ የኩሽ ምድር ትባልም ነበር፡፡ በዚህም ከእሥራኤል የመጡት 40 ሺ ወንዶች በሶስት ሺ ዓመታት የኢትዮጵያ ቆይታቸው ‹‹ሴማዊ ደማቸውን›› አጥተው ‹‹ኩሻዊ ደም›› ያዙ፡፡

በኢትዮጵያ የሚኖሩ ኣግኣዚዎች የአይሁድ እምነታቸውን ጠብቀው ከመያዛቸው በቀር በአካል ከተቀሩት ኢትዮጵያውያን ምንም የማይለዩ የሆኑት ለዚህ ነው፡፡ በርግጥ ቀዳማዊ ምኒልክ ቋንቋቸውን ግዕዝን የሥርወ-መንግሥቱ የይፋ ቋንቋ ስላደረገው አባብሶባቸዋል፡፡ ከ2,000 ዓመት በፊት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ ጋር ተያይዞም ግእዝ በአድገቱ ቀጥሏል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ተተረጎመበት፤ የእግዚአብሔር ቃል ይሰበክበት ጀመር፤ ቅዱስ ያሬድ መዝሙራቱን ቀመረበት፤ በሌላ አባባል ግዕዝ የቤተክርስቲያን ቋንቋ ሆነ፡፡ ባሕላዊ እምነታቸውን ጠብቀው ከኖሩት ከኦሮሞዎች ጋር ሲነፃፀሩ በርካታ አማሮች ወደ

ክርስቲያን ተዋሕዶ ሃይማኖት ተሰወጡ። ብዙ ቁጥር ያላቸው ግእዝን እየተማሩ ቀሳውስት ሆኑ። በዚህ ሳቢያ በሁሉ ነገራቸው በዘራቸው ሳይቀር ሴማውያን መሰሉ። ሀቁ ግን እንደ ሥጋ ዘመዶቻቸው እንደ ኦሮሞዎቹ ኩሻውያን መሆናቸው ነው። ልክ ገዢዎቹ አግአዚዎች አማርኛን የመንግሥታቸው የሥራ ቋንቋ አድርገው ስለሠሩበትና የተወለኑ አማሮች ወታደሮች ሆነው መንግሥቶቻቸውን፣ ሃይማኖታቸውንና ያገራቸውን ዳር ድንበርና አንድነት ስመጠበቅና ለማስከበር በመላ አገሪቱ ደፋ-ቀና በማለታቸው የገዢው መደብ አባላት ተደርገው ሲታዩ እንደኖሩት በማንነታቸውም እንደ ሴማዊ ተቆጠሩ።

‹‹ሀበሻ›› የሚለው ስም ወይም አምደ-ቃል አማሮችን አይወክልም። ይህንን ነጥብ ለማስረገጥ መነሻውን መዳሰስ ያስፈልገናል። ቃሉ መስሎ እንደሚታየው አዎንታዊ ፍቺ ያለው አይደለም። ይልቅስ የወረደ ትርጉም ነው ያለው። መጀመሪያ የተጠቀሙበት ፈላሻ አይሁዶች ሲሆኑ አጠቃቀማቸውም አግአዚያን አይሁዶችን ለመስደብ ነበር። ሁኔታው ባጭሩ ሲቀርብ የሚከተለውን ይመስላል፤ በ598 ዓ.ዓ ባቢሎናውያን እሥራኤልን በወረሯት ወቅት በርካታ እሥራኤላውያን ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አግአዚዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ 400 ዓመት ሆኗቸው ነበር። አግአዚዎች ከኢትዮጵያውያን ጋር እየተጋቡ በባሕል ተመሳስለውና ራሳቸውን ኢትዮጵያውያን አስመስለው መኖራቸውን አዲሶቹ መጪዎች አይተው ‹‹ካልተገረዙ ጋር ተቀላቅለው አይሁድነታቸውን አርክሰዋል›› በሚል ነቀፏቸው። በዚህ ምክንያት ‹‹ሀበሻ›› የሚል ስም አወጡላቸው። ትርጉሙም ‹‹ድቅል፣ ንፁህ ያልሆነ ወይም የተካለሰ ›› ማለት ሲሆን በተራዘመ ፍቺው ደግሞ ‹‹የተበከለ፣ የቆሸሸ›› ማለት ነው። አግአዚዎቹ ደግሞ በአፀፋው አዲስ መጤዎቹን ‹‹ፈላሻ›› አሏቸው። ‹‹ስደተኛ›› ማለት ነው። በተራዘመ ፍቺው ደግሞ ‹‹አገር-አልባ›› ማለት ይሆናል። ይህ ነው ሁኔታው። ይህ እንግዲህ በሁለቱ የአይሁድ ቡድኖች መካከል የተፈፀም አተካራ ሲሆን ከአማራ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። አማሮች አበሾች አይደሉም። ራሱን እንደ ሀበሻ የሚቆጥር ማንኛውም አማራ ካለ ታሪኩን የማያውቅ ብቻ ሳይሆን ራሱን የሚዋርድም ነው። **‹‹ኢትዮጵያ››** የሚለው ስም ኦሮሞን + አማራን እና ሁሉን ኢትጵያውያንን የሚያቅፍ እና የታላቁን ፃድቅ አባታችንን የ**‹‹ኢትዮጵ››**ን መጠሪያ የያዘ በመሆኑና ፍቺውም ‹‹**ለእግዚአብሔር የሚበረከት የቢጫ ወርቅ ሥጦታ**›› ማለት ስለሆነ እኛ ሁላችንም **‹‹ኢትዮጵያውያን››** ተብለን ነው መጠራት ያለብን። ከ**‹‹ኢትዮጵያ››** በላይ የሚያኮራ ታላቅ ስም ከቶ የለምና!።





ፈላሻዎቹ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹን የአይሁድ ሰፋሪዎችን አግአዚዎቹን ሴማዊነታቸውን ትተው ኩሻውያን ወይም ኢትዮጵያውያን በመሆን ሀበሻ ሆነዋል ሲሉ ትክክል ነበሩ። ቀደም ብዬ እንዳልኩት ከማይታወቅ ጊዜ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ታሪክ የምናምንበት ከሆነ በኖህ ዘመን ከደረሰው የጥፋት ውኃ በኋላ ኩሽ በኢትዮጵያ ከሰፈረበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን የኩሽ ህዝብ ነበር የምንባለው። አግአዚንና ፈላሻዎችን ጨምሮ የተለያዩ ሴማውያን ሕዝቦች በአነስተኛ ቁጥር ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ከኢትዮጵያውያን ጋር እየተቀላቀሉ በኩሻዊነት ውስጥ እየሰመጡ ቀርተዋል። በሌላ አባባል አዲስ መጪዎቹ ሴማውያን በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ውስጥ ጠፍተዋል ወይም ተውጠዋል። በባሕሩ ውስጥ ጠብታ ውሃ ሆነዋል ማለት ነው። ስለዚህ በባሕሩ ውስጥ ሟሙ እንጂ ባሕሩን አልበከሉትም።

አማሮች ከመነሻቸው ከጎጃም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ኩሻውያን ናቸው። ካንዳንድ ሴማውያን ጋር መዳቀል ቢኖርም ኩሻዊነታቸውን ቅንጣት አልለወጠውም። ከጥንት ከመነሻቸው እንደነበሩት አሁንም ያው ኩሽ ናቸው። ሴማዊነቱ ሙሉ በሙሉ ያልተረጋገጠውን ቋንቋ እንደ መስፈርት ወስዶ **‹‹አማርኛ ሴማዊ ስለሆነ አማሮች ሴማውያን ናቸው››** ብሎ መደምደም ስህተት ነው። ከዚህ በላይ ደግሞ ቋንቋ ሁል ጊዜ የሰውን ዘር እንደማያረጋግጥ እስተውሰናል። ለምሳሌ በርካታ አፍሪቃውያንና አፍሪቃ-አሜሪካውያን እንግሊዝኛ፣ ስፓንኛ እና ፈረንሳይኛ አቀላጥፈው ይናገራሉ። ቢሆንም ዘራቸው አንግሎ-ሳክሶን፣ ሂስፓኒክ እና ፈረንሳይ ነው ብለን አንደመድምም። ቋንቋቸው ሴማዊ ቢሆን እንኳ ለአማሮችም ልክ እንዲሁ ቋንቋቸው ሴማዊ ስለሆነ እነሱም ሴማውያን ናቸው አንልም።

ያለ አማሮች ወታደራዊ ድጋፍ፣ አግአዚ/ሰለሞናዊ እና በኋላም አግአዚ/ኦሮሞ ስርወ -መንግሥታት ገና ከመነሻቸው በተንኮታኮቱ ነበር። ያ ብቻ አይደለም፤ የኢትዮጵያ ነፃነት ሳይቀር አደጋ ላይ ይወድቅ ነበር። ለዚህ ተግባራቸው ኢትዮጵያውያን በሙሉ የአማሮች

ውስታ አስባቸው። አማሮች የኢትዮጵያ ነፃነት ጠባቂዎች ሆነው ባከናወኑት የመስዋዕትነት ተግባር ባንፃራዊ መልኩ ይበልጥ ጠንከር ያለ የኢትዮጵያዊነት ስሜት አዳብረዋል። ስዚህ ነው አማሮች ዘረኝነትን ከሚያራምዱ ነገዶች በተቃራኒው ከምንም ነገር በፊት ከአማራነትም በላይ ኢትዮጵያዊነት እጅግ ጎልቶ የሚበልጥባቸው።

አንዳንድ ሰዎች አንኮበሬ የሚባሉትን ከጠቅላላው አማራ ጋር ያምታታሉ። ሸዋ ውስጥ ከሚገኘው ከአንኮበር በመነሳት አንኮበሬዎች የሚባሉት የሸዋ ልዑላን እና ነገሥታት ፈጽሞ ራሳቸውን እንደ አማራ አይቆጥሩም ወይም የአማራ ሥርወ-መንግሥት እንወክላለን ብሰው አያውቁም። ራሳቸውን የሚቆጥሩት የአግአዚ-እስራኤል-ሰሎሞናዊ ሥርወ-መንግሥት ዝርያ አድርገው ነው። አንኮበሬዎች አማሮች ቢሆኑ እንኳ አሁን በሥልጣን ዐታቸው ላይ የሉም። ከ42 ዓመት በፊት አፄ ኃይለሥላሴ ከስልጣን ሲወርዱ ከፖለቲካው ተወግደዋል። ስለዚህ እነሱ በተጨባጭ ማስረጃ አጥፍተዋል ከተባለ የነሱ መጥፎ ሥራ ነው የሚባለውን መቆፈር ለዛሬው ችግራችን ምንም መፍትሄ አይሆንም።

አንዳንዶቻችን ስለ ገዳ ሥርዓት ማዳነቅ እና መከራከር እንወዳለን። ባንድ ወገን እውነታችንን ነው። ህዝብን በሚውክሉ በህገር ሽማግሎች በጎ ፍቃድና ከትውልድ ትውልድ በተላለፈ ደንብ የሚመረጡት ጎልማሶች እያንዳንቸው ግዛታችውን ለስምንት ዐመታት አስተዳድረው ጊዜያቸው ሲያበቃ ያለ ደም መፋሰስ መሰናበት እውነተኛ ዲሞክራሲ ነው። በዚህ ረገድ ከአሜሪካ ዲሞክራሲ ጋር መሳ ለመሳ ይራመዳል። "ከስልጣኔ ሞት ብቻ ይገላግለኝ" ለሚሉት የአፍሪካ መሪዎችም ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው። ይህን ስርአት የፈለሰፉት አባቶቻችን ክብር ይገባቸዋል። ዛሬ ላይ ሆነን ግን የገዳ ሥርዓት ጊዜ አላለፈበትምን? በምርጫ መስተዳደር ደስ የሚለውና የሚያኮራ አንዱ የገዳ ስአርት ገጥፅታ ሲሆን ሌላው ገፅታው ግን ያነጋግራል። ሙሉው የገዳ ስርአት ዛሬም በ21ኛው ክፍለ-ዘመን በኢትዮጵያ ሊሠራ ይችላልን? ባሁኑ ወቅት የገዳ ሥርዓትን ለወግ እና ለማስታወሻ ሳይሆን፥ በተሟላ መልኩ ወይም ገፅታው የሚሠሩበት ኦሮሞዎች ስንቶች ናቸው? እነሱስ እነማን ናቸው? የትስ ናቸው? የገዳ ሥርዓትን ከእነ ሙሉ ገፅታው መተግበር ጊዜ ለማሳለፍ ሽርሽር መውጣት አይደለም። ድንቅ ከሆነው እና በአርአያነት ከሚታየው





ዴሞክራሲያዊነቱ ባሻገር ዘረፋን፣ ጦርነትን፣ ወረራንና ግዛት ማስፋትትን ያበረታታል፤ ምርኮኞችን መስለብን እንደ ጀግንነት ይቆጥራል። አዲሱ ሉባ ካለፈው የተሻለ ሆኖ ለመገኘት እነዚህን ድርጊቶች መፈፀም ይጠበቅበታል። የዛሬይቱ ኢትዮጵያና የዐለም ሁኔታ እውነታ ግን ይህን አይፈቅድም። ስለዚህ እኛ ተምረናል የምንለው ሰዎች ከገዳ ስርዐት መጥፎውን ትተን መልካሙን፥ ማለትም የዲሞክራሲ ባህሪውን እና ጥበትን አስመውደዱን ብቻ አድንቀን እነሱን እንቀስማልን።

የድሮውን ለማውሳት ያህል ግን ፥ ኦሮሞዎች በኬንያ፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲ፣ በማሊ፣ በኒጀር እና በናይጄሪያ ዛሬ የሚገኙት ለምንድነው? የገዳው አዳዲስ ወጣት ሉባዎች አዳዲስ ግዛቶችን ለመያዝ ባደረጉት እንቅስቃሴ ነው። የገዳ ተፈጥሮው ወይም አንድ መሰረታዊ ባህርዩ በስፋት ሆነው ሳይጣበቡ መኖር ነው። ‹‹ኦሮምያ›› በተባለች አንዲት ጠባብ ክልል መወሰን የገዳ ባህርይ አይደለም። የኦሮሞ ቀልብ እና መንፈስ በጠባብ ቦታ መታጨቅና መታሰር አይወድም። ስገዳ ሥርዓት የሚሟገቱ ከሆነ ከጠባብነት በተቃራኒው ያለውን የሰፊነት ጠባዩን መቀበል ይኖርብዎታል። ኬኩን ሊያስቀምጡትም ሊበሉትም አይችሉም። ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ ከጠባብ ክልል እና ከሰፊው አገር ምረጥ ቢሉት ሰፊውን ነው የሚመርጠው። ምክንያቱም ለዘመናት በገዳ ሥርዓት የተቃኘው ተፈጥሮው እንደዚያ ነዋ!

ክፍ ሲል የትልቁ የኢትዮጵ ፥ ዝቅ ሲል የነቢዩና የፈላስፋው የደሸት ልጆች የ ሆኑት እውነቶኞቹ ኦሮሞዎች አገራቸው ድፍን ኢትዮጵያ የኔ ናት ብለው ያስባሉ ። ኦሮምያ ብቻ በምትባል ጠባብ ስፍራ መወሰን አይሹም። መጣበብ እና መጨነቅ ባህሪያቸው ስላልሆነ። አሮምያ ተብሎ የተሳለ አንድ ካርታ ዐይቼ ነበር። ይህን ካርታ በተመለከተም የምለው አለኝ፤ ካርታው ጎጃምንና ጎንደርን አላካተተም። ለምን? እሮሞ ከ3,500 ዓመት በፊት ከአማራ ጋር የተፈጠረው እኮ ጎጃም ነው። ኦሮሞዎች ጎጃምን ተንከባክበዋል፤ አሳድገዋል። የሩቁን ዘመን ትተን የዛሬ 400 ዓመት በንጉሠ-ነገሥት ሱስንዮስ ዘመን የሆነውን እንኳ ብናነሳ በጎጃም እንቅስቃሴ ውስጥ ኦሮሞዎች በጣም ትልቅ ሚና ነበራቸው። ከጣና በስተደቡብ ያሉ ሌሎች ቦታዎችን ሳናነሳ የዛሬዎቹ ኢልማና እና ዴንሳ ዓበይት

የኦሮሞ ሰፈራ ቦታዎች ነበሩ። ቡሬ አጠገብ ወንበርማ፣ ደንግጂዳ፣ መተከል ዙሪያ እና እንዲሁም ወንበራ የሰፈራ ቦታዎቻቸው ነበሩ። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ራሱን የሚያሞኝ ካልሆነ በስተቀር በደም ሥሩ ውስጥ ትንሽ የኦሮሞ ደም የሌለበት እውነተኛ ጎጃሜ የለም። አንዳውም የኦሮሞ ደም የሌለበት ጎጃሜ ደበናንሳ ነው የሚባለው። ይህ የሚመሰክረው፥ የጎጃም አማሮች በኦሮምነታቸውም እንደሚኮሩ ነው። ጥንትም የአማራውም የኦሮሞውም አባት የዛው የጎጃም ንጉሥ የነበረው ፈላስፋውና ነቢዩ ደሸት ወይም ደሌት ነበርና። እንዲሁም ኦሮሞዎች በጎንደር ውስጥ ኖረው ከሱስንዮስ እና ከልጁ ከፋሲለደስ ጋር ጎንደርንም ገንብተዋል። ‹‹የጋላ አገር›› እየተባለ የሚጠራ የተለየ መኖሪያ ቦታም ነበራቸው። በዘመነ-መሳፍንት መግቢያ በኢዮኣስ ዘመን የጎንደር ቤተ-መንግሥት በኦሮሞዎች የተሞላ ነበር። በዘመነ-መሳፍንትማ ሁለቱም፣ ጎጃምም ጎንደርም የእነርሱ ነበሩ። ታዲያ በአዲሱ የኦሮምያ ካርታ ላይ ጎጃምንና ጎንደርን የማናክለው ለምንድነው?

የኦሮምያ ካርታ ትግራይን፣ አፋርን፣ ኦጋዴን-ሶማሌን እና ደቡብ ክልልን ጭምር የማያካትተውስ ለምንድነው? ትግራይ የራስ ቱሉ በዳሳ ልጆች ዶሪ በሚል ልዩ ስም የሚታወቁት ንጉሦች እና የየጁ ቤተሰብ የኦሮሞው የሴሩ ጓንጉል ቤተሰቦችና ነበረች እኮ። የኦሮሞ ልዑላን ለምሳሌ ሁለቱን ለማንሳት ያህል ራስ ዶሪ እና ባህርነጋሽ ይስሐቅ የትግራይ እና ኤርትራ ገዢዎች ነበሩ። ከሁሉም በላይ በአሁኑ ወቅትም የተወሰነው አካባቢ እዛው በቀል ነዋሪዎች በሆኑት በራያ መደባይ ኦሮሞዎች እንደተያዘ ነው። በደቡብና በኦጋዴን-ሶማሊ ክልሎች በርካታ ኦሮሞዎች እንደሚኖሩ ሁሉ በአፋር ምድርም ከረዩ የተባሉ ኦሮሞዎች ይኖራሉ። በርግጥ ኦሮሞና ሶማሊ የአፍሪቃ ቀንድን ሲጋሩ ዘመናት ተቆጥረዋል። አካባቢው ለሁለቱም በእኩልነት የጋራቸው ነው። ታዲያ በእነዚህ ክልሎች ውስጥ ኦሮሞዎች የሰፈሩባቸው አንዳንድ ቦታዎች በኦሮምያ ካርታ ውስጥ ለምን አልገቡም? ኦሮሞው በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ አካባቢ ውስጥ ድርሻ አለው። አማራውና ሌሎቹ ኢትዮጵያውያንም ቢሆኑ ድርሻ አላቸው። ኦሮሞ የኖረባቸውና ታሪካዊ ትስስሮሽ የፈጠረባቸው ክልሎች በኦሮምያ ካርታ ውስጥ መጠቃለል አለባቸው ብዬ አስባለሁ። ረጋ፣ ለከን ብዬ ሳስብ ደግሞ በነዚህ ክልሎች ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው





ብሔረሰቦች ለምሳሌ አማራ፣ ትግሬ፣ አፋር፣ ሶማሊ፣ የደቡብ ሕዝቦችና ሌሎች ኢትዮጵያውያንም ስለሚኖሩ ሁሉንም እጠቃሎ ‹‹ኦሮምያ›› ብሎ መጥራት ተገቢ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሐዊ እና ትክክል እንዳልሆነ እገነዘባለሁ። እንዲህ ዓይነቱ ጭፍን አስተያየት ኦሮሞ ላልሆኑት ኢትዮጵያውያን ትክክል አይደለም። ጠቅላላው የኢትዮጵያ ግዛት ‹‹ኦሮምያ›› ተብሎ ቢጠራ ኦሮሞ ያልሆኑት ብሔር ብሔረ-ሰቦች ከካርታው ላይ ይፋቁና ማንነታቸው አደጋ ላይ ይወድቃል። ቀድሞ-ነገር እንዲህ ያለውን የበላይነትና ከምድረ-ገጽ የማጥፋት ተግባር ፈጽሞ አይቀበሉትም። በአፍሪቃ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ቀውስና ብጥብጥ ነው የሚነሳው። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱን አደገኛ ሃሳብ አላቀነቅንም። እንግዲህ እንደዚያ ቢደረግ ኦሮሞ ያልሆኑት ግላዊና ልዩ የሆነውን ማንነታቸውን ማጣታቸው ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸው የመኩራት ስሜታቸውም ይሞታል። ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ ምንም ነገር ቢደረግላቸው ራሳቸውን ኢትዮጵያውያን ብለው አይጠሩም። ስለዚህ መፍትሔው ሁሉንም ክልል ‹‹ኢትዮጵያ›› ብሎ መጥራት ነው። ምክንያቱም ቃሉ ሁሉንም ያካትታል። ከዚህ በላይ ደግሞ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የትግሬ፣ የአፋር፣ የሶማሊ፣ ጋምቤላዎች፣ የሲዳማዎች፣ የወላይታዎች፣ የሃዲያዎች፣ የደቡብ ህዝቦች እና የሁሉም ኢትዮጵያውያን አባት የሆነውን የኢትዮጵን ስም ይዟል።

ቀደምት አባቶቻችን የተወሰነ ክልል ከልለው ‹‹ኦሮምያ›› ብለው ያልሰየሙበት ምክንያት መላዋ ኢትዮጵያ የነሱ ስለሆነችና እንድትሆንም ስለፈለጉ ነው። ይህ አንዱ ምክንያት ነው። ሌላው ምክንያት ከእኛ ተምረናል ከምንለው ኦሮሞዎች ይልቅ የጥንት እባቶቻችን መነሻ አባታቸው ኢትዮጵያ የተሰየመችበት ኢትዮጵ መሆኑን ይበልጥ ወደ ውስጥ ዘልቀውና ጠልቀው ስለሚያውቁ ነው። በዚህ ምክንያት የገዛ አባታቸው የመሰረታትን አገር ለማፍረስ አልደፈሩም። ስለዚህ የመስፋፋት፣ የመሻሻልና የመበልጸግ ትግላቸው ጥንተ-አባታቸው ኢትዮጵያ ብሎ በሰየማት አገር በመላ ነው እንጂ ቆርሰው እና አጥብበው ‹‹ኦሮምያ›› በሚሏት፤ ባንፃሩ ትንሽ መሬት ላይ ራሳቸውን ነጥለውና ገድበው አይደለም። ትንሽዋ መሬት፥ ቁጥሩ ከሁሉም ይበልጣል ለሚባለው የኦሮሞ ህዝብ አይበቃውም። ለንግድ፥ ለኢንዱትሪ መስፋፋት፥ ለኤኮኖሚ መዳበር፥ ለእርሻ፥ ለተለያዩ

ሥራዎች ሁሉ ይጠበዋል። የህዝቡ ቁጥር እያደገ ሲሄድም መጨናነቅ ይገጥመዋል።

በአዲሱ የኦሮምያ ፖለቲካ ካርታ መሰረት ጎጃምና ጎንደር ብቻ ናቸው ለአማራ የተወሰኑት። አማሮች በመላ አገሪቱ ስለሚኖሩ ሰፋ ያለ ምርጫ ቢሰጣቸው በነዚህ በሁለቱ አካባቢዎች ብቻ ራሳቸውን የሚገድቡ አይመስለኝም። መላዋ ኢትዮጵያ የኛ ናት ብለው ነው አማሮች የሚያስቡት። ምክንያቱም ባለፉት 3000 ዓመታት ውስጥ በውትድርና ሙያቸው መንግሥታትን ሲጠብቁ እና የአገሪቱን ዳር ድንበርና የግዛት አንድነት ሲያስከብሩ ጠንካራ የኢትዮጵያዊነትና ብሔራዊ ስሜት ገንብተዋል። ለኢትዮጵያ ሀገርነት መኖር ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን የፈፀሙት ታላቅ ጀብድ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፥ ስለእውነት ብለን እውነት ብንናገር፥ በኢትዮጵያ ነፃነት ላይ አማሮች የመሪነት ሚና ባይጫወቱ ኖሮ ቅኝ ገዢዋ ጣልያን ኢትዮጵያን በቀላሉ ድል አድርጋ ለመያዝ በቻለች ነበር። የዚህም ምስክሩ ጣልያን ናት። የአማራን ወሳኝ ሚና በመረዳትዋ ጣልያን ከሁሉም በፊት አማራንና ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን ነበር ለማጥፋት የተነሳችው። አማሮች ከተበታተኑ ኢትዮጵያም እንደምትበታተን ጣልያኖች በሚገባ ያውቁ ነበር። ኢትዮጵያን አዳክመው ለመቆጣጠር የሚሹ ከባህር ማዶ የመጡም ሆኑ የውስጥ ኃይሎች ሁሉ ይህንኑ አድርገዋል። የአማራ ጠላት የበዛውም ለዚሁ ነው። ይህ ማለት ግን የኦሮሞ አርበኞች እና ሌሎችም ነፃነት ወዳድ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ስመጠበቅ ያደረጉትን የጀግንነት ተጋድሎ ማሳነስ አይደለም።

‹‹አገሬ ጎንደር፣ ጎጃም ወይም ሸዋ ነው›› የሚል አማራ አጋጥሞኝ አያውቅም። እንዲህ ከማለት ይልቅ ‹‹ጎንደሬ ነኝ፣ ጎጃሜ ነኝ ወይም የሸዋ ኢትዮጵያዊ ነኝ›› ይላል። ብዙዎቻችን ስለዜግነታችን ስንጠየቅ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን እንደዚህ እንደምንል አምናለሁ። ሰፋ ባለ አነጋገር ሁሉም የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝቦች ማንነታቸውን የሚያያይዙት ከኢትዮጵያዊነት ጋር መሆኑ በ1896 እና በ1936 የተሞከሩትን የኢምፔሪያሊቶችንና የፋሺስቶችን ወረራዎች ለመቀልበስ ባሳዩት ጠንካራ አንድነት አረጋግጠዋል። በቅርቡ ትውስታችን ሟቹ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያውያን የብሄራዊ ስሜት የላቸውም እያለ ደጋግሞ ቢናገርም በባድመ የተነሳ ትግራይ በኤርትራ ስትወረር የኢትዮጵያ ሕዝቦች እጆቻቸውን አጣጥፈው ‹‹ጦርነቱ በትግራይና በኤርትራ





መካከል ነው፤ እኛ ምን አገባን!›› አላሉም። ይልቁንም የኢትዮጵያ ወጣቶች ጥሪ ሲደረግላቸው ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ሁሉም ከዳር እስከዳር ተነቃንቃው ትግራይን ለማዳን ዘመቱ። ምክንያቱም ጠንካራ የሆነ የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት አላቸዋ! በዚህም ያቶ መለስ ዜናዊን ዲስኩር ውድቅ አደረጉት።

የኦሮምያ ካርታ ትንሽ ውስብስብነት ይታይበታል፤ ለአብነት ከአዲስ አበባ ወደ ወሎ ስንጓዝ የአማራና የኦሮሞ ቦታዎች በጂኦግራፊያዊ አቀማመጣቸው ተቆላልፈው እናገኛቸዋለን። ከአዲስ አበባ ወጣ እንዳልን ሸኖን እናገኛለን የኦሮሞ መሬት ናት። እሷን አለፍ እንዳልን የአማራ መሬት የሆኑት ደብረ-ብርሃን እና ሸዋ ሮቢት ይገኛሉ። ከዚያ የኦሮሞ መኖሪያ የሆኑት ጂሌ እና ከሚሴ ከተማ ይለጥቁና ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩባቸው ከምቦልቻ እና ደሴ ከተሞች ይከተላሉ። ዘልቀን ከተጓዝን ደግሞ በአማራዎች ወደ ተያዘው የጁ እንደርሳለን። የጁን ስናልፍ የኦሮሞዎች መኖሪያ የሆነውን ራያ እና አዘቦ እናገኛለን። አዩ ምን ያህል የተጠላለፈ እንደሆነ? ይህ እንግዲህ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ያለ እውነታ ነው። በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሁኔታው ይመሳሰላል። እርግጥ ነው በነዚህ አካባቢዎች የሰፈሩ አማሮች እንደዚህ መጨናነቃቸውን የሚፈቅዱት እና ማንነታቸውን ሲያጡም ደስ የሚላቸው አይሆኑም። ከዚህ የምንማረው አንድ ትምህርት እነዚህ ሁለት ሕዝቦች፣ ኦሮሞና አማራ፣ አንድ መሬት እየተጋሩ እና አንድ ዓይነት ባሕል እየተወራረሱ የሚለያቸው የድንበር መስመር ሳያሰምሩ፣ ሆነ ብሎ እንዳይገናኙ የሚያደርጉዋቸውን የወሰን ምልክቶች ሳያስቀምጡ ለረጅም ዘመን አብረው ኖረዋል። ለእነዚህ ሕዝቦች ሁነኛው መፍትሔ ከማኅበራዊነታቸው ባሻገር ግለሰባዊ ማንነታቸውንም ማስጠበቅ ነው። ከማንነት ጥያቄም በላይ አጅግ አሳሳቢ የሆነው ችግር አካባቢውን እንዳለ ከተቀረው ኢትዮጵያ ገንጥሎ አዲስ አገር ለመፍጠር፣ እነዚህን ህዝቦች ለመነጣጠል እና ለመለያየት ከኦሮሞም፣ ከአማራም ሆነ ከተቀረው የኢትዮጵይ ህዝብ ሙሉ ፍላጎት ውጭ በአንድ የፖለቲካ ልሂቃን ድርጅት እየተቀነቀነ ያለው እቅድ ነው። እንዲህ ዓይነቱ እቅድ ወደ ግጭት እና ወደ ኢኮኖሚ ድቀት ይመራል እንጂ ለሁሉም ወገኖች ዘላቂ ሰላም እና ብልጽግና አያመጣም።




የኦሮምያ የፖለቲካ ካርታ

ልሂቃን የጎሳቸውን ክልል ለመገንጠልና ለመግዛት ሲቋምጡ ሕዝበ-ውሳኔን እንደ ሽፋን ይጠቀማሉ። የመገንጠል አጀንዳቸውን ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ የሚያስመስሉበት ሥልታቸው ህዝበ-ውሳኔ ነው። በውጤቱም ለፊው ሕዝብ ጠብ የሚልለት አንዳች ነገር የለም። ህዝበ-ውሳኔ ተብየው ነገር በጠረጴዛ ላይ መቀመጥ የለበትም። ምክንያቱም ለመገንጠል ያቆበቆቡ ልሂቃን በዘዴ በጃቸው ያስገቡትና በህዝቡ ስም ሥልጣን ላይ ፊጥ ይሉበታል። ለፊው ህዝብ ሁል ጊዜ የታቀደለትን እንዳደረገ እና የልሂቃን መጠቀሚያ እንደሆነ ነው። ፕሬዝዳንት እና ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን ምኞት የተቃጠሉ እንዲህ ዓይነት ልሂቃን ‹‹ነፃነት ወይስ ባርነት›› የሚሉ ኣማራጮችኝን ብቻ ያስቀምጡና ህዝቡ መገንጠልን እንዲመርጥላቸው በዘዴ





ያስገድዱታል። በኤርትራ ጉዳይ ላይ እንደተደረገው ማለት ነው። ‹‹ባርነት ወይስ ነፃነት›› የሚል ምርጫ ሲሰጥ ‹‹ባርነት›› ብሎ ማን ይመርጣል? ሕዝበ-ውሳኔ ማካሄድ የግድ አስፈላጊ ክሆነ ባለ ድርሻ አካላትን በሙሉ መጋበዝ፣ የሚመለከታቸውን የነገድ እና የጎሣ አባላት በሙሉ ማቀፍ፣ የአናሳ ሕዝቦችንም መብት በመጠበቅ በክልሉ የተወለዱትን እና ቢያንስ ለ10 ዓመት የኖሩትን ሁሉ ማስገባትና ባጠቃላይም የኢትዮጵያን ህዝብ ሁሉ ማሳተፍ ያስፈልጋል። ምክንያቱም መገንጠሉ የሚነካው ተገንጣዩን ቅርንጫፍ ብቻ ሳይሆን የሚገነጠልበትንም ግንድ ጭምር ነው። ልሂቃኑ ህቀኞች ክሆኑ ‹‹የብሔር ብሔረ-ሰቦች ነፃነት እስከ መገንጠል መብት!›› የሚለውን ጊዜ ያለፈበትን ማርክሲስት-ሌኒኒስት-እስታሊኒስት መርህ ትተው *‹‹የብሔር ብሔረ-ሰቦች መብት ለውስጥ አስተዳደር ነፃነት ራስ ገዝነትን ጨምሮ›* ማለት ይኖርባቸዋል።

ሕዝበ-ውሳኔ ተካሄደም አልተካሄደ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚነሳ የብሔር ጥያቄ (የጎሳ ጥያቄ ነው፥ ትክክለኛው አባባል!) የሚበጀው መፍትሔ የዜግነት መብቶችን፣ ሰብዓዊ መብቶችን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን እና ሌሎችንም የሃይማኖት፣ የኤኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የጽሁፍ፣ የሚዲያ ወ.ዘ.ተ. ነፃነቶችን በማስጠበቅ የሁሉንም ኢትዮጵያውያን መብቶች በሕግ የምታረጋግጥ አንዲት ኢትዮጵያዊት አገር መገንባት፥ ሕገ-መንግሥታዊት ሪፑብሊክ አገር መፍጠር ነው።

ሪፐብሊክ የብዙሃኑንም የግለሰቡንም፣ የሁለቱንም መብቶችና ፍላጎቶች በሕግ የሚያስከብር ሥርዓተ-መንግሥት ነው። አሁን ባገራችን ያለው ሁኔታ ሲታይ የብዙሃኑ መብት እየተጠበቀ አይደለም። ብዙሃኑም ቢሆን በክልሉ ያሉትን አናሳዎች ይጨቁናሉ። በቅርቡ የተፈፀመ አንድ እውነታ ብናነሳ በቤንች ማጂ እና በቤንሻንጉል-ጉሙዝ በአማሮች ላይ የተፈፀመው በደል የሚጠቀስ ነው። እነዚህ አማሮች በማይረባ ሰበብ ቤት ንብረታቸውን አጥተው፣ መሬታቸውን ተነጥቀው፣ ገንዘባቸውን ተቀምተው፣ ሰብአዊ ክብራቸውን ተገፈው ሜዳ ላይ ተጥለዋል፡ጅብ የበላቸውም እንደ አሉ ተነግሮአል። ኢትዮጵያውያን እንዳልሆኑ ሁሉ በገዛ አገራቸው ይህ ሁሉ ግፍ ተፈፅሞባቸዋል። ኢትዮጵያውያን ባይሆኑም እንኳ የሰው ልጆች ስለሆኑ እንደዚያ መደረግ የለባቸውም።




የኦሮሚያ የፖለቲካ ካርታ

ስለ ዲሞክራሲያዊና በተቃራኒው ስላለው ስለ ሪፐብሊካዊ የመንግሥት ቅርፆች ጥቂት ለማለት ያክል ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ጥሩነቱ ለምርጫ ሂደትና ለድምጽ ቆጠራ ብቻ ነው። ያም ቢሆን በአፍሪቃ ውስጥ ማታለያና ማጭበርበሪያ ሥርዓተ-ሂደት ሆኗል። ሪፐብሊክ ግን በህዝብ የሚመረጡና ለመረጣቸው ሕዝብ ተጠያቂዎች የሚሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን የሚይዝ ሥርዓት ነው። በሥልጣን የሚባልጉ ባለሥልጣናትን ከሥልጣናቸው ለማውረድ፣ የሕግ ጥሰትንና የሰብአዊ መብት ረገጣን እንዲሁም የኢኮኖሚ መድልዎንና ጭቆናን ለማጋለጥ እና ለማስቆም ሕዝቡና ሚዲያው መብት አላቸው። ዲሞክራሲያዊ ቅርፀ-መንግሥት ግን በብዙሃን አገዛዝ ስም የግለሰቦችን የዜግነት መብቶች ለሚረግጡና ሥልጣንና ሀብት ለሚያከማቹ አምባገነኖች እና ለአምባገነንነት በር ይከፍታል። በህግ የተደነገገ እና ለህግ ተገዢ የሆነው ሪፐብሊክ ግን የየግለሰብን መብት በህግ ስለሚያስጠብቅ የሁሉንም ዜጋ መብት ያስከብራል ማለት ነው። ከሪፐብሊክ በተቃራኒ ያለው ይህ የዲሞክራሲ ጽንሰ-ሃሳብ ወደ ፊት በጥልቀት መጠናት ያለበት ነው።

ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የታሪክ ጊዜያት በተለይዩ ቦታዎች ላይ መስፈራቸውን በተመለከተ ሸዋ እና ወሎ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። የዛሬን ጀማ ወይም ዠማ ወንዝ እና አካባቢውን እንደ ምሳሌ አድርገን ፤ ግራርጌ፣ ሲኮ፣ ካቢ እና ገነቲን ጨምረን እንይ። በእነዚህ አካባቢዎች ከ3000 አመት በፊት አማራና ጀማ ሰፍረውባቸው ነበር። አማራ እና ጀማ - የኦሮሞውች አባት የደሸት የልጅ ልጆች ናቸው።- ወንድማማቾች ናቸው። ዛሬ ሸዋ የሚባለው ከ3000 ዓመት በፊት አማሮች ሲኖሩበት ግራርጌ ነበር የሚባለው። ከዚያ በኂላ በቅደም ተከተል ኡይዝ ፣ገበታን፣ቤጋን፣ እየተባለ ተጠራና በቀዳማዊ ሚኒልክ ጊዜ ሸዋ ተባለ። ኡይዝ ተብሎ ሲጠራ መደባይ/ኦሮሞ/ ይኖሩበት ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት እስከ ንግሥት ሳባ ልጅ እስከ ቀዳማዊ ምኒሊክ ጊዜ ድረስ ኦቺ ይባል ነበር። ቀዳማዊ ምኒልክ “ሸዋ” በሚል ስም ቀየረው ። በሱባ ቋንቋ “ሸዋ” ማለት “የጦርሰራዊት›› ማለት ነው። የምኒልክ ልጅ ቶማይ ጦሩን /ሸዋ የሚባለውን/ በአማራ መሬት ላይ አሰፈረና አገሩም “ሸዋ” ተብሎ ይጠራ ጀመር። ይኩኖ አምላክ ከኦሮሞ ከአማራ እና ከሌሎችም ነገዶች በተውጣጣ ፈቃደኛ ሰራዊት ድጋፍ የሰለሞናዊውን ሥርወ-





መንግሥት እንደገና ሲመልስ እና ሲነግሥ ያንን የረዳውን ፈቃደኛ ጦር ቋሚ ጦሩ አደረገውና በሸዋ ውስጥ አሰፈረው። ከዚህ ጦር ውስጥ አብዛኛው አማራ ነበር። አህመድ ግራኝ ሸዋን ሲይዝ የኦሮሞ ጦሩን በአማራ መሬት ላይ አሰፈረ። በዚህም ግራርጌ ይባል የነበረው ሰሌ ወይም ሰላሌ ተባለ። ምክንያቱም ሰላሌ ተብሎ የሚጠራ የግራኝ ጦር እዚያ ስለሰፈረ ነው። አሁን ወሎ የሚባለው የአማራ አገር ጥንት “ሰኮ” ነበር የሚባለው። በ16ኛው ክፍለ-ዘመን አህመድ ግራኝ ከአጼ ልብነ-ድንግል እና ከተከታዮቻቸው ጋር በሚዋጋበት ወቅት የተወሰኑ ኦሮሞዎች እዚያ ሰፈሩ እና በአባታቸው ስም “ወሎ” ብለው አካባቢውን ጠሩት። ሁለቱም አማራም ኦሮሞም ያንድ ሰው፣ ማለትም የኢትዮጵ ዝርያ የሆነው የደሸት ልጆችና ልጅ ልጆች ስለሆኑ፥ እንዲሁም ሁለቱም ዘመዳሞች በዛ ቦታ ላይ ሲኖሩ እነዚህ ቦታዎች አሁን ለማን ይሰጡ? ወደ ማንኛቸውስ ይከለሉ? ሁለቱም (ኦሮሞም አማራም) የኔ ነው ስለሚሉ እውነታቸውን ነው፥ የሁለቱም ነው። የሁለቱም ንብረት ከሆነ ደግሞ በሰላም አብሮ ለመኖር እና ለጋራ ፍቅር ሲባል ያለ ራስ ወዳድነት ስሜት ሁለቱም ቢካፈሉት ለዘላቂ ሰላም እና ብልፅግና ይበጃል። ለሸዋ ኦሮሞዎችና አማሮች ደግሞ ይህን ማንም አይነግራቸውም። እነሱ ተቻችለውና ተዛምደው አብረው ለ 3000 ሺህ ዐመታት በሸዋ ኖረዋል። የተለያዩ ኢትጵያውያንም በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የኢትዮጵያ መሬቶች እየሰፈሩ ኖረዋል። 100 ዓመት ወደኂላ ሄዶ የመሬት ይገባኛል ጥያቄ ማንሳት ፍሬ-ቢስ ነው። አንዱ ጎሳ ሌላውን ሳይጫንና ያንበሳ ድርሻ ይገባኛል ሳይል የኢትዮጵያን ምድር ሁሉም የኢትዮጵ ልጆች በፍትሃዊነት እና በእኩልነት ሲኖሩባት ይገባል። ባሁኑ ዘመን ስግብግብነት እና ራስ ወዳድነት ዋጋ ያስከፍላሉ። በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ፍትሃዊ መቂዋደስ ነው ለሁሉም ሰላምን እና ብልጽግናን ሲያሰፍን የሚችለው። ልጆችዋ ከስሜታዊነት ይልቅ ምክንያታዊ ቢሆኑ፣ እርስ በርሳቸው ቢፋቀሩ እና ቢተሳሰቡ ኢትዮጵያ ከሰው በሃጢያት መውደቅ በፊት፥ ማለትም አዳም በገነት ከመሳሳቱ በፊት እንደነበረችው ምድረ-ገነት ትሆናለች። አዳዲስ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ገነትም የነበረችው ኢትዮጵያ ውስጥ ነበርና።

# ማጠቃለያ እና መደምደሚያ

ከላይ ከቀረቡት ሦስት አበይት ርዕሶች ኢትዮጵ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ጥንተ-አባት መሆኑን ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ብዙ እንዳበረከቱ፣ ኦሮሞ እና አማራ ካንድ አያትና አባት የተገኙ ወንድማማቾች፣ ባንድ አገር በኢትዮጵያ፣ ባንድ አካባቢ በጎጃም የበቀሉ አንድ ዘር መሆናቸውን ተምረናል። ዋና ከተማው አክሱም የነበረውን የሰሰሞንን ሥርወ- መንግሥት ስንመረምር ከምታፈቅረው ባልዋ ተወስዳ ለንጉሠ-ነገሥት ጃንሰገድ የተዳረችውን ማርብላ የተባለችውን አማራ ሴት አግኝተናል። ልጅዋ አአልሜዳ ንጉሠ-ነገሥት ሰይፈ-አርዕድ ተብሏል። ሌላዋ አሃዬ የተባለች ከፊል አማራ የሆነች ሴት አልአሜዳን እግቢታ ንግሥት አብርሂት እንደተባለችና አብርሃ እና አጽብሃ የተባሉ መንትያ ልጆችን እንደወለደች አይተናል። የተጠቀሱት ሁለቱም ሴቶች ልጆቻቸው ህጻናት በነበሩበት ወቅት ሰሰሞናዊውን ዙፋን መጠበቃቸውንና ንግሥት አሃዬ ከመንታዎቹ ልጆቿ ጋር ሆና ክርስትናን ማስፋፋቷን ተመልክተናል። እጼ ናግሺሬ፡ አዶር ወልዱ የተባለ ወንድም የነበራትን ሶሪያዊት ሴት እንዳገቡ እና በትልቁ አሌክሳንደር ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱት ሶርያውያን እና ባቢሎናውያን እግአዚዎቹን ድል አድርገው ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሥልጣን ለወገኖቻቸው እንዳስገኙም ዳስሰናል። በዚህ ወቅት የኦሮሞ ዝርያ የሆኑ ንጉሦች እና ንግሥቶች ባያጋጥሙንም ዋና ከተማቸውን ሸዋ ውስጥ ተጉለት ያደረጉ በርካታ የኦሮሞ ዝርያዎች የሆኑ ንጉሠ-ነገሥቶችን እና ንግሥተ-ነገሥታትን በሰሰሞናዊው ዙፋን ላይ ተቀምጠው አግኝተናል። ተጉለት መናገሻ የሆነችው ኦሮሞ ከሆነችው ክሃዊ ጊፍቲ መንዲያ በሚወለዱት በአጼ ይኩኖ አምላክ ነው። ዋና ከተማቸውን ተጉለት፣ ሸዋ እና ላስታ አድርገው በሰሰሞናዊው እና በዛጉዬው ሥርወ-መንግሥታት ዙፋኖች ላይ ከተቀመጡት ውስጥ አንድም አማራ የሆነ ንጉሠ-ነገሥት ወይም አማራ የሆነች ንግሥተ-ነገሥታት አላገኘንም። አማሮች እና አማርኛ ግን በሁለቱም ሥርወ





መንግሥታት የተፈቀዱ ነበሩ። ምክንያቱም ይኩኖ እምላክንም ላሊበላንም ሥልጣን እንዲይዙ አማሮች ስለረዱዋቸው። ይሁን እንጂ በአማራው ስም በኢትዮጵያ ምድር ንጉሠ-ነገሥት ሆኖ የገዛ አንድም ሰው አላገኘንም። ይልቁንስ አጼ ሱስንዮስ እና አጼ ኢዮአስ እንዲሁም ኦሮሞዋ የአጼ ኢዮእስ እናት ንግሥት ወሰተቤርሳቤህ በ15ኛውና በ18ኛው ክፍለ-ዘመናት የኦሮሞ መሳፍንትና መኳንንትን በአማራው ላይ ነፍጠኞች አድርገው በጎንደር እና በጎጃም ይሾሙ እንደነበር አይተናል። በዘመነ-መሳፍንት ወቅት ጎንደር ከትመው የነበሩ የየጁ የኦሮሞ መሳፍንት በሰሰሞናዊው ዙፋን ላይ አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥት ለስሙ እያስቀመጡና እነሱ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ እየሆኑ እውነተኛውን ሥልጣን በመጨበጥ ሰሜንና ምእራብ ኢትዮጵያን ለ70 አመታት እንደገዙ ተገንዝበናል። ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ሀቅ የኦሮሞ ዝርያዎች ከአማራም ሆነ ከሌሎች ጎሣዎች በላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ሆነው ላለፉት 700 ዓመታት ኢትዮጵያን ሊገዙ፣ ሊመሩ እና ሊያስተዳድሩ የኖሩ መሆናቸውን ነው። አንዳንድ የኦሮሞ ልሂቃን ግን ይህን ታሪካዊ ሀቅ በወጉ የተገነዘቡት ስለማይመስል ግንዛቤያቸውን ማደስ እና ከእውነታው ጋር ማጣጣም ይጠበቅባቸዋል።

በጎሳና በነገድ፥ በዘርና በቋንቋ፥ በብሄርና በጎሳ፥ በሃገርና በዜጋ መሃል የአሉትን ልዩነቶች ሁሉ ተመልክተናል።

በዚህ ጽሁፍ ይዘት ውስጥ የተሰያዩ ነገሥታት እና ኢማም አህመድ ግራኝ አማራና ኦሮሞ ወታደሮቻቸውን ዛሬ ሸዋ እና ወሎ ብለን በምንጠራቸው ቦታዎች በማስፈራቸው በሸዋ ውስጥ “ግራርጌ” በማዕከላዊ የአማራ ክልል ደግሞ “ሊኮ” ተብለው ባማርኛ ይጠሩ የነበሩ ቦታዎች በስተኋላ በመጡ ኦሮሞ ሰፋሪዎች ስያሜአቸው “ሰላሌ” እና “ወሎ” ወደሚሉት መለወጡን ተገንዝበናል። እንዲሁም የሰሰሞናዊው እና የዛጉዬ ስርወ-መንግሥታት አጼዎች ዙፋኑን እና ፍጹማዊውን ሥልጣን ለራሳቸው ብቻ አድርገው በየክልሎቹ የሚሾሟቸው እና ሉኣላዊ ገዢነታቸውን ተቀብለው የሚገብሩላቸው ንጉሦች ግዛቶቻቸውን በነፃነት እንዲያስተዳድሩ መብት የሚሰጥ ፌዴራላዊ ዓይነት ሥርዓት እንደነበራቸው ተረድተናል። ከነዚህ እውነታዎች ጋር የሁለቱም ሥርወ-መንግሥታት ንጉሠ/ንግሥተ/-ነገሥታት የሚወክሉት፣ የሚጠብቁትና የሚንከባከቡት ራሳቸውን እና ቤተ-

ሰቦቻቸውን ብቻ እንጂ የኦሮሞን እና የአማራን ሰፊ ሕዝብ ፍላጎት እንዳልነበረ እውቀናል።

እንዲሁም በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ዙፋን ላይ እየተቀመጡ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ኢትዮጵያን የመሩ እና ያስተዳደሩ ኦሮሞዎች ነበሩ እንጂ አማሮች እንዳልነበሩ ተገንዝበናል። ከዚህ በተጨማሪ ኦሮሞና አማራ በጣም የተቀራረበ ባሕላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሥነ-ልሳናዊ እና ሥነ-ሕይወታዊ ትስስሮሽ እንዳላቸው ተምረናል። ይህ ጥናት በኦሮሞና በአማራ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ቢያተኩርም የተቀሩት ኢትዮጵያውያንም ኢትዮጵያን የመሰረታትና መጠሪያዋንም የሰጣት የኢትዮጵ ልጆች መሆናቸውንና ላለፉት 4,000 ዓመታት በጋብቻ፣ በማህበራዊና መንፈሳዊ ሕይወት፣ በባህላዊ መስተጋብር እና በመሳሰሉት እንደቅደም ተከተሉ ከኦሮሞና ከአማራ ጋር እየተሳሰሩ መዛመዳቸውን የኢትዮጵያን ታሪክ ስንቃኝ አይተናል።

የላቲኑን ወይም የኢትዮጵያውያን ፊደል ስለመጠቀም ጉዳይ አንስተን በላቲን ፊደል ለንባብ አስቸጋሪ እና ሳፃፃፍ የተንዛዛ የሆነው በኢትዮጵያው ፊደል ግን ሳነባበብ ቀና እንደአጠራሩ የሚጻፍ፣ እንደተጻፈው የሚነበብ፣ እና ሳፃፃፍ ቀልጣፋ (ፊደል፣ገንዘብና ጊዜ ቆጣቢ) እንደሆነና የኢትዮጵያ ፊደላት ለሚውሉበት ኣላማ እጅግ ተስማሚዎች መሆናቸውን በዚህም ኦሮሞዎች እና ሌሎችም ኢትዮጵውያን ከላቲኑ ፊደል ይልቅ በኢትዮጵያ ፊደል ቢጽፉ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተረድተናል።

ስለ ኢትያኤል ታዋቂ በሆነችበት መጠሪያዋ ‹‹ንግሥተ-ሳባ›› ስለምትባለዋ ማንነት እና በርግጠኝነት መኖር አንብበናል። በንባባችንም ኢትያኤል(ንግሥት ሳባ) የኢትዮጵ ዝርያ እንደሆነች፣ አያትዋ አጋቦና በአጼ አሰያኤል የተመሰረተችው የሳባ ከተማ ንጉሥ እንደነበረ፣ ሳባ የተሰኘው የኢትያኤል መጠሪያም ከዚች ከተማ የመጣ መሆኑን ጨብጠናል። ከኤትያኤል ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያዊ ምንጭ ያላት ቢልቂስ በኢትያኤል ፈቃድ የአረቢያ ንግሥት ሆና በአግአዚዎች እገዛ እንደ ነገሰች አንብበናል።

ኢትዮጵያ ረጅምና ዝነኛ ታሪክ ያላት አስገራሚ አገር ናት። ህዝቧም ቅይይጥ መልክ ያለው የተለየ ሕዝብ ነው። የኢትዮጵያውያን መልክ





የተለያዩ ቀለማት እንዳሉት ውብ አበባ የሚወደድና የማይጠገብ ነው። የተለያዩ ቋንቋዎቿ ባህሏ፣ ሙዚቃዋ፣ ዳንኪራዎችዋ ፣ የምግብ አሰራሯ፣ አልባሳቷ፣ የፀጉር አሠራር ዘዴዎቿ እንዲሁም የንድፍ ጥበብዋ እና እደ-ጥበብዋ ይህ ሁሉ በያንዳንዱ ነገድዋ ውስጥ ሲታይ ኢትዮጵያን ከልክ በላይ በፀጋ የታደለች አገር ያደርጋታል። ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ብዙ ቋንቋዎች እና በርካታ ባህሎች ላላቸው ማኅበረሰቦች ጥሩ ሞዴል የምትሆን አገር ናት። በርካታ ነገዶች ያሏት አገር መሆኗ አያያዙን ካወቀችበት በሰውር ያለ ጸጋ ነው። መሪዎቿ ብልሆች፣ አርቆ አሳቢዎች እና ራዕይ ያላቸው ከሆኑ ነገደ-ብዙነቷን ለመከፋፈልና ለውድቀት ሳይሆን ለአንድነት፣ ለጥንካሬ እና ለብልጽግና መሰረት አድርገው ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ዳሞ፣ ሐዲያ፣ ጎጃም፣ ኮንሺ፣ ሴኑካ፣ ጪላሎ፣ መጋል እና ጋውል የተባሉ ሰምንት ንጉሦች መደባይ፣ መንዲ እና ጂማ ከተባሉ ወንድማማቾች ከሆኑ የደሼት/ደሴት/ ልጆች እንደተወለዱ እና በየዘርፋቸው የኢትዮጵያን ነገዶች እንዳስገኙ፤ ሁሉም ደግሞ የኢትዮጵ ዝርያዎች እንደሆኑ እውቀናል። እነዚህ ንጉሶችና ነገዶች የኖሩት ከ3,200 ዓመት በፊት ነው። ከእነዚህ ነገዶች አብዛኞቹ እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ መኖራቸውና ሁላችንም የኢትዮጵና የደሼት ዝርያዎች ለመሆናችን ህያው ማስረጃዎች መሆናቸው የሚያስደንቅ ነው። እነሱም መደባይ፣ ማጂ፣ ጋፋት፣ ጂሬ፣ ዋጂራት፣ ቦነጋ፣ ጎጃም፣ መንዲ፣ ወንጌ፣ ቦረና፣ ቱሰማ፣ አባታሊት፣በርቱማ፣ ጋሊ፣ ጂሎ፣ ኢሳ፣ ሃሼን፣ ሲዳማ፣ ማያ፣ ሆሮ-ወላቦ፣ ቦረን፣ ኢቱ እና ወረማያ ናቸው። ለ3200 ዓመታት ያለማቋረጥ ሲፈሱ የኖሩት ወንዞቻቸውም አሁንም ይፈሳሉ። ግዮን፣ ዋቢ፣ ነገሌ፣ ገናሌ፣ አዋሽ፣ ጊቤ፣ እና ጁባ ናቸው። እነዚህ ለ3200 ዓመታት በኢትዮጵያ ምድር ላይ የኖሩ ኢትዮጵያውያን ነገዶች ተራብተውና ቅርንጫፎቻቸውን አራብተው ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ የምንኖር መላ ኢትዮጵያውያንን አስገኝተዋል። በዛን ጊዜ ከ350 ዓመት በኋላ የዛሬ 2850 ዓመት ከነገሰው ከንጉሠ-ነገሥት አከሱማይት ዘመን ጀምሮ እንኳ የነበሩ ነገዶች በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ እንዳየነው ዝርዝራቸው ብዙ ስለሆነ እንደገና እዚህ ለመድገም አልሻም።

እድሜ ለቴክኖሎጂ! ሰፊዋ ዓለም ዛሬ ጠባብ መንደር ሆናለች። የመለያየት፣ የመበጣበጥ እና የመጠላላት መንፈስ ጊዜው አልፎበታል።

ለኢትዮጵያ ችግር ሁነኛው መፍትሄ የህግ የበላይነትን በሚያሰፍን ሪፐብሊካዊ ሥርዓተ-መንግሥት ስር በእውነተኛ እኩልነት ላይ የሚመሰረት አንድነት ነው። መበታተንና መገነጣጠል ለማንኛውም ወገን ምንም አልፈየደም። እንደኛ የተለያዩ ነገዶች፣ ሃይማኖቶች፣ ቋንቋዎች እና ባሕሎች ያሏት አገር ማድረግ ያለባት ሁሉንም በእኩልነት ማየት፣ ለሁሉም እኩል ድጋፍ ማድረግ፣ ሁሉንም እኩል ማወደስ፣ እኩል ማሳደግ እና እኩል ማክበር ነው። ኢትዮጵያም ይህንኑ ነው ማድረግ ያለባት። ርግጥ ነው የጋራ አገራችንን እየገነባን የየግል ኑሯችንን ስንኖር ለሁላችንም የመተሳሰሪያ እና አርስበርሳችን የምንግባባበት፣ መንግሥትም ሥራውን የሚያካሂድበት አንድ ብሔራዊ የሥራ ቋንቋ ያስፈልገናል። አዲስ የጋራ ቋንቋ በመፍጠር ሀ ብለን ከምንጀምር ላለፉት አንድ ሺ. ዓመታት ብሔራዊ መግባቢያ ሆኖ ሲሰራበት የቆየው አማርኛ ስላለን በእሱ መጠቀማችንን ብንቀጥል ብልህነት ነው። ኦሮምኛ ደግሞ ሁለተኛው ብሔራዊ መግባቢያችን መሆን ይችላል። አማርኛ ቁዋንቁዋ መቀጠል ያሰበት፥ በቃላት የበለጸገ፣ ሰፊና ጥልቅ ሃሳቦችን በጥቂት ቃላት የሚያስተላልፍ፣በዐለም ላይ ወደር የሌለ ቅኔ የሚገለፅበት፥ ተረትና ምሳሌዎች፣ሥነ-ቃሎች፣ አባባሎችና ፈሊጣዊ አነጋገሮች የታጨቁበት ከመሆኑም በላይ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚረዳው ቋንቋ ስለሆነ ነው። እስካሁን እንደ አማርኛ ያለውን መንግሥታዊ ቋንቋ ማወቅ በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት አውቀው የተገለገሉበት ነገዶች በጣም ጥቂት የሆኑ "ጮሌዎች" ብቻ ናቸው። እነዚህ ጮሌዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ ልሳነ-ብሄራት የሆነውን አማርኛንም አጥርተው ያውቃሉ። በዚህም ከሌሎቹ በትምህርት መሰጫነቱ እና በጋራ መግባቢያነቱ ከማይጠቀሙበት ዜጎች ይበልጥ የተሻለ የትምህርት፣ የሥራ እና የኤኮኖሚ ዕድል ሊያገኙበት ኖረዋል፤ በማግኘትም ላይ ናቸው። አማርኛን መማር ይጠሉ የነበሩ ዜጎች አማርኛን ከአማራ ጋር ያምታቱ የነበሩ ናቸው። ብዙ ዕድል አምልጧቸዋል። አማርኛን በማውገዝ ይታይ የነበረው ፍንደቃ እና የራስን ቋንቋ ብቻ የማራመድ አባዜ አሁን ጋብ ያለ ይመስላል። ጥቂት መምህራን በየ ክልላቸው በሚነገሩ ቋንቋዎች ሥርዓተ-ትምህርት ነድፈው የህጻናት ትምህርት ቤቶችን ከፍተው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። በርካታ ወላጆች ግን አማርኛ በሥርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ ካልተካተተ በሚል ልጆቻቸውን ወደነዚህ ትምህርት ቤቶች ለመላክ ፈቃደኞች አልሆኑም።





ምክንያቱም፥ መንግሥት በድፍን ኢትዮጵያ በይፋ የሚጠቀምበትን አማርኛን ረግጦ ጥሎ በራስ ቁዋንቁዋ ብቻ መናገርና መማር ወንዝ የማያሻግር በመሆኑ ልጆቻቸው እንዳይጎዱባቸው በመቆርቆር ነው።

ፖለቲካንና ጥላቻን ገሸሽ አድርገን አባታችን ኢትዮጵ ባሻሻላው ኢትዮጵያዊ ፊደሎች ለመጻፍ መልካም ፈቃድ ሊኖረን ይገባል። ምክንያቱም ለሰፊው ሕዝባችን እንግዳ በሆነው በላቲን ፊደል ከምንጽፍ ይልቅ በኢትጵያዊ ፊደል ብንጽፍ በርካታ ጥቅሞች እናገኛለን። አማርኛ ቋንቋ እና የግዕዝ ፊደሎች ኦሮሞን ወይም ሌላ ማንኛውንም ሰው አልገደሉም፣አልገረፉም፣ አላሰቃዩም። ይልቅስ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር እየተግባቡ አውቀት፣ ሃሳብ፣ ፍቅር፣ መረጃ እንዲለዋወጡ በማስቻል የተሻለ ሻይወት እንዲኖሩ ይረዷቸው ነበር እንጂ። ከአፍ መፍቻ ቋንቋ በተጨማሪ በሰፋት የሚነገር አንድ ‹‹ብሔራዊ›› ቋንቋ ማወቅ ለግል ህይወት እና ለሀገር እድገት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

እናም ሀገራችንን ስንገነባ የሁሉንም ኢትዮጵያውያንን እውቀት፣ ክህሎት እና ልምድ እንጠቀማለን። በግንባታ ጥረታችን ሁሉ በፍጥነት ለማደግ ገንቢዎቹ ብሔራቸው ምንም ይሁን ምን ችሎታው ያላቸው ነው መሆን ያለባቸው። ዘር ለሥራ ቅጥር እና ለሹመት መስፈርት መሆን የለበትም። አውቀት፣ ክህሎት፣ አቅም፣ የሙያ ብቃት እና የሥራ ፍቅር ናቸው ለቅጥር እና ለሹመት መስፈርት መሆን ያለባቸው። ዘር ብቻውን ቤት፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ ግድብ አይሠራም ወይም የታመመ አያከምም። እነዚህን ተግባራት ማከናወን የሚችሉ የተማሩ ኢንጅነሮች እና የሰለጠኑ ሀኪሞች ናቸው። የስነዘርኪቻው ሀሳቦች በሥራ ላይ ቢውሉ አገራችን ባጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ትጠቀማለች። ያለፈውን ቅራታ መቆፈር የዛሬውን ችግር አይፈታም። ያለፈውን ስንቆፍር ብንውል አመድ ብቻ ነው የምናፍሰው። አመድ ደግሞ ለማንም ምንም አይፈይድም። ነገን የተሻለ ለማድረግ በዛሬው እውነታ ላይ በቀና ልቦና፣ ባስተዋይ ኅሊና፣ በጥሩ መንፈስ እና በጋለ ፍላጎት ማቀድ አለብን። የወቅቱ እውነታ ለሰላም፣ ለእርቅ፣ ለፍቅር እና ለጋራ መግባባት ይጣራል። የጋራ ተጠቃሚዎች እንድንሆን ይህንን ጥሪ እንቀበል። በመደምደሚያዬ ላይ አጽንኦት ለጥቸ ማስተላለፍ የምፈልገው ይሕን ህቅ ነው።

## Notes:

The Extent of Amara Participation in the Dynasties of Ethiopia

1.Wikipedia, 2015.

2. ibid., 2015.

3*መፅሐፈ ሱባኤ ዘበአማን ካልዑአዲስ አበባ፥በራስ ህትመት፥ ገፅ*.59

. Aman Belai, Metsihafe Subael Kale, p.59.

4. Aman Belai. ibid., p.140.

5. Aman Belai. Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik. p.208.

6.Aemro Nigusse, Tintawi Ye Ethiopia Ye Selam Tibeka Tarik, p.6.

7.Aman Belai, *Metsehafe Subae*, pp. 49-51.

8.Aman Belai.ibid., p.167.

9. Amabn Belai. ibid. pp., 169-173.

10. Aman Belai. ibid., p.181.

11. Aman Belai. *Metsahife Abrihit*. p.144.

12. Aman Belai. Ye Tintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik. p.116.

13. Aman Belai. *Metsihafe Abrhit*. pp. 118—119.





14 Aman Belai. Yetintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik. p.116.

15 Aman Belai. Hezbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tari, p.30.

16. Tsehafe Tizaz Gebre-selassie. *Tarike Zemen Degmawi Minilik*. p.22.

17. Aman Belai.*Metsihafe Abrihit*, p.143.

18. Aman Belai. loc.cit.

19. Belai, Aman, Yetintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik. p. 200

20. Aman Belai ibid., p.185

21. Bairu Tafla, *Atsme-giogis and His Works*, p. 280.

22. Bairu Tafla. ibid., p. 284.

23. Belai, Aman, ibid., p. 209.

24. F. Josephus, *Jewish Antiquities*, ed. J. Thaceray and R. Marcus, Loeb Classical

Library, London, 1961, Vol. VIII, pp. 165-175.

25. *The Holy Bible*, I Kings X: 1-10.

26. Aman Belai, Metsihafe Subae Zebea`man Kale, pp.59-60.

27.*The Holy Bible*, Mathew, 12, 42., Luke, 11, 31.

28.ibid., I, Kings, 22.

29. ibid., I Kings, 22, 48.

30. Aman Belai. Ye Tintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik, p.62.

31.N.Pearn and V. Barlow, *Quest for Sheba*, London, 1964, pp. 250-251.

32 Sergew Hable Selassie, Ancient and Medival Ethiopian History to 1270, pp. 38-39.

33 Aman Belai, *Metsihafe Subae Zebeaman Kale* pp.116-117.

34. Aman Belai, Metshafe Subae Ze Be Aman Kale, pp. 305-306.

35. Aman Belai. Ye Tintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik, pp. 60-61

36. Mohammed Hassen. *The Oromo of Ethiopia*. p. 133.

37. Mohammed Hassen, ibid. p. 177-178.

38. Mohammed Hassen.ibid. p. 81.

39. Aman Belai, Yetinantinawa Ethiopia Negestat Tark, pp. 249-250.

40. Aman Belai, ibid. p. 307.

41. Tekletsadki Mekuria, Atse Tewodros ina Ye Ethiopia Andinet, p.186.

42. Belai, Aman, ibid. pp. 265—266.

43 Bairu Tafla, *Atsme-giorgis and His Works* , p. 564.

44 Aman Belai,ibid., p. 22.

45. Tekle-tsadik Mekurai, ibid., p. 275.





46. Berihun Kebede, *Ye Atse Haile Selassie Tarik* pp. 147-148.

47. Aman Belai. *Metsehafe Subae Kale*, p. 308.

48. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, pp. 37—3

49. Teshafe Tiza Gebre-selassie, *Tarike Zemen Ze Dagmawi Menilik*, p.34.

50. Gebreselassie. ibid., p.277.

51. Gebreselassie. ibid., p. 220.

52. Tilahun Birhane-selassie Bete, Ye Hayangaw Kiflezemen Ethiopia, andenga metsihaf,

pp., 130-131.

53. Berihun Kebede, ibid., p. 155.

54. Aman Belai, Yetinatinawa Ethiopia Negestat Tarik, p.180.

55. Aman Belai, Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik, p. 68.

56. Aman Belai. Hzbawl Kedamawi Ye Ethiopia Tarik, p. 42.

;

## ስለ መልከፀዲቅ ተጨማሪ ማብራሪያ

ስለ የሳሌም (ኢየሩሳሌም) ንጉሥ መልከፀዲቅ ስናወሳ የእሱን ማንነት አስመልከቶ ውዥንብር አለ;; መልከጸዲቅ በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ በኦሪት ዘፍጥረት (11. 18-21)፣ በቅዱስ ዳዊት መዝሙር (109-110. 4) እና የቅዱስ ጳውሎስ መልእከት ወደ እብራውያን (ምእራፍ 7) ተጠቅሶአል;; --

በእሪት ዘፍጥረት (14. 18-21) ስለ አብርሃም እና መልከፀዲቅ እንዲህ ይላል;--

»አብርሃም ኮሎዶጎምርንና ከእሱ ጋር የነበሩትን ነገሥታት ወግቶ ከተመለሰም በሁዋላ የሶዶም ንጉሥ የንጉሥ ሸለቆ በሆነው የሴዊ ሸለቆ ሊቀበለው ወጣ;; የሳሌም ንጉሥ መልከፀዲቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ;; እርሱም የልኡል እግዚአብሄር ካህን ነበረ;; ባረከውም (አብርሃምን)– አብርሃም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልኡል እግዚአብሀር የተባረከ ነው;; ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልኡል እግዚአብሄርም የተባረከ ነው፣ አለውም;; አብርሃምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው;;»

በዳዊት መዝሙር ደግሞ (109—110‹ 4) እግዚአብሄር አብ፣ በዳዊት አፍ ውስጥ ስለ እየሱስ ከርስቶትስ ዘላለማዊ ካህንነት ምሎአል--

»እንደ መልከፀዲቅ ሥርዐት አንተ የዘላለም ካህን ነህ ብሎ፣ እግዚአብሄር ማለ፣ አይፀፀትም;;; ..

ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ (እብራይስጥ 7) በመጀመሪያ ስለ መልከፀዲቅ፣ ቀጥሎም መልከፀዲቅ ምሳሌው ስለ ሆነው ስለ እየሱስ ክርቶስ ይናገራል;; እንዲህ ሲል--

..የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሄር ካህን የሆነው ይህ መልከፀዲቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፤ ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አስራትን አካፈለው;; የስሙም ትርጉዋሜ በመጀመሪያ የፅድቅ ንጉሥ ነው;; ሁዋላ ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው;;» (ስለ እየሱስ ከርስቶስ ማንነት ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ እያይዞ ሲናገር) አባትና እናት፣ የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት፣ ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሄር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል;;»





ስለ እየሱስ ከርቶስ ቅዱስ ጳውሎሰ ሲናገር »አባትና እናት፣ የትውልድም ቁጥር የሉትም» ያለውን ቆንጽሎ በማውጣት እያሌ መጽሃፍ ቅዱስን እናውቃለን የሚሉ ሰዎች ይህን አባባል ለኢየሩሳሌም ንጉሥ ለ መልከፀዲቅ በመስጠት »መልከፀዲቅ አባትና እናት ስሌለውና ዘመኑ ጥንት፣ ትውልዱ ቁጥር፣ ህይወቱም ፍጻሜ ስለሌለው መልከፀዲቅ ከአናትና አባት የተወለደ አጥንትና ሰጋ የነበረው ሰው አይደለም;; እሱ ራሱም ልጆች ሊወልድ አይችልም፤» ይላሉ;; ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ »አባትና እናት፣ የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት፣ ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በአገዚአብሄር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል;;» የአለው ስለ እየሱሰ ክርስቶስ እንጂ ስለ ሳሌም ንጉስ እነዳልሆነ አይገነዘቡም;; የእየሱስ ከርስቶስ ምሳሌ የሆነው ንጉሥ መልከፀዲቅ የተባለው ትልቅ ሰው ግን የዛሬ 4000 ዐመት በከህነት እና ንጉሥነት ኖሮ ሞቶአል;; በመሞቱም ህይወቱም፣ መንግሥቱም ከህነቱም አልፈዋል;; ሞቶአል የምለውም ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ነበር፣ ስለሚል ነው;; የት ነው ይህን የሚለው? በዛው በእብራውያን ምእራፍ 7 ቁጥር 4. እንዲህ ይላል--

»የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፋው የሚሻለውን አሰራት የሰጠው **ይህ ሰው** (ይህ ሰው የሚለውን በአፅንኦት እንየው፤) እንዴት ትልቅ እንደነበረ እስኪ ተመልከቱ;;» አዎን ሰው ለሰነበር ሞቶአል;; መንገሥትና ከህነቱም አልፈዋል;; እሱ ምሳሌ የሆነለት የእየሱሰ ከርቶስ መንግሥት፣ ህይወት እና ከህነት ግን ዘላለማዊ ናቸው;; እሱ የማይሞት ዘላለማዊ ነወና;; አባታችንን፣ ማለትም የኢትዮጵን አባት መልከፀዲቅን፣ ቅዱሰ ጳውሎስ »ይህ ሰው ትልቅ እንደነበረ እስቲ ተመልከቱ፤» ባለው ደስ እያለኝ ከእሱ አባባል እስማማለሁ; አዎን በአባታችን ትልቅነት ሁላችንም የኢትዮጵ ልጆች ኢትየጵያውያን ልንደሰት እና ልንኮራ ይገባል;; ቅዱሰ ጳውሎስ፣ አባታችንን መልከፀዲቅን ትልቅ ሰው ካሰባቸው ምክንያቶች ዋነኛው የእየሱስ ከርቶስ ስርዐተ-ከህነት አነስተኛው የዕብራዊው የሌዊ ስርዐተ-ከህነት ሳይሆን የአባታችን የኢትዮጵ አባት፣ ስለዚህም የኛ አባት የሆነው ትልቁ የመልከፀዲቅ ስርዐተ-ከህነት መሆኑ ነው;; እሱ አባታችን ስለሆነ ከእብራውያኑ ከነ ሙሴና እና ከነ ቅዱስ ጳውሎስ የበለጠ ስለ እሱ ማንነት መረጃ አለን;; በመጀመሪያ ነገር፣ ከቅዱስ ጳውሎስ እስቀድሞ ስለ መልከፀዲቅ በጥቂቱም ቢሆን የጻፈው ሙሴ ነው;; ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ሙሴ በጻፈው ላይ ተመርኩዞ ከተበ;; ሙሴ ራሱ መረጃውን ያገኘው ከኛው ከኢትዮጵያውያን ነው;;

እንዴት ቢባል፣ እንደ መልከፀዲቅ ካህን ከነበረው ከመልከፀዲቅ ዝርያ፣ ከኢትዮጵዊው አማቱ ከየቶርአብ ጋር 40 ዐመት ሙሉ በኢትዮጵያ ሲኖር እኛ የአባታችንን የመልከፀዲቅን ትውልድ ታሪክ በዝርዝር የዘገብንበትን መጽሃፈ ዣንሸዋ ን አግኝቶ ስለ አነበበ;; ሙሴ

አስቀድሞ የኛን መጽሃፍ ማንበቡን ራሱ አምኖአል፣ መሰከሮአልም። ይህንንም የመሰከረው በ መጽሃፈ ሆልቆ (21፥ 14) ነው። ይህን እውነት አንባቢው በቀና ልቦና ሊመረምረው ይችላል።

በዛው በ እብራውያን 7 እና 8 ላይ ቅዱስ ጳውሎስ፣ በእግዚአብንር ቀኝ የተቀመጠ የዘላለም ሊቀ-ካህን አለን የሚለውም ፈጣሪን እየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንጂ ሰው የሆነውን አባታችንን መልከፀዲቅን ሊሆን አይችልም። ለአብርሃም ህብስትና ወይንጠጅ ያበረከተለት (ከማንም አስቀድሞ ያቆረበው ማለት ነው፣) ሊቀ-ካህኑ አባታችን መልከፀዲቅ አንጂ እየሱስ ክርስቶስ ራሱ ስጋ ለብሶ፣ ገዝፎና ታይቶ አልነበረም። እየሱስ ክርስቶስ ከ ቅድስት ማርያም ስጋ ነስቶ የዛሬ 2000 ዐመት ከመወለዱ በፊት ስጋ ሆኖ ገዝፎ ለሰው ተከሰቶ ነበር፣ ማለት የስህተት ስህተት ነው። ከሴት ሳይወለድ ስጋ ለመሆን ቢፈቀድ ኖሮ ለምን ከቅድስት ማሪያም ተወልዶ የሰውን ልጅ ከሃጥያቱ ለማዳን አቀደ?

በእርግጥ መልከፀዲቅ አባታችን ስጋ ለባሽ ሰው ነበር። ሰው ስለነበረ ነው ከእናትና አባት የተወለደውና ራሱም ልጆች የወለደው። ከመጽሃፍ ቅዱስ በፊት በተጻፈው፣ ሙሴ እኛ ዘንድ ሳለ ባነበበው ዣንሸዋ በተባለው መጽሃፋችን ውስጥ የአባታችን ትውልድና ልጆች የዘር ሃረግ ተመዝግቦአል። በዚህ መጽሃፋችን ውስጥም መልከፀዲቅ ከናምሩድ፣ ማለትም የባቢሎንን ግንብ ከገነባው ታላቅ ንጉሥ ዘር ይጠቅሳል። እንዲህም ይላል – »ናምሩድ አዳማን ወለደ፣ አዳማ ራፌልብን፣ ራፌልብ ቄናን፣ ቄና ደግሞ ጌራን። ጌራ በክህነት ስሙ መልከፀዲቅ የተባለው ነው። ጌራ (መልከፀዲቅ) በበኩሉ እናታችንን ሳሌምን (የነገሥባትን ከተማ በእስዋ ስም ነው ሳሌም ወይም ኢየሩሳሌም ያለው፣) አግብቶ ከእስዋ ዐራት ሴቶችና ሶስት ወንዶች ልጆች ወልዶአል። የወንዶቹ ስሞች ኢትኤል (አባይን ተከትሎ ሄዶ ጣና ላይ ሰፍሮ በሁዋላ ›ኢትዮጵ‹ የተባለው አባታችን) ሃሙኤል (ሃሙራቢ ተብሎ ወደ ባቢሎን ተጉዞ የሃሙራቢን ህጎች Hamurabi's Code of Lawን የሰጠው) እና አቡመሊክን (የፍልስጥኤማውያን ንጉሥ የሆነውን) ወልዶአል። ከእሱ አብራክ እኛን ኢትዮጵያውያንን ያስገኘን እግዚአብሄር ይከበር ይመስገን። ታዲያ ይሄ ሁሉ ለምን መጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ አልሰፈረም? ሙሴ መጽሃፍ ቅዱስን ከመጻፉ ወይም ከማጻፉ በፊት ይህን ታሪካችንን ጠንቅቆ ያውቃል። አንቦታልና። ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ለምን በኦሪት ዘ ፍጥረት ውስጥ እንዳላካተተው ትክክለኛውን መልስ ሊሰጠን የሚችለው ነቢዩ ሙሴ ብቻ ነው። እሱ ስላልከተበው ግን የኛ እውነተኛ ታሪክ የለም ማለት አይደለም። መጽሃፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት የእኛን ጉዳይ እኛው ከትበነዋል። ስለዚህ፣ እሱ ስላልከተበው ብዙ አይጨንቀንም። ይህ ለሁሉም ሰው ግልጽ ሊሆን ይገባል።





መጽሀፍ ቅዱስን *መጫፈ ቁልቁሉ* ብለው በገዕዝ ፊደላት ተርጉመው፣ የኦሮሞው ተውላጅ ፓስተር ኦናሲሞስ ነሲብ የዛሬ 120 ዓመት በአጼ ምኒልክ ዘመን ያሳተሙት የኦሮምኛ መጽሀፍ ቅዱስ፣ የገዕዝ-ኢትዮጵያ ፊደላት ካላቲኖቹ በተሻለ ኦሮምኛን ለማስተናገድ እንደሚችሉ አረጋግጠዋል። የዛሬ 120 ዓመት ይህን ማድረግ ከተቻለ፣ ዛሬ የግዕዝ ፊደላት የኦሮምኛን እና የሌሎቹንም የኢትዮጲያ ቋንቋዎች እንዲያስተናግዱ ተመቻችተው ስለተቀረጹ በኦሮሞዎች በኩል በጎ ፍቃደኝነት ከአለ፣ አሁንማ በጣም ይቻላል። ከ *መጫፈ ቁልቁሉ* ርዕስ ገጽ ከ እዚህ በታች ተቀምጦአል።



# መጫፈ ፡ ቁልቁሉ ።

እንስ ፡

መጫፎተ ፡ ኪኩ ፡ ሞፋቲፊ ፡ ኪኩ ፡ ሃራ ።

አፋን ፡ ኦሮሞት ።

ሂኬ ፡

ኦኒሲሞስ ፡ ነሲብ ፡

ነሞ ፡ ብየ ፡ ኦሮሞ ።

[illegible]





FACSIMILE LETTER FROM RAS ALULA

To face page 66.

ከአፍሪካ የግራ ብብት ስር እስከ ደቡብ አፍሪካ ድረስ ያለው ውቂያኖስ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ይባል እንደነበር የሚመሰክር ካርታ

ዛሬ የህንድ ውቅያኖስ የሚባለውም ድሮ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ይባል ነበር። ምክንያቱም ደቡብ ህንድ የኛ ስለነበረች።




ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት ላአላይ እና ታህታይ ኢትዮጵያ ተሰኝቶ መላው አፍሪካ ኢትዮጵያ ይባል እንደነበር የሚመሰክር ካርታ



ከአፍሪካ የግራ ብብት ስር እስከ ደቡብ አፍሪካ ድረስ ያለው ውቀያኖስ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ይባል እንደነበር የሚመሰክር ካርታ

ዛሬ የህንድ ውቅያኖስ የሚባለውም ድሮ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ይባል ነበር፡፡ ምክንያቱም ደቡብ ህንድ የኛ ስለነበረች፡፡




ከሁለተ መቶ ዓመታት በፊት ላእላይ እና ታህታይ ኢትዮጵያ ተሰኝቶ መላው አፍሪካ ኢትዮጵያ ይባል እንደነበር የሚመሰክር ካርታ





ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ

ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ፣ /ፒ.ኤች.ዲ./ ገጣሚ፣ ጸሐፌ-ተውኔት እና ከ60 በላይ መጽሐፎችንና መጣጥፎችን በአማርኛ፣ በጀርመንኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች አሳትሞ ለንባብ ያበቃ ምሁር ነው፡፡ በጀርመን እና በአሜሪካ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ አስተምሯል፡፡

*** *** *** ***

ኦሮሞዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማለትም የዛሬ 500 ዓመት አካባቢ ከእስያ ተነስተው በማደጋስካር አቋርጠው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የውጪ ወራሪዎች ተደርገው አጉል ስም ይሰጣቸዋል፡፡ ኦሮሞው መጤ ነው ወይንስ ሃገር-በቀል?

አማራውን እወክላለሁ ብሎ ያወጀ ንጉሠ-ነገሥትስ ይኖር ይሆን?

አማሮች፥ ንጉሠነገሥታት እና ንግሥተነገሥታት ሆነው ላለፉት 3000 ዓመታት እንደገዙት እንደሰለሞን ሥርወ-መንግሥት አባላት ተቆጥረዋል፡፡ አማሮች ይህን ሁሉ ነበሩን?

ለመሆኑ በአለፉት 700 ዐመታት ኢትዮጵያን የገዛ ኦሮሞው ነው ወይንስ አማራው?

እንዴው ለነገሩ በኢትዮጵያ ሥርወ-መንግሥታት ውስጥ የአማሮች ተሳትፎ ምን ያህል እና እስከ ምን ድረስስ ነበር?

እስከነአካቴው አማራ የሚባል ህዝብ አለ ወይስ የለም?

ንግሥተ-ሳባስ ተረት ነች ወይንስ እውን?

ለኦሮሞዎች የሚበጀው በላቲን ወይንስ በኢትዮጵያ ፊደላት መጻፍ? እነዚህን ሁሉ ዐቢይ ጉዳይዎች መመርመር የዚህ መፅሃፍ ዋና ዓላማ ነው፡፡

ዋጋ $ 25

PRINTED@FASTIMAGING BERKELEY,CA